# የሕዳሴ አብዮት

ኅዳር 2007ዓ.ም

© ኅዳር 2007 ዓ.ም
የአሳታሚው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው

የመጀመሪያው ዕትም - ኅዳር 2007 ዓ.ም

የውስጥ ገፆች ጽሑፍና ቅንብር - ቤቴልሔም አመነሸዋ
የሽፋን ቅንብር - ነቢዩ መስፍን

ዋና አከፋፋይ - 091 176 2544





# ማውጫ

መግቢያ ........ 4

ክፍል አንድ - ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት ........ 8

- በሙሉነህ አያሌው

ክፍል ሁለት - የኢትዮጵያ አብዮት ........ 58

- በኃይለመስቀል በሽዋምየለህ

ክፍል ሦስት - ሕዳሴውን እንደ ቬልቬት ........ 74

- በዳዊት ታደሠ

ክፍል አራት - ሠላማዊ ትግል ........ 96

- እስክንድር ነጋ

ክፍል አምስት - የሕዳሴው አብዮት ........ 156

- ተመስገን ደሳለኝ

# መግቢያ

ከኢትዮጵያ ሁለንተናዊ ዕጣ-ፈንታ ጋር በተያያዘ መጪው ጊዜ ያስቀመጠው ምርጫ አንድ ብቻ መስሏል፡፡ ባሳለፍናቸው ዘመን ተሻጋሪ የታሪክ ሂደቶች በፖለቲካዊ ባህላችን የተመሰለው አምባገነንነት፣ ስልጣን ላይ ለነበሩት ሥርዓታት መገለጫ ሆኖ ነበር፡፡ በዚህ የረዥም ዓመታት የግፈኝነት ጉዞ ከአገዛዙና ከገገርዎቹ ውጪ ህዝብ ሲጠቀም የታየበት ኢጋጣሚ አለመኖሩ ደግሞ በደሉን የመረረ አድርጎታል፡፡ እንደ አለመታደል ሆኖ ዛሬም ከዚህ ኋላቀር የፖለቲካ ስርዓት አልወጣንም፡፡ የስልጣን ብቸኛው ምንጭ ህዝብ እንዲሆን ለማረጋገጥ በሺዎች መስዋዕትነት ቢሞከርም ማሳካት ግን አልተቻለም፡፡ ይህ ለምን ሆነ? የእስከዛሬው መከራ አላማውን ያላሳካው ለምንድን ነው? ባህላችን ዴሞክራሲን ማስተናገድ ስላቃተው ወይስ የተሞከረበት መንገድ ስለማያዋጣ? የቀደሙት የለውጥ ሙከራዎች ውድቀት የተስፋ ቢስነታችን ማረጋገጫ ሊሆኑ ይችላሉ? የዚህች ታሪካዊ አገር መጨረሻ በዚህ እንደማይደመደም ያመንን ጋዜጠኞች በፖለቲካ ህይወታችን እስከአሁን ባልተሞከረ የትግል ስልት፣ ለውጥ ማዋለድ ይቻላል ብለናል፡፡ የምናምንበት የአብዮታዊ ጋዜጠኝነት ኀልዮትም፣ ለዚህ ህልም ያስገዛናል፡፡ አገሪቱን በዋናነት እየናጡ የሚገኙትን





የተለያዩ የፖለቲካ ፍላጎቶች አኪታች የሆነ አብዮት ለውጡን ስር -ነቀል፤ ግቡንም ዴሞክራሲያዊ እንደሚያደርገው አንጠራጠርም፡፡

በዳግማዊ አብዮት ይህችን አሪታዊት (ጥንታዊት) አገር የመምራት ዕድል ያገኘው የሽፍቶች ስብስብ፣ ለሃያ ሶስት ዓመታት መሰንበት ቢችልም አገሪቷን ወደፊት ከመውሰድ ይልቅ ቁልቁል አውርዷታል፡፡ በደህረ -ደርግ ማግስት፣ የተሻለ አቻቻይ ፖለቲካዊ ስርዓት ለማበጀት ከውስጥም ከውጪም የነበረው ተስፋ፣ በጥቂት ዓመታት ውስጥ ወደ ታላቅ ቀቢፀ -ተስፋነት ተለወጠ፡፡ ዴሞክራሲያዊ ተቋማትን መገንባት፣ የሀገር ግንባታውን የቀደሙ ጉድለቶች ማረም፣ ነፃ የኢኮኖሚ ስርዓት መዘርጋት፣ ሀሳብ እንጂ ጠብ-መንጃ የማይነግስበት አደባባይ መፍጠር በሁለቱ ዓስርታት ውስጥ አፈር የለበሱ ህልሞች ሆነዋል፡፡ አብዮት ያስፈልገናል፣ ይመጣልም የምንልበት አንዱ ስረ-ምክንያትም እነሆን የተሸነፉ የሚመስሉ ህልሞችን ዳግም ወደየልቦናችን ለመመለስ ነው፡፡ ይሄን የቋሚ ሽፍቶች ቡድን በምርጫ ፖለቲካ የሚቀየር ብቻም ሳይሆን ለመገራት እንኳን የሚፈቅድ አለመሆኑም፤ የአብዮቱን ናፍቆት አገንግኖታል፡፡ ከደም-አልባ አብዮት ውጪ፣ ኢትዮጵያን እንደ አገር ማቆየት እንደማይቻልም እንድናምን አስገድዶናል፡፡

የ"ሕዳሴ አብዮት" በሚል ስያሜ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተካተተው ተተግባሪ ሀሳብ መጪውን ጊዜ ካለፈው ዘመን ጉድፍ ለማንፃት አቅም እንዳለው ታምኖበታል፡፡ በተለይ በባህል፣ በአመለካከትና ቢታሪክ የተገፉ ስብስቦች በዴሞክራሲያዊ ጥላ ስር በእኩል ውክልና ወደ አደባባዩ የሚወጡበት መንገድ በመፍትሔነት ተቀምጧል፡፡ ቀጣዩ የአገሪቱ ዋነኛ ፈተና ሊሆን እንደሚችል የሚገመተው ይህ የተዘነጋ አገራዊ እውነት መቋጫ ካላገኘ ማኅበረሰብን ላመፍረስ ጉልበት እንዳለው ይታመናል፡፡ የሕዳሴ አብዮት የተነሳበትና እንደግብ ካስቀመጥናቸው ግቦች መካከል ይህ ርዕስ

ጉዳይ ከፊት ቀዳሚ ይሆናል፡፡ የኦሮምኛ ቋንቋ ተናጋሪ እና የእስልምና ሀይማኖት ተከታዮች ደግሞ በዋንኛነት ተነስተዋል፡፡

አገሪቷ አብዮታዊ የለውጥ ማዕበል ያስፈልጋታል ስንል ለውጡ መምጣት አለበት ብለን የምናምነውም ሰላማዊ እና ሁሉን አሳታፊ በሆነ የትግል ስልት መሆኑ መዘንጋት የለበትም፡፡ በሰላማዊ ህዝባዊ አብዮት ወደ መንበረ-ሥልጣን ብቅ ያሉ አብዛኞቹ አብዮቶች ከሌሎች የመታገያ መስመሮች በተሻለ ዴሞክራሲያዊ መንግስትን በማነበር እጅግ ውጤታማ መሆናቸው በብዙ መልኩ ተስተውሏል፡፡ መጽሐፉ የሰላማዊ የትግል ስልት ጠቀሜታን በሚመለከት በሰፊው ለመዳሰስ መሞከሩም፣ ከዚህ መነሾ የሚቀዳ መሆኑን ለመጠቆም እንፈልጋለን፡፡

የዚህ መጽሐፍ ሌላው አካል የቀደመውን የኢትዮጵያ አብዮት መገምገም ነው፡፡ ከአርባ አመታት በፊት የተነሳው ይህ ስር -ነቀል ለውጥ ንጉሱንና ከፊል ፊውዳላዊ ስርዓቱን ማፈራረስ ቢችልም ካነገባቸው ጥያቄዎች መካከል ዋናዎቹን የሳተ ነበር፡፡ የ"መሬት ላራሹን" ትውልዳዊ ህልም ወታደራዊው መንግስት ያሳካ ቢመስልም ስልጣንን ወደ ህዝብ ባለቤትነት ለመመለስ የተከፈለው የደም ዋጋ ግን በከንቱ ሆኗል፡፡ በቡድን የተዋቀረው የወቅቱ የትግል ጉዞ አንዱን ለወንበር ባለቤትነት ሌላውን ደግሞ ለአገር አልባነት ያበቃ ነበር፡፡ የወታደሩን ልሂቅ በጉልበት ያንበረከከው የሰሜን ኢትዮጵያ ሰብሰብ በበርካቶች ደምና አጥንት አራት ኪሎ ቢደርስም፣ ሲያቀነቅን የሚሰማውን የብሔር እኩልነት እንኳን ማረጋገጥ ተስኖታል፡፡ የኢትዮጵያ አብዮት ከሰጠን ይልቅ የነጠቀን በዝቷል የምን ለውም እነዚህንና ሌሎች የውድቀት ምክንያቶችን በመንተራስ ነው፡፡ ከዚህ ሀሳብ በተከታይነትም፤ የኢትዮጵያዊነት የታሪክ፣ የባህል እና የማንነት መለዮዎች ተተንትነዋል፡፡ በተከታታዮቹ ስርዓታት የተስተዋለው ኢትዮጵያዊነት ከፍታዎቹ እና ጉድለቶቹ፣ ለቀጣዩ አብዮት መንፈስ በሚዛመድ መልኩ ተቀምጠዋል፡፡ የሕዳሴው አብዮት ከኋላ ወደፊት የሚመለከት እንጂ





የቀደመውን በማፍረስ የሚጠመድ አይደለምና የኢትዮጵያን መለዮዎች ደግሞ የመበየንን አስፈላጊነት ያስረግጣል፡፡

ኢትዮጵያን ጨምሮ አለማችን ያስተናገደቻቸው አብዮቶች የሚዋዋሱ የበዙ ባህሪያት አሏቸው፡፡ ከለውጡ ስልት ጀምሮ እስከ አብዮቱ ውጤት ድረስ የሚስተዋሉት ክስተቶች፣ ለሌሎች ተጨዳኞች መነቃቂያም ሆነ ተስፋ ማንጠፊያ ይሆናሉ፡፡ በዚህ መፅሀፍ የሚወሳው አብዮት ፍፁም ሰላማዊ እንደመሆኑ የቼኮዝሎቫኪያን የቬልቬት አብዮት መልክ እንዲኖረው ታልሟል፡፡ ደም-አልባ፣ የገዢው ፓርቲ አባላት የተሳተፉበትና በድርድር የተጠናቀቀ ስር-ነቀል የንቅናቄ ውጤት መሆኑ የቬልቬትን ተሞክሮ የምንማርበት ያደርገዋል፡፡ ከመፅሐፉ ጥቂት ክፍል የተካተተበት መነሾም በየትኛውም መስፈርት የለውጡ ሂደት መወደሱ ነው፡፡

የስርዓቱ ቅጥ-ያጣ ክፋት፣ ማኅበረሰቡ ላይ ያዘነበው ትውልድ ተሻጋሪ መከራ አልፎም እርስ በእርስ የመተላለቂያ የፅብ መስመሮች፣ የዘመኑን ገዢዎችም ሆነ በክፉ ዓይን የሚተያዩ የተቃውሞ ል ሂቃኑን፣ በቀጣይ በምትኖረው አገር ዴሞክራሲያዊ መሆን ብቻ ላይ በመተማመን፣ በይቅርታ እና በፍቅር ኅብረት የሕዳሴውን አብዮት መቀስቀስ ይገባል እንላለን፡፡

በኢሕአዴጓ ኢትዮጵያ ዝግመታዊ የሞት ሂደት ላይ ከተስማማን፣ መፍጠን እንደሚያስፈልገን ግልፅ ነው፡፡ እንደ መድበሉ አዋጪዎች እምነት፣

ማዋለጃነት መጠቀም እንችላለን፤ ይገባናልም፡፡

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!



ጋዜጠኛ ሙሉነህ አያሌው

# ክፍል አንድ

# ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት



የሕዳሴ አብዮት----------

ምዕራፍ አንድ

- ኢትዮጵያዊነት. . .

ምዕራፍ ሁለት

- የኢትዮጵያ ታሪክ አተራረክ

ምዕራፍ ሦስት

- እስልምናና ኢትዮጵያዊነት

ምዕራፍ አራት

- የኢህአዴግ አዲሲቷ ኢትዮጵያዊ መልክ

ምዕራፍ አምስት

- ተሃድሶ የሚሻው የኢትዮጵያዊነት ብያኔ

# ምዕራፍ አንድ

# ኢትዮጵያዊነት. . .

ኢትዮጵያ የሚለው ስያሜ መሰረቱ ግሪክ ሲሆን፣ ከክርስቶስ ልደት በፊት በውል ከታወቀችው ከግብፅ በስተደቡብ የሚገኘው የአፍሪካ ክፍል የሚጠራበት አጠቃላይ ስም ነበር፡፡ ይሁንና ከክርስቶስ ልደት በኋላ አገባቡ ጠበብ እያለ አሁን ኢትዮጵያ የምትገኝበት አካባቢ መጠሪያ ለመሆን በቃ፡፡ ስያሜው በዚህ በጠበበና እስከአሁንም ቋሚ በሆነ መልኩ የምናገኘው፣ በ4ኛው ምእተ ዓመት ለመጀመሪያ ጊዜ የክርስትና እምነት የተቀበለው የአክሱም ንጉስ ዔዛና በድንጋይ ላይ ባስቀረፀው አንድ ጽሑፍ ላይ ራሱን «የኢትዮጵያ ንጉሥ» ብሎ ሲጠራ ነው፡፡ ከዚያም በተከታታዮቹ ምእተ-ዓመታት በጊዜው በተጻፉ ጽሑፎች አክሱም «የኢትዮጵያዊያውያን ከተማ»፣ አፄ ካሌብ ደግሞ «የኢትዮጵያውያን ንጉሥ» ተብለው ሲጠቀሱ ስናይ፣ ስያሜው ቋሚ መልኩን እየያዘ መምጣቱን እንረዳለን፡፡ በ14ኛው ምእተ-ዓመት መጀመሪያ ላይ የተጻፈው ክብረ-ነገሥት የተሰኘውና ንግሥት ሳባ ወደ ንጉሥ ሰለሞን ያደረገችውን ጉዞ የሚያትተው መጽሐፍም «ኢትዮጵያ»





የሚለው ስያሜ የአሁኒቱ ኢትዮጵያ ካለችበት ግዛት ጋር ያለውን መያያዝ ይፋ (ኦፊሴዬል) አድርጎታል፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የኢትዮጵያ ነገሥታት መደበኛ መጠሪያም «ንጉሠ ነገሥት ዘ-ኢትዮጵያ» ወይም «ንጉሠ ኢትዮጵያ» ሆኖ ቆይቷል፡፡ ለፐሮፌሰር ታደሰ ታምራት «የኢትዮጵያዊነት መሰረቱ አንድም ጥንታዊ መሆኑ ነው፡፡ ኢትዮጵያዊነት የአንድ መቶ ዓመት ጉዳይ አይደለም» ይላሉ፡፡ «ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት፣ በተወላጆቹ የህልውና መዛግብት ብቻ ሳይሆን፣ በዓለም ታሪክም ውስጥ ቋሚ ምስክርነት ያለው እውነታ ነው፡፡ ኢትዮጵያ የሚለው ስም፣ እኛ ላለንበት የአፍሪካ አካባቢ፣ በግሪኮች የተሰጠው የዛሬ 3000 ዓመት ያህል ሲሆን፣ በተለይ የዚህች የኛይቱ ኢትዮጵያ ጥንታዊ አባቶች፣ ራሳቸውን «ኢትዮጵያዊ» ብለው መጥራት የጀመሩት፣ ከዛሬ 1650 ዓመታት በፊት ነው፡፡

«ይህም በመሆኑ፣ ከግሪኮች ዘመን ጀምሮ ስለ ኢትዮጵያ ይባል የነበረው ጥሩ ዝና፣ በመጽሐፍ ቅዱሱም በየቦታው ለሚደረጉ ጥቅሶች ሁሉ፣ ይህችው የኛይቱ ኢትዮጵያ ተቀናቃኝ የሌላት ወራሽ ሆናለች፡፡ እንኳን እኛ እራሳችን ኢትዮጵያውያንና፣ የሰለጠነው ዓለም በመላ፣ ሂንዱ፣ ክርስቲያኑ፣ እስላሙ ዓለም ሁሉ፣ አገራችንና ሕዝቦቿን ባጠቃላይ የሚያይዋት ከዚህ ከጥንታዊ ዝና አቅጣጫ ነው፡፡ ይህ አጠቃላይ የጥንት ታሪክ እውነታ፣ ሀገራችንን የሥልጣኔ ምንጭ ከሆኑት ከግብፅ፣ ከግሪክና ከመጽሐፍ ቅዱስ ሕዝቦች ጋር በቅርብ ስለሚያገናኛት፣ ለኛ ለሕዝቦቿ ትልቅ መንፈሳዊ ኩራት ይሰጠናል» ይላሉ፡፡

የፐ/ር ታደሰ ሁለተኛው የኢትዮጵያዊነት ትርጓሜ «አገሪቷ አብዛኛውን ጊዜ ብቸኛና በአካባቢው ተፎካካሪ የሌለው ጠንካራና ህልውናው ሳይጠፋ እስከ ዛሬ የደረሰ የመንግስት ባለቤት ሆና መቆየቷ» ነው፡፡ «ግብፅ፣ ግሪክና የመጽሐፍ ቅዱስ ሕዝቦች ሁሉ ሳይቀሩ፣ በተለያዩ ኋላ-መጥ ኃይሎች ስር ገብተው የቅኝ ግዛት ሲሆኑ፣ ይህች የኛይቱ ኢትዮጵያ ግን ማንነቷ ሳይነካ፣ በአካባቢዋ ራሷን ችላ ለዘመናት ኖራለች፡፡»

ለፕ/ር መስፍን ወ/ማርያም ደግሞ ኢትዮጵያዊነትን በሙሉ ኃይል ለመግለጽ ሶስት መሰረታዊ ነገሮች የተጣመሩ እንደሆነ ነው ሲሉ ይገልጻሉ፡፡ «ኢትዮጵያዊነት ከጥርጣሬ የጸዳ እውቀት፣ የማይናወጥ እምነትና የደም ስርን የሚነዝር ስሜት አጣምሮ የያዘ መሆን አለበት» የሚል እምነት አላቸው፡፡ እነዚህ ሶስት ነገሮች በአንድ ላይ የተጣመሩበት ማንነት ኢትዮጵያዊነትን ለመግለጽ አስፈላጊ መሆናቸውን ይገልጻሉ፡፡

ከጥንት አንስቶ በኢትዮጵያ እና በኢትዮጵያዊነት ዙሪያ ጥናትና ምርምር ያካሄዱ ምሁራን የኢትዮጵያን ህዝቦች የተለያየ ገፅታ፣ ባህል፣ ቋንቋ፣ እምነት፣ ሥርዓተ-ማህበርን መሰረት በማድረግ፤ ኢትዮጵያውያን ምን አይነት አንድነት ነበራቸው፣ አሁንስ ምን አይነት ተመሳስሎ ኖሯቸው ነው በአንድ የአገረሰብ መጠሪያ ሊሰባሰቡ የቻሉት? የሚሉ መጠይቆችን አንስተው ሲከራከሩ ይስተዋላል፡፡ የኢትዮጵያ የጥንት ወዳጅ ተደርገው የሚቆጠሩት አሜሪካዊው ምሁር ዶናልድ ሌቪን፣ ለእንዲህ አይነት ጥያቄ መሰረታዊ ምላሽ ይሰጣል ብለው ያሰቡትን የመፍትሄ አማራጭ መነሻ ሃሳብ አድርገን በመውሰድ ኢትዮጵያዊ መልኮች ምን እንደሚመስሉ በጥቂቱም ቢሆን ለማየት እንሞክር፡፡

ፕ/ር ዶናልድ ሊቪን፣ የኢትዮጵያ የአንድነት ህልውና በሶስት ተዛማች አዕማዶች ስር ይጠቃለላል ሲሉ ያትታሉ፡፡ እነርሱም ልዩ ልዩ የኢትዮጵያ ሕዝቦች ባለማቋረጥ የእርስ በርስ ግንኙነት የማድረጋቸው ሂደት፣ በርከት ያሉ ኢትዮጵያን ዐቀፍና ኢትዮጵያን መሰል የሆኑ የወል የባህል ቅርሶች መኖራቸው፣ በየጊዜው ባዕድ ሕዝብና ባዕድ ባህል በአገሪቱ ጉዳይ ላይ ጣልቃ ለመግባት በሚቃጡበት ጊዜ ለመከላከል አብረው መቆማቸው መሆኑን ይጠቅሳሉ፡፡

በመጀመሪያ መደብ ስር የሚያርፈው ከጥንት አንስቶ የኢትዮጵያ ሕዝቦች ባለማቋረጥ የእርስ በርስ የንግድ ትስስር የማድረጋቸውን ሁኔት ይጠቅሳሉ፡፡ እነዚህ ማህበረሰቦች የእርስ-በርስ ንግድ ልውውጥ





በሚያደርጉባቸው በነዚያ አመታት እንደዛሬዋ ኢትዮጵያ በማዕከላዊ አስተዳደር የሚጠቃለሉ አልነበሩም፡፡ ተበታትነው ይኖሩ የነበሩ ማህበረሰቦችን በማስተሳሰር ረገድ ንግድ ከፍተኛውን ሚና ተጫውቷል፡፡ ኢትዮጵያውያን ከቅርብ ጐረቤቶቻቸው ብቻ ሳይሆን ሩቅ ናቸው ከሚባሉ ጐሳዎች ጋር ሁሉ ሳይቀር ‹የሲራራ› በሚባሉ ነጋዴዎች አማካኝነት የእርስ በርስ ግንኙነት መስርተው እንደነበር ታሪክ ምስክር ነው፡፡ በጊዜው ማንኛውም ጐሳ ሆነ ነገድ ለብቻው ተለይቶ መቆየት የሚያስችለው ጥሬ ዕቃ ያለው ባለመሆኑ ንግድ የምርጫ ብቻ ሳይሆን የህልውናም ጥያቄ ነበር፡፡

የያው የአገሪቱ የገበያ ማዕከላት ሁለት መልክ እንደነበራቸው የታሪክ ድርሳናት ያወሳሉ፡፡ ቀዳሚው የንግድ ልውውጥ ማዕከል አካባቢያዊ ገበያ (Local Market) ተብሎ ይጠራ የነበረው ነው፡፡ አካባቢያዊ የሚባለው የገበያ ማዕከል መጠኑ አነስ ያለ ሆኖ በሳምንት አንድ አሊያም ሁለት ቀናትን ለግብይት የሚጠቀምና ከሁለትና ሶስት ያልበለጡ ጐሳዎች በንግድ ልውውጥ ያሳትፍ የነበረ ነው፡፡ ሁለተኛው ከአንዱ የኢትዮጵያ ጫፍ ወደሌላኛው ጫፍ ረጅም ርቀት በመጓዝ ሸቀጦችን የሚያመላልሱ የአገሬው ነዋሪዎች የሚሳተፉበት የንግድ መስመር ነው፡፡ እነዚህ የንግድ ማዕከላት ሰፊውን የአገሪቷ ክልል በማገናኘት ረገድ ከፍተኛ ሚና ነበራቸው፡፡

ለምሳሌ ደብረታቦር አካባቢ የቅማንት ቀበሌ ከሆነው ከጭልጋ ጅንጅብል፤ ከአማራው ወረዳ ከጋይንት የሱፍ ብርድ ልብስ፣ ከወልቃይት ከትግራይ ጥጥ፤ ከድብልቅ ጐሳው ከወሎ ደሴ የብር ስራ፤ ከሰሜን አፋር ጨው፤ ከኦሮሞ ጅማ ቡና ይዘው ወደ ደብረታቦር ገበያ ይመጡ እንደነበር ፀሐፊያኑ ይመሰክራሉ፡፡ ደብረ ታቦር የንግድ ማዕከል በመሆን አንድ ማሳያ ትሁን እንጂ በሰሜን አክሱም፣ በደቡብ ምስራቅ ሐረር፣ በሰሜን ምዕራብ ጐንደር በደቡብ ምዕራብ ቦንጋ ከፋ የንግድ ማዕከልነታቸው ተጨማሪ ማሳያዎች ናቸው፡፡

በአንዳንድ የገበያ ቦታዎች ታድመው ከሚታዩ ጐሳዎች መካከል በሙሉ አማሮች ከጐጃምና ከሸዋ፣ ኦሮሞዎች ከጊቤ ግዛት (ጉማ፣ ጌራ፣

ሊሙ ኢናርያ፣ ጅማ) ከሀይቆችና ከአሞ ሕዝቦች፣ ጠንባሮን፣ ቀቤናን ከፋን፣ ጃንጀሮን፣ ወላይታን፣ ኮንታንና ሌሎችንም በርከት ያሉ ከኦሞቴ ጎሳዎች የሚወክሉ ነጋዴዎች ብዙ ነበሩ፡፡ በላስታ የሚገኘው የሰቆጣ ገበያ በሰሜን በኩል ከየጁና ከራያ ኦሮሞዎች ጋር፣ በደቡብ በኩል ደግሞ ከጉራጌ፣ ከከፋ ከጉማ እና ከሌሎች ከብዙዎቹ ከደቡብ ማዕከሎች ጋር ግንኙነት ነበረው፡፡

ረጅሙን የኢትዮጵያ ግዛት በማገናኘቱ በኩል የሙስሊም ነጋዴዎች ትልቁን ድርሻ ተወጥተዋል፡፡ ከነዚህም መካከል በሰሜን (የአማራና የትግራይን አካባቢ በሚያካልለው ግዛት) ጀበርቲ የተባሉት ነጋዴዎች ሸቀጦችን ከአንዱ አካባቢ ወደ ሌላ በማዟዟር ዕውቅና ያተረፉ ሲሆን፣ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ የሙስሊም ኦሮሞ ነጋዴዎች አፍካላ በሚል መጠሪያ የአካባቢውን ሸቀጦች ወደተለያዩ የአገሪቷ ክፍሎች በማሻገር ለሕዝብ ለሕዝብ ትስስሮሽ የበኩላቸውን አስተዋፅኦ አበርክተዋል፡፡

የጀበርቲና የአፍካላ ነጋዴዎች ከሱማሌ እስከ ቦረና ምድር ድረስ መረባቸውን ዘርግተው ይንቀሳቀሱ እንደነበር የታሪክ ፀሐፍት ያወሳሉ፡፡ በነዚህ የሲራራ ነጋዴዎች ትልቅ እገዛ ምክንያት በሰሜንና በደቡብ ኢትዮጵያ፤ በመሀልና በሰሜን ኢትዮጵያ መካከል የነበረውን የደበዘዘ ግንኙነት ያጠበበ ከመሆኑም በላይ የየአካባቢዎቹ ህዝቦች ተቀራርበው መኖር የሚችሉበትን እድልን አመቻችቷል፡፡

የኢትዮጵያዊነት አዋሃጅ ትልቁን ድርሻ ከሚወስዱ መካከል የእምነት ተቋማት ወደተለያዩ ከባቢዎች መስፋፋት ዋነኛው ነው፡፡ የክርስትናና የእስልምና እምነት መስፋፋት ከንግድ ትስስሮሽ ባለፈ ማህበረሰቡ በመንፈሳዊው መስመርም የጠበቀ ግንኙነት እንዲፈጥሩ አግዟቸዋል፡፡ ምንም እንኳ በዘመነ ዘርዓ-ያዕቆብና በዘመነ ዮሐንስ አራተኛ እንዲሁም በዘመነ ግራኝ ሕዝቡ ኃይማኖትን በግዴታ እንዲቀበል የተደረገ ቢሆንም፣ አብዛኛውን ጊዜ ነጋዴዎች በከፈቱት የንግድ ጐዳናና





ዲፕሎማሲያዊ ትብብር በመሻት ሰበብ የእምነት መስፋፋት በሰላም እንዲከናወን ምክንያት ሆኗል፡፡ በ8ኛውና በ16ኛው ምዕተ-ዓመታት መካከል የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ-ክርስቲያን መነኮሳት በሰሜን የመጃ ዘላኖችን፣ በሰሜን ምዕራብና በመሀል ክፍለ ሀገር የአገውን ሕዝብ፣ በደቡብ ምዕራብ ደግሞ የወላይታንና የከፋን ንጉሶችና ብዙ ሌሎች ለማጥመቅ ችለዋል፡፡

በነዚህ ምዕተ-ዓመታት እስልምና በሱማሌ ጠረፍ ተነስቶ በምስራቅ ሸዋ እስከ ይፋት፣ በስተ-ደቡብ በኩል ደግሞ እስከ ደዋሮና ባሌ፣ ከዚያም እስከ ምስራቅ ኤደን ድረስ ሊስፋፋ ችሏል፡፡ የክርስትናና የእስልምና ሃይማኖቶች መስፋፋት ኢትዮጵያን ከነገድ አልፎ በእምነት እንዲተባበሩ ሲረዳ፣ በሌላ በኩል ደግሞ አብዛኞቹ ኢትዮጵያውያን በሃይማኖቶቹ ሳቢያ ወደ ውድድር (ፉክክር) እንዲገቡ አድርጓል፡፡

ከዚህም ባለፈ የእምነት ተቋማት በኢትዮጵያ የስነ-ጽሁፍ ታሪክ በጎ አሻራቸውን አሳርፈዋል፡፡ ጽሑፍና ትምህርት በጥንታዊ የደአማት፣ የሳባ፣ የግዕዝና የግሪክ ፊደላትና ቋንቋዎችን በድንጋይ ላይ መጻፋቸውን ታሪካዊ ሰነዶች እንደሚያሳዩን፤ በኢትዮጵያ ታሪክ ባህላዊ የፊደልና የጽህፈት መሳሪያ ከተፈጠረ እስከዛሬ ድረስ 2500 ዓመታት የሚቆጠር ዘመን አልፏል፡፡ ከጥንታዊ የድንጋይ ጽሕፈት ሌላ የኢትዮጵያ ሁለቱ ታላላቅ የክርስትናና የእስልምና ሃይማኖቶች በየፊናቸው በቅደም ተከተል በግዕዝና በአረብኛ በብራና የተጻፉ ሰነዳዊ ቅርሶች አውርሰውናል፡፡ በጥንት ዘመን በግዕዝ ቋንቋ በብራና የተጻፉት የነገስታት ዜና መዋዕሎችና የቅዱሳን ገድሎች በአገሪቷ ታሪክ በአገርና በአለም አቀፍ ደረጃ በጣም የታወቁ ናቸው፡፡

በጥንታዊ የሸዋ፣ የአዳል፣ የሐረር፣ የአውሳ አካባቢ መንግስታት በአረብኛ ቋንቋ የተጻፈ ታሪካዊ የጽሁፍ ቅርስ መገኘቱ በብዙ ኢትዮጵያውያን ዘንድ ብዙ የታወቀ አይደለም፡፡ በአረብኛ ቋንቋ ተጽፈው ከታላቋ የሐረር ከተማ ከተገኙ ጥንታዊ ሰነዶች መካከል ልዩ ዋጋ ያላቸው

ከ890 እስከ 1880 ድረስ በአስር ምዕተ-ዓመታት በፈረቃ ስለተነሱ እስላማዊ የሸዋ፣ የይፋት፣ የአዳል፣ የአውሳና የሐረር አካባቢ መንግስታትና ሥርወ-መንግሥታቶችን የሚገልጹ ጽሑፎች ናቸው።

ከነገስታት መካከል አፄ ዘርዓ-ያዕቆብ በተለይ፣ ሕዝብን ከሕዝብ፣ ባህልን ከባህል በማገናኘትና በማዋሃድ ረገድ የብዙ ሕዝቦች የውስጥ ታሪክ እስከዛሬ ይጠቅሳቸዋል። በተለይ በጉራጌ አገር ልዩ ልዩ ቀበሌዎች፣ በስልጤ፣ በሐዲያ፣ በከምባታ ሕዝቦች ታሪክ ውስጥ ተደጋግሞ ይወሳል። በከምባታና ሐዲያ ውስጥ ስማቸው ከንግስት እሌኒ ጋር ይበልጥ ይነሳል። በውበታቸው፣ በረቂቅ እውቀታቸው፣ ጥልቅ በሆነው የክርስቲያን ኃይማኖተኝነታቸውና፣ በከፍተኛ ኢትዮጵያዊ አርበኝነታቸው በዘመኑ የሀገራችን ታሪክ በጣም የታወቁት ንግስት እሌኒ፣ ከነገስታት ቤተሰብ ተመርጠው ለአፄ ዘርዓ-ያዕቆብ የተሰጡ የሐዲያ ቆንጆ ልዕልት እንደነበሩ የታወቀ ነው።

እኚህ የሐድያዋ ቆንጂት እሌኒ፣ ለዘርዓ-ያዕቆብ ተመርጠው የተሰጡት ገና በሕፃንነታቸው ዘመን ስለነበር፣ ንጉሡ ባላቸው ከሞቱም በኋላ፣ በተጨማሪ ለሶስት ትውልዶች በተከታታይ ለነገሡት የዘርዓ-ያዕቆብ ወራሾች፣ ማለትም ለበዕደ-ማርያም፣ ለእስክንድር፣ ለናዖድና ለልብነድንግል፣ ታላቅ አማካሪ ሆነው፣ ለሃገሪቱ የሀገር ውስጥና ዓለም-አቀፍ ፖለቲካ፣ ለብዙ አመታት የበሰለ አመራር ሲሰጡ እንደኖሩ ታሪክ ይመሰክርላቸዋል። በሰባት ቤት ጉራጌ፣ በተለይ በጉመር፣ በጌቶና በኤነር አካባቢዎች፣ ዘርዓ-ያዕቆብና ልጃቸው አፄ በዕደ-ማርያም፣ በሕዝቡ ጥንታዊ የታሪክ ትውስታ ታላላቅ ስፍራ አላቸው። የጉራጌ ቆንጃጆች ከዚያ ጊዜ በፊት ጀምሮ፣ በተለይ እስከ ንጉሥ ሣህለ-ሥላሴና እስከ አፄ ኃይለ-ሥላሴ ድረስ፣ ለቤተ መንግስቱ ልዩ ፀጋ ሆነው መቆየታቸው የታወቀ ነው።

«ሮም በአንድ ጀንበር አልተገነባችም» እንዲሉ፤ ለዛሬዋ መልክአ-ኢትዮጵያ እልፍ አእላፍ የዘውግ አጥር ያላገዳቸው አባትና እናቶች ከመሪነት





እስከ ተራ ወታደርነት በመሰለፍ የማገልገላቸውን ሀቅ ያሳያል። ይህንን ጉዳይ በቀላል ምሳሌ ከሚያስረዱ ታሪካዊ ገድሎች መካከልም የዐድዋ ድል አንዱ ነው። ዳግማዊ ምኒልክ ዛሬ የሚወቀሱባቸውን በርካታ አካባቢዎች ሀገር በማቅናት ዘመቻ ከማዕከላዊ መንግስቱ ጋር የቀላቀሉት ከዐድዋው ጦርነት በፊት ነበር። ሌላው ቀርቶ የተቆረጠ ጡት ሐውልት ለመታሰቢያነት በቆመለት አኖሌ የተደረገው ውጊያ ከዐድዋው ድፍን አስር ዓመት የቀደመ መሆኑ ይታወሳል። በወቅቱ በአካባቢው የጎሳ መሪዎች ከነበሩት መካከል ሱፋ ኩሶ እና ዳሙ ኩሶ በሰላማዊ መንገድ የንጉሱን አስተዳደር ለመቀላቀል ሲወስኑ፤ የተቀሩት ደግሞ ሀሳቡን ውድቅ በማድረጋቸው ጦርነት መቀስቀሱን በርካታ የታሪክ ድርሳናት አትተዋል።

ኢትዮጵያ ዳር ድንበሯ ዓለም አቀፍ እውቅና አግኝቶ አሁን በውስጧ የተካተቱ የተለያዩ ብሔር ብሔረሰቦች የያዘች፤ በተማዕከለ መንግስት የምትተዳደር አገር ከሆነች አንድ ምዕተ ዓመት አልፏል። ሁላችንም እንደምናውቀው አሁን በሀገሪቷ የሚገኙ ህዝቦች በአንድ ማዕከላዊ መንግስት አስተዳደር ሲገነቡ ሕዝቦች ፈቃዳቸው እየተጠየቀ የአውሮፓ የጋራ ማህበረሰብ ሕዝቦች እንዳደረጉት ሕዝበ-ውሳኔ እየተካሄደ፣ በጋራ በተስማሙባቸው ውሎች አማካኝነት የተከወነ አልነበረም። በወቅቱ ይህ ሊሆን የሚችልበት አንዳችም ታሪካዊ ዐውድ ሊኖር ይችል ነበር ተብሎ አይታሰብም።

በኢትዮጵያ የዘመናዊ ሀገርና መንግስት ምስረታ በቀጥታ የተፈፀመው በመሳሪያ ኃይል ነው። ኃይለኛው ደካማውን አስገብሮ ነው። በሰሜን ጐጃምን፣ ጐንደርን፣ ወሎን፣ ትግራይን፣ በመሳሪያ ኃይላቸው ያስገበሩትና በደቡብም ተመሳሳይ በሆነ መንገድ በጣም ብዛት ያላቸውን የራሳቸውን ታሪክ፣ ባህል፣ ቋንቋ የመሬት ስሪት አስተዳደር ወዘተ የነበራቸውን ሕዝቦች በግዛታቸውም ያጠቃለሉት እነዚሁ መሳፍንት ናቸው።

የግዛት ማስፋፋት ዘመቻ በመሰረቱ በሰሜንም ይሁን በደቡብ ከነበሩ ሕዝቦች የእድገት ደረጃ ማለትም በኢኮኖሚ፣ በቴክኖሎጂ፣ በባህል፣

አብዱላሂ፤ ከደጃዝማች ባልቻ ሰፎ እስከ ራስ መንገሻ ዮሐንስ... የፈጸሙት አኩሪ ጀብዱ የጋራ ለሆነው አንድነታችን ድልድይ ሆነው አገልግለውናል።

እነዚህን ጀግና አባቶች ለአንድ ዓላማ፣ አንድ ግንባር ያዋላቸው ሀገራዊ አጀንዳ እንጂ፣ ንጉሳዊ ፍቅር ወይም አድርባይነት አለመሆኑ ከማናችንም ባይሰወርም፤ የዘመኑ የታሪክ ከሀደት ስብከት ተነድተን በአንድነት የሚያቆሙንን መስተጋብሮች አፍርሰን፣ የተናጥል ማንነትን የምንሻ ከሆነ፣ ነባሩን እውነታ ፍቀን አዲስ ማንነት ፈጥረን ወደ ገደሉ አፋፍ መገፋታችን የጊዜ ጉዳይ ከመሆን የሚታደገው አይኖርም። ለዚህ ምዕራፍ የፐ/ር መስፍን ጽሑፍ መደምደሚያ ይሁነን።

*«ኢትዮጵያዊነት ለብዙ ሺህ አመታት በመንግስትነት ታውቃ የኖረች ጥንታዊት የሰር መሰረታችን፣ የእናቶቻችንና የአባቶቻችን አገር መሆኗን ማወቅ ነው። ኢትዮጵያ ኅብረ ቋንቋ፣ ኅብር ሃይማኖት የሚንፀባረቁባት የሙሴ፣ የክርስቶስና የመሐመድ አገር መሆኗን ማወቅ ነው። ኢትዮጵያ ነፃነትዋን ያለማቋረጥ አስከብራ የኖረች ከሌሎች ጥቂት አገሮች ጋር ብቻ የምትሰለፍ መሆኗን ማወቅና ያንን ታሪክ ለመቀጠል ቃልኪዳን መግባት ነው።*

*«ኢትዮጵያ ለነፃነትዋና ለብሔራዊ ክብሯ በተለያዩ ዘመናት ቁጥር ስፍር የሌላቸው ልጆቿ በቆራጥነት የተሰውባት መሆኗን ማወቅና የዚህን መስዋዕትነት ዋጋ ለመክፈልና የአባቶቻችንን መስዋዕትነት በእኛ ለማደስ መቁረጥ ነው። ከሁሉ በላይ ኢትዮጵያዊነት በደስታም በሐዘንም፣ በግፍም በመከራም፣ በክብርም በውርደትም፣ ኢትዮጵያዊነትን መኖር ነው፤ ካልተኖረ ኢትዮጵያዊነት ባዶ ወግ ነው፤ ሲሞቅ የሚያወልቁት ሲበርድ የሚደርቡት ካባ አይደለም።»*

ኢትዮጵያዊነት

ኢትዮጵያዊነት ማተብ ነው፣ በአካልና መንፈስ ፅናት፣
በአበው ታሪክ እምነት መኩራት።





ኢትዮጵያዊነትን መካድ፣ የፍቅር አምላክን ሲሳይ፣
መርገጥ ነው እንደ አኩይ ጠባይ፣
የአንድነት አድባር ፈንግሎ፣ ለመናፍቃዊ ግዳይ፣
በትውልድ ላይ ሰቆቃ፣ የአካልና መንፈስ ስቃይ፣
ማንገሥ ብቻ ነው ውጤቱ፣ በራስም ላይ በሕዝብም ላይ።
የኢትዮጵያዊነት መሥፈርቱ፣ ነፃነት ነው ለአንድ ዜጋ፣
መንፈሳዊ ነው እሴቱ፣ የማይዳሽቅ ሲሥጋ፣
የማይገብር ለጠመንጃ፣ የማይተመን በዋጋ፤
መንፈሱን ቆርሶ ለመሸጥ፣ ሳይሆን እንደ ባንዳ መንጋ።
ወይ እንደ ትላንቶቹ፣ ለዙፋኑ ባርነት ሳይሆን፣
ወይ ለጦር መኮንኖች ምርጥ፣ ለማንበደድ ለአንድ ሰሞን።
ኢትዮጵያዊነት ክብር ነው፣ ለኃያል ከንድ የማይዳር፣
ሕዝባዊነት ነው መሥፈርቱ፣ የሕዝብ ወገን የሕዝብ እጋር፣
እንጂ፣ ለዘረኞች ቁማር፣ ለአንድ ጎጣ ቡድን ገባር፣
ሊሆን እንደሚጣል ዕጣ፣ አይደለም ሎተሪ ቢጋር።
የየጎጣው ከልል ጣኦት፣ እፍ እንዳለበት ጭቃ ጡብ፣
የሚፍጠረጠር ለቀን ሩብ።

......

*ባለቅኔው ሎሬት ፀጋዬ ገ/መድኅን*
*«ኢትዮጵያዊነት» በማለት ከገጠመው የተቀነጨበ*

# ምዕራፍ ሁለት

# የኢትዮጵያ ታሪክ አተራረክ

የታሪክ ሰነድ በአንባቢ ዘንድ ተቀባይነት አለው ሊባል የሚችለው ለእውነታው የሚያቀርበው ምንጭ ሲኖረው ነው፡፡ ከእውነታ ተነስቶ፤ ምንጭ ኖሮት በመረጃ የተደገፈ ታሪክ ተቀባይነቱ ከፍ ይላል፡፡ እንዲህ አይነት የታሪክ ሰነድ በየትኛውም መስፈርት ሊካድ የሚችል አይደለም፡፡ በኢትዮጵያ ታሪክ ጥናት እክል እንደሆነ የሚነገርለት የታሪክ አመዘጋገብም ይሁን አተራረክ መሰረቱ ሁለትና ሶስት ትርጉሞች ያሉት መሆኑ ነው፡፡ አንደኛው ወገን የታሪክ አመዘጋገብና አጠናን ዘዴ (Historical Methodology) ምንጭና መዳረሻ አለው ብሎ የሚነሳ ነው፡፡ በዚህ መንገድ የተጠኑ የታሪክ ሰነዶች በኢትዮጵያ የታሪክ አመዘጋገብ የራሱን እይታ ይዞ የሚበየን ነው፡፡ ሁለተኛው ወገን የታሪክ አመዘጋገብ ከዜና መዋዕል፣ ከአፈ-ታሪክና መሰል የመረጃ ቋቶች ተሰብስበው በህዝብ ዘንድ ተቀባይነት ያገኙ





የታሪክ ድርሳናትን ይወክላል፡፡ እነዚህ ድርሳናት የታሪክ አመዘጋገብ ከሚሻቸው ከመረጃ፣ ከተዓማኒነትና ጥሬ እውነታን መሰረት ካደረጉ ሁነቶች አንፃር ጉድለቶች ያሉበት ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

በእስከአሁኑ ሂደት መረጃና ምንጭን መሰረት ያደረጉ የኢትዮጵያ የታሪክ ድርሳናትን ለመስራት ሙከራ የተደረገባቸው ጅምር ስራዎች በህዝብ ዘንድ ገና አልሰረፁም፡፡ ከዚህም በላይ የምርምር መንገድን በመጠቀም የተጠኑ የአገሪቷ የታሪክ ድርሳናት ከኢትዮጵያውያኑ ይልቅ የውጭ ሀገር ባለሙያዎች የተሻለ የሚያውቋቸው ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡ ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ የተጠኑ የታሪክ መዛግብት ለሕዝቡ መዳረስ አለመቻላቸው፤ በአንፃሩ ሕዝቡን ለተሳሳተ የታሪክ ትርክት ተጋላጭ እንዲሆን አድርጎታል፡፡ በመሆኑም አብዛኛው ሕዝብ በአፈ-ታሪክ፣ በዜና መዋዕሎችና በስማ በለው ላይ የተመሰረቱ ታሪኮችን በደፈናው ለመቀበል ተገዷል፡፡

ከነዚህ የመረጃ ቋቶች የሚቀዱ የታሪክ ድርሳናት አብዛኛውን ሕዝብ ለተሳሳተ የታሪክ አተራረክ ከማጋለጡም በላይ፣ ታሪክ የተወሰነን ቡድን ፍላጐት ማሟያና አተራረኩም ወገንተኝነት የተጫነው እንዲሆን አድርጎታል፡፡ በ1920ዎቹ አካባቢ የኢትዮጵያ ታሪክ ይከትቡ የነበሩ ልሂቃን የጽሁፎቻቸው ዋነኛ ተልዕኮ ለመንግስት ባለሥልጣናት በሚመች መልኩ የተከተበ መሆኑን ማረጋገጥ ነበር፡፡ የወቅቱ የአፃፃፍ ዘዴ ክርስቲያናዊ ዳራዎችን በመጠቀም፤ ዙፋኑንና አገዛዙ እውቅና እንዲያገኝ ከመትጋቱ ባለፈ፤ የሥርዓቱን ቅቡልነት የማሳደግ ፖለቲካዊ ዓላማ ያነገበ ነበር፡፡ እንዲህ ያሉ ተረኮች መነሻቸው መጽሐፍ ቅዱስ መሆኑ ለሁለት አበይት ክፍተቶች ተጋላጭ አድርጓቸዋል፡፡

የመጀመሪያ ክፍተት መጽሐፍ ቅዱስን መሰረት ያላደረጉ የእምነት ክፍሎች በዚህ መንገድ የቀረበውን የኢትዮጵያ ታሪክ አምነው እንዲቀበሉ ማድረግ አለመቻሉ ነው፡፡ ከክርስትና (የተወሰነው የክርስትና ክፍል) ወገን የሆኑ የተወሰኑ የሕብረተሰብ ክፍሎች የተረኩን እውነታና ይዘት አግባብ

መሆኑን መቀበላቸው ብቻውን የታሪኩን ሙሉ ገፅ የሚያስረዳ አይሆንም፡፡ የሥርዓቱን ዙፋን ለመጠበቅ ሲባል በወቅቱ የእምነት ድርሳናትን ማዕከል አድርገው የተከተቡ የታሪክ ድርሳናት ዘመን ተሻጋሪ መሆን አልቻሉም፡፡ በአሁኑ ጊዜ የቀደመ አተራረክ መንገድ አልያም መዛግብት ጠቅሰን «የኢትዮጵያ ታሪክ ይህን መሰል እውነታ ነበረው» ብለን በጋራ ለመስማማት የሚያስደፍር እውነት እንዳይኖረን አድርጎናል፡፡ የአገር ታሪክ የአንድን ወገን ፍላጎት ማርካት መሰረት አድርጎ ሲከተብ፤ በሁሉ ዘንድ ሊኖር የሚገባው የተዓማኒነት ጥያቄ ጉደሎ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡

ሁለተኛው ክፍተት የቀደመው የታሪክ አመዘጋገብ ዘመን ተሻጋሪ በሆነ ቁጥር የወቅቱን የታሪክ እውነታ ወደ አፈ-ታሪክነት ደረጃ እንዲያሽቆለቁል የማድረጉ እውነታ ነው፡፡ መነሻቸውን መፅሐፍ ቅዱስ አድርገው ወደሕዝብ የሚወርዱ ተረኮች በሂደት የመዛግብት አካል ከመሆን ይልቅ እንደ ተረት ተረት ከትውልድ ትውልድ በቅብብሎሽ የአፈ-ታሪክ ባህርይን ለመላበስ ይገደዳሉ፡፡ በዚህ መንገድ የሚተላለፉ ድርሳናት መሰረታቸው በተጻፈ መረጃ ላይ የተደገፈ አለመሆኑ፣ ብሎም አፍአዊ ቅብብሎሹ ጎልቶ መደመጡ ወደኋላ መለስ ብሎ የፅሁፍ ማስረጃዎችን ለሚፈልግ አካል የሚቻል እንዳይሆን ያደርገዋል፡፡

ከዚህ ሁሉ ውጥንቅጥ ጀርባ የኢትዮጵያ ታሪክ ወገንተኛ እንዲሆን ካደረጉ ምክንያቶች መካከል ፖለቲካ ዋነኛው ነው፡፡ በትውልድ አልያም በታሪክ አጋጣሚ የፖለቲካ የበላይነት የነበረውና ያለው (መንግስትም ሊሆን ይችላል) ማንኛውም አካል ታሪክን የሚመዘግብበት መንገድ ለወገንተኝነት እንዲጋለጥ ያደርገዋል፡፡ መንግስታት ባስተዳደሩባቸው ዘመናት የነበሩ የታሪክ እውነታዎች በሚመቻቸው መንገድ አዛንፈው ከመመዝገባቸው ባለፈ፤ ያለፈውን ዘመን የሚያዩበት መነፅር የተንሻፈፈ መሆን፤ ለቀጣዩ ትውልድ የተዛባ መረጃን በማሻገር የበኩላቸውን አሉታዊ ሚና ይጫወታሉ፡፡

አንድ ሥርወ-መንግስት በሌላ ሥርወ-መንግስት፣ ርዕዮተ-ዓለም በሌላ ርዕዮተ-ዓለም ሲተካ፤ አዲሱ ተተኪ የወደቀውን ሥርዓት ህፀፆች





አጉልቶ በማውጣት፤ ሥርዓቱ በእኩይ ምግባሮቹ ብቻ እንዲታወስ የማድረግ ዘመቻ ይከፍታሉ፡፡ ለምሳሌ በኢትዮጵያ የሥርወ-መንግስት ታሪክ ለአጭር ጊዜ ብቻ እንደቆየ የሚነገርለት የዛግዌ ሥርወ-መንግስት ምንነት ተመዝግቦ የሚገኘው ከእርሱ በኋላ በተተካው የሰለሞናዊ ሥርወ-መንግስት መሆኑ የትርክቱ ተዓማኒነት ዙሪያ ጥያቄዎች እንድናጭር እንገደዳለን፡፡

ለዚህም ነው የሰለሞናዊው ሥርወ-መንግስት የዛግዌን ታሪክ ሲፅፉ ከአሉታዊው የታሪክ ክፍል ጐን ለጐን እራሳቸውን የዘንፈቱ አስተካካይ አድርገው ለማሳየት ሲጥሩ የምንመለከተው፡፡ የአፄ ቴዎድሮስ ታሪክ ሌላኛው ማሳያ ነው፡፡ በወቅቱ በነበሩ መሳፍንትና የቤተ-ክርስቲያን ፀሐፍት አንፃር ሲታይ የአፄ ቴዎድሮስ ታሪክ ሙሉ ለሙሉ የጨካኝና የጨፍጫፊ ግብር ባለቤት አስመስሎ ያቀርባቸዋል፡፡ ንጉሰ ነገስቱ የመሳፍንቱን ግዛት በኃይል እየነጠቁ ለመሬት አልባ ደሃ ከማከፋፈላቸው ጎን ለጎን ሀገሪቷን ወደ አንድ ቅርፅ ለማምጣት ባደረጉት ጥረት ጥቅማቸው የተነካባቸው ግለሰቦችና ተቋማት የሚጽፏቸው ድርሳናት ቅኝቱ ከዚህ የዘለለ እንዳይሆን አድርጎታል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ ሰፊ መሬት የያዘችውን ቤተ-ክርስቲያን መሬቷን እየቀነሱ ለድሆች ከማደላቸው በተጨማሪ የቤተክርስቲያን አገልጋይ ካህናት ቁጥር የሚገደብ ህግ ማውጣታቸው ካህናቱና አስተዳዳሪዎቹ የንጉሠ-ነገሥቱን እርምጃ በበጐ አይን እንዳይመለከቱ አድርጓቸዋል፡፡

ከዚህ በተቃራኒ በ1960ዎቹ አካባቢ የነበረው ‹ያ ትውልድ› የአፄ ኃ/ሥላሴን መንበር ለመፈንቀል ከተጠቀመባቸው የማነቃቂያ ስልቶች መካከል የአፄ ቴዎድሮስ ምግባር ዋና ሆኖ ሲቀርብ እንመለከታለን፡፡ ንጉሠ-ነገሥቱ ከዝቅተኛ የሕብረተሰብ ክፍል ወጥተው ለታላቅ መንበር ከመብቃታቸው በተጨማሪ ለአገር አንድነት የከፈሉት ዋጋ ተምሳሌትነቱ በትውልዱ ልቦና ውስጥ እንዲሰርጽ በሥነ-ፅሁፉ እየተመዘገበ፣ በቴአትር እየተመደረከ ምስላቸው እንዲጐላ ተደርጓል፡፡ እንዲህ አይነት የፖለቲካ

ካርድ ጨዋታ ታሪክን ለሥርዓት ማባበያነት ከመጠቀም ባለፈ የታሪክ ፋይዳ የሚያበላሽ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

ታሪክና ፖለቲካ ለየቅል መታየትም መተርጎምም ይኖርባቸዋል፡፡ የታሪክ ክስተቶችን የሚያሳዩ መዛግብት የትናንትናን ሁነት የሚያሳዩ ሲሆን ተጠየቁም በጊዜው መሆን ይገባዋል፤ ፖለቲካ በበኩሉ የሚተነተነውም ይሁን ለተጠያቂነት የሚቀርበው በዛሬ ማንነቱና ነገ ሊሰራ ባቀደው አግባብ ብቻ መሆን ይገባዋል፡፡ በመሆኑም ወደኋላ ተመልሶ በዛሬ የልኬት ሚዛን ያለፈውን የታሪክና የፖለቲካ ሁነት እያመዛዘኑ ትክክለኝነቱን ለማስረገጥ መሞከር ፍፁም የተሳሳተ አካሄድ ነው፡፡

ከላይ የቀረቡ ማሳያዎች መሰረት አድርገን ካየን ሁላችንንም ሊወክል የሚችል «የጋራ ታሪካችን» ብለን የምንቀበለው ታሪክ የነጠረ እውነታን መሰረት አድርጎ የተቀመጠ የሆነ እንደሆነ ብቻ ነው፡፡ ይህ ማለት ግን ማንኛውም በመረጃ ደረጃ የተቀመጠ ታሪክ ከነጥሬ ማንነቱ እንቀበል ማለትም በራሱ አደገኛ አካሄድ ነው፡፡ የትኞቹም የታሪክ መረጃዎች የባለሙያ ትርጓሜንና ትንታኔ ይሻሉ፡፡ በደፈናው በጥሬው የሚዋጡ አይደሉም፡፡ በመሆኑም የመዛግብቱን ትክክለኛነት ከተለያዩ የማስረጃ መፈተሻ መንገዶች አንጻር አስቀድሞ ፈትሾ ማረጋገጥን ያስፈልጋል፡፡ የመረጃው አይነት ቀዳማይ ምንጭን (Primary Source) እና ካልአይ ምንጭን (Secondary Source) መሰረት አድርጎ፣ ከግራም ከቀኝም ያሉ ሰነዶችን መርምሮና ፈትሾ ከሚገኝ ጨመቅ የሚወጣ ድርሳን የጋራ ታሪክ ብለን ልንቀበለው እንችላለን፡፡ እውነተኛው የታሪካችን አካል ነው ብለን የምንወስደውም የዚህ ሁሉ ውጤት የሆነውን ጥራዝ ይሆናል፡፡

የታሪክ መዛግብት የባለሙያ ትርጉም ያስፈልጋቸዋል የምንለው የቀደመውን የታሪክ ክስተት ምንነት ለመረዳት የጊዜውን ማህበረሰብ፤ ቋንቋ፣ ባህል፣ የአስተዳደርና የፖለቲካ ባህል መረዳት ስለሚፈልግም ጭምር ነው፡፡ ያለበለዚያ በወቅቱ የተባሉ ንግግሮችን በደፈናው በአሁንኛ ቋንቋ





ለመተርጎም መንደርደር ከእውነታው እጅግ እንድንርቅ ከማድረጉም በተጨማሪ ጉዳቱ ያይላል፡፡ በአንድ ወቅት አፄ ቴዎድሮስ ለእንግሊዟ ንግስት ቪክቶሪያ የጻፉትን ደብዳቤ በማሳያነት እንጥቀስ፡-

*«...እስተዛሬ ድረስ አባቶቼ ነገሥታት ፈጣሪአችንን ቢበድሉት መንግስታቸውን ለጋላና ለቱርክ አሳልፎ ሰጥቶባቸው ነበር፡፡ ዛሬ ግን እኔ ከተወለድሁ ፈጣሪዬ ካመድ አንስቶ ኃይል ሰጥቶ ባባቶች መንግስት አቆመኝ፡፡ በእግዚአብሔር ኃይል ጋያሎችን አሰለቀቅኋቸው፣ ቱርኮች ግን ያባቴን መሬት ልቀቁ ብላቸው እንቢ ብለውኝ በእግዚአብሔር ኃይል ይኸው ልታገል ነኝ»*

የዚህን ደብዳቤ ጥሬ ትርጉም መስጠት የሚሻ ማንኛውም አንባቢ ጥቅሱ በደፈናው ሲታይ ንጉሱ «ኦሮሞዎች አገሪቷን ለማስተዳደር የሚመጥኑ አይደሉም» የሚል ትርጓሜ ሊሰጠው ይችላል፡፡ የታሪክ ልሂቃን የደብዳቤውን መልእክት ከጥሬ ትርጉሙ በዘለለ ንጉሱ በወቅቱ የገለፁብትን ቋንቋ፣ የመንግስት አስተዳደር ሥርዓት ምን መልክ እንደነበረው አስቀድሞ በማተት የተለየ ትርጉም ሲሰጡት እንመለከታለን፡፡ በምሁራኑ አተናተን የንጉሱ ንግግር «በኢትዮጵያ የነገሥታት ታሪክ ለረጅም አመታት ፀንቶ የቆየውና በፍትሐ መንግስቱም እውቅና ያለው መሪ ከሰለሞናዊ ሥርወ-መንግስት የሚቀዳ መሆን እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ በአባቶች መበደልና በፈጣሪ መቀየም ምክንያት ለዘመናት ፀንቶ የቆየውን የይሁዳ ነገድ ንግስና መንበር ከነገስታቱ ነጥቆ ለሌላ ወገን መተላለፉን ለማሳየት ንጉሱ ተጠቅሞበታል» ሲሉ ያትታሉ፡፡

የታሪክ ድርሳናትን በገለባው ለመተርጎም መሞከር፤ በተለይ በአንድ አገር ለምንኖር ዜጎች፤ የጋራ ታሪክ የሚባል ነገር እንዳይኖረን ስለሚያደርግ የባለሙያዎች ትርጓሜ የግድ ያስፈልጋል፡፡ በመሆኑም በኢትዮጵያ የታሪክ አተራረክ ዙሪያ ተቀራራቢ መግባባት እንዲኖር ትልቁን ድርሻ መወጣት የሚገባው የታሪክ ባለሙያ ነው የሚባለው፤ የታሪክ መዛግብት የባለሙያ ትርጓሜና አንድምታ የሚያስፈልገው በመሆኑ ነው፡፡

በኢትዮጵያ ታሪክ መሰረታዊ ችግር ተደርገው ከሚወሰዱ አበይት ሁነቶች መካከል የታሪክ ጐደሎ አቀራረብ ሌላኛው ነው፡፡ የኢትዮጵያ ታሪክ ተብሎ በተደጋጋሚ የሚጠቀሰው የነገስታቱን ታሪክ አጉልቶ የሚያቀርበው ክፍል ነው፡፡ ከነገስታቱ ቀጥሎ በስፋት የሚጠቀሰው የክርስቲያኑ ማሕበረሰብን የሚወክለው የኢትዮጵያ የታሪክ ክፍል ነው፡፡ ብዙውን ጊዜ የኢትዮጵያ ታሪክ የሚለው ቃል የአክሱም፣ የዛግዌ፣ የጐንደር፣ የሸዋ በጥቅሉ የሰሜኑን የአገሪቷ ክፍል የሚወክለው እንደሆነ ተደርጎ ሲቀርብ ይስተዋላል፡፡

የኢትዮጵያ ታሪክ ጎዶሎነት ችላ ብለን የተፃፈውን እንኳን ብንመለከት በገሀድ የማዳላትና የውግና ተረኮችን በስፋት መታዘብ እንችላለን፡፡ ለምሳሌ በ1519 አሕመድ ኢብን ኢብራሂም ወይም በተለምዶ አጠራሩ አሕመድ ግራኝ የተባለ የአዳል መሪ በክርስቲያኑ መንግስት ላይ ጦሩን አነሳ፡፡ በሚያስደንቅ የጦር አመራር ስልት የራሱን መንግስት ሊያጠፋ አኮብኩቦ የነበረውን የአፋርና የሶማሌ ሕዝብ ፍልሰት ገርቶ በክርስቲያኑ መንግስት ላይ ተደጋጋሚ ድሎች ተጎናጸፈ፡፡ በ1521 ሽምብራ ኩሬ ላይ በክርስቲያኑ ንጉሥ አፄ ልብነ-ድንግል ላይ የመጀመሪያውን ታላቅ ድል አገኘ፡፡ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ልብነ-ድንግል ለዐስራ ሦስት ዓመታት ካንድ ግዛቱ ወደሌላ እንደተዋከበ ሕይወቱ አለፈች፡፡ ይህ ማለት ከአፄ ድልናዖድ እስከ አፄ ልብነድንግል ባሉ ተከታታይ የንግስና ዘመናት ለአስራ አምስት አመታት ያህል የአህመድ ግራኝ ዘመነ-መንግስት በኢትዮጵያ ቢነግስም፣ መኖሩ እንኳ እስኪዘነጋ በታሪክ ጸሐፍት ዘንድ ሲዘለል እንመለከታለን፡፡

በሌላ በኩል ይህንን የጦርነት ታሪክ በሚመለከት የታሪክ ፀሐፊያኑ የአህመድ ግራኝን ገድል ወረራ በማለት ሲገልጹት፤ እነ አፄ ልብነድንግልም ሆኑ ቀደምቶቻቸው ያደረጉትን ተመሳሳይ ዘመቻ ግዛት ማስፋፋት የሚል ተቀጥላ ሲሰጡት ይስተዋላል፡፡ እንዲህ አይነት አጻጻፎች አንዱን ወገን ሲያስደስቱ ሌላውን የሚያስኮርፉ ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡ በዚህ መልኩ የሚጻፉ ተረኮች በተቀበልና አልቀበልም ንትርክ ምክንያት የጋራ የሚባል ታሪክ እንዳይኖረን እያደረገን ይገኛል፡፡





በኢትዮጵያ ታሪክ ከቤተ-መንግስት አንስቶ እስከ ንግድ ግንኙነት ብሎም እስከ ጦርነት ድረስ ልክ አሁን ባለው መልኩ የብሔር ስብጥር ነበር፡፡ ነገር ግን አሁን ላይ በግልፅ እንደሚታየው የተለያዩ ጉዳዮችን ታሳቢ በማድረግ ማለትም የጭቆናን ግብር ለአንዱ፤ የተጨቋኝነትን ጥቃት ለሌላው ለግቶ ለማከፋፈል በማሰብ ራስን ከታሪክ ተሳትፎ የማንፃት ሙከራ ይስተዋላል፡፡ ለምሳሌ ያህል ከ16 መ.ክ.ዘ አንስቶ ኦሮሞዎች ያልተሳተፉበት ጦርነትና ወረራ የለም፡፡ ከቀደሙ ነገሥታት መካከል አፄ ሱስንዮስ ከኦሮሞዎች ጋር የጠበቀ ግንኙነትና ወዳጅነት ነበራቸው፡፡ ንጉሱ ገና ባባታቸው ቤት ሳሉ በሕጻንነታቸው ቦረን የሚባሉ ኦሮሞዎች አባታቸውን ገድለው እርሳቸውን ማርከው ወስደው እንደልጃቸው አድርገው በመልካም አኳኋን ይዘዋቸዋል፡፡ በኋላም ቦረኖች ዳሞትን ሊወጉ ሄደው ከደጅአዝማች ዐስቦ ጋር ሲጋጩ ዐስቦ ድል መትተው «ሱስንዮስን ካላመጣችሁ እንጨርሳችኋለን» በማለታቸው ሱስንዮስን መልሰዋቸዋል፡፡ እነዚህና መሰል ተረኮች ከላይ የተጠቀሰውን አይነት የምደባ አመለካከት ለመሸሽ ሲባል ያልነበሩ እስኪመስል ድረስ ይዘለላሉ፡፡

ሌላኛው በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ የምንመለከተው ችግር የታሪክ ቅደም-ተከተላዊ አሰዳደር ነው፡፡ ግኙውም አንድን ታሪክ ከመነሻው ሳይሆን ከታወቀበት ጊዜ በመነሳት ከሌላኛው የማስከተል አሰራር ነው፡፡ ይኸውም አካሄድ የታሪኩ ባለቤት በሆነው ህዝብ ዘንድ የበታችነት ስሜት ከማሳደሩም በላይ በጠቅላላው የታሪኩ አወራረድ ምልዐት እንዲጎድለው ያደርገዋል፡፡ በመሆኑም ይሄ ትውልድ ሚናው ታሪክን መውረስ ሳይሆን ከየአቅጣጫው ያሉትን በእኩል መርምሮ በማዋሀድ የተሟላ የታሪክ ምስል መከሰት ይገባዋል፡፡

ለምሳሌ አጋዴንን ያስገበሩት ራስ መኮንን ናቸው፡፡ የአጋዴን ታሪክም ያለው ከዚህ በኋላ ነው ማለት ነው፡፡ ይኼ ትውልድ ግን ከዚያ በፊት ያለውን የአካባቢውን ታሪክ ከአፈ-ታሪኮች፣ ከስነ-ቃሎች ወይም

ከተረቶች በማሰስ በተለያዩ መንገዶች ማጣራትና እንደአንዱ የኢትዮጵያ ታሪክ አድርጎ መቀበል ይኖርበታል፡፡ እርግጥ ነው ይኼን ለመከወን ብርቱ የታሪክ ተመራማሪዎች ወይም ማህበራት መኖርን የግድ ይላል፡፡

እንግዲህ ይሄ ተፅፎ የሚገኘው የኢትዮጵያ ታሪክ የቤተ-ክርስቲያንና የነገስታት እንዲሁም የእጅ ፅሁፈት ሙያ የነበራቸው ጥቂት ብሄሮች ታሪክ ነው፡፡ የቀረው የኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክ የሚፅፈው አልተገኘም፡፡ በመሆኑም ጎደሎውን የኢትዮጵያን ታሪክ ስለማሟላት ከተወራ ቀዳሚው ወይም አዋጭ መንገድ የሚሆነው ከትውልድ ትውልድ በአፈ-ነቢብ የተላለፉ ታሪኮችን በመሰብሰብ፣ በተለያዩ መለኪያዎች ውስጥ እያሳለፉ በማንጠር ወደ እውነታው ለመጠጋት መሞከር ነው፡፡

ሌላው ደግሞ ከነጉድለቱና ወገንተኝነቱም ጭምር የኢትዮጵያ ታሪክ ከአንድ አቅጣጫ ማለትም ከፖለቲካና ከነገስታት አንፃር ብቻ መፃፉም ምልዐትን ይነሳዋል፡፡ የኢትዮጵያን የጋራ ታሪክ ምስል ለመፍጠር ወይም ከተድበሰበሰበት ወደብርሃን ለማውጣት የህዝቦች ህይወት ሊፃፍ ይገባዋል፡፡ ይኸውም ማለት የሀገሪቱ ህዝቦች የንግድ ታሪክ፣ የማህበራዊ ግንኙነት መስተጋብር ከመሳሰሉት ሌሎች አንፃሮች ማጥናትና መመርመር ከተቻለ እጅግ ጠቃሚ አስተዋፅኦ ይኖረዋል፡፡

የህዝቦች ታሪክ ሲባል እንግዲህ ዝርዝሩ ብዙ ነው፡፡ ማለትም የባህል ታሪክ፣ የንግድና ኢኮኖሚ ታሪክ፣ የጥበብ ታሪክ፣ የሀይማኖት ታሪክ፣ የፖለቲካ ታሪክ ወ.ዘ.ተ ተደምረው ነው ታሪክ ሊባሉ የሚችሉት፡፡ በታሪክ ውስጥ አነስተኛ ስፍራ የሚሰጠው የፖለቲካ ታሪክ፣ በኢትዮጵያ በግልባጩ ብቸኛ የታሪክ ስፍራን ይዞ በመገኘቱና የፖለቲካ መጠቀሚያ በመሆኑ ነው ምንጊዜም የችግሮች ሁሉ መፍለቂያ ሆኖ የተገኘው፡፡





## ምዕራፍ ሦስት

# እስልምና እና ኢትዮጵያዊነት

ነቢዩ መሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) እ.ኤ.አ. ከ610-615 መካ ውስጥ ያስተምሩ በነበረበት ወቅት በደረሰባቸው ብርቱ ተቃውሞና ማሳደድ ከጥቂት ተከታዮቻቸው መካከል ብዙውን ቁጥር (ልጃቸው ሩቅያን እና አጎታቸውን ጨምሮ) ወደ ኢትዮጵያ ለመላክ ተገደው ነበር፡፡ ይሄ ክስተት በዓለም የእስልምና ታሪክ ከፍተኛ ቦታ ማግኘት የሚገባው የተቀደሰ ተግባር ቢሆንም፤ በኢትዮጵያ የታሪክ-ውስታ የተሰጠው ቦታ እጅግ አነስተኛ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ የቀደሙ ፀሐፍት የኢትዮጵያን ታሪክ ከክርስትና ጋር ብቻ አቆራኝተው መመዝገባቸው ከዚያ ውጪ ያሉ እውነታዎች ታፍነው ለመቆየታቸው በምክንያትነት ይጠቀሳል፡፡

ነቢዩ መሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) በወቅቱ ተከታዮቻቸውን መጠለያ ይሆናችኋል ብለው መላካቸው በአገሪቷ አስተዳደር ላይ ያላቸውን መተማመን ከማሳየቱም በተጨማሪ፣ በወቅቱ ክርስትና የነበረበትን የእምነት

ሥነ-ምግባር ከፍታ የሚያሳይ ነው፡፡ ነቢዩ በባህል፣ በቋንቋና በሥነ-ልቦና የሚቀርቧቸውን እንደ ግብፅና ሶርያ ያሉ የአካባቢው አገራትን ትተው ኢትዮጵያን መምረጣቸው፤ ሰው በሰዋዊው ዝምድናና ማንነት የመከባበርና የመዋደድ አቅሙ የት ድረስ መሄድ እንደሚገባው ለማስተማር ፈልገው መሆኑን የታሪክ ምሁራን ያወሳሉ፡፡

የነቢዩ መሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ተከታዮች ወደ ኢትዮጵያ መምጣት በቀላል ቋንቋ «ስደት» ተብሎ ሊገደብ የሚችል አይደለም፡፡ በሳዑዲ አረቢያ እጅግ ከተከበረ ጎሳ የተገኙ ሰዎችና ሌሎች ተሰሚነት (የፖለቲካ ቁመና) ያላቸው ግለሰቦችም የጉዞው አካል መሆናቸው፤ ጉዞው ደህንነት የጋረጠው ስጋት ብቻ አለመሆኑን እንድንረዳ ያግዘናል፡፡ የጉዞው ተልዕኮ ተከታዮችን ከአደጋ ስጋት ማዳን ብቻም ሳይሆን፣ እስልምናን የማስፋፋት መንፈሳዊ ተልዕኮ ያነገበ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

ወደ ኢትዮጵያ የመጡት የነቢዩ ተከታዮች ከነቢያቸው ጋር የቆዩት ለአምስት አመታት ብቻ በመሆኑ፣ የሚያውቁት የቁርዐን ክፍል ውስን እንዲሆን አድርጎታል፡፡ እስልምና ዓለም-አቀፋዊ እምነት መሆን እንዳለበት የተገነዘቡት ነቢዩ መሐመድ (ሰ.ዐ.ወ)፤ የተከታዮቻቸው የተገደበ (ደኢፍ) የቁርዐን እውቀት ተምሳሌትነቱ፤ አማኞች በተገደበ አስተምህሮም ቢሆን እምነቱን ጠብቀው መዝለቅ እንደሚችሉ ለማሳየት ተጠቅመውበታል፡፡

የእምነቱ ምሁራን፣ ነቢያቸው እስልምና ህልውናው ተጠብቆ ሊዘልቅ የሚችልባቸውን ዐውዶች በሦስት ዋናዋና መንገዶች አሳይተዋል ብለው ያምናሉ፡፡ የመጀመሪያው ‹የመካ ሞዴል› የሚባለው ነው፡፡ ነቢዩ መሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) እስልምናን ማስተማር በጀመሩበት በመካ ከተማ የነበሩ ገዢዎች የእምነቱን ተከታዮች በማሳደድና በመግደል ይታወቃሉ፡፡ ምሁራኑ የመካን ተሞክሮ በመጥቀስ እስልምና ጨቋኝ በሆኑ ስርዐታት ውስጥ በእምነቱ ተከታዮች ላይ ግፍ እየተፈፀመም ቢሆን እስልምናን ከነህልውናው ማቆየት እንደሚቻል አስተምረዋል ይላሉ፡፡ ሁለተኛው የመዲና ሞዴል





የሚባለው ነው፡፡ በወቅቱ የመዲና ከተማ ለእስልምና መስፋፋት ትልቅ ስፍራ የሚሰጣት ምቹ ቦታ ናት፡፡ የመዲናን ተሞክሮ በመጥቀስ እምነቱ፣ በእስላም መንግስትና በሙስሊም ማህበረሰብ ውስጥ ተደላድሎ ሊኖር የሚችልበት እድል መኖሩን ነቢዩ ማመላከታቸውን የእምነቱ ምሁራን ያትታሉ፡፡ ሶስተኛው ከኛ ጋ የሚገናኘው የአቢሲኒያ ሞዴል የሚባለው ነው፡፡ ይኸውም እስልምና በሌላ ኃይማኖት ተከታዮች ውስጥ (በክርስቲያን መንግስት ስር) ሆኖም ቢሆን መፅናትና መስፋፋት እንደሚችል የኢትዮጵያን ተሞክሮ ለማሳያነት ተጠቅመውበታል፡፡ ኢትዮጵያ በነዚህና መሰል ተሞክሮዎች የተነሳ በእስልምና ታሪክ የገዘፈ ዓለም አቀፍ ቦታ ያላት ቢሆንም፤ እነዚህን እሴቶች በአግባቡ መጠቀም አለመቻላችን የአንድነት ታሪካችንን ጎዶሎ አድርጎብናል፡፡

እስልምና በኢትዮጵያ ታሪክ ሰፊ ቦታ ያለው ቢሆንም፤ የእምነቱ ነጻነት ከመንግስታዊ ሥርዓታት ጋር በእጅጉ የሚያያዝ በመሆኑ ተሞክሮውም እንዲሁ ይለያያል፡፡ ዶ/ር እድሪስ እስልምናን በመንግስት ሥርዓታት መፈራረቅ ያለውን መልክ በሚመለከት ያቀረቡት አጭር ጽሑፍ እውነታውን ጠቅልሎ ስለሚያሳይ እሱን መጥቀስ በቂ ይሆናል፡፡ የአክሱማዊት ኢትዮጵያ ሆነ እርሱን በተካው ረጅሙ ሰለሞናዊው ሥርወ-መንግስት (1285-1974) ታሪክ ውስጥ ስለ ሃይማኖት ነፃነት ተጠቃሽ መረጃ ማቅረብ ለታሪክ ሰዎች አዳጋች ይመስለናል፡፡ በርግጥ በ7ኛው ክፍለ-ዘመን አክሱማዊው ንጉስ (አስሀማ-ነጃሺ) ለመጀመሪያዎቹ የኢስላም አባላት የሰጠው ዲፕሎማሲያዊ ከለላ በታሪክ ከሚጠቀሱ የዴሞክራሲ መገለጫዎች ዋነኛ በመሆኑ ድንቅና የመላው ኢትዮጵያውያን ኩራት ነው፡፡ የሃይማኖተኞች ችግር እንጂ የሃይማኖቶች ግጭት የሌለብን መሆኑን አመላካችም ክስተት ነው፤ ስለ ክርስትናና እስልምና ኢትዮጵያዊ ግንኙነትም ስንገልጽ ይህ ታሪካዊ እውነታ በዋነኛነት የአስተሳሰባችንን ቅኝት እንዲመራው እንሻለን፡፡

በዛጉዌ ሥርወ-መንግስትም (1130-1285) በክርስትናና በእስልምና ኃይላት መካከል የነበረው ግንኙነት ከወራሹ ሰሎሞናዊው ሥርዓት አንጻር

የተሻለ ገጽታ እንደነበረው አይካድም፡፡ በዚህ ወቅትና በአክሱማዊቷ ኢትዮጵያ የመጨረሻ ዘመነ-ዓመታት ኢስላም በኢትዮጵያ እንደሰሜኑ ክርስትና መንግስታዊ መዋቅር ዘርግቶ እንደነበር ይታወቃል፡፡ የሸዋ ሱልጣኔት በቀጣይም የኢፋት ሱልጣኔት፤ የአዳልና የሐረር፣ የቤኒሻንጉል እንዲሁም የጂማና የጊቤ ኦሮሞ-ሙስሊም ሥርዓቶች፤ በወሎ የወረ ሼኾችና የማመዶች መስተዳድር፤ በዘመነ መሳፍንት የታየው ልፍቃሪ ሙስሊም የኦሮሞ ባላባቶች ሥርዓት ወዘተ… አገራችን ክርስቲያናዊ ብቻ ሳይሆን ኢስላማዊ ባህሪ የተላበሱ ሥርዓቶችን ጎን ለጎን ያስተናገደች ለመሆኗ አብይ ማስረጃዎች ናቸው፡፡

ከመካከለኛው ክፍለ-ዘመን ጀምሮ የአፄ ምኒሊክ "ኢምፓየር" እስከተገነባበት ባለው ዘመን ድረስ ይህች አገር ይበልጥኑ ደጋማ በሆነው አቢሲኒያ እና ሰፊ የቆዳ ስፋት በነበረው ቆላማው ኢትዮጵያን በሰፈው ተቆጣጥረውት በነበሩት ሙስሊሞች መካከል ዘመን-ጠገብ ግጭቶች (የግጭቶቹ ዋነኛ ምንጩና ምክንያቱ ሃይማኖት ወይም ኢኮኖሚ ወይም የሁለቱም ድምር ስለመሆኑ መሞገት እንሻም) እንደተስተናገዱ አይካድም፡፡ በአገሪቱ በአንድ ሃይማኖት ሥር የተነሱ የቀኖናና የሥነ-መለኮት ግጭቶችን በውይይትና በመቻቻል የማስተናገድ ሰፊ ባህል እንደሌለ ሁሉ ኢስላምንና ሙስሊሞችን በተመለከተ የተለየ ግንኙነትም አልነበረም፡፡ ሙስሊሞች የፖለቲካ ኃያሉን ይዘው በነበሩበት ዘመንም (በቂ ጥናት ባይኖረንም) ከእምነት ገደብና መረብ ወጥቶ ሌላውን እንደ ዜጋ የማቀፍ መንፈስ አላየንም፡፡

የኢትዮጵያን መንግስት በማዕከላዊው የዘውድ ሥርዓት ስር ያደራጁት አፄ ቴዎድሮስ፣ አፄ ዮሐንስ፣ አፄ ምኒሊክና አፄ ኃ/ሥላሴ «የክርስትና ሃይማኖት ለሀገር አንድነትና ለሀገር ግንባታ መሰረት ነው» የሚል አቋም ነበራቸው፡፡ ነገስታቱ ከተግባራዊ ጥቅም አንፃር በመውሰድ በአገሪቱ የእስልምና ሃይማኖት በተስፋፋባቸው አካባቢዎች የሃይማኖት





ፖሊሲያቸውን ለፖለቲካ ስትራቴጂ ሲጠቀሙ ተስተውሏል፡፡ በተለይም በ1870 ዓ.ም በቦሩ ሜዳ ጉባዔ የኢትዮጵያ ነገስታት የመንግስቱን ሃይማኖት ለሀገር ግንባታ ዋናው የፖለቲካ መሳሪያ አድርገው ከመውሰዳቸው በተጨማሪ፤ የሌላ እምነት ተከታይ የነበሩ የአገሪቷ ዜጎች በአገሪቱ መሰረት እንዳይኖራቸው ለማድረግ ያልተሳካ የፖለቲካ ውሳኔ እንዳስተላለፉ የታሪክ ድርሳናት ያስረዳሉ፡፡ በሀገሪቱ ዘመናዊ ታሪክ የእስልምና እምነትንና ሌሎች የሚሲዮናውያን ትምህርትን የሚቃወሙ ብዙ ተግባራት በነገስታት ትዕዛዝ ተፈጽሟል፡፡

የ1966ቱ ሕዝባዊ ንቅናቄ ያስገኘው ታላቅ ትሩፋት የሺህ ዓመታት የመንግስትና የሃይማኖትን ጋብቻ ፍቾ ማብሰሩ ነው ብንል ማጋነን አይሆንም፡፡ ጅምሩን ደርግ ወደ ሌላ አለማዊ ፅንፈኝነት (ወታደራዊ ሥርዓት) ባይቀለብሰው መልካም ነበር፡፡ አልሆነም፡፡ ይሁንና በእምነትና ሃይማኖት ካርድ ሳይሆን በዜግነት ላይ የተመሠረተ አለማዊ ኢትዮጵያ መገንባት አማራጭ የሌለው፣ በማንኛውም ወገን ሊቀለበስ የማይገባ አቅጣጫ መሆኑን እንገነዘባለን፡፡

የአገራችን እስልምና ከየትኛውም የዓለማችን ማሕበረሰብ ይልቅ የረጅምና ገናና ታሪክ ባለቤት ነው፡፡ የእስልምና ሃይማኖት ከሌሎች አገራት አስቀድሞ ኢትዮጵያን መዳረሻው እንዳደረገ ታሪክ ምስክር ነው፡፡ ይሁንና እምነቱን ከቀደመው ኢትዮጵያዊ ማንነቱ ጋ የሚያስተሳስረው የታሪክ ክፍል በአብዛኛው ማህበረሰብ ዘንድ እምብዛም ሳይታወቅ ለአመታት ቆይቷል፡፡ ለዚህ አንዱ ምክንያት የኢትዮጵያ የእስልምና ታሪክ በአግባቡ ተጠንቶ ለተቀረው ሕዝብ መድረስ አለመቻሉ ነው፡፡ በኢትዮጵያ የሙስሊሙን ማሕበረሰብ የሚመለከተው የታሪክ አካል በሚፈለገው መጠን ተመዝግቦ እንዲቀመጥም ይሁን እንዲነገር እንቅፋት ነበሩ ተብለው ከሚጠቀሱ መካከል የታሪክ ጸሐፍት ሚና ተጠቃሽ ነው፡፡ በታሪክ አመዘጋገብ ሂደት በወቅቱ የነበሩ እውነታዎችን ሆን ብለው በማምረጥ፣ ያልፈለጓቸውን

በመዝለልና የጠሉትን በማጠልሸት የታሪክ ጸሐፍት የተጫወቱት አሉታዊ ሚና ዋነኛው ነው፡፡

ከዚህ አንጻር የኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች ታሪክ የጸሐፍቱ የተዛባ ምልከታ ሰለባ እንደሆነ የእምነቱ ምሁራን ይጠቅሳሉ፡፡ አሕመዲን ጀበል እስልምና በኢትዮጵያ የነበረው አቢይ ቀለም ጎልቶ እንዳይታይ ከላይ የተዘረዘሩት የመረጣ፣ የመዝለልና ማጠልሸት ስልቶች ሰለባ መሆኑን ዘርዘር አድርጎ አትቷል፡፡

በኢትዮጵያ ታሪክ የእስልምና እምነት በታሪክ ጸሐፍት ዘንድ የመረጣ ስልት ሰለባ ሆኗል ከሚላቸው ወቅ ቶች መካከል ከ4ኛው እስከ 7ተኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ፤ ከ13ተኛው እስከ 16ተኛው መቶ ክፍለ ዘመን፤ እንዲሁም ከ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን አጋማሽ በኋላ ያሉ ጊዜያት ጉልህ ስፍራ ይዘው ይገኛሉ፡፡ በነዚህ ወቅቶች «ከነገሥታት መቀመጫዎች መካከል የአክሱም፣ የላሊበላ፣ የጎንደር፤ ከእምነት ተቋማት የኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን፣ ከሥርወ -መንግስታት የሰለሞናዊ ሥርወ-መንግስት ከሌሎቹ ይበልጥ ጎልተው እንዲታዩ የተደረገበት ወቅት ነበር» ይላል፡፡

ሁለተኛው የመዝለል አልያም ሆን ብሎ መተው የሚባለው ስልት ነው፡፡ በኢትዮጵያ ታሪክ በመዝለል እና ሆን ብሎ በመተው መንገድ ሰለባ ሆኗል የሚባለው የሙስሊሙ የታሪክ ክፍል መካከል የሙስሊም ሱልጣኔት በነበሩባቸው ወቅቶች የታዩ ጉልህ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ፣ እና ኢኮኖሚያዊ ክስተቶች፤ በወቅቱ የሐረር ከተማ በኢትዮጵያ ታሪክ የነበራት ጉልህ ስፍራ በሰፋት ሊጠና ሲገባው በጸሐፍቱ የመተው ስልት ምክንያት የሚገባትን ቦታ ማግኘት አለመቻሏ፣ ፀሐፊው በተለይም የኢትዮጵያ ኢስላማዊ ታሪክ ስፊ አሻራውን ያስፈረበት ዘመን ማለትም እስልምና ወደ ኢትዮጵያ የገባበትና የተስፋፋበት ዘመን (ከ7ተኛው መቶ ክፍለ ዘመን እስከ 12ተኛው መቶ ክፍል ዘመን) እውነታው ከነአካቴው ሆን ተብሎ መዘለሉን ይጠቅሳል፡፡





ሶስተኛው አንድን የታሪክ ወቅት፣ ክስተት ወይም ታሪካዊ ሰብዕና ማጠልሸት የሚባለው ስልት ነው፡፡ ከእስልምና ጋ በተያያዘ የ16ተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የሙስሊም ሱልጣኔቶች፤ በተለይም የአዳል ሱልጣኔት፤ በምስራቅና በመካከለኛው የኢትዮጵያ ግዛቶች የበላይነት ያገኘበት ታሪካዊ ወቅት አብዛኞቹ ጸሐፍት «የግራኝ አሕመድ ወረራ» የሚል ስያሜ ሰጥተውታል፡፡ የ«ግራኝ ወረራ» የሚለው መጠሪያ፤ በጊዜው ጦርነቱን ተከትሎ ለተፈጠሩ ውድመቶች የጥፋቱ ምንጭ የአንድ ወገን ካልተገባ የጦር አውርድ ዘመቻ ጋ የተሳሰረ ነው በሚል አጠልሽቶ የማቅረብ አካሄድ ነበር፡፡ የቀደሙ ነገስታት ከሙስሊም ኢትዮጵያውያን ጋ በተለያዩ ጊዜያት ያደረጓቸው ጦርነቶች የክርስትናን እምነት፣ ባሕልና ቁሳዊ ንብረቶች አውድሟል፣ የክርስቲያን ማህበረሰብ ግዛት በመፈረካከስ ለአገር ግንባታ ሂደት አሉታዊ አስተዋጽኦ አበርክቷል፤ የሚሉና መሰል ትንታኔዎች በጥቅሉ ለማህበረሰቡ የተዛቡ መልዕክቶችን አስተላልፏል፡፡

ቀዳሚው መልዕክት ከ13ተኛው እስከ 16ተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ባለው የኢትዮጵያ ታሪክ በሰሜንና በመካከለኛው ኢትዮጵያ አካባቢ ይኖሩ የነበሩ ሕዝቦች በእምነት፣ በዘር፣ በቋንቋ፣ በማሕበራዊና ፖለቲካዊ አቋማቸው ከገዢ መደቡ ጋር ተመሳሳይ የሆኑ ሕዝቦች ብቻ ያሉበት አካባቢ አስመስሎ ማቅረቡ ነው፡፡ ምንም እንኳ ጉዳዩ በዚህ መንገድ ተዛብቶ ይቅረብ እንጂ በአካባቢው የነበረው እውነታ ግን ከሚባለው የተለየ ነበር፡፡ በጊዜው የእስልምና ማሕበረሰብ እንደ ክርስቲያኑ ወገኖቹ ሁሉ በነዚህ አካባቢዎች ከጥንት አንስቶ የሰበሰበውንና ያዳበረውን ባህላዊና መንፈሳዊ ቅርስ ለዘመናት አስጠብቆ ካቆየባቸው መካከል ተጠቃሽ ነው፡፡

ሁለተኛው መልዕክት ከዚህ ቀደም የተካሄዱ ጦርነቶች በሙሉ ክርስቲያናዊ ለሆነው ባህላዊና መንፈሳዊ ቅርሶች ብቻ አውዳሚ ተደርጎ የመቆጠሩ ሁነት ነው፡፡ በጊዜው የተካሄዱ ጦርነቶች ላስከተሏቸው ውድመቶች ተጠያቂው የሙስሊሙ ማሕበረሰብ ብቻ ሳይሆን የክርስቲያን ወገን እጅ ያለበት መሆኑን መካድ አይገባም፡፡ የሙስሊሙ ማሕበረሰብ በዛ

ብለው በኖሩባቸው አካባቢዎች (በተለይ በንግድ ዘርፍ ተሰማርተው ይገኙ የነበሩ ዜጎች) የተካሄዱ ጦርነቶች፤ ለሃብትና ንብረት ውድመት ከፍተኛውን አስተዋጽኦ አበርክቷል፡፡

እነዚህና መሰል ሁነቶች እስልምናን የኢትዮጵያውያን መገለጫ ከሆኑ ሁነቶች መካከል አንዱና ዋነኛው አድርጎ እንዳይቀርብ አ ድርጎታል፡፡ ከዚህ ይልቅ እምነቱ፤ የውጭ ኃይል ፍላጎት የሚወክል ተቋም ተደርጎ መቅረቡ፤ እስልምና በኢትዮጵያ የነበረውን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ታሪካዊ አበርክቶት፤ በጽሑፍም ይሁን በቃል የተላለፉ ቅርሶች፤ እምነቱ አካባቢያዊና አገራዊ ውህደትን በማምጣት ረገድ የተጫወተው ሚና ቦታ እንዳያገኝ ምክንያት ሆኗል፡፡

በኢትዮጵያ የእስልምና እምነትንና የእምነቱን ተከታዮች በሚመለከት የደረጀ መረጃ ብለን ከምንጠቅሳ ቸው ሰነዶች መካከል አብዛኞቹ ምንጫቸው የአረብ ጸሐፍያን፣ አውሮፓውያን ተጓዦች እና የኢትዮጵያ ክርስቲያን ነገስታት ዜና መዋዕል ፀሐፊያን ደጃፍ ነው፡፡ እነዚህ መረጃዎች የኢትዮጵያ ሙስሊም የታሪክ ጥናት በሚመለከት የሚኖራቸው ፋይዳ እንደ ፀሐፊያኑ ፍላጎትና አላማ የተዛቡ እንዲሆን አድርጎታል፡፡ በተጨማሪም እስልምና ተኮር የሆኑ አብዛኞቹ ጥናቶች ከሰሜኑና መካከለኛው የኢትዮጵያ ክፍል ውጭ ባሉ የእምነቱ ተከ ታዮች ብቻ ላይ የሚያተኩር መሆኑ፤ የጥናቶቹ ይዘት ጎደሎ እንዲሆን አድርጎታል፡፡

እስልምና ተኮር የሆኑ ጥራዞች፤ በታሪክ ሙስሊሙ በርከት ብሎ በሚገኝባቸው አካባቢዎች ይታዩ የነበሩ የለውጥ እንቅስቃሴዎችም ይሁን ከክርስቲያኑ መንግስት ጋር ያደረጓቸው ግጭቶች ምክንያታቸው የውጭ ኃይል ፍላጎት የተንጸባረቁባቸው እንደነበሩ የሚያትቱት ይበዙበታል፡፡ ጸሐፊያኑ የግብጽ፣ የኦቶማን ቱርክና የአረብ መንግስታት ከግጭቶች ጀርባ የነበራቸው ሚናና ፍላጎት ላለመግባባቱ በዋና ምክንያትነት ሲጠቅሱት ይስተዋላል፡፡ (Islam in the Nineteenth Century Wallo, Ethiopia..... Hussein Ahmed-2001)





በመጨረሻም ዶ/ር እንድሪስ ሙሐመድ ኢትዮጵያን ማን ይታደጋት? በተሰኘ መጽሐፍ ውስጥ በባስተላለፉት ኃሳብ ጽሑፉን እንደምድም

*«ባለፉ ታሪካችን ውስጥ የተፈጸሙ ስህተቶቻችን በስህተታቸው አምነን ዛሬ ላይ ሊ ታሰቡና ሊደገሙ የማይገባ መሆኑን ተማምነን አዲስ አቅጣጫ እንዳንተልም እንቅፋት ሆኖናል፡፡ ታሪካዊ ሂሳችንን ሳንውጥ የተጨቆነውን አልተጨቆንክም ኢያልነው መልካም መንፈስ ይሰፍናል ብዬ አላምንም፡፡ ውጤቱ አደገኛ ነው፡፡ በታሪክ ተጠቃሚ የነበረው ወገን ለእርሱ የማይመችን ትንተና በተለያየ ሰበብ ሊገፋው ቢታይም ይህ ግን የተባበረን ኢትዮጵያ ሊገነባ አይችልም፡፡»*

# ምዕራፍ አራት

# የኢህአዴግ
# አዲሲቷ ኢትዮጵያዊ መልክ

ገዥው-ፓርቲ፣ በድል አድራጊነት መንግስታዊ ሥልጣኑን ጠቅልሎ ከያዘ በኋላ፣ መሪዎቹ ባዘጋጁቸው «የታሪክ ድርሳናት»፤ በውይይት መድረኮች እና በቁጥጥሩ ስር ባዋላቸው መገናኛ ብዙሀን አማካኝነት ኢትዮጵያ የምትባለዋ የ3 ሺህ ዓመታት ቀደምት ገናና ባለታሪክ ሀገር፣ በተሟላ ቅርፅ የተፈጠረችው በግንቦት ሃያው «ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች» ድል ማግስት እንደሆነ ለማሳየት በርካታ መንገዶችን ተጉዟል፡፡ ለዚህ ሰሁት ሰብከቱም በደጋፊ ማስረጃነት የሚያቀርበው የማዕከላዊ መንግስቱን ምስረታ የዘመናት ሂደት ሲሆን፤ ሂደቱንም «ታገልኩለት» ለሚለው ዘውግ ተኮር ፖለቲካ ቅቡልነት ሲል ለዘረፋ እና ለወረራ (ለቅኝ ግዛት) የተደረገ አስመስሎ እስከ ማቅረብ አድርሶታል፡፡

ኢህአዴግ ከአንድነት ይልቅ፣ በተናጠል ማንነት ላይ በተመሰረተ አዲስ ታሪክ እንዲቆሙ ያስገደዳቸው ህዳጣን ጨምሮ፤ በሀገሪቱ ከፍተኛ





ቁጥር ያላቸው ዘውጎችንም በራሱ የታሪክ ብያኔ አፍርሶ እንደ አዲስ ለመስራት አሀዱ ያለው ገና የሥልጣን እርካቡን እንኳ አደላድሎ ባልረገጠበት ጊዜ እንደነበር ይታወሳል፡፡ በተለይም ሰፊው አሮምኛ ቋንቋ ተናጋሪን፣ ራሱን የባለፈው ዘመን ብቸኛ የጥቃት ሰለባ አድርጎ በመውሰድ እንዲብሰለሰል ሲገፋ፤ አማርኛ ተናጋሪውን ደግሞ በቀደሙት አባቶቹ ታሪክ የሚያፍርና የሚሸማቀቅ ሆኖ እንዲቀር ለሁለት አስርታት ያልከለሰው ድርሳን፤ ያልደመሰሰው መዛግብት አልነበረም፡፡

አብዮታዊ ግንባሩ በታገለለት የዘውግ ፖለቲካ የሚበየነው ስርዓት ህልውናን ለማስረገጥ፤ በደምና አጥንት የቆሙ የአንድነት አምዶችን አፈራርሷል፤ የሕዝብ ለሕዝብ መስተጋብርን ለዘመናት ያፀኑ ቅፅሮችን ለመንደር ፖለቲካው ትግበራ ሰውቷል፡፡ ለከፋፋይ አስተዳደሩም በሀገር አቅኚነት ራዕይ ስር የተፈፀሙ የማንነት ጭፍለቃዎች፣ የራስ ገዝ አስተዳደር መናድ፣ የጦር ሜዳ እልቂቶች፣ የንብረት ውድመቶችን... እያጎነ ትልቁን ምስል ለማደብዘዝ ያለመታከት ሰርቷል፡፡ ለዚህ አይነቱ አፍራሽ ዓላማም እንደማቀጣጠያ የተጠቀመው የ«ታሪክ ተጎጂ» ወይም «ሰለባ» እንደሆኑ ቀን ከሌት የሚሰብካቸው ህዳጣን በጥቂት ልሂቃኖቻቸው ግፊት ያቀነቀኑትን የ«ተረሳን» አጀንዳ፤ እንዲሁም በኦሮሚያ፣ በደቡብ፣ በሐረር የተለያዩ ከተሞች የአፄ ምኒልክ ሠራዊት ያደረጋቸውን ዘመቻዎች ማሳካትን ተከትሎ የተከሰቱ የእርስ በርስ ጭፍጨፋዎች እና የባሕል ተፅእኖዎችን ነው፡፡

ከዚህም ሌላ ሥርዓቱ ለእንዲህ አይነቱ ትርክት ያመቸኛል ብሎ የመዘዘው የታሪክ ሰበዝ በጊዜው አማራጭ ያልነበረውን ጠንካራው፣ ደካማውን ጨፍልቆና አስገብሮ አሀዳዊ ሀገር የመገንባት ሂደትን በማንሸዋረርና ፈጠራ በመጨመር ለመሆኑ በርካታ ማሳያዎችን ማቅረብ ይቻላል፡፡ በዚህ አይነቱ ታግሎ የመጣል ትንቅንቅ ከዛላንበሳ እስከ ቦረና፤ ከቋራ እስከ ኦጋዴን የሚመተረው የዛሬይቷ ኢትዮጵያ ወሰን መፈጠሩን ሲክድ ቅንጣት ታህል ማንገራገር አልተስተዋለበትም፡፡ በነገራችን ላይ የዚህ

የፖለቲካ ጨዋታ አመንጪዎች ማዕከላዊ መንግስትን ለመመስረት የሚደረጉ ሙተጋግሎች ከነፍጥና መስዋዕትነት በቀር የተሻለ አማራጭ እንደሌላቸው፣ በዓለም ታሪከም የእነምኒሊክ የመጀመሪያው አለመሆኑን፤ እንደ አሜሪካንና አውሮፓውያንም ያሉ ታላላቅ ሀገራት በዚህ መሰል የእርስ በእርስ ደም መፋሰስ ውስጥ አልፈው፣ ዛሬ እኛም ጭምር በምኞትና በሰደት የምንቀላውጠውን ነፃነትና ብልፅግና የተትረፈረፈበት ሀገር መገንባት መቻላቸውን ጠንቅቀው የማወቃቸው ጉዳይ አከራካሪ አይደለም፡፡ እናም ሌላ ሌላውን ትተን ከእነአሰቃቂው ጭፍጨፋ ለዘመናዊቷ ኢትዮጵያ ምስረታ ጅማሮ የተከፈለውን ውጣ-ውረድ ብናስተውል፣ ሙት ወቃሽ የሆንባቸው በተከታታይ የመጡ ነገሥታትን ውለታ እንዲህ በቀላሉ ዘርዝሮ መጨረስ አይቻልም፡፡

የተዛነፈው ታሪክ

«ነገስታቱ የአንድን ብሔር የበላይነት ለማረጋገጥ ሲሉ የአገሪቷን ታሪክ ከእውነታው እጅግ ባፈነገጠ መልኩ ተይበዋል» በሚል መደምደሚያ የሚነሳው አዲሱ የኢትዮጵያ የታሪክ ድርሳን፤ «የተዛነፈ» ያሉትን አገራዊ እውነታ ለማስተካከል፤ የቀደመውን ትርክት ገልብጦ፣ በአዲሱ የታሪክ አተራረክ መከተብ ብቸኛው አማራጭ ሆኗል፡፡ ቀዳሚው ድርሳን በአዲስ መልክ ሲጻፍ፤ ያለፈውን ስህተት በማስተካከል ሰበብ ሌላ ስህተት መጨመር ግድ ብሏል፡፡ አዲሱ ስህተት የቀደመውን ጎዶሎነት ከመሙላት ይልቅ ይበልጥ አደገኛ ሁነቶችን የትረካው አካል ለማድረግ መሞከሩ፤ ተጨማሪ ቅራኔዎች መጨመሩ አልቀረም፡፡

«የኢትዮጵያ ታሪክ በጥቅሉ የጨቋኝ (አገዛዙ) እና ተጨቋኝ (ሕዝቦች) መካከል የነበረ ግንኙነት ነው» የሚል እምነት ያላቸው የአሁኖቹ ባለሥልጣናት፤ ግድግዳውን ለመናድ የጀመሩት አዲሱ የታሪክ ከታብ ከቀደመው ይበልጥ የከፋ ትርጉም እንዲይዝ ተደርጓል፡፡ በግንቦት ሃያ ማግስት የተጻፈው የኢትዮጵያ ታሪክ ማሕበረሰቡን በሁለት ከፍሎ





የሚበይን ሲሆን፤ ከቀደሙ ነገስታት የዘር ሃረግ ጋ ትስስር ያላቸው የሕብረተሰብ ክፍሎች፤ ከአጥፊ ጎራ መድቦ የሚወነጅል ሆኗል፡፡ የፖለቲካ ልሂቃኑ «ከዚህ ቀደም የነበረው የኢትዮጵያ ታሪክ አጻጻፍ የአንድን ማሕበረሰብ የበላይነት ለመበየን የተሰየመ በመሆኑ ማፍረስ ያስፈልጋል» በሚል መነሻ፤ የተዛባውን ጎዶሎ ከመሙላት ይልቅ፣ አዲስ ታሪክ መጻፍ ብቸኛ መንገድ አድርገውታል፡፡

በዚህ አገር ሥልጣን የያዘ ማንኛውም አካል የቀደመ ታሪክን የማፍረስና በምትኩ አዲስ የመጻፍ፤ ብሎም በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ በትውልዱ አዕምሮ ውስጥ የማስረጽ አቅም አለው፡፡ የአሁኑን የከፋ የሚያደርገው የተሳሳተውን መስመር ፈር ማስያዝ ይችሉ የነበሩ ምሁራን በእድሳት ሂደቱ ድምጽ እንዳይኖራቸው መደረጉ ነው፡፡ በኢትዮጵያ የታሪክ ትርክቶች ዙሪያ ልዩነት መኖሩ በራሱ ከፋት ባይኖረውም፤ ቅራኔዎቹን አጥብቦ ተቀራራቢ ወደሆነና አብዛኛው ማሕበረሰብ ሊቀበለው የሚችለው አገራዊ የታሪክ እውነታን መጻፍ አለመቻሉ፤ ልዩነቱ እንደሰፋ እንዲቀመጥ አድርጎታል፡፡

ከዚህ ቀደም በኢትዮጵያ ለግጭት ምክንያት የነበሩ፤ የብሔር ቅራኔዎች ለልዩነቱ ሞገደኛ ምክንያት አድርገው ሲያቀርቡ የሚሰማው ዘመናዊቷን ኢትዮጵያ ለመገንባት ከተከፈለው መስዋዕት ጋር የሚያያዝ ነው፡፡ የአገር ምስረታ ሂደት በሚመለከት የፖለቲካ ልሂቃኑ የያዙት አቋም ጫፍ ለጫፍ መቆም፤ ለልዩነት መባባስ ከፍተኛውን ድርሻ ይወስዳል፡፡

ሁሉን ሊያግባባ ይችል በነበረው «የኢትዮጵያ ታሪክ» የሚለውን «ኢትዮጵያዊነት» በሚመለከት የየብሔሩ ልሂቃን ያላቸው መረዳት አንድ መልክ ያለው አይደለም፡፡ ምሁራኑ እንወክለዋለን የሚሉት ብሔር ያለፈበት ውጣ ውረድ ሲተርኩ ግለሰባዊ ስሜታቸውን ይበልጥ ማጎናቸው፤ ተቀራራቢ የሚባሉ ምልከታዎች ቦታ እንዳያገኙ በሩን ዘግቷል፡፡ ከሙያ ውጭ በሆነ መንገድ ግለሰብ አልያም የተወሰነ ቡድን የኢትዮጵያን ታሪክ

በተረዳበትና በመሰለው መንገድ ተርጉሞ ማቅረቡ፤ የጋራ የሚባል እውነት ብቻም ሳይሆን በጋራ ሊያቆመን የሚችል የአንድነት መሰረት እንዳናገኝ እያደረገን መጥቷል፡፡ ያለፈን ታሪክ መለስ ብሎ ከመረዳት አንጻር አሁን ያለው የብሔር ቅራኔ ሶስት መሰረታዊ ምክንያቶች ያሉት ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

የመጀመሪያውን የኃሳብ መስመር የሚጋሩ የፖለቲካ ልሂቃን «የቀደሙ ነገስታት በኢትዮጵያ ያደረጓቸው የእርስ በርስ ጦርነቶች የቀድሞዋንና ገናናዋን ኢትዮጵያ ወደ ቀደመ የግዛት አንድነት ለመመለስ የተደረገ ዘመቻ ነው» የሚል እምነት አላቸው፡፡ «ዘመነ መሳፍንት» እየተባለ የሚጠራው የመካከለኛው የኢትዮጵያ ታሪክ የአገሪቷ ማዕከላዊ መንግሥት መፈራረሱና የአገሪቷ የግዛት አንድነት መናጋቱ ለቀደመ የግዛት አንድነት መበታተን ምክንያት ሆኗል ይላሉ፡፡ በወቅቱ በግዛት አስተዳዳሪዎቹ (መሳፍንቶቹ)ና ሥርዓቱን ለመናድ ነፍጥ ባነገቡ ኃይሎች መካከል የተካሄዱ ጦርነቶች «የተበታተነውን ማዕከላዊ መንግስት ፈር ለማስያዝ ብሎም ኢትዮጵያን ወደ ቀደመ ዝናዋ ለመመለስ፣ የተበታተኑ ግዛቶቿን ዳግም ለማዋሀድ የተደረጉ ናቸው» ብለው የሚያምኑ ምሁራንን ይወክላል፡፡ በምሁራኑ አመለካከት በአፄ ቴዎድሮስ ዘመነ-መንግስት እንደተጀመረ የሚነገርለት የግዛት አንድነት ዘመቻ፤ በአፄ ምኒልክ መገባደዱን ያትታሉ፡፡ በዚህ መንገድ የተገባደደው የአገር አንድነት ዘመቻ ኢትዮጵያን አንድ የማድረግ በጎ አላማ ያነገበ በመሆኑ፤ ሂደቱ ከዚህ አንፃር መታየት እንዳለበት ይሞግታሉ፡፡

ኢህአዴግ መንበሩን ከተቆናጠጠበት ዕለት አንስቶ ይህንን የታሪክ ትረካ ሲታገለው ቆይቷል፡፡ የግዛት ማስፋፋት ዘመቻዎች ከቀደመው የኢትዮጵያ ገናና ታሪክ ጋር የሚያያዝ አለመሆኑን ለማስረዳት፤ የኢትዮጵያ ታሪክ ከመቶ አመት የተሻገረ አይደለም ሲል ተከራክሯል፡፡ የግዛት አንድነት ኃሳብ አቀንቃኝ የሆኑ የአገሪቷ ምሁራን «የነፍጠኛ ሥርዓት ናፋቂ» በሚል ማሸማቀቂያ ከአደባባዩ ገለል እንዲሉ ተደርገዋል፡፡

ሁለተኛውን የኃሳብ መስመር የሚጋሩ ምሁራን የማርክሲስት-ሌኒኒስት ግራ ዘመም ፖለቲካ አቀንቃኝ የሆኑ የፖለቲካ ልሂቃን የሚወከሉ





ናቸው፡፡ ምሁራኑ የኢትዮጵያ ታሪክ የብሔር ቅራኔ የተፈራረቀበት መሆኑን የሚቀበሉ ቢሆንም፤ በቅራኔዎቹ አጻጻፍ ዙሪያ ከመጀመሪያዎቹ በተለየ የራሳቸውን አተያይ ያቀርባሉ፡፡ ልሂቃኑ ከዚህ ቀደም የተከሰቱ ግጭቶች መሰረታዊ መነሾው ተጠንቶ መፍትሔ ሊያገኝ የሚገባ መሆኑን ይጠቁማሉ፡፡ በመሆኑም እንደ ልሂቃኑ አረዳድ «ከዚህ ቀደም በኢትዮጵያ ፖለቲካ የገዢነቱን መንበር የተቆናጠጡ ነገስታት አገዛዝ ባህሪ በጥቅሉ ብሔራዊ ጭቆናን (National oppression) በአገሪቷ ያሰፈነ ነበር» ሲሉ ይመሰክራሉ፡፡ ይህ እውነታ ሲጨቆኑ ለነበሩ የሕብረተሰብ ክፍሎች መጥፎ አሻራ ትቶ አልፏል ብለው ያምናሉ፡፡

ነገስታቱ ሁሉን ሕብረተሰብ በእኩል ዓይን ከማየት ይልቅ ዘር፣ ቋንቋ፣ ሃይማኖትን ማዕከል ላደረጉ ልዩነቶች ትልቅ ቦታ ይቸሩ እንደነበር ያምናሉ፡፡ በመሆኑም የኢትዮጵያ ፖለቲካ መፍትሔ ያገኝ ዘንድ የብሔራዊ ጭቆና አራማጅ ግለሰቦችንና ሥርዓት መፍረስ በጊዜው ወሳኝ እንደነበር ያምናሉ፡፡ «የብሔሮች ጥያቄ ተገቢውን መልስ ሲያገኝ የኢትዮጵያ ህልውና በዚህ መሰረት ላይ ይታነጻል» የሚል አመለካከት አላቸው፡፡ በመሆኑም የቀድሞ መንግሥታትን ለመገርሰስ የተካሄዱ ትግሎች ዓላማ «ብሔሮች የራሳቸውን እድል በራሳቸው እንዲወስኑ ሲፈቀድላቸው ይስተካከላል» የሚል ነበር፡፡

ኢህአዴግ ታግልኩለት የሚለው ዓላማ ይህ እንደነበር ከባለሥልጣናቱ አንደበት በተደጋጋሚ ይነገራል፡፡ በየዓመቱ ህዳር 29 «የብሔር ብሔረሰብ ቀን» ተብሎ በከፍተኛ ወጪ እንዲከበር አዋጅ እስከ ማውጣት የተደረሰለት ድግስ የዚህ ዓላማ ተቀጥላ ነው፡፡ ምናልባትም የኢህአዴግን ፕሮፓጋንዳ በፍፁም ልቦና በማመን ይህ ጉዳይ የእርስ በእርስ ግንኙነትን ለማጥበቅና የልምድ ልውውጥ ለማካበት ታስቦ የተዘጋጀ ይመስል ይሆናል፡፡ ደጋግመን እንደተመለከትነው የበዓሉ ዋነኛ ማድመቂያ ከምዕተ-ዓመት በፊት «ተፈፀሙ» የተባሉ አገዛዛዊ በደሎች፣ ዘውግ-ተኮር ጥቃት መስለው እንዲቀርቡ በማድረግ ላይ ያነጣጠረ መሆኑን ነው፡፡

በየከብረ-በዓሉ ሰሞን አንዳንድ ፀጉራቸው ላይ ላባ የሰኩና ቆዳ ያገለደሙ ሰዎች በቴሌቭዥን እየቀረቡ ያለፉት ሥርዓታት ምን ያህል በደል እንዳደረሱባቸው ከመናገር ባለፈ፣ ዛሬም ቢሆን ተቃዋሚ ፓርቲዎች በብሔር ብሔረሰቦች ትግል ወደተሸነፈው አገዛዝ ለመመለስ የሚሰሩ መሆናቸውን አስታውሰው የኢትዮጵያ ሕዝብ በንቃት እንዲከላከልና የተገኘውን ድልም ነቅቶ እንዲጠብቅ ሲመከሩ ማድመጣችን ከበዓሉ ጀርባ ያለውን ቴአትር እንድንመለከት ይረዳናል፡፡

ከብረ-በዓሉ አዲሱ የታሪክ አተራረክ ላይ ተቀምጠው ሁለት ጠርዝ ያላቸውን ሀሳቦች ሲያቀነቅኑ እንመለከታለን፡፡ የኢትዮጵያ ታሪክ ብሔራዊ ጭቆና መሠረት ያደረጉ ግጭቶች የተፈራረቁበት በመሆኑ ሕገ-መንግስቱ በአንድ በኩል መፍትሄ ሰጥቶታል የሚል እምነት አላቸው፡፡ በሌላ መልኩ ከቀደሙ የብሔር ጭቆናዎች ጀርባ የተወሰነ የማሕበረሰብ ከፍል እጁ ያለበት መሆኑን በመፈረጅ፤ በአዲሱ ሥርዓት እርስ በርስ መተማመኑ እንዳይኖር ሴራው ተተብትቧል፡፡

በሶስተኛ ደረጃ ላይ የምናስቀምጣቸው ልሂቃን «በቀደሙ ነገስታት ዘመን የተካሄዱ የግዛት ማስፋፋት ጦርነቶች ከምዕራባውያን የቅኝ ግዛት ዘመቻ የተለየ አይደለም» ብለው የሚያምኑ ልሂቃን ይወከላል፡፡ የምሁራኑ ኃሳብ በአንድ ሉዓላዊ የአገር አንድነት ጥላ ስር ተሰባስቦ የቆየን ማሕበረሰብ ህልውና በተረጋጋ ሁኔታ ለማስቀጠል የሚያስችል አንዳችም ፋይዳ ያለው ባይሆንም፤ አመለካከቱ በዚህ ደረጃም ቢሆን ለከርከር መቅረቡ በራሱ ከፋት የለውም፡፡ ይሁንና ኃሳቡን ወደ አደባባይ ይዘው ብቅ በማለት የሚታወቁ የብሔር ልሂቃን፤ የሥርዓቱን ድከመት በመጠቀም ወጣቶች የኃሳቡ ማደሪያ ማድረግ መጀመራቸው ለአገር ህልውና አደገኛ መሆኑ አይቀርም ብለው የሚያምኑ ታዛቢዎች ይበረክታሉ፡፡ በዚህ መንገድ አቋማቸውን ማንጸባረቅ የሚሹ ግለሰቦች ትግላቸው ሁለት በሚጣረሱ ፍላጎቶች የተሞሉ መሆኑን ማየት ይቻላል፡፡





የልዩነት ሰበዞችን ይበልጥ በመምዘዝ፤ ኢትዮጵያ በውድቀት መንገድ ላይ መሆኗን የሚያጎሉ አስተያየት ሰጪዎች በርክተዋል፡፡ ፖለቲከኞቹ ለኢትዮጵያ ታሪክ ከሰጡት ጠባብ ትርጉም በመነሳት ብዙዎች «አንድን ብሔር በሌላ ብሔር ላይ እነሳስቶ፣ ሕዝቡን እርስ በርስ አጫርሶ፣ አገር አፍርሶ ይደመደማል» ብለው የሚተነብዩ ቢኖሩም፤ በአንጻሩ አገራዊ ውድቀት ከአንድ የልዩነት ጫፍ ተነስቶ ፍጻሜውን በቀደደው ቦይ የሚደመድም እንዳልሆነ የሚሞግቱም አልጠፉም፡፡

የኢትዮጵያ ፖለቲካ ከዕለት ወደ ዕለት ባለመረጋጋት ቀውስ ሲኳትን መታየቱ፤ መጨረሻው ከአገር ህልውና መክሰም ጋ ብቻ መነጸጸር የለበትም፡፡ የአገር አጣብቂኝ ተሞክሮዎች አንድን የፖለቲካ ማህበረሰብ ከገባበት ድብት ፈልቅቆ ወደ አዲስ ምዕራፍ የመሸጋገር ጅማሮ አድርገን ልንወስደው እንችላለን፡፡ በየአካባቢው የእርስ በርስ ግጭት መደራረብ፣ የግፋዐን ድምጽ መበራከት፣ የሥርዓቱ አመራሮች እርስ በርስ መተጋተግ፣ መከኖ በመውደቅ ላይ ካለው ኢህአዴጋዊ ፖለቲካ ሥርዓት ቀጥሎ ሊመጣ ለሚችለው የአዲሱ ትውልድ ተተኪ አመራር መንገድ ጠራጊ መሆኑንም መዘንጋት የለብንም፡፡

አገሪቷን ከተበላሸው የፖለቲካ አዙሪት ፈንቅሎ በማውጣት ከነህልውናዋ ሊታደጋት የሚያስችል የመፍትሄ ኃሳብ ያሻታል፡፡ ምን አልባትም በፖለቲካ አስተዳደር ምክንት፤ ወደፊት በሕዝቦች መካከል ሊፈጠሩ ከሚችሉ አለመግባባቶች ብሎም መጨራረሶች አገሪቷን ለመታደግ፤ ምሁራኑ ሚናቸውን አጉልተው የማሳየት ኃላፊነት አለባቸው፡፡ ይህ መሆን ካልቻለ፣ በቀላሉ ሊታረቁ የሚገባቸው የታሪክ እውነታዎች መፍትሄ ባለማግኘታቸው፤ ከገመትነውም የከፋ ውጤት አገሪቷ ልታይ እንደምትችል ማወቅ ተገቢ ነው፡፡

ውስጥ ምን ክፍተት ነበር? በኃይማኖት ታሪካችን ምን ህጸጽ ገጥሞን ነበር? በእርስ በርስ ግንኙነት ላለመግባባት ምክንያት የነበሩ ችግሮች ምን ነበሩ? የሚለውን ጥያቄ በሚገባ ነቅሰው በማውጣት፤ የቀጣዩ ዘመን የታሪክ አጠናን ምን መልክ ሊኖረው እንደሚገባ የጋራ መግባባት ላይ መድረስ ችለዋል፡፡ በመካከለኛው የአውሮፓ ታሪክ በተለያዩ ጊዜያት የተካሄዱ የእምነት ተሃድሶዎች (reformations) እና የአስተሳሰብ አብርሆቶች (renaissance) የዘመናዊው የታሪክ አጠናን ዘዴ ለውጥ ውጤት ናቸው፡፡ አውሮፓውያኑ ባለፈ ታሪካቸው የኃይማኖት ለውጥ ያስፈልግ እንደነበር ማመናቸው የእምነት ተኃድሶ እንዲመጣ ምክንያት ሆኗል፤ ኋላ ለቀረው አስተሳሰብ ለውጥ እንደሚያስፈልጋቸው በመረዳት በዚህም መስክ የተኃድሶ እንቅስቃሴ ማድረግ ችለዋል፡፡ ምዕራባውያኑ ዛሬ ለደረሱበት የቁስና የታሪክ ከፍታ ዘመናት ፈጅቶባቸዋል፤ ብዙ ዋጋም አስከፍሏቸዋል፡፡ የእርስ በርስ ግንኙነቱ ብዙ ወጣ ውረዶች ተስተናግደውበታል፡፡ አገራቱ የቀደመ የታሪክ አጠናን ዘዴያቸውን መቀየር መቻላቸውና የወደፊቱን በብልሀት ለመተለም መሞከራቸው፤ ዛሬ ለፀናው የፖለቲካ-ኢኮኖሚ ስርዓት መሰረት ሆኗል፡፡

ከዚህ አንጻር የአገራችን ምሁራን የታሪካችን ጠንካራና ደካማ ጎን፣ የነበሩ ክፍተቶችን በቅጡ መርምረው፣ ተረድተው ለቀጣዩ ትውልድ መረማመጃ የሚሆን መሰረት ማበጀት ሲገባቸው ይህንን ሲያደርጉ አንመለከትም፡፡ ለኢትዮጵያን ዘርፈ-ብዙ ችግሮች መፍትሄ ከፖለቲከኞች ስፈር ያለ ይመስለናል፡፡ ቢሮክራቶቹ የአገሪቷን ችግሮች የመፍቻው ቁልፍ በእጃቸው እንዳለ ከፍተኛ እምነት አለን፡፡ አገሪቷ የተዘፈቀችባቸው ኢኮኖሚያዊ፣ ባህላዊና ፖለቲካዊ አዙሪቶች በሙሉ በፖለቲካ ልሂቃኑ ብቸኛ አስተዋጽኦ የሚፈታ ይመስለናል፡፡

ያለፈውን፣ የአሁኑን እንዲሁም የመጪውን አጠቃላይ ሁነት በተግባር ማጥናትና ለቀጣይ ትውልድ የሚሆን ፍኖተ-ካርታ ማዘጋጀት የምሁራኑ፣ የፈላስፋውና የአሰላሳዮች ኃላፊነት መሆን ሲገባው፤ እኛ ግን





ለፖለቲከኞቹ ትተንላቸዋል፡፡ ፖለቲከኞች እቅድ አስፈፃሚዎች እንጂ ፕሮጀክት አርቃቂዎች መሆናቸውን ዘንግተናል፡፡ የአገራችን ፖለቲከኞች በሁሉም ቦታ መገኘትንና፤ ለሁሉም የአገሪቷ ችግሮች መፍትሄ አፍላቂ መስሎ ለመታየት መሞከራቸውን ካላወገዝን፤ እጣ-ፈንታችን ወደኋላ ከመንሸራተት የሚያቆመው አይኖርም፡፡

ከፖለቲከኞች የሁሉን «አዋቂነት» አባዜ ባለፈ የአገሪቷ መሰረታዊ ችግር ብለን ከምንጠቅሳቸው ምክንያቶች መካከል ከውጭ የተቀዳው የዘመናዊ ትምህርት ሌላኛው ማሳያ ነው፡፡ ለዘመናት የተሞከረው፣ አሁንም ድረስ ተግባራዊ እየሆነ ያለው የኢትዮጵያ የዘመናዊ ትምህርት በእስከአሁኑ ጉዞው ምን የሚጨበጥ ለውጥ አመጣ? የትምህርት ሥርዓቱ ኢትዮጵያዊ ለሆነው የጋራ ባህላችን፣ ታሪካችን፣ ማንነታችን ጠብቀን ለቀጣዩ ትውልድ እንድናሸጋግር ምን ሚና ተጫውቷል? የትምህርት ሥርዓቱ ምን ያህል ተመራማሪ፣ ጠያቂ፣ አሰላሳይ ትውልድ ፈጥሯል? የከፍተኛ ትምህርት ተቋሞቻችን ካለፉ ትውልዶች የተሻለ ማሰብ የሚችል ዜጋ አፍርተዋልን? ለሚሉ መሰረታዊ ጥያቄዎቻችን የምናገኘው ምላሽ ምንም የሚል ነው፡፡

የአፄ ኃይለሥላሴ ዘመናዊ ትምህርትና ዘመናዊ ትምህርቱ ያፈራቸው ዜጎች ከአላማው ጋ አራምባና ቆቦ መሆን ለትምህርት ሥርዓቱ መክሸፍ አንድ ማሳያ ነው፡፡ ኢትዮጵያ ለረጅም ዘመናት በኃይማኖታዊ አስተምህሮና ባህላዊ እሴቶች የተገነባች አገር መሆኗ ይታወቃል፡፡ የኃይለ ሥላሴ የዘመናዊ ትምህርት ሥርዓት ያፈራቸው ተመራቂዎች እነዚህን እሴቶች የሚያፈርሱ ሆነው ብቅ ብለዋል፡፡ ተማሪዎቹ ከአገሪቷ ነባራዊ ሁነትና፣ ከሥርዓቱ መሰረት ጋር በሚቃረን የትምህርት ሥርዓት ስር ማለፋቸው በስተኋላ ለተከሰተው ምስቅልቅል በር ከፋች ሆኗል፡፡ ዘመናዊ ትምህርት ሲከታተሉ የነበሩ የያ-ትውልድ ወጣቶች የተማሯቸውና ያነበቧቸው ጥራዞች የግራ–ዘመም ርዕዮተ-ዓለም ውላጅ የሆነው የኮሙኒዝም-ሶሻሊዝም መርህ የሚፈለገውን ውጤት ማምጣት ሳይቻለው

አለመቻላችን ነው፡፡ ምንአልባትም የዚህች አገር ታሪክ ከስሜት ነፃ በሆነ መንገድ ተጠንቶ ቢሆን ኖሮ በጎውን ብቻ ሳይሆን ደካማ የሚባሉ የታሪክ ውርሶቻችን ሁሉ እንኳ ሳይቀር ከነደካማ ማንነታቸው ጭምር የጋራ ታሪካችን ውህድ አድርገን በተቀበልናቸው ነበር፡፡

ያለፉ በጎም ይሁን ክፉ እውነታዎችን በመካድ ወደየጋራ ታሪክ ማዕቀፍ መምጣት መሞከር ከጥቅሙ ጉዳቱ ያይላል፡፡ አፄ ዮሐንስን ጨምሮ ሌሎች ነባር መንግስታት በሙስሊም ወንድሞቻችን ላይ ያደረሱትን በደል ፍትሃዊ ነው ብሎ፤ በአንፃሩ አህመድ ግራኝ በቤተክርስቲያናት ላይ ያደረሳቸው ውድመቶች ኢ-ፍትሐዊ ናቸው ብሎ መፈረጅ በሌላ መልኩም የግራኝ አህመድን ጦርነት «ወረራ» ብለን የአፄ ምኒልክ ወደ ደቡብ ያደረጉት ዘመቻ «ግዛት ማስፋፋት» ነው ካልን፤ ሚዛናችን ከወገንተኝነት የፀዳ ስለማይሆን ተቀባይነቱም የዛኑ ያህል ይሆናል፡፡ እውነታዎቹ በአንድ ወቅት የአገሪቷ አጥፊ የታሪክ ክስተቶች መሆናቸውን መቀበል ካልቻልን፤ ንትርኩ ሁኔታዎች በነበሩበት እንዲቀጥሉ እድል ከመስጠት የዘለለ ፋይዳ አይኖረውም፡፡

የታሪክ ግምገማችን ከወገንተኝነት የጸዳ ከመሆኑ ባሻገር ከዋኔዎችን ለመበየን ድርጊቱ ከተፈጸመበት ወቅትና አውድ አፈንግጦ ለማየት መሞከር የሚገባ አይሆንም፡፡ ከዘመናት በፊት የተፈፀሙ ሁነቶችን በዛሬ ግንዛቤ ለመዳኘት መሞከር ፍፁም የሆነ ስህተት ላይ እንድንወድቅ ያደርገናል፡፡ አንድ የታሪክ ሁነት የተፈፀመበትን ወቅት ጊዜውን ሊገልጽ የሚችል የራሱ የሆኑ ቀለሞች ይኖሩታል፡፡ እነዚህ ቀለሞች በወቅቱ የነበረውን የባህል፣ የስነ-ልቦናና የመንግስታዊ ስርዐት መልኮች ብለን ልንከፋፍላቸው እንችላለን፡፡

በመሆኑም ባለፈው ታሪካችን በጋራ የምናምናቸው ስህተቶች ይኖራሉ፡፡ በአንጻሩም በጋራ ትክክል ናቸው ብለን የምንቀበላቸው ድርጊቶችም ይኖራሉ፡፡ ሌሎች እንዲሁ በጋራ ሊያስማሙን የማይችሉና





ሁላችንም የማንቀበላቸው ጉዳዮች ይኖራሉ፡፡ ቁም-ነገሩ ከዚህ በኋላስ ምን መሆን አለበት የሚለው ነው፡፡ የውይይታችን መድረሻ ከዚህ በፊት በነበረው መንገድ እንቀጥል የሚል ከሆነ ውጤቱ ምን ሊሆን እንደሚችል መገመት አይከብድም፡፡ ከላይ እንዳየነው ከሌሎች አገራት የጦርነት ታሪኮች አጥፊነቱ በእጅጉ ያነሰው የአገራችንን የጦርነት ታሪክ በአዲስ አረዳድ ለመመልከት ያልተቻለባቸው የተለያዩ ምክንያቶች አሉ፡፡ የትምህርት ቤቶቻችን አወቃቀር ድክመት፣ ስርዓተ-ትምህርቱ ጥናትና ምርምርን ማዕከል ያደረገ አለመሆን፣ ታሪኮቻችንን በአብዛኛው የሚፅፉልን የውጭ አገር ዜጎች መሆናቸው፣ የአገር ቤቶቹ ታላላቅ የታሪክ ፀሐፍት የሚፅፏቸው መፃህፍት ለአውሮፓ ዩኒቨርስቲዎች መሆኑ፣ ጥናቶች የሚታረሙትም የሚገመገሙትም እዚያው መሆኑና አንዳንድ ጥራዞች ወደሀገራችን ሲመጡም በላይብረሪ ተገድበው መቀመጣቸው ህዝቡ ዘንድ የመድረስ አቅማቸው እጅግ ውሱን አድርጎታል፡፡

በኢትዮጵያ የታሪክ ጥናት ትላልቅ ስራዎችን አበርክተዋል ከምንላቸው ምሁራን መካከል ፕ/ር ታደሰ ታምራት፣ ፕ/ር መርዕድ ወ/አረጋይ፣ ፕ/ር ሁሴን አህመድ፣ ፕ/ር ባህሩ ዘውዴ፣ ዶናልድ ሌቪን እና ማርካኪስን ተጠቃሽ ናቸው፡፡ ከዚህ ውጭ በሙያቸው የታሪክ ተመራማሪ ያልሆኑ ነገር ግን በፍላጐትና በተሰጥዖ የታሪክ ምርምር ያበረከቱ ግለሰቦችም ቀላል ግምት የሚሰጣቸው አይደሉም፡፡ ሌሎች በበኩላቸው ህዝባዊ ተደማጭነት ኖሯቸው ነገር ግን የታሪክ ተመራማሪ ባልሆኑ ግለሰቦች የሚተረኩ ታሪኮች አሉ፡፡ በነዚህ ግለሰቦች የሚተረክ ታሪክ ከሙያተኞቹ ይበልጥ በህዝቡ ዘንድ ከፍተኛ ተቀባይነት ሲያገኝ እንመለከታለን፡፡ ከባለሙያዎቹም ይሁን ታሪክን በፍላጎት ከሚሰሩትም በላይ እነዚህ ግለሰቦች ያላቸው ተደማጭነት የታሪክ እውነታዎችን በማዛነፍና በማጣረስ ረገድ አሉታዊ ሚናቸው ከፍተኛ ነው፡፡

ታሪክን በአዝማሪዎች ቅኝት ለመረዳት መሞከር፣ ከዜና መዋዕል ፀሐፊዎች ትረካ እውነታውን የምንለካ ከሆነ እውነትን በፍጹም



ጋዜጠኛ ኃይለመስቀል በሸዋምየለህ

# ክፍል ሁለት

# የኢትዮጵያ አብዮት





- የ'ያ ትውልድ'ሬ ስር-ነቀልተኝነት
- የልሂቅነት ዕዳ
- ምን አይነት አብዮት?
- አብዮቱ ከሸፈል?

ሩህሩህ አባት ሆነው ለመታየት (በተለይ ለምዕራባውያን) ካላቸው ፍላጎት አንፃር ያለ የሌለ የመንግስታቸውን የአፈና መሳሪያዎች አለመጠቀማቸውም ጠቅሟቸዋል፡፡

ተማሪዎቹ ለምን ስር-ነቀል ሆኑ? ለሚለው ጥያቄ የተለያዩ መላ - ምቶች ይቀርባሉ፡፡ በዋናነት ግን ‹ዝግመታዊ› እና ‹ጥቅል› በሚል በሁለት ልንከፍላቸው እንችላለን፡፡

የመጀመሪያው ‹ዝግመታዊ› የሚባለው ሙግት መዋቅራዊነትን በመያዝ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ኀልዮትን ይመረኮዛል፡፡ እንደዚህ መላ- ምት ከሆነ በዋናነት በአፄው ስርዓት የተከሰተው የኢኮኖሚ ውድቀት ለስር - ነቀልተኝነት ዋና ምክንያት ነበር፡፡ የኢኮኖሚው ድቀት የሀገሪቱን አራሾች ከመጉዳት አልፎ ተማሪዎቹን እንኳን የዩኒቨርስቲ ትምህርታቸውን ሲጨርሱ ስራ-አጥነት እጣ ፈንታቸው እንዲሆን አድርጓል፡፡ በተለይም የነዳጅ አምራች ሀገራት ህብረት (ኦፔክ) የነዳጅን ዋጋ በአራት እጥፍ መጨመሩ፣ ይህንን ተከትሎም የተካሄደው የታክሲ/ሴቸይንቶ ነጂዎች አመፅ በዋናነት ይጠቀሳል፡፡

በዚህም የስራ-አጥነት ጥያቄ ተማሪዎቹን ወደ ስር -ነቀልተኝነትና ይህንንም ስሜት ወደሌሎቹ ተማሪዎች እንዲያስተላልፉ አድርጓቸዋል፡፡

ከዚህ ተለዋጭ ጋር ተያይዞ የሚነሳው የአጠቃላይ ሀገራዊ ማሻሻያ እጦት ነው፡፡ የዘመናዊት ኢትዮጵያ ታሪክ እንደሚያሳየው መጀመሪያ በአፄ ምኒልክ ቀጥሎም በአልጋ ወራሽ ተፈሪ ዘመን በተለያየ መንገድ፤ ለዘመናዊ ትምህርትና ተያይዞ ለሚመጣው የዝመና እሴት የተጋለጡት ቀዳሚዎቹ ዘመናዊ ልሂቃን፣ መጀመሪያ ከኢያሱ ለጥቆም ከተፈሪ ጋር የተለያዩ ሪፎርሞችን በማድረግ ሀገሪቱን ለማዘመን ታትረዋል፡፡ አልጋ ወራሹ ተፈሪ ግን ወደ አፄነታቸው መንበር ሲጠጉ፤ ተጠግተውም መሰንበት እንደሚችሉ ሲያምኑ በአንፃራዊነት ዘመናዊ ሊባል የሚችል ህገ -መንግስት ካስረቀቁ በኋላ የልሂቃኑን ሀሳብና ልሂቃኑን ወደጎን ገፉቸው፡፡ ስርዓታቸውም ተቃዋሚ





ማሻሻያ ከማድረግ ይልቅ ባለበት እንዲረግጥ በመገደዱ የሀገሪቱ ችግሮች እየባሱ ሄዱ፡፡ ይህ ሁኔታ ሪፎርም ለሀገሪቱ እንደማይበጃት እንዲታመን አደረገ፡፡ ስርዓቱን ከመገልበጥ በመለስ መፍትሄ እንደሌለም ተሰበከ፡፡ እንደተባለውም "ጊዜው እየነጎደ ሲሄድ፣ ለህመሙ የሚታዘዘው ክኒን ምሬትም እየጨመረ መጣ፡፡"

የዚህ መላ-ምት ችግር ተጨባጭ ሁኔታውን በአግባቡ ያለመረዳት ይመስላል፡፡ ተራማጅ ስር-ነቀልተኝነት ከሪፎርም ሙከራ በኋላ (ያለመሳካቱን ተከትሎ) አብዮት እንደሚከተል ያምናል፡፡ እውነቱ ግን እንዲህ አይመስልም፡፡ ወጣቶቹን ወደ ስር -ነቀልተኝነት የመራቸው፣ የሀገሪቱን ችግሮች (ተጨባጭ ሁኔታዎች) በተለያዩ ኀልዮቶች ታግዘው በመመርመር የደረሱበት ድምዳሜ ነበር፡፡ ይህ ማለት የሀገሪቱን ችግሮች ለመመርመር የተጠቀሙበት ኀልዮት (Marxism-Leninism) ችግሮቹ ምንም ያህል ቅርፃቸውን ሳይቀይሩ መፍትሄውን ግን ከሪፎርም ወደ አብዮታዊ መልስ መሩት፡፡ የስር-ነቀልተኝነታቸው መንስኤ የሀገሪቱ ችግሮች ጥልቀት ሳይሆን ወጣቶቹ ለርዕዮተ -ዓለሙ የነበራቸው የቀደመ አፍቅሮት ነበር፡፡ ለርዕዮተ-ዓለሙ የነበራቸው ቅጥ-ያጣ ፍቅር ከታሪካዊ ዕውነቶች በላይ በለጠባቸው፡፡ የዛን ጊዜዋ ኢትዮጵያ የሆነችውን ሳይሆን ‹ሶስቱ የሶሻሊዝም ስላሴዎች› የተናገሩት ሁሉ የተሻለ ዋጋ ተሰጠው፡፡ ተጨባጭ የታሪክ ሀቆች ለኀልዮቱ እንዲስማሙ ተደርገው ይከለሱ ያዙ፡፡

ማርክሲዝ-ሌኒኒዝም «የብሄር ጥያቄ መሠረታዊ ተቃርኖ ነው» ስለሚል ብቻ፣ የኢትዮጵያ ታሪክ ለጥያቄው እንዲስማማ ተደርጎ ይተርጎም፣ ይተነተን ጀመረ፡፡ ለምሳሌም ያህል የትግራይ ወጣቶች፣ ትግራይ ከኢትዮጵያ ተነጥላ ኖራ የምታውቅ ይመስል «አገረ -መንግስት ('Nation') ነች» ብለው ያምኑ ነበር፡፡

ሌላኛው የዚህ መላምት ችግር የሚነሳው፣ ብዙዎቹ አብዮተኛ ወጣቶች የመጡበትን የተሻለ የቤተሰቦቻቸውን የኢኮኖሚ ደረጃ መዘንጋቱ

እ.ኤ.አ. በ1963 ዓ.ም. ከዛ ቀደም ብሎ የማርክሲስት ሌኒኒስትን ፅሁፎች ማንበብ የጀመሩ ወጣቶች በተጠቀሰው አካዳሚክ ዓመት ራሳቸውን 'Crocodile' በሚል «ህቡዕነትን ፤ ሚስጥሯዊነትን፣ አደገኛነትንና የማይገመት ባህሪን» ሲያመለክት የቻለ ስያሜ በመስጠት እንቅስቃሴያቸውን ጀመሩ፡፡ በዋናነት በብርሃነ መስቀል ረዳና ጥላሁን ግዛው የሚመራው ይሄ ቡድን እንደአንዳንዶች ግምት ከ50-75 አባላት ነበሩት፡፡ ራሳቸውን ሌኒን ለሚለው «የሙሉ ጊዜ አብዮተኝነት» ፅንሰ ሀሳብ ያስገዙት ወጣቶች ዩኒቨርስቲውን ዕውቀት እንደማግኛ ሳይሆን ፖለቲካዊ የማደራጃያ ተቋም አደረጉት፡፡ [ከዘመናት በፊት ይህን መሰል ጉዳይ ማኦ ዜዱንግ ሃህናን ፈርስት ኖርማል ቲቸርስ ትምህርት ቤት ሲገባ መፈፀሙን እነህ ወጣቶች ማንበባቸውን ልብ ይሏል፡፡] ሀሳባቸውን በመግለፅ ላይ የደረሰውን አፈና ከሙተቸት አልፈው ውስጥ ለውስጥ ከፍተኛ የሆነ የማደራጀት ስራ ለመስራት ችለዋል፡፡ ይሄን ፍላጎታቸውን ዕውን ለማድረግም አዲስ አበባ ውስጥ ያሉት ዩኒቨርስቲዎችና ኮሌጆች ያሏቸውን የየራሳቸውን የተማሪ ማህበራት አፍርሰው አንድ ወጥና ለሶሻሊስት ስርዓት የተገዛ ማህበር ለማቋቋም ታተሩ፡፡ ከብዙ ውጥንቅጥ በኋላ እ.ኤ.አ. በ1966ዓ.ም. ተሳካላቸው፡፡ ከዛ በፊት የተለያዩ የተማሪ መጽሔቶች ቢኖሩም፣ ዋንኛ ግባቸው ቀሪውን ሰፊ ተማሪ በአዕማድ አፍራሽነት ስነ-ልቦና የሚገራ፣ «አብዮት የ‹ራት ግብዣ› እንዳልሆነ እና ወደግማሽ ከፍለ-ዘመን እየተጢጋ የነበረውን ግዙፍ ስርዓት ለማውደም አገሪቷን በደም ባህር መዝፈቅ የዘመኑ መንፈስ እንደሆነ» የሚሰብኩ መጽሔቶች ተተኩ፡፡ እንደታመነውም ሆነ፡፡

## የልሂቅነት ዕዳ

የኢትዮጵያ ዘመናዊ ትምህርት አንዱ ችግሩ ልሂቅነትን ማበረታታቱ ነው፡፡ የዚህ ልሂቅነት መለዮ የትኛውም ኢትዮጵያዊ እና ባህላዊ (ሀገር-በቀል) የሆነው ሁሉ የሚናቅበትና እንደኋላቀር የሚቆጠርበት፤ በሌላ ጎኑ የትኛውም ምዕራባዊ የሆነ ሁሉ ዋጋ እንዳለው የሚታሰብበት





ነው፡፡ ዘመናዊ የተባለው የትምህርት ስርዓት ያበቀለው ልሂቅ ነት፤ የቀደሙትን መምህራን በሙሉ በህይወት እንዳለ «አፅመ-ቅሪት» የሚቆጥር፤ ከዚህም የተነሳ እነርሱን ያለመስማት መብት ለራሱ የሰጠ ማንነት ነው፡፡ በዚህ ዓይነት ስርዓት ውስጥ ያደጉት ወጣቶች ራሳቸውን አይነኬ እና ምትክ አልባ የኢትዮጵያ ህዝብ አዳኞች አድርገው አሳመኑ፡፡ ይሄን አይነት ናርሲዚዝም /Narcissism/ የተጠናወተው የዛን ጊዜው ልሂቅ፤ አንደኛው መነሻው ሀገሪቱ ራሷን ለማዘመን ከመረጠች ው አማራጭ ጋር የሚጋመድ ነው፡፡ ይኸውም መዘመን ማለት ሌሎች ምዕራባውያን ሳይንስና ቴክኖሎጂን ተጠቅመው ስለሰለጠኑ፤ ኢትዮጵያም ‹የተማሩ› ልጆቿ ይሄን መንገድ እንደሚያስጀምሯት ማመኗ ነበር፡፡ ስለዚህም ለተማሪዎቿ ከፍተኛ ግምት ነበራት፡፡ በዘመናዊ ትምህርት ውስጥ ማለፍ የሳይንስን እውቀት ስለሚያስጨብጥ በብዙ ኢትዮጵያዊያን ዘንድ ልሂቃኑ ሀገሪቷን ከጥልቅ ኋላቀርነት ወደ ዝመና እንደሚያደርሷት ታምኖ ነበር ፡፡ እናም እነርሱ የሚሉትን ከመስማትና ከመከተል ያለፈ ምርጫ አልነበረም፡፡

የተማሩትም ያልተማሩትም ኢትዮጵያውያን ዘመናዊ ትምህርት ይዞት የሚመጣውን ማህበረሰባዊ ስልጣኔ ዋጋ የሰጡበት ሌላኛው ምክንያት፤ እያይዞ የሚያስተረጉመውን ምዕራባዊ ማንነት በመገንዘብ ነበር፡፡ ሁለቱም የማህበረሰብ ክፍሎች የሀገሪቱ ችግሮች ከባህላዊ ኋላቀርነት ጋር እንደሚያያዝ ማመናቸው፣ መጀመሪያ ባህሉን ምዕራባዊ ማድረግ የዝመና ጅማሮ እንደሆነ እንዲታሰብ አድርጓል፡፡ ለአፄው ስርዓት መዘመን ማለት ሀገሪቱን ከታላቅ ዕንቅልፏ መቀስቀስ ነበረ፡፡ ይህን ለማድረግ ከቴክኖሎጂ ዕውቀት በፊት የምዕራባውያኑ ሀሳቦች፣ ዕሴቶችና ተቋማት ቀድመው ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገቡ (አልያም እንዲጠለፉባት) ተደረጉ፡፡ ስለዚህም ነበር የአፄ ኃይለሥላሴ ዩኒቨርስቲ ሲመሰረት መስራች የነበሩት የቴክኖሎጂ አልያም የሳይንስ መምህራን ሳይ፣ሆኑ የሃይማኖት ሰዎች እን ዲሆን የተመረጠው፡፡ ሀገሪቱን የማሰልጠን ተልዕኮ የተሰጠው ዘመናዊው የትምህርት ስርዓት ሀገር-በቀሉን ልሂቅ ወደጎን ትቶ ሀገሪቱን ያደረጓትን

ያደረጓት ዘንድ ለወጣቶቹ አሳልፎ ሰጣት፡፡ ወጣቶቹም ‹ነቅታችኋልና አዘምኑን› መባላቸውን እንደታሪካዊ ዕዳ ቆጠሩት፡፡ ይህን እምነት ምሉዕ ለማድረግም ፖለቲካዊ መሪነትን መያዝ እንዳለባቸው አመኑ፡፡ አልያም ደግሞ ሁኔታውን በደንብ እንዲያሳየን «ቻሌንጅ» መጽሔት ላ ይ ወጣቶቹ ከፃፉት እንጥቀስ - እንዲህ ብለውን ነበር፡-

> *"አገራችንን ከረዥም ዘመናት እንቅልፏ መቀስቀስ እና ህዝቧን ከጠንካራው የአምባገነንነት ሸምቀቆ ማላቀቅ፤ ትከሻችን ላይ የተጣለ ሸክም ነው፡፡"* (ትርጉም)

ይህን መሰሉን እስከዚህ ጊዜ የተራዘመ የዘመናዊ ልሂቅነትን ዕዳ፣ አንድ የዘመኑ አጥኚ፤ እንዳለው «ኢትዮጵያ ፀረ -ቅኝ ግዛት ጦርነቶቿን በሜዳ ላይ አሸነፈች፤ የትምህርት ክፍል ውስጥ ግን ተሸነፈ ች» በማለት ያስቀምጠዋል፡፡

## ምን አይነት አብዮት?

ይህንን የኢትዮጵያ አብዮት አስመልክቶ፣ በሊቃውንቱ የሚቀነቀኑ ኃቲቶችን በሶስት ገፆች ልንከፋፍላቸው የሚቻል ይመስላል፡፡

የመጀመሪያው ሀቲት፣ አብዮቱን ብሉይ ማህበራዊ ለውጦችን ያስተናገደ አድርጎ የሚያቀርበው አረዳድ ነው፡፡ በዚህ ምልከታ መሰረት፣ በአነስተኛ ወታደራዊ መኮንኖች የተመራው የለውጥ ሂደት ወደምልዓት የሚጠጋ ሶሻሊስታዊ ሽግግር ነው፡፡ ምዕራባዊ መነሾ ያላቸው አጥኚዎች በሶስተኛው ዓለም ከተካሄዱት አብዮቶች በስኬታማነቱ አቻ የለውም የተባለውን ለውጥ በከፍታነቱ ባለመመዝገባቸው የሚወቅሰው ይኸ ሁቲት፤ ለማሳያነት ዋንኛ የሚላቸውን ስር-ነቀል ለውጦች በማስረገጫነት ያነሳል፡፡ የከተማና የገጠር መሬት በማዕከላዊ መንግስቱ ስር መሆን፣ የምርት ሂደቱን የሚያሳልጡ ተቋማት ወደ መንግስታዊ ባለቤትንት መዞር እና በተለይም የገጠር የገበሬ ማህበራት መቋቋም በቀዳሚነት ይጠቀሳሉ፡፡ የድህረ -አፄዋ





ኢትዮጵያ ዓለም አቀፍ ዝምድና ከምዕራብ ወደ ምስራቅ መሻገሩን ጨምሮ፣ ፍፁም ስር-ነቀል ማህበራዊ ነውጥ ተካሂዶ በአንድ ሁሉን ጠቅላይ በሆ ነ የማርክሲዝም-ሌኒዝም ርዕዮተ-ዓለም ምሪት ስርዓታዊ አወቃቀሩ መከወኑ፤ የሶሻሊስት አብዮት ለመሆኑ ተሟጋቾቹ ይከራከራሉ፡፡

ሁለተኛው ጫፍ፣ በዘውግ ብሄርተኞች የሚቀነቀነው ሁቲት ነው፡፡ ክርክሩን አጥብቀው በመያዝ የሚታወቁት የኦሮሞና የትግራይ ብሄርተኛ ልሂቃን ናቸው፡፡ በእነርሱ ክርክር መሰረት፣ ኢትዮጵያ እንደ ሀገር የቆመችው በአፄ ምኒልክ የደቡብ ወረራ በመሆኑ እስከ አብዮቱ መነቃቃት ድረስ በቅኝ-ገዢ እና ተገዢ ብሄሮችና ይህንኑ የገዢ -ተገዢነት ነባራዊ ሁነት በሚያስቀጥል ማህበረ-ፖለቲካዊ ስርዓት ነበር፡፡ ዓመፁ የተፀነሰው በዋናነት በዚህ በቅኝ ገዢ ስርዓት መንበር የተነሳ ቢሆንም፣ አብዮት መባል እንደማይችልም ይከራከራሉ፡፡ በዓመፁ የወደቀውን የመሬት ስሪት ላይ የተመሰረተውን አውቶክራቲክ ስርዓት ባህሪያት፣ ሁለቱም የተጠቀሱት የክርክር መስመሮች ቢጋራ የሚቀበሉት ቢሆንም፤ በድህረ -አብዮቱ የተቋቋመውን መንግስታዊ መዋቅር በአንድ ገፅ አይመለከቱትም፡፡ ለዘውግ ብሄርተኞቹ የወደቀው የሸዋ-ክርስቲያን የበላይነትን ያነበረው ገዢ መደብ ቢሆንም፣ የተተካውም ሆነ አብዮቱ የተመራው ከዚያው የቋንቋና የሃይማኖት ስብስብ ነው፡፡ የመሬት ጥያቄውና ተከትሎት የመጣው የመሬት ስሪት ማሻሻያ ስር-ነቀል አዋጅ፣ በዋናነት በወቅቱ በነበረችው ደቡብ ኢትዮጵያ የሰፈነውን የጭሰኝነት ማህበራዊ ስርዓት ቢበታትነውም፣ የማዕከላዊ መንግስቱ ከአንድ አካባቢ (ቋንቋ) በመጡ የበታች ማዕረግ መኮንኖች መዋቀሩ ‹የማን አብዮት?› ሲሉ እንዲጠይቁ እንዳደረጋቸው በስፋት ፅፈዋል፡፡ የመጀመሪያው የወያኔ አመፅ መነሾም ሆነ ከወሊጋ አሮሞ ኮንፌደሬሽን አንስቶ እስከ ባሌ የገበሬ አመፅ ድረስ ያሉትን ንቅናቄዎች ማህበረ-ባህላዊ ጥቅል ቅሬታዎች አላስተናገደም የሚሉት እነዚህ ልሂቃን፤ ከአማርኛ ቋንቋ ተናጋሪው ውጪ ላለው የትኛው ማህበረሰብ ክፍል የ66ቱ አብዮቱ የቅርፅ እንጂ የይዘት ለውጥ እንዳላመጣላቸው ያምናሉ፡፡

ሦስተኛው ዕይታ ማዕከለኛውን መንገድ የሚመርጠው ክርክር ነው፡፡ ብሉይ ማህበራዊ አብዮት ተካሂዷል የሚሉትንም ሆነ አብዮት በፍፁም አልተካሄደም ከሚሉት ተሟጋቾች የተመረጡ የክርክር ጭብጦችን የሚወርሰው ይኸኛው መሟት፣ አብዮት ከሚለው ቃል ይልቅ ‹ሽግግር› የሚለውን ይመርጣል፡፡ ሽግግሩ በአብዮትነት እንዳይጠራ ያደረገው፣ ስር - ነቀል ለውጦች ባለመካሄዳቸው ሳይሆን በጎ አገራዊ ትሩፋት ባለማምጣታቸው እንደሆነ ይጠቀሳል፡፡ የዘመኑ ዋንኛ መሰባሰቢያ የነበረው የመሬት ባለቤትነት ጥያቄ ምላሽ እንደተሰጠው ቢቀርብም፣ የገበሬውን ማህበረ-ኢኮኖሚያዊ ህይወት ባለመቀየሩ አብዮት ለመባል እንዳይችል ተደርጓል፡፡ የገበሬው ሁሉ-ዓቀፍ መከራ በድህረ-አብዮት ዘመንም መቀጠሉ፣ የማዕከላዊ መንግስቱ መሰረቶች ከመጠናከር ይልቅ በከፍተኛ ሁኔታ መላላታቸው፣ የምርት ሃይሎቹ ከቅድመ-አብዮቱ በላቀ መልኩ ኢኮኖሚያዊ ለውጦችን ያለማምጣታቸው፤ በዚህ ዕይታ ገፊዎች የሚጠቀሱ ነጥቦች ናቸው፡፡ በባህር ማዶ እና በሀገር ውስጥ መምህራን የሚውጠነጠኑት እነዚህ ሶስት ክርክሮች፣ በብዙ ገፁ ግራ-ዘመም የአብዮት መተንተኛ ማዕቀፉን ከመጋራታቸው አኳያ፣ አልፎም በቀጥታም ሆነ በአካላዊ ርቀት ተሳታፊ በነበሩ (ወይም ለአንዱ ዕይታ የቀደመ ፖለቲካዊ ዝማሜ ባላቸው) ፀሐፊዎች መቅረባቸው፣ አብዮቱ ላይ ያሉ ት አተካራዎች ለረዥምም ጊዜ የሚቆዩ ይመስላል፡፡

## አብዮቱ ከሸፏል?

በግብታዊ አነሳስና ጉዞው ላይ ክርክር የማይሰማበትን ያን አብዮት፣ ያሳካቸውን እና ረግጦ ያለፋቸውን የቀደሙ ማህበራዊ ጥያቄዎች በማንሳት፣ እንደከሸፈ የሚናገሩ ድርሳናት በርከት ያሉ ናቸው፡፡ ተሳክቷል ከሚሉት ይበልጥ በውድቀቱ ልክ ላይ የሚነታረኩ ፀሐፊያን በዛ ያሉ ናቸው፡፡ የሁለቱንም ክርክሮች ስንፈትሽ የምናገኘው አንድ፣ በጥምዝምዝ የሚቀርብ መነሻዊ መላምት አለ፡፡ ይኸውም፣ ክስተቱን እንደ ፖለቲካዊ





አብዮት ወይስ እንደ ብሉይ ማህበራዊ አብዮት ይመለከቱታል የሚለው ነው፡፡ ከተለምዷዊው ሲባዛ ማርክሲስታዊ፣ አነስ ሲል ደግሞ ሌኒንስታዊ በሆነ ሀሳባዊ ማዕቀፍ አብዮቱን የሚገመግሙ በከሸፈቱ ላይ ክርክር አያነሱም፡፡ ነገር ግን፣ ከቀዝቃዛው የዓለም ጦርነት ማብቃት ወዲህ የተሻለ የአብዮት ማጥኛ ዘዬ ሆኖ የወጣውን ሊበራል የሆነ ፓራዳይም ስንተራስ፣ የኢትዮጵያ አብዮት ከገጠመው አልያም ከሆነው የተለየ እንዲሆን መጠበቅ የሚቻል አይመስልም፡፡ «አብዮት ያለ ደም» እንደማይከወን ኀልዮቶችም ሆኑ የታሪክ መዝገቦች ከመመስከራቸው ባሻገር፤ ያ አብዮት በብሉይ ማህበራዊ አብዮትነት ከተለካ፤ ከአቻዎቹ የፈረንሳይ፣ የሩሲያና የቻይና አብዮቶች የተለየ መንሸራተት እንዳልገጠመው ይነሳል፡፡

የእነዚህ ሶስት ማህበራዊ አብዮቶች አጥኚዎች በስፋት እንደሚከራከሩት፣ ማንኛውም ወደ ማህበራዊ አብዮት የሚያዘግም ህዝባዊ እንቅስቃሴ ሁለት እርከኖች አሉት፡፡ የመጀመሪያው፣ የስርዓቱን ምሰሶዎች የሚነቀንቀውና ተቋማቱን ወደ ሁሉን ፍላጎት አቻቻይነት ለመቀየር የማሻሻያ አማራጭን የሚከተለው ፖለቲካዊ አብዮት ነው፡፡ በዚህ ስያሜ እንደሚጠሩት የእንግሊዝ፣ የአሜሪካና የቅርብ ጊዜው የአረብ ፀደይ እንቅስቃሴዎች ሁሉ፣ የዚህ መሰሉ አብዮት ግብ ገዢውን መደብ በሌላ ዴሞክራሲያዊ መብቶችን ወደሚያከብር ስርዓት መቀየር እንደሆነ ምሁራን ይናገራሉ፡፡

በኢትዮጵያ አውድም፣ የአፄ ኃይለሥላሴን ስርዓት ፖለቲካዊና ሲቪል መሰል መብቶችን ወደሚያከብር ሕገ-መንግስታዊ ስርዓት በመቀየር ብቻ የተነሳሳ ንቅናቄ ቢሆን፣ እንደፖለቲካዊ አብዮትነቱ እነዚህን መብቶች የሚያከብር ስርዓት ባለመገንባቱ በከሸፈት ሊነቀስ ይችል ነበር፡፡ ነገር ግን የአብዮቱ ሁለቱ መሰረታዊ ጥያቄዎች እንቅስቃሴውን ከየፖለቲካ አብዮትነት በላይ እንዲሻገር የሚያስገድዱ ነበሩ፡፡ የመሬት ለአራሹ እና የብሄር እኩልነት ጥያቄዎች፣ ማዕከላዊ መንግስቱን ዴሞክራሲያዊ በማድረግ ብቻ የሚመለሱ

አልነበሩም፡፡ በጭሰኝነት ማህበራዊ አወቃቀር ላይ የቆመውን ባላባታዊ ስርዓት እና በአንድ ቋንቋ፣ ባህላዊ ዕሴት እና የሃይማኖት የበላይነት የተዋቀረችውን አገር፤ በስር-ነቀልተኛ አመፅ ደግሞ ማዋቀርን ግድ ማለቱ፤ እንቅስቃሴውን ከፖለቲካ አብዮትነት በላይ አሻግሮታል፡፡ ይኼ ነባራዊ እውነትም፣ የሂደቱን ሁለተኛ ዕርከን ወልዷል፡፡ ማህበረ-ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ አወቃቀሩን አፍርሰው በመገንባት የተሻለች ኢትዮጵያን እንደሚያዋልዱ ያመኑ ግራ-ዘመም መሀከለኛ ምሁራን፣ ተማሪዎች እና የቢሮክራሲው አባላት፤ እንቅስቃሴውን ወደብሉይ አብዮትነት መርተውታል፡፡ እንደሌሎች ሀገራት አብዮቶች ሁሉ (ፈረንሳይ፣ ቻይና እና ሩሲያ) ይኸኛው ሁለተኛው እርከን፤ የግራ-ቀኝ ልሂቃንን ደም አፋሳሽ ትንቅንቆችን መቀስቀሱ ነባራዊ ግዴታ ሆኗል፡፡ በትንቅንቁ ሂደትም፣ ስር-ነቀልተኛ ልሂቃን የአብዮቱን የመጨረሻ ማህተም ያሳርፋሉ፡፡ የኢትዮጵያው አብዮትም፣ የተነሳበትን ሁለት ዋንኛ ጥያቄዎች በሚገባ መልኩ ስርዓታዊ ተካታችነት እንዲኖራቸው ለማድረግ፣ ማህበራዊ አብዮቶች ግድ የሚሉትን ሂደቶች መጓዙን ተከትሎ የታዩትን ሁነቶች በመጥቀስ በከሸፈትነት ማንሳት ብዙም ረብ እንደሌለው ይጠቀሳል፡፡ አቻቻይ ፖለቲካዊ ስርዓት ያለመፈጠርንና የህዝባዊ መንግስትን አለመምጣት መሰል ነጥቦችም ለዚሁ አብዮቱ ከሽፏል ለሚለው ክርክር በማሳያነት ይነሳሉ፡፡ ነገር ግን የትኞቹም ማህበራዊ አብዮቶች እነዚህን የተጠቀሱ ጭብጦች አላዋለዱምና የኢትዮጵያውንም የተለየ የሚያደርገው ነገር ያለ አይመስልም፡፡ በቻይና ማኦ፣ በሩሲያ ሌኒን፣ በፈረንሳይ ናፖሊዮን እንደመጡት፤ በኢትዮጵያም መንግስቱ ኃይለማርያም መውጣቱም፤ እንደማህበራዊ አብዮት ተ ጠባቂነት ስለሚኖረው፤ አብዮቱ አልተሳካም የሚለውን መከራከሪያ ጎደሎ ያደርገዋል፡፡

በነዚህ በከፊል ከተጠቀሱት የክርክር ነጥቦች ባሻገር፣ ስለአብዮቱ ከተሰተዋሉ ጉድለቶች ሁለት ጉዳዮችን ማንሳት ግን ይገባል፡፡ የመጀመሪያውና ብዙውን ጊዜ ሰፋ ያለ ቦታ የማይሰጠው ጭብጥ፣ የአብዮቱ





ከተማ ተኮር የመሆን ጉዳይ ነው፡፡ በዋጋ ንረት ግብታዊ ጅማሮውን ሲያገኝ፣ የተደረጉት ተደጋጋሚ ሰላማዊ ሰልፎች የተደራጁት በከተሜ ሰራተኛው መደብ ነበር፡፡ በቀጣይ ሲከወኑ የነበሩት ከፊል ድርጅታዊ እንቅስቃሴዎችም በዋናነት በዋና ከተማዋ ብቻ የተቀነበቡ መሆናቸው፣ ሰፋ ያለ ህዝባዊ መሰረትና አሳታፊነት ሳይኖረው እንዲካሄድ መደረጉ፣ ሊገኙ ይችሉ የነበሩ ሀገራዊ ጥቅሞችን አጉድሏል፡፡ በተለይም፣ አብዮቱ የተጠነጠነባቸው ጥያቄዎች ከከተሜው የማህበረሰብ ክፍል ይልቅ የሰፊውን ገበሬ እና አርብቶ አደር ህልውና የሚመለከቱ ቢሆኑም፤ ይህ ን አርሶ አደር የአብዮቱ ማህበራዊ መሰረት አድርጎ መንቀሳቀስ አለመቻሉ ሁነቶቹን በፍጥነት ወደአሉታዊነት ቀይሯቸዋል፡፡

ሌላኛው ጉድለት ተደጋግሞ የሚጠቀሰው የተደራጁ ስብስቦች አለመኖር ነው፡፡ ድርጅቶቹ ዘግይተው ለመምጣታቸው የአብዮቱ ግብታዊነት በምክንያትነት ቢነሳም፤ ዋንኛው ክፍተት ግን አብዮተኞቹ ቅድመ-አብዮታዊ ነባራዊ ሁነቶቹ አብዮቱን እንደፀነሱ በሚገባ ካለመረዳታቸውም እንደሆነ መጥቀስ ይቻላል፡፡ እ ነርሱ ከታመኑለት ርዕዮተ-ዓለም አኳያም፣ የአብዮተኝነት መሰረታዊው መለዮ፤ ያሉት ሏብዮታዊ ሁኔታዎች አብዮትን ለመቀስቀስ የሚኖራቸውን ድርሻ በቅጡ መገንዘብ መሆኑን ስናከል፣ ጉድለቱ የእንቅስቃሴው መፍጠን ብቻም ሳይሆን የልሂቃኑ ከሁነቶቹ የነበራቸው አእምሯዊ ተነቃይነትም ጭምር እንደሆነ እንገነዘባለን፡፡



ጋዜጠኛ ዳዊት ታደሠ

## ክፍል ሦስት

# ሕዳሴውን እንደ ቬልቬት





- ቼኮዝሎቫኪያ
- የፉሀረር ወረራ
- ነፃነትና አገዛዝ
- የፐራግ ፀደይ
- የመጨረሻው መጀመሪያ



ጋዜጠኛ ዳዊት ታደሠ

# ሕዳሴውን እንደ ቬልቬት

በሰው ልጆች ታሪክ ውስጥ ጭቆናን እምቢ ብሎ ለለውጥ መንቃት ጥንታዊ ነው፤ ዓለማችንም እስከዛሬ ድረስ በዚህ መንፈስ የተቃኙ ታሪካዊ የለውጥ አብዮቶችን አይታለች፡፡ የአብዮት ታሪክ ጥንታዊ ቢሆንም፣ በተለይ በታላቅነቱ የሚወደሰው የፈረንሳይ አብዮትና ከአስራ ዘጠነኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ ወዲህ ደግሞ፣ በማርክሲስት ርዕዮተ ዓለም በተመሩ ንቅናቄዎች አማካኝነት ጉልህ ትርጓሜን አግኝቷል፡፡ ባሳለፍናቸው መቶ ሃምሳ ዓመታት፣ በግራ ዘመሙ ፍልስፍና የተቃኙ አብዮቶች በብዙ ሀገራት ተደርገዋል፡፡ ከቀዝቃዛው የአለም ጦርነት በፊት ባለው የአንድ ክፍለ ዘመን ታሪክ ውስጥም በዚህ መርህ የተነቃቁ በቁጥር የበዙ ስር ነቀል የስርዓት ለውጦች ተስተናግደዋል፡፡ በዚህም መነሻነት፣ ከአብዮት ዘመነኛ ትርጓሜዎች መካከል የማርክሲስቱ መንገድ ቀዳሚ ሆኗል፡፡ የማህበረሰብን አወቃቀር ከማይታረቅ የመደብ ቅራኔ አንፃር የሚመለከተው ይህ ቁሳዊ እይታ፣ የታችኛውን መደብ በዓለማችን ላይ የታዩትን የለውጥ ታሪኮች ከፊት ሆኖ እንዲመራ አጭቶታል፡፡ ከ19ኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ በኋላ የምድራችንን ጥንች





እንኳን ሳይቀር በአብዮት ንቅናቄ የቃኘው ይህ የለውጥ መንፈስ ዛሬም ድረስ አለመርገቡ ለትርጉሙ ከፊት የሚጠራ ምርጫ ሆኗል፡፡

ቀደምት አሰላሳዮች ዘመን ተሻጋሪና ተተግባሪ የለውጥ ፅንሰ - ሀሳቦችን ለውጥን ለናፈቁ አብዮተኞች ትተው አልፈዋል፡፡ ጨቋኞችን ማንበርከኪያ መርሆቻቸውን ተከትለው ለድል የበቁ ሁሉ ስለውሊታቸው ያመሰግኗቸዋል፡፡ ከክርስቶስ ልደት በፊት ከነበሩት ቀዳሚዎቹ ጀምሮ ዛሬ ም እስካሉት ጉምቱ የለውጥ ሃዋርያት ድረስ በርዕሰ -ጉዳዩ ላይ ብዙ ብለዋል፡፡ ነፃነት በነፃ የሚገኝ አይደለም፡፡ የትኛውም አይነት መስዋዕትነት ለነፃነት ቢከፈል ዋጋው ሁሌም የከበረ ነው፡፡ የሰው ልጅ ይህን እሴት እንዲናኝበት ለመጠቆም የዋተቱት የሃሳብ መንገድ ጠቋሚዎች፣ የታለመው ድል ይሳካ ዘንድ ያበረከቱት የአእምሮአቸው ጭማቂ ውጤ ት በስኬት የተደመደመ ነበር ማለት ይቻላል፡፡ ደም-አፋሳሽ ከሆነው እስከ ደም-አልባው ንቅናቄ ድረስ የሚዘረጉት የትግል መንገዶች ለነፃነት የቀሩት ብቸኛ አማራጭ ስልቶች ናቸው፡፡ መንገዱ የትኛውም ቢሆን፣ ለነፃነት የተከፈለ እስከሆነና ነፃ ማውጣትንም እስካሳካ ድረስ ተቃውሞ ሊቀርብበት አይችልም፡፡ የተነሳበት አላማ ጭቆናን መጨፍለቅ የሆነ አብዮት የሚለካው በውጤቱ መሆን ካለበት መስዋዕትነቱ ለከበረው ድል የተከፈለ ዋጋ ሆኖ በክብር ይዘከራል፡፡ በሽሚያ ሞታቸውን ያስቀደሙት ሰማዕታት የሚካሱትም በሞታቸው የተገኘው የአብዮታዊው ድል መነሾዎችን በማረጋገጥ ይሆናል፡፡

የአብዮት ግብ ነፃነትን በስር-ነቀል ተራማጅነት ማረጋገጥ እስከሆነ ድረስ ሰላማዊው የትግል ስልትም ጉልበትን ከቀላቀለው እኩል ዋጋ አለው፡፡ ሰላማዊውን አዋጭ የሚያደርገው ፈጣንና በአነስተኛ የህይወት ዋጋ መጠናቀቁ ነው፡፡ በተለይ ደግሞ በኮሙዩኒዝም ርዕዮተ ዓለም የተቃኙ አገዛዞች ከተፈረካከሱበት ወቅት ጀምሮ እስከ አረቡ መነቃቃት ድረስ ያለው የታሪክ ሂደት የሚነግረን ሰላማዊ ት ግል የዘመናችንን መንፈስ የዋጀ መሆኑን ነው፡፡ እንዲህ ማለት ግን የትጥቅ ትግል ዋጋ ቢስ ነው ማለት አይሆንም፡፡

አብዮታዊው መንገድ በሰላማዊ ስልት የተቃኘ ሆኖ ውጤት አልባ ከሚሆን ደም-አፋሳሽ ሆኖ ውጤቱ የተሳካው ንቅናቄ የተሻለ ነው፡፡ ያለ ደምና መስዋዕትነት ዴሞክራሲን ማነበር ግን ከስኬትም በላይ የሚነገርለት ስለመሆኑ የሚያጠራጥር አይደለም፡፡ ለሌሎች ተጨዳኞችም በአርአያነት የሚወሰድ ቁም ነገር ይኖረዋል፡፡

ቀደም ብለን ያወሳነው የሶሻሊስቱ የለውጥ መንፈስ በስር -ነቀልነቱ በእርግጥም የተሳካ ነበር፡፡ እንደአለመታደል ሆኖ ግን፣ ጭቆናን በጭቆና በመተካት የተጠናቀቀ አብዮታዊ መከራን ከስሩ ወለደ፡፡ በማርክሲስት ርዕዮተ-ዓለም እንደሚመሩ ካወጁ የስርዓት ውጤቶች አብዛኞቹ፣ አለማችንን በደም በማጠብ ለታሪክ ሌላ መልክ ሰጥተው አልፈዋል፡፡ ይህ የሰው ልጅ ብሽቀት ሆኖ ይወሳል፡፡

በህዝባዊነትና በነደደ የለውጥ ናፋቂነት ወደስልጣን ከመጡ ግራ ዘመም አብዮተኞች የበዙት፣ የስልጣን ዕድሜያቸው የረዘመው በጉልበት ነው፡፡ እስርና ግድያ በዘመናቸው ለኖሩ ዜጎች የማያመልጡት ዕዳ ነበር፡፡ በፍጹም መነቃቃትና ለታሪክነት በበቃ ስር -ነቀልነት ወደስልጣን መንበር የመጡት እኚህ አምባ-ገነን ስርዓታት ወደመቃብር የወረዱት በሚያሳፍር ተንበርካኪነት መሆኑን ስንረዳ ደግሞ ስለለውጥ መንገዱ በድጋሚ እንድናስብ ያስገድደናል፡፡ በጉልበትም ቢሆን ህዝባዊ ጥሪ እንዳላቸው ከሚወተውቱት መካከል የሚመደበው የቼኮዝሎቫኪያ የኮሙዩኒስት ስርዓት ስልጣኑን በመለጠጥ ወደ ጨፍጫፊነት የተቀየረ እንደነበር የአገሪቱ ታሪክ ይነግረናል፡፡ በወታደራዊ አቅሙ የታመነው ይህ ስርዓት የተፈታው ለዓይን በማይሞሉ ሰላማዊ አብዮተኞች ነበር፡፡

በዚሁ መጽሐፍ ላይ በዋናነት የተነሳው የሕዳሴው አብዮታችን የቼክ ወጣቶች ያሳኩትን የቬልቬት አ ብዮትን በምሳሌነት ማውሳቱም አገሪቱ ከእኛ ጋር ባላት ታሪካዊና ባህላዊ ተመሳስሎሽ ነው፡፡ ከዚሁም ባለፈ በአብዮቱ ወራት ከታየው ጨዋነትና ፍጹም ሰላማዊነት የምንዋሰው





ይኖራል፡፡ የቬልቬት አብዮትን እያወደስን በምናወሳበት በዚህ የመጽሐፍ ክፍል ምናልባት አላስፈላጊ የሚመስሉ የታሪክ እውነታዎች ይኖሩ ይሆናል፡፡ የእያንዳንዱ ክስተት መመዝገብ ግን ትክክለኛውን የአብዮቱን ጉልበት ለመረዳት የሰፈረ መሆኑን አንባቢ እንዲረዳው ያስፈልጋል፡፡

የቼኮዝሎቫኪያን ታሪካዊና ማህበረሰባዊ መልክ ስንመረምር ከኢትዮጵያ የዘውጎች አሰፋፈር ጋር ተቀራራቢ የሚመስል ገፅ እናገኛለን፡፡ ቼኮች መጀመሪያ በቦሄሚያ አካባቢ ከ6ኛው ክ/ዘመን ጀምሮ መኖራቸውን ታሪክ ይነግረናል፡፡ የጀርመንኛ ቋንቋ ተናጋሪ ሰደተኞች ደግሞ በቦሄሚያ ዳርቻ አካባቢ ከ13ኛው ክ/ዘመን ወዲህ ኑሮ መጀመራቸው ተረጋግጧል፡፡ እ.ኤ.አ. በ1526ዓ.ም በሄሚያ በሃብ ስበርግ ስርወ-መንግስት ስር ወደቀች፡፡ የስርወ-መንግስቱ አገዛዝ ግን ብሄራዊ የመነቃቃት መንፈስን ፈጥሮ ተገዢዎቹን ለተለየ ትግል አነሳሳ፡፡ ካረጀው የንጉሳዊ ቤተሰብ ግዞት ስር ለመላቀቅ የተለያዩ ስልቶችን በመንደፍ አገዛዙን ማዳከም ተጀመረ፡፡ የነፃነቱ ጉዞ ረዥምና አድካሚ ነበር፡፡ ዘመናትን ያስቆጠረው ትግል ውጤት አካባቢያዊ ብሔርንና የቋንቋን ውክልና በማስተዋወቅ መሀሉ ረገብ ያለ ቢመስልም አንደኛው የአለም ጦርነት ግን የአስትሮ -ሃንጋሪያዊያኑን ሥርወ-መንግስት እንዳያበቃለት አድርጎታል፡፡ ቼኮችና ስሎቫኮችም፣ ጦርነቱ በፈጠረው የተመቻ ሁኔታ ተጠቅመው ነፃነታቸውን አወጁ፡፡

በ20ኛው ክ/ዘመን መጀመሪያ ላይ «ቼክ -ስሎቫክ» የሚለው ሃረግ በሁለቱ የዘውግ አመራሮች ዘንድ ተደጋግሞ ይነሳ ነበር፡፡ ከዚህም አልፎ በሁለቱ ግዛቶች መካከል መቀራረብና የህዝብ ለህዝብ ግንኙነቱ እንዲጠነክር ሙሉ ጊዜያቸውን ሰጥተው የሚ[illegible] በርካቶች በወቅቱ ተስተውለዋል፡፡ ሁሉ ነገራቸውን ለውህደት [illegible] አልታጡም፡፡ ለዚህ ደግሞ በተለይ የሁለቱ ዘውጎች ምሁራን ሚና [illegible]ከራ ነበር፡፡ ልዩነቶቻቸው ከሃብስበርግ ነፃ ለመውጣትና በፍቃደኝነት ለመዋሃድ አላገዳቸውም፡፡

በአንደኛው የአለም ጦርነት ኢጋማሽ ላይ በቶማስ ማሳሪክ አማካኝነት የቼኮዝሎቫኪያ ብሔራዊ ም/ቤት ተቋቋመ፡፡ የዚህ ምክር ቤት

መመስረት ሁለንተናዊ ለሆነው የማሳመንና የማግ ባባት ስራ ትልቁን ሚና አዋጥቷል፡፡ ወጣቶችና አዛውንቶች በአውሮፓ ምድር ያፈሰሱት ደምም ፈጣኑን እንቅስቃሴ አሳከቷል፡፡ 1.4 ሚሊዮን የሚጠጉ ቼኮች በጦርነቱ መሳተፋቸውና 150 ሺህ ያህሉም የህይወት መስዋዕትነት መክፈላቸው ለውህደቱ የዲፕሎማሲ ድጋፍ ማስገኘቱ ይወሳል፡፡

## ቼኮዝሎቫኪያ

እ.ኤ.አ. በጥቅምት 28 ቀን 1918ዓ.ም. የቼኮዝሎቫኪያ አገርነት በዋና ከተማዋ ፕራግ ላይ ታወጀ፡፡ ስሎቫኮችም ማርቲን በተባለች ከተማቸው ላይ በመሰባሰብ ግዛቲቱን መቀላቀላቸውን ሁለት ቀን ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ይፋ አደረጉ፡፡ ጊዜያዊ ህገ-መንግስት በማርቀቅና ቶማስ ማሳሪክን ፕሬዝዳንት በማድረግ ተግባራዊው ሀሳብ መጠናከር ጀመረ፡፡ በቅዱስ ዥርሜይን ስምምነት ላይም የቼኮዝሎቫኪያ ምስረታ እውን ሆነ፡፡ ሩቴኒያ የተባለው የህዳጣን ግዛትም በትሪያኖን ውል የግዛቲቷ አካል ለመሆን በቃ፡፡ በዘውግ አወቃቀር፣ በታሪክ፣ በሀይማኖት፣ በባህልና በማህበራዊ አደረጃጀታቸው የተለያዩት ቼክና ስሎቫክ አንድ አገርን መሰረቱ፡፡ እንግዲህ በዚህ መጽሐፍ ላይ ሊወሳ የታሰበውና የኮሙዩኒስቱን እምባ-ገነን አገዛዝ የፈረካከሰው የቬልቬት አብዮት የተመራው ልዩነቶቻቸው አይታረቅም ተብሎ በሚሰጋለት በቼኮዝሎቫኪያ ህዝብ ነበር፡፡ በአብዮቱም አገዛዙ ላይመለስ ዴሞክራሲም ላይቀለበስ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ተተክሏል፡፡

አዲሲቷ አገር ስትመሰረት የህዝቧ ቁጥር 13.5 ሚሊዮን ሆኖ ነበር፡፡ የአውስትሮ-ሃንጋሪ አገዛዝ አካባቢውን ሲለቅ ትቷቸው የሄደው ኢንዱስትሪዎች ለአገሪቱ ኢኮኖሚ መነሻ ሀብቶች ነበሩ፡፡ በቼኮች አካባቢ የነበረው የፋብሪካ ብዛት ከስሎቫክ አንፃር በብርካቴው ያይላል፡፡ ሰደተንላንድ በተባለችውና የጀርመንኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች በሰፈሩባት አካባቢም የኢንዱስትሪ እንቅስቃሴው አብዛኛውን ዜጋ አሰርቶ ይመግብ





ነበር፡፡ የስርዓቱ አወቃቀር በፓርላማ የሚመራ ዴሞክራሲያዊ ውክልናን የሚከተል ሲሆን፣ ቼክና ስሎቫክ ደግሞ የአገሪቱ የስራ ቋንቋዎች ሆነው እንዲያገለግሉ ውሳኔ ላይ ተደርሷል፡፡ ይህች አገር በተረጋጋ ፖለቲካዋና በደህንነቷ ለሌሎች ምሳሌ ለመሆን ብትበቃም፣ እንዳለመታደል ሆኖ ግን ይህ መረጋጋትና ሰላም ለረጅም ዓመታት የዘለቀ አልነበረም፡፡

## የፋህረር ወረራ

ምንም እንኳ ቼኮዝሎቫኪያ በይፋ ከተመሰረተች በኋላ ባሉት ዓመታት፣ በመካከለኛው አውሮፓ እርሷን የሚስተካከላት ዴሞክራሲያዊ አገር ባይኖርም፣ የዘውግ ተኮር አለመግባባቶች ግን ስርዓቷን ይፈትን ነበር፡፡ በተለይ የጀርመንኛ ቋንቋ ተናጋሪው ህዝቧ የአገር ግንባታውን ከሚነቀንቁት መካከል ከፊት የሚቆሙት መሆናቸው ዛሬም ድረስ በከፋ ለሚነሳው ስራቸው ምክንያት ሆኗል፡፡ ከአጠቃላይ የህዝብ ቁጥር ውስጥ 25 ከመቶ (1/4ኛውን) የሚሸፍነው ይህ የማህበረሰብ ክፍል ልቡ ወደጀርመኖች ያደላ ነበር፡፡ በዚህም የቼኮዝሎቫኪያን እንደአገር መቆም የሚያጣጥሉ አንዳንድ ምልክቶች መታየታቸው የሚገርም አልነበረም፡፡

አዶልፍ ሂትለር አንሽለስ በተባለው የጀርመኖች መንገድ ኦስትሪያን ሲቆጣጠር ፊቱን ወደ ቼኮዝሎቫኪያም እንደሚያዞር ቅድመ-ግምት ላይ ተደርሶ ነበር፡፡ ከፈረንሳይና ከእንግሊዝ ጋር ያደረገው የአፒዝመንት (Appeasement) ፖሊሲ ደግሞ ቼኮች ከ ጀርመን ወታደሮች የሚደርስባቸውን ጥቃት ብቻቸውን እንዲጋፈጡ አስገድዷቸዋል፡፡ ምዕራባውያን አገራት ናዚን በምንግዴነት የተውት ወደእነርሱ እንደማይመጣ በመተማመን ነበር፡፡ በዚህም ቼኮዝሎቫኪያ የጀርመን ኢላማ ሆነች፡፡

በአገሪቱ የሚገኙ የጀርመንኛ ቋንቋ ተናጋሪ ቼኮች በኮንራድ ሄንሌይን በመመራት ከጀርመን ጋር ለመቀላቀል የሚረዳቸውን ንቅናቄ

ጀመሩ፡፡ ሂትለርም ከኋላ የማያቋርጥ እርዳታውን ማቀበል ስራው አደረገው፡፡ ታጣቂ ጦር በማሰማራት ጭምር አጋርነቱን አሳየ፡፡ ብዙም ሳይቆይ ቼኮዝሎቫኪያ ለሙኒክ ስምምነት እንድትንበረከክ ተገደደች፡፡ በውሉም መሰረት ሲደተንላንድ የተባለችው ግዛት ለጀርመን ተላልፋ ተሰጠች፡፡ በግዛቲቱ ይኖሩ የነበሩት የሌላ ቋንቋ ተናጋሪ ማህበረሰብ አባላት ከአካባቢው በግድ እንዲፈናቀሉ ተገደዱ፡፡ የወቅቱ የቼኮዝሎቫኪያ ፕሬዝዳንት ቤኔስም፣ አገሩን ለቅቆ ወደለንደን አመራ፡፡ ኤሚል ሃቻ ደግሞ ተሰዳጁን በመተካት አገሪቱን ማስተዳደር ጀመረ፡፡ አስተዳደሩ ግን የስሎቫክ ግዛት ከነበረው 1/3ኛ ያህሉን በሃንጋሪ ከመነጠቅ ማዳን አልተቻለውም፡፡ ፖላንድም ይገባኛል ያለችውን የዛኦልዜን አካባቢ ወደግዛቷ ቀላቀለች፡፡ ቼኮሎቫኪያ የቼክ ዜግነት በሌላቸው ኃያላን አገራት ለቅርምት ታጨች፡፡ በውጤቱም የተዳከመችና የማንም መፈንጫ የሆነች ስም አልባ የአገር ቅሪት መሰለች፡፡

ሂትለር ፕሬዝዳንት ሃቻ እጅ እንዲሰ ጥ በማስገደድ የቀሪዋን ቼኮዝሎቫኪያ አብዛኛውን ክፍል ተቆጣጠረ፡፡ በቀረችው የስሎቫክ ምድር ላይ ደግሞ በጆሴፍ ቲሶ የሚመራ ለአይን የማይገባ የስሎቫኮች መንግስት ተቋቋመ፡፡

ተሰዳጁ የቤኔስ መንግስት ከከተመባት ለንደን በመሆን አለም - አቀፉ ማህበረሰብ «የቼኮዝሎቫኪያ መንግስት በስደት» ለተባለው ቡድን እውቅና እንዲሰጥ ዲፕሎማሲዊ ተማፅኖውን ገፋበት፡፡ የተሳካው ጥረትም በመጀመሪያ ከእንግሊዝ በመቀጠልም ከ ራሺያና ከአሜሪካ እውቅና ተለገሰው፡፡ የሂትለር ጦር በጥምሩ ጦር መፈረካከስ ሲጀምር ከተለያዩ አቅጣጫዎች የሚሰነዘርበት ኃይልም እየበረታ መጣ፡፡ በምዕራብ በኩል የአሜሪካ፣ የእንግሊዝና የፈረንሳይ ጦር ብዛት ካላቸው አገራት ከተውጣጡ የሰራዊት አባላት ጋር በመተባበር ለጀርመን ኃይል መገዝገዝ ዋጋ ከፈሉ፡፡ በምስራቅ በኩል የነበረው የራሺያው ጦር ኃይል ደግሞ በግንባሩ በኩል





ያለውን እያፀዳ ለቼኮዝሎቫኪያ ነፃ ነት ተረፈ፡፡ የቼክ አርበኞች ከጥምር ጦሩ ጋር በመተባበር አገራቸውን መልሰው የራሳቸው አደረጓት፡፡

## ነፃነትና አገዛዝ

ከጀርመን ሽንፈት በኋላ ቼኮዝሎቫኪያኑ በተስፋ ተሞልተው ነበር፡፡ በተለይ ከጦርነቱ ማብቃት ማግስት የታሰበው ብሔራዊ ምርጫ የዜጎችን ህልም አነቃቅቷል፡፡ ውጤቱ ምንም ይሁን ምን ለዚህ መብቃታቸው ደስተኛ አድርጓቸዋል፡፡ እ.ኤ.አ. በ1946 ዓ.ም. የተካሄደው ምርጫ ለኮሙዩኒስቱ የኬ.ኤስ.ሲ. ፓርቲ ወደስልጣን የመውጫ ዕድልን ከፈተለት፡፡ ኤድቫር ቤኔስ የፕሬዝዳንትነቱን ቦታ እንደያዘ ቢቀጥልም ከኮሙዩኒስት ፓርቲ የተወከለው ክሌመንት ጎትዋልድ የጠቅላይ ሚኒስትርነቱን ቦታ ያዘ፡፡ ቁልፍ የሚኒስትር ቦታዎችንም ይኸው ፓርቲ ተቆጣጠረ፡፡ በማርሻል ፕላን ዕቅድ ውስጥ ቼኮዝሎቫኪያ እንድትካተት ቢታሰብም በራሺያ ገፋፊነት ከእቅዱ እንድታፈገፍግ ገገርው ፓርቲ ወሰነ፡፡

እ.ኤ.አ በ1947ዓ.ም. የራሺያው መሪ ጆሴፍ ስታሊን፣ ሞስኮን እንዲጎበኛት ለጎትዋልድ ጥሪ አቀረበለት፡፡ ከጉብኝቱ መልስ የነበረው የኮሙዩኒስቱ ፓርቲ ቀድሞ የሚታወቅ አልነበረም፡፡ ፍፁም የስልት ለውጥ አደረገ፡፡ የባህሪ ለውጡ ያሰጋቸው 12 ኮሙዩኒስት ያልሆኑ ሚኒስትሮች ስልጣናቸውን በፈቃዳቸው ለመልቀቅ ወሰኑ፡፡ የፈሩት አምባ -ገነንነት በአደባባይ መታየት ጀመረ፡፡ ብዙም ሳይቆይ በ1948 ዓ.ም. የመፈንቅለ - መንግስት አደጋ ተከሰተ በሚል ምክን ያት የወታደሩና የፖሊስ ሰራዊቱ አቅም እንዲጠናከር ተደረገ፡፡ ፕሬዘዳንት ቤኔስ የሚኒስትሮቹን መልቀቂያ እንዲቀበል ተገደደ፡፡ የምርጫው ጥያቄ ደግሞ በድጋሚ ሳይነሳ በሩቅ ተቀበረ፡፡ በጠ/ሚኒስትር ጎትዋልድ አቅራቢነት አዲስ ካቢኔ ተዋቀረ፡፡ አቻቻይ እንደሆኑ የሚነገርላቸው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ዣን ማሳሪክ ራሳቸውን አጥፍተው ሬሳቸው እንደተገኘ ተነገረ፡፡ የኬ.ኤስ.ሲ. ፓርቲ

ሙሉ ለሙሉ ስልጣኑን ተቆጣጠረ። ቼኮዝሎቫኪያም ወደ ጨለማው አገዛዝ ቁልቁለቱን ጀመረች። «ህዝባዊ ዴሞክራሲ» በተባለ የስርዓቱ ማዋቀሪያ፣ መደምደሚያውን ኮሙዩኒዝም ያደረገ የሶሻሊስት ስርዓት መንገዱን ተያያዘው።

ከተቃውሞ ጎራ መሰለፍ በአገር ጠላትነት ማስፈረጅ ጀመረ። ከማህበረሰቡ የተለያዩ ክፍሎች ውስጥ የተለየ አመለካከት ያላቸው ግለሰቦችም ሆኑ ስብስቦች አንድ በአንድ በጉልበት መወገድ ዕጣ -ፈንታቸው ሆነ። ህዝባዊ ዴሞክራሲን የሚገዳደር እስኪጠፋ ድረስ ግድያዎችና የጅምላ እስሮች ተበራከቱ። ይህ መንግስታዊ እርምጃ ያልገባበት ቤት፣ ያልጎበኘው ተቋም አልነበረም። ማርክሲዝም-ሌኒኒዝም የካቶሊካዊቷን ቤተ-ክርስቲያን ደጅ እንኳን አልቀረውም። ሶሻሊስት ሪያሊዝም ቼኮዝሎቫኪያን መድረሻ አሳጣት። ባህላዊውና ምሁራዊው የዜጎች ህይወት በአዲስ ሀሳብ መጠመቅ ግድ ሆነበት። የእዝ ኢኮኖሚ የአገሪቱ ኢኮኖሚያዊ ጓዳ ማስተዳደሪያ እንዲሆን ተወሰነ። የግል ሀብት አፍርቶ ለትርፍ ማዋል ተረት ሆኖ ቀረ። በፖለቲካው ረገድ ደግሞ ራሺያ የቼኮዝሎቫኪያ የጡት አባት ሆነች። በፖላንድ ዋና ከተማ በተመሰረተውና ዋርሰው ፓክት ተብሎ በሚታወቀው የሶሻሊስት አገራት ወታደራዊ ስምምነት ላይ በመፈረምም የስብስቡ አካል መሆኗን አረጋገጠች። የስሎቫኩ ኮሙዩኒስት ፓርቲ ኬ.ኤስ.ኤስ ከገርው ኬ.ኤስ.ሲ ጋር ተጣመረ። አምባ -ገነንነት በቼኮዝለቫኪያ ሰማይ ስር ተደፋ።

የፕሬዝዳንትነት ዘመኑ በፈተና የተወጠረው ቤኔስ፣ በመጨረሻ ላይ ላለማፅደቅ ባንገራገረበት የ«ግንቦት ዘጠኝ» ህገ-መንግስት ምክንያትነት ስልጣኑን ለቀቀ። ቀድሞውንም በሌሎች በሚዘወር የስልጣን ወንበር ላይ መቀመጡን አልወደደውም ነበር። የህገ-መንግስታዊነት ጥያቄውን በማንሳት ያሰበውን ፈፀመበት። በእግሩም ጨካኙና ባለብረት መዳፉ አምባ -ገነን ጎትዋልድ የጠ/ሚኒስተርነቱን ቦታ በመልቀቅ ፕሬ ዝዳንት ሆነ። ይህ ሰው በተለይ በስልጣኑ የመጨረሻ ዘመን ላይ በወሰደው እርምጃ ሰሙ





ከአረመኔነት ጋር ዛሬም ድረስ ይወሳል። እርሱ በሚመራው ገዢው ፓርቲ ውስጥ በአመራርነት ከተቀመጡት ግለሰቦች መካከል ॥ ያህሉን በሞት አስቀጥቷል። ይህም፣ ለተቃውሞው ጎራ ቀርቶ ለራሱም ወዳጆች የማይመለስ ስርዓት እንደተገነባ መልእክት ትቶ አለፈ። ጎትዋልድ ከሚወደው ስልጣን በሞት ቢለይም፣ የጭካኔ ራዕዩን የሚያስቀጥሉ አልታጡም።

የራሺያው ጆሴፍ ስታሊን የቼኮዝሎቫኪያ መሪ እስኪመስል ድረስ በእያንዳንዱ አገራዊ ጉዳይ ላይ እጁን ያስገባ ነበር። ከወታደራዊ ጣልቃ ገብነት እስከ ኢኮኖሚ አማካሪነት፣ ከፖሊሲ ቀራጭነት እስከ ተቃውሞ ድምፅ አፋኝነት በሚዘረጋና ከልካይ በሌለው ጉልበተኝነት ቼኮዝሎቫኪያን አዘዙባት። እ.ኤ.አ. በ1953ዓ.ም ቼኮችን እንዲያስተዳድር በመሪነት የተተካው ዛፖቶኪ፣ በሞት እንደተለየው ጎትዋልድ ሁ ሉ ለስታሊን ቃል የተገዛ ነበር። ይህ መንገድ እንደማያዋጣ የታዘቡ ጥቂት የኮሙዩኒስት አመራሮች በህዝቡ ማጉረምረም በመታገዝ የፖለቲካ ማሻሻያ እንደሚያስፈልግ መወትወት ጀመሩ። የራሺያ ጥገኝነት እንዲያበቃም ጥያቄን አነሱ። ዛፖቶኪን በፕሬዝዳንትነት የተካው ኖቮትኒ ለጥያቄው እጅ ወደመስጠቱ ተቃረበ። የስታሊን ፈላጭ-ቆራጭነት በራሺያ ብቻ የሚገደብበት ጊዜም የመጣ መሰለ።

## የፕራግ ፀደይ

ቼኮዝሎቫኪያን ከስታሊኒዝም የማፅዳቱ ዘመቻ በ1960ዎቹ መጀመሪያ ላይ ይፋ ሆነ። ቆሞ የቀረውን ኢኮኖሚያዊ እድገት ለመቀስቀስ የእዝ ስርዓቱ ላይ ማሻሻያዎች ተጨመሩበት። ጥቂት የነፃ-ኢኮኖሚ ፅንሰ-ሀሳቦች ለሙከራ ያህል ተካተቱ። ከኢኮኖሚ ማሻሻያው ተከትሎም ፖለቲካዊ ማሻሻያዎች ቀጠሉ። ዴሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት በድጋሚ መበየን እንዳለበት ውሳኔ ላይ ተደረሰ። ዴሞክራሲን የሚያቀነቅኑ መሪ

ሀሳቦች በቦታው ተተኩ፡፡ የማሻሻያ ጥያቄዎቹን ወደፊት በመግፋት የሚታወቀው አሌክሳንደር ዱብቼክ የኮሙዩኒስት ፓርቲው ሊቀ-መንበር መሆኑ ደግሞ ለውጡን የማይቀር አስመሰለው፡፡

ዱብቼክ የፓርቲውን የማሻሻያ እርምጃዎች ወደ ሊበራሊዝም አሳደገው፡፡ የፕሬዝዳንት ኖቮትኒ ከስልጣን መልቀቅ ደግሞ የበለጠ ምቹ ሁኔታን የፈጠረ መሰለ፡፡ ሳንሱር ተነሳ፡፡ ፕሬስ፣ ሬዲዮና፣ የቴሌቪዥን ጣቢያዎች እየታየ የመጣውን ለውጥ በማወደስ ተጠመዱ ፡፡ ሶሻሊዝምን ዴሞክራሲያዊ የማድረግ ጥረቱ ሰፊ ህዝባዊ ድጋፍን አገኘ፡፡ የህትመት ውጤቶች ፀረ-ራሺያ ርዕሰ-ጉዳዮችን የፊት ገፅ ማድመቂያ አደረጉት፡፡ ከኮሙዩኒስቱ ፓርቲ የተውጣጡ አንዳንድ ግለሰቦችም የሶሻል ዴሞክራት ፓርቲን ለመመስረት ሙከራ ጀመሩ፡፡ የወጣቶች ፖለቲካዊ ክበቦችም እዚህም እዚያም ማበባቸው ተሰማ፡፡ በአለም ላይ ያሉትን አገራት ከስርዓታቱ የርዕዮተ-ዓለም ጎራ ሳይሆን ቼኮዝሎቫኪያን ከሚያስ ገኙላት ዘላቂ ጥቅም አንፃር መመልከት በአማራጭነት ተወሰደ፡፡ ዱብቼክ ሰዋዊ መልክ የሚገለፅበትን ሶሻሊዝም በመተግበር የርዕዮተ-ዓለሙን አስፈሪነት ለማለዘብ የቻለውን ያህል ጥረት አደረገ፡፡

ውስጣዊ የፖለቲካ ማሻሻያዎችና የውጪ ጉዳይ ፖሊሲ ለውጦች ግን ለቼኮዝሎቫኪያኑ በጎ ዜና ይዞ አልመጣም፡፡ ወግ -አጥባቂ የኬ.ጂ.ቢ. አመራር አባላት እየታየ ያለው ለውጥ ስልጣናቸውን እንዳያሳጣቸው ስጋት ገባቸው፡፡ ከእውቅናቸው ውጪ አደገኛ መንግስት እየተገነባ ስለመሆኑ ወሬዎችን ማሰራጨት ጀመሩ፡፡ ለዋርሶው ፓክት አባል አገራትና ለዋና ሰብሳቢዋ ራሺያ የሀሰት መረጃዎችን በማቀበል አገራቸው ጥርስ እንዲነከስባት የተቻላቸውን ያህል ሞከሩ፡፡ በእርግጥም ጥረታቸው ውጤት ነበረው፡፡ ከሩማንያ ውጪ ያሉ ሁሉም የዋርሶው ስምምነት ፈራሚ አገራት ቼኮዝሎቫኪያ ላይ ወታደራዊ ዘመቻ እንዲፈፀምባት ውሳኔ ላይ ደረሱ፡፡ ራሺያም ከየአባል አገራቱ የተውጣጣውን ሰራዊት እንድትመራ ሀላፊነት





ተሰጣት፡፡ ነሐሴ 20 ቀን 1968ዓ.ም ውድቅት ላይ ጥምር ጦሩ የሉዓላዊቷን ቼኮዝሎቫኪያ ድንበር ጥሶ ገባ፡፡ ከገዢው የኮሙዩኒስት ፓርቲ አባላት መካከል 2/3ኛው ጣልቃ ገብነቱን ቢቃወሙም የተባበረውን ጦር ግን የሚያስቆም አልተገኘም፡፡

የቼኮዝሎቫኪያ መንግስት ድንበሩን ጥሶ የገባውን ሰራዊት ያለግብዣ እንደመጣ በመናገር ለቆ እንዲወጣ ጥያቄ አቀረበ፡፡ የሶሻሊስትን መርህ፣ አለም-አቀፉን ህግና የተባበሩት መንግስታት ቻርተርን የጣሰው የዋርሰው ቡድን ለስምምነቶቹ ተገዢ እንዲሆን ተማፅኖውን አስተላለፈ፡፡ ሰሚ ግን ጠፋ፡፡ ህዝቡም በበኩሉ ያለጥሪ አፈራቸውን የረገጠውን ጦር መቃወም ጀመረ፡፡ የተለያዩ መፈክሮችን በማንገብ ፍፁም ሰላማዊ በሆነ መንገድ ቅሬታውን አሰማ፡፡ እንግዳ ተቀባዩ ቼኮዝሎቫኪያዊ ለእነዚህ ግን ፊቱን አጠቆረ፡፡ የተቃውሞውን ጥግ ለማሳየትም አንድ ወጣት ተነሳሽነቱን ወሰደ፡፡ ዣን ፓላች ወደታዋቂው የዌንቼስላስ አደባባይ በማምራት ራሱን በእሳት እያይዞ ማገደ፡፡ ትግሉ በመግደል ሳይሆን በመሞት እንደሚመራም ለጨካኙ ጦር አሳየ፡፡ የፕራግ ፀደይ ተብሎ በሚታወቀው በዚህ ህዝባዊ የተቃውሞ ንቅናቄ እሰርና ግድያ የዕለት ተዕለት ትዕይንት መሆኑ ግን አልቀረም፡፡

ጥምሩ የዋርሰው ውል ጦር የሚፈልገውን ሳይፈፅም እንደማይወጣ በተግባር ማሳየት ጀመረ፡፡ የፓርቲውን ሊቀ -መንበርና የማሻሻያ ጥያቄዎቹን አንቀሳቃሽ ዱብቼክን በማፈን ወደራሺያ ወሰደ፡፡ የፖለቲካ ማሻሻያው ላይ እጃቸው የነበረበት የፓርቲው አመራሮችንም እንዲሁ በሚስጥር ወደ ሞስኮ አመጣቸው፡፡ የወቅቱ የራሺያ ፕሬዝዳንት የነበረው ብሬዥኔቭ አስገዳጁን ውል በማዘጋጀት እንዲፈርሙ አማራጭ የሌለው ምርጫን ሰጣቸው፡፡ ዱብቼክ ከፓርቲ ሊቀ-መንበርነቱ እንዲነሳ ተደረገ፡፡ ገዢው የኮሙዩኒስት ፓርቲ በወግ-አጥባቂዎች መልሶ እንዲጠናከር፣ የታየው የፕሬስ መነቃቃት በመንግስት ቁጥጥር ስር እንዲወድቅ እንዲሁም አዲስ የተመሰረተውና

እውቅናን እያገኘ የመጣው የሶሻል ዴሞክራቲክ ፓርቲ እንዲፈራርስ የሚያስገድደውን ስምምነት በኃይል እንዲፈርሙ ተገደዱ፡፡ ስምምነቱም በአጭር ጊዜ ውስጥ ተግባራዊ ሆነ፡፡

ቼኮዝሎቫኪያ የጀመረችው የፖለቲካ እና የኢኮኖሚ ማሻሻያዎች በዋርሶው ውል አባል አገራት ውድቅ ተባሉ፡፡ የቁልቁለት ጉዞው በድጋሚ ተጀመረ፡፡ «ኖርማላይዜሽን» በመባል የሚታወቀው የማረጋጊያ ስራ በመንግስታዊ ተቋማት መሪነት መተግበር ጀመረ፡፡ ከማሻሻያ እንቅስቃሴ በፊት ወደነበረው የአምባ-ገነን አገዛዝ መመለስ አገራዊ አጀንዳ ለመሆን በቃ፡፡ የለውጡ አራማጆች በሙሉ በዚህ እንቅስቃሴ ተወገዱ፡፡ ቼኮዝሎቫኪያም ከጥቂት ጊዜያት በፊት ወደነበረችበት መልክ ተመለሰች፡፡ ፓርቲውን በሊቀ-መንበርነት መምራት የጀመረው ጉስታቭ ሁዛክ ራሺያ ያስላችውን እቅድ በሙሉ አስፈፀመ፡፡ ህዝቡንም ወደ ፍዝ ማህበረሰብነት ቀየረው፡፡ የፕራግ ፀደይም ለቬልቬት አብዮት መጠንሰስ ምክንያት በመሆን በመስዋዕትነት አለፈ፡፡

የፓርቲ መሪነት ያልበቃው ሁዛክ እ.ኤ.አ. በ1975 ዓ.ም የአገሪቱ ፕሬዝዳንትነትን ማዕረግ ደረበ፡፡ በአንድ ወቅት በገዛ ፓርቲው «ከበርቴ» የሚል ውንጀላ ቀርቦበት ለእስር የተዳረገው ይህ ሰው የቼኮዝሎቫኪያ ቀዳሚ ወካይ ለመሆን በቃ፡፡ ዝግ በሆነ የኢኮ ኖሚ እንቅስቃሴ የአገሪቱን ሀብት ማሟጠጥ ጀመረ፡፡ የተቃውሞ ድምፅ እንዳይሰማም አፈናን ብቸኛው አማራጭ አደረገ፡፡ አገሩም ከንፈር የሚመጠጥላት አሳዛኝ ተመፅዋች ለመሆን ዳርዳርታውን ተያያዘችው፡፡

እንዲህ ባለ የአጣብቂኝ አገዛዝ ስር ያለ ማህበረሰብ መቼም አይነቃም ብሎ መደምደም የዋህነት ነው፡፡ የአምባ-ገነኖች ገራገርነት የሚገኘው በዚህ ድክመቶቻቸው መካከል ነው፡፡ ነቅቶ የሚያነቃ ግለሰብም ሆነ ስብስብ ቼኮዝሎቫኪያ እጥታ አታውቅም፡፡ ማህበረሰቡ መድረሻ ባጣ በዚያን ወቅት «እምቢ» ያሉ ጥቂት ሰዎች ተገኙ፡፡ «ቻርተር 77» የተባለ





የሲቪክ ፎረም የመጀመሪያው የተደራጀ ተገዳዳሪ ኃይል ሆኖ ወደአደባባዩ ወጣ፡፡ እ.ኤ.አ. በጥር 6 ቀን 1977 ዓ.ም. ቻርተር 77 የሚል መጠሪያ ያለው ማኒፌስቶ በማዘጋጀት በምዕራብ ጀርመን ጋዜጦች ላይ አሳተመ፡፡ በፍጥነትና በተለያየ አይነት የማስራጫ መንገዶች የተበተነ ው ይህ ማኒፌስቶ መንግስቱን ከፋኛ ይኮንናል፡፡ ራሱ ያረቀቀውን ህገ-መንግስትና አለም-አቀፍ ቃል-ኪዳኖችን በመጨፍለቅ የዜጎችን ህይወት ፈታኝ ያደረገው ግራ-ዘመም አገዛዝ ሰብዓዊ መብትን ያለአንዳች ቅድመ-ሁኔታ እንዲያከብር በማኒፌስቶው ላይ ተጠይቋል፡፡ ከጥበብ ሰዎች፣ ከቀድሞ ባለስልጣናትና ከአደባባይ ምሁራን የተውጣጡ 243 ግለሰቦች በንድፈ-ሃሳቡ ላይ ፈርመዋል፡፡ የሁሉም እጣ ፈንታ ግን መከሰስ፣ መታሰር ና ከስራዎቻቸው መባረር ነበር፡፡ ስብስቡን ግን በእንዲህ መሠል ማዋከብ ማቆም አልተቻለም፡፡ ለውጥን በእስር ማቆም ቢቻል ኖሮ የቼኮዝሎቫኪያው ሰው-በላ መንግስት ዛሬም ድረስ በቆየ ነበር፡፡

## የመጨረሻው መጀመሪያ

እ.ኤ.አ. ህዳር 17 ቀን 1989 ዓ.ም. የተማሪዎች ቀን ተብሎ በአለም-አቀፍ ደረጃ ይከበር ነበር፡፡ የቼኮዝሎቫኪያ ወጣቶች ዕለቱን ለማስታወስ ያሰቡት ግን በተለየ ሁኔታ ነው፡፡ ዣን አፕሌታል የተባለውንና የአገሩ ድንበር በናዚ ወታደሮች ሲደፈር መታገስ አቅቶት ባሳየው ቁጣ የተገደለው ወጣት ቢሰዋም ‹ክብር ይገባሃል› ሊሉት ቀጠሮ ያዙ ፡፡ የሰልፉ አስተባባሪዎች ፍፁም ሰላማዊ የሆነ ሰልፍ ለማድረግ ቃል ተገባቡ፡፡ ትዕይንቱ የሚፈጥረውን መነቃቃት የፈራው መንግስት ደግሞ ሁሌም የሚተማመንበትን ጦር ሰራዊት በተጠንቀቅ አቆመ፡፡

የገዢው ፓርቲ የወጣቶች ክንፍ ዕለቱን ለመዘከር ፍቃድ በመጠየቁ ሰልፉ ፈቃድ ተቸረው፡፡ በእነዚህ ወጣቶች አዕምሮ ውስጥ ይመላለስ የነበረው ግን ከለውጥ ፈላጊዎቹ ሀሳብ ጋር የሚስማማ ነበር፡፡

የዩኒቨርስቲ ተማሪዎችና የከተማ ወጣቶች አላማ ም አንድ ሆነ። በጠዋት የተያዘው ቀጠሮ በ15 ሺህ ሰው ስብስብ ጉዞውን ጀመረ። በቪሴህራድ የመቃብር ቦታ ላይ ሊጠናቀቅ እቅድም ተይዞለታል። በአነቃቂ መዝሙሮች፣ በመፈክሮችና በአዝናኝ ክስተቶች የተዋዛው ደማቁ ሰልፍ የመንገደኞችን ቀልብ ገዛ። በእስርና በግፍ፣ በኑሮ ውድነትና በስቃይ የታሸው ህዝብ የራሱን ጥያቄ እያነሳ ሰልፉን እንደነገሩ ተቀላቀለ። የትዕይንቱ መዳረሻ ተረሳ። የፐራግ ታላቁ አደባባይ ወደሆነው ወደ ዌንቼስላስ የሰልፈኞቹ እግር አመራ። በተጠንቀቅ እንዲቆም ትዕዛዝ ወርዶለት የነበረው አድማ በታኝ ጦርም እጁን እያፍታታ ጠበቃቸው።

ናሮድኒ ጎዳና ላይ እንደደረሱ የሰልፉ ማክተሚያ እንዲሆን ተገደደ። የማምለጫ መስመሮቹ በሙሉ በታ ጣቂዎቹ ተዘጉ። የተገኙት መሹለኪያዎች በሙሉ ከጉልበተኞቹ ዱላ ለማምለጫነት አገለገሉ። በመካከሉ ግን ከተማሪዎቹ ወገን በርከት ያሉት ለጉዳት ተዳረጉ። በዚህ መንግስታዊ እርምጃ ንቅናቄውን የገታ የመሰለው አገዛዝ የመውደቂያውን የመጀመሪያ ከስተት ራሱ እንደለኮሰው ግን አልተረዳውም። የአምባ -ገነኑ ስርዓት መጨረሻ በዚህች ቀን በተከሰተው የግፍ ስቃይ ተጀመረ፣ የቬልቬት አብዮት ማብሰሪያ ደውል ተሰማ። በዚሁ ዕለት ምሽት ተማሪዎችና የቲያትር ባለሞያዎች በአድማው ለመቀጠል ተስማሙ።

በቀጣዩ ቀን ከተማሪው የተወከሉ ሁለት ወጣቶች የወቅቱን ጠ/ሚኒስትር ላዲስዓቭ አዳሜክን ለማናገር ወደ ቤተ -መንግስቱ ተጋበዙ። ከአንድ ቀን በፊት የሆነውንም በድፍረት አብራሩ። በናሮድኒ ጎዳና ውሎ ያዩትንና የሰሙትን መሰከሩ። በተመሳሳይ ሰዓት ከቤተ-መንግስቱ ውጪ ታሪክ እየተከተበ ነበር። ቲያትር ቤቶች የስራ ማቆም አድማ ውን ጀመሩ። አዳራሹንም ለህዝባዊ ውይይቶች ብቻ ክፍት አደረጉ። ተማሪዎች ም በበኩላቸው የትምህርት ማቆሙን አድማ አቀጣጠሉት። ስርዓቱም እስኪፈራርስ ወደ ትምህርታቸው አልተመለሱም።





በመላው ቼኮዝሎቫኪያ የግል የሚዲያ ውጤት ባለመኖሩ ፅሁፎች በበራሪ ወረቀቶች ላይ እየተከተቡ ቤት ለቤት መሰራጨት ጀመሩ። በአንድ ቀን ልዩነት ውስጥ ታሪክ መገለባበጡን ያዘ። የነፃ አውሮፓ ሬዲዮ (Radio Free Europe) ጣቢያ፣ የተሳሳተ ዘገባ ቢሆንም፣ አንድ ተማሪ ከአመፁ ጋር በተያያዘ መገደሉን በዜና አወጀው አሰራጨ። ይህም የመህል ቤት ፖለቲካ የሚያራምደውን ዜጋ ወደተቃውሞ ገፋው። የጥበበና የስነ -ፅሁፍ ማህበራት የተቃውሞውን እንቅስቃሴ ተቀላቀሉት። ከሲቪክ ማህበር የተውጣጣ አንድ ቡድን ሁለት ጊዜ መልቀቂያ እንዳስገቡ ወደተነገረላቸው ጠ/ሚኒስትሩ ቢሮ በግብግብ አመሩ። ነውጥ የሌለበት የለውጥ ጥያቄ ማንሳት እ ንደሚችሉም ከባለስልጣኑ እንደበት ማረጋገጫን አገኙ። በስሎቫኪያ አካባቢ የተዋቀረውና መንግስታዊ ጥቃትን ከህዝብ ለመከላከል የተቋቋመው ቡድን በተማሪዎች ላይ የተደረገውን ጥቃት ከፉኛ ኮነነ። የለውጡ አካል መሆኑንም በዚያኑ ዕለት አወጀ።

በቲያትር ድርሰት ፀሀፊነትና አዘጋጅነት የሚታወቀው ቫክላቭ ሀቨል በእርሱ ከሚመራው የቻርተር 77 የሲቪክ ተቋም ጋር በመሆን የፖለቲካ እስረኞች በሙሉ እንዲፈቱ፣ ተማሪዎ ቹ ላይ የተወሰደው እርምጃ በገለልተኛ ቡድን እንዲመረመርና ጥፋተኛ ሆነው የተገኙ ባለስልጣናትም ከስልጣን እንዲወርዱ የሚል በቁጣ የተሞላ መግለጫ አወጣ። ይህ የማይፈፀም ከሆነ ደግሞ በተማሪዎች፣ በቲያትር ቤቶችና በመንግስት ተቋማት ሰራተኞች የተጀመረው አድማ እንደማይቀለበስ አረጋገጠ። በመንግስት ቁጥጥር ስር ያሉ መገናኛ ብዙሃን ይህን የሚቃወም የማስፈራሪያ መልዕክት እያስተላለፉ ነበር። የተመረጡ የመን ግስት ባለስልጣናት በቴሌቪዥን በመቅረብ ሰላም እንዲወርድና ከተሞች ወደ መደበኛ ስራቸው እንዲመለሱ ማሳሰቢያቸውን አስተላለፉ። በነፃ አውሮፓ ሬዲዮ ተገድሏል ተብሎ ሲነገርለት የነበረው ማርቲን ስሚድ በቴሌቪዥን ጣቢያው በመቅረብ በእርሱ ላይ የተናፈሰው ወሬ ብቻ መሆኑን በመናገር በህይወት እንዳለ ለማረጋገጥ ሞከረ። አንዴ ከቤቱ የወጣውን ህዝብ ግን የሚያቆመው

አልተገኘም፡፡ ለዘመናት ሲገፉ የኖረ ህዝብ እም ቢ ያለ ቀን የትኛውም ማባበያ ከጉዞው አይገታውም፡፡

የተማሪዎቹና የቲያትር ባለሞያዎቹ አድማ በቀጣዩም ቀን እንደቀጠለ ነው፡፡ በህገ-መንግስቱ የተደነገገው የኮሙዩኒስት ፓርቲው ገዢነት እንዲሻር ጥያቄዎች መሰማት ጀመሩ፡፡ በዕለቱ በከፍተኛ ቁጥር የተኮናከረ አድማ በታኝ ፖሊስ ቢሰማራም ህዝቡን ከቤት መመለስ ግን አልቻለም፡፡ ህዳር 20 ቀን አንድ መቶ ሺህ ያህል ሰልፈኛ ዋና ከተማዋን ፕራግን ወረራት፡፡

ፈጣኑና ተከታታዩ የለውጥ ንቅናቄ መሰረት መያዝ ጀመረ፡፡ አገዛዙም ለውጥ ፈላጊውን አካል ማዳመጥ ግዴታ እንደሆነበት ተረዳ፡፡ በሲቪክ ማህበሩና በጠቅላይ ሚኒስትሩ መካከል ይፋዊ ውይይት መኖር እንዳለበት ተወሰኖም ህዳር 21 ቀን በቤተ-መንግስቱ ውስጥ ተገናኙ፡፡ የመንግስት ተወካዩ ባለስልጣን ከዚህ በኋላ ምንም አይነት ጉልበት እንዳይጠቀሙ ለአድማ በታኝ ፖሊሶች ትዕዛዝ እንደሚያስተላልፉ ቃል በመግባት ሶሻሊዝም ላይ ግን ድርድር እንደማይኖር ለተወያዮቹ ተናገሩ፡፡ በተመሳሳይ ሰዓት ግን ታዋቂው የዌንቼስላስ አደባባይ በህዝብ ማዕበል ተጥለቅልቆ ነበር፡፡ የተማሪዎችና የቲያትር ባለሞያ ተወካዮች ደግሞ የሰራተኛውን ድጋፍ ለመሰብሰብ በየፋብሪካዎች እየዞሩ የቅስቀሳውን ስራ እያጣደፉት ነበር፡፡ በመጪው ህዳር 27 በተዘጋጀው አገር-አቀፍ የስራ ማቆም አድማ ላይ ሁሉም እንዲስማማ የማግባባቱ ተግባር ዋናው ስራቸው ነበር፡፡

የፖለቲካ እስረኛው ግን ካርኖጉርስኪ እንዲፈታ የሚጠይቅ ሰልፍ ደግሞ በጎን ሲካሄድ ነበር፡፡ በሚገርም ሁኔታ ይህን ህዝባዊ ትዕይንት የመራው የመንግስት ባለስልጣን የነበረውና የማሻሻያ እርምጃ መኖር ይገባዋል ሲል የተሟገተው አሌክሳንደር ዱብቼክ ነበር፡፡ የሰልፉ ውጤታማነት የተለካውም ትዕይንቱ ሳይጠናቀቅ እስረኛው በመፈታቱ





ነበር፡፡ የዕለቱ ሌላው ስኬት ደግሞ ካቶሊካዊቷ ቤተ-ክርስቲያን ለተማሪዎች ድጋፏን ማሳየቷ ነው፡፡ ካርዲናል ቶማሴክ፣ ገዢውን ፓርቲ በአደባባይ በመንቀፍ ለውጥ እንደሚያስፈልግ በምዕመኑ ፊት ተናገሩ፡፡ ልባዊ ፀሎታቸውም አምላክ ከወጣቶቹ ፊት እንዲወጣ መሆኑን መሰከሩ፡፡ በመንግስት የቴሌቪዥን ጣቢያ በመቅረብ የመጨረሻ እርምጃ እንደሚወሰድ ያወጁት ባለስልጣን ቃላቸው ከዛቻ መዝለል ያልቻለው በእነዚህ ተከታታይ እርምጃዎች ውጤታማነት ነበር፡፡

በስሎቫኮች በኩል የታየው እምቢ-ተኝነትም አስገራሚ የሚባል ነው፡፡ ዛሬ ከእናት ሀገሯ ቼክ ሪፐብሊክ ጋር ተለያይታ ራሷን ማስተዳደር የጀመረችው ስሎቫክ ታሪክ ተሰርቶባታል፡፡ ቼኮች የቬልቬት በሚሉትና እነሱ ደግሞ ጀንትል ብለው በሚጠሩት በዚህ የአብዮት እንቅስቃሴ ውስጥ ታላቅ ሚና ተጫውተዋል፡፡ በዚህ ጥምር ንቅናቄ መፍረክረክ የጀመረው የኮሙዩኒስት አገዛዝ አደባባዮች የሞላውን ህዝባዊ አመፅ ሊቋቋመው አቅቶታል፡፡ በአስገዳጅ ሁኔታዎች ወደድርድር ማዘንበሉን ተያይዞ ታል፡፡

ህዳር 22 ቀን በትዕይንቱ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ ስለሰልፉ የሚያወሳ ዜና በመንግስት የቴሌቪዥን ጣቢያ ቀረበ፡፡ በዘገባው የታየው የህዝብ ቁጥርና በድምፅ የቀረበው ሀተታ ግን ሀሰት የተቀላቀለበት ነበር፡፡ የሸፈተ ሀሳብ መያዣ የለውም፡፡ የስሎቫክ ፌዴራላዊ የቴሌቪዥን ጣቢያ ሰራተኞች ይህን ስህተት አይተው ማለፍ አቃታቸው፡፡ እውነተኛ የመረጃ ምንጭ ማስተላለፍ ያቃተውን መስሪያ ቤታቸውን በመልቀቅ አድ ማ እንደሚመቱ አስጠነቀቁ፡፡ ቁጣቸው በእርግጥም የተሳካ ነበረ፡፡ ከዚህ ዕለት ጀምሮ እስከ መንግስታዊው ለውጥ ድረስ የነበረው ህዝባዊ ትዕይንት በቀጥታ በየቤቱ ባሉ ቴሌቪዥኖች መተላለፍ ጀመረ፡፡ በየመሀሉም ምንም አይነት የሀይል እርምጃ እንደማይወሰድና ህዝቡ ግን ወደቤቱ እንዲገባ መነገሩ አልቆመም ነበር፡፡ ስንቱን ገድዬ እጨርሳለሁ ያለ የሚመስለው

ሰራዊትም ሁኔታውን በጥንቃቄ ከማየት ውጪ ሊያደርግ የሚችለው አልነበረም።

ህዳር 25 ቀን 1989 ዓ.ም በተቃውሞ ሀይሉና በመንግስት መካከል የተደረገ ውይይት በመገናኛ ብዙሃኑ በቀጥታ ተላለፈ። ከዚህ ውይይት በኋላ የመንግስት ጋዜጣ ተብለው በልምድ የሚታወቁት ጋዜጦች በርዕስ - አንቀፅ ደረጃ ለውጥን ማቀንቀን ጀመሩ። እየታየ ባለው ፈጣን ለውጥ የተነቃቁ በርካቶች ውሎና አዳራቸውን አደባባዮች ላይ አደረጉ። የዌንቼስላሱ ሰልፈኛ ወደ አንድ ሚሊዮን ሲደርስ በብራቲስላቫ አደባባይ የነበረው ደግሞ ከአንድ መቶ ሺህ አልፎ ነበር። በታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜም እርሱ ባይኖር ኖሮ የቬልቬት አብዮት አይሳካም ነበር ተብሎ የሚወደሰው ቫክላቭ ሀቬልና ጠ/ሚኒስትሩ አዳሜክ ፊት ለፊት ተገናኝተው ተወያዩ። የሁለቱን ሰዎች ውይይት ተከትሎ የአገዛዙ መጨረሻ መቃረቡን የሚገምቱ ቁጥራቸው እየበዛ መጣ። በተለይ በሀቬል ውጤታማ ውይይት ማግስት የተደረገው የሁለት ሰዓት አገር -አቀፍ አድማ የመንግስት ስልጣን ከእጅ እየወጣ እንደሆነ አሳየ። መንግስታዊ ትዕዛዞች መደመጥ አቆሙ። በተቃራኒው በተቃውሞ ጎራ የተሰለፉት ቃል እንደሀይማኖታዊ ትዕዛዛት ይቆጠሩ ነበረ።

ህዳር 29 ቀን ኮሙዩኒስታዊው መንግስት ብቸኛ የአገሪቱ ወካይ መሆኑን የሚያውጀው የህገ-መንግስት አንቀፅ በይፋ ተሰረዘ። የቼኮዝሎቫኪያ እፎይታም ተቃረበ። በታህሳስ 10 ጥቂት የኮሙዩኒስቱ አባላት ብቻ የተካተቱበት ጊዜያዊ መንግስት ቃለ -መሃላ ፈፀመ። ይህም አንድም መስኮት እንኳን ያልተሰበረበት እየተባለ ለሚነገርለት የቬልቬት አብዮት ታላቅ ስኬት ነበር።

አብዮት ሲባል ፈጣንና ስር -ነቀል ነውና በጊዜያዊው መንግስት ላይ የታየው ቀዝቃዛ ስሜት በህዝቡ አልተወደደም። አገሪቱን በፕሬዝዳንትነት እንዲመሩ በጊዜያዊነት የተሾሙት ጉስታቭ ሁዛክ ስል ጣናቸውን በገዛ





ፈቃዳቸው ለቀቁ። እርሳቸውን ለመተካት ሰው ሲፈለግም የአብዮቱ መሪ ቫክላቭ ሀቬል ተገኘ። ታህሳስ 29 ቀን 1989 ዓ.ም ስልጣኑን በአደራ ጠባቂነት ተረከበ። ቼኮዝሎቫኪያ ወደኋላ ላትመለከት ጉዞዋን ጀመረች። ዴሞክራሲ የአምባ-ገነኑን ታሪክ በመፋቅ ተተካ። የህዝብ ብሶት የተሻለች አገርን ፈጠረ።



ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ

# ክፍል አራት

# ሠላማዊ ትግል





ምዕራፍ I - ሕዝባዊ እምቢተኝነት Civil Disobedience
- «ሕዝባዊ እምቢተኝነት» በጥንት ዘመን
- የሕዝባዊ እምቢተኝነት ፅንሠ-ሃሳብ

ምዕራፍ II – የሠላማዊ ትግል ስልቶች ምንድን ናቸው?
- ስለሠላማዊ ትግል ዋነኛ ጭብጦች

ምዕራፍ III - የሠላማዊ ትግል ስልቶች
- የረሃብ አድማ እንደ ሠላማዊ ትግል ስልት
- አቤቱታ (Petition) እንደ ሠላማዊ ትግል ስልት
- ማገቶ (PicKeting) እንደሠላማዊ ትግል ስልት
- የሥራ ማቆም አድማ እንደ ሠላማዊ ትግል ስልት
- ቁጭ በሉ (Sit in) እንደ ሠላማዊ ትግል ስልት

ምዕራፍ IV - ሠላማዊ ትግል የሚሳካው እንዴት ነው?
- የሠላማዊ ትግል ጠቀሜታዎች
- የሠላማዊ ትግል ቅድመ ሁኔታ ዓላማን ለይቶ ማወቅ
- ሠላማዊ ትግል መቋቋም የሚኖርበት ፈተናዎች

ምዕራፍ V - የሠላማዊ ትግል ተሞክሮዎች
- የተለመዱ የህዝባዊ እምቢተኝነት ክሶች
- የህዝባዊ እምቢተኝነት ተቆጣጣሪዎች
- የህዝባዊ ሠልፈኞችና የፖሊስ መብቶች

ምዕራፍ VI - ቤተ-ክርስቲያንና ሠላማዊ ትግል
- የ«ሥነ-መለኮታዊ አርነት» ፅንሠ-ሀሳብ Liberation Theology

ምዕራፍ IIV – ህዝባዊ እምቢተኝነት በኢትዮጵያ ሊሠራ ይችላል ወይ?



ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ

# መታሰቢያነቷ

ዕለተ-ረብዕ ሰኔ አንድ 1997 የአዲስ አበባ አየር ተከፍቶ ነበር፡፡ ከማለዳው አንስቶ ጨፍጋጋና ደመና ያጠላበት አዲስ አበባ፣ የጦር ቀጠና መስላ በብረት ለበስና በከባድ መኪናዎች የተጫኑ ሰራዊቶች እንቅስቃሴ የከተማውን ህዝብ ስጋት ውስጥ ጥለውት ነበር፡፡ በዚህ ዕለት፣ ከማለዳ አንስቶ የታክሲ ሹፌሮች፣ እንዲሁም፣ ነጋዴዎች ባደረጉት የስራ ማቆም አድማ የከተማዋ እንቅስቃሴ ቆሞ ነበር፡፡

በዚህ መንፈስ ውስጥ ነበር፣ በአውቶብስ ተራ፣ በጐጃም በረንዳ፣ በመሳለሚያና በተክለኃይማኖትና በአብነት አካባቢ የተንቀሳቀሱ ታጣቂዎች፣ ሰላማዊና ንፁህን ዜጐች ላይ ተኩስ ከፍተው አሰቃቂውን አደጋ ያደረሱት፡፡ በታጣቂዎቹ ጥይት 4 0 የሚደርሱ ኢትዮጵያውያን ህይወታቸው ሲያልፍ፣ በርካታ ወገኖች ለአካል ጉዳት ተዳርገው በሰቃይ ላይ ይገኛሉ፡፡

እናት ኢትዮጵያ በንፁህን ልጆቿ ላይ በተፈፀመው ግፍ አንገቷን ደፍታለች፡፡ እንደዋዛ በፈሰሰው የሰላማዊ ዜጐች ደም የአዲስ አበባ ጐዳናዎች ታጥበዋል፡፡ ስለተፈፀመው ግፍ «ሄሎሄ... ሄሎሄ...» ሲሉ ኢትዮጵያውያን ወደ ፈጣሪያቸው ጮኸዋል፡፡

የዚያ ዕለት ግድያ፣ ከአንድ ቤት ሁለት ልጆችን በልቷል፣ ታ ዳጊው ህፃን ነቢያ አለማየሁ፣ ዩኒፎርሙን ለብሶ ደብተሩን እንደያዘ በትንሹ ልቡ ውስጥ ጥይት ተሰቆበታል፡፡ «ጉሽ ለልጄ ሰትል ተወጋች» እንዲሉ፣ ልጄን ብለው የወጡት እናትም በታጣቂዎቹ በተተኮሰባቸው ጥይት ህይወታቸውን አጥተዋል፡፡

ሰርቶ አዳሪ፣ ቤተሰብ አስተዳዳሪ ወጣቶች፣ ህፃናት እዛውንት ሳይቀሩ በዚያ ዕለት በጥይት ተጨፍጭፈው ሬሳቸው እንደ ውሻ በጐዳናዎች ላይ ወድቋል፡፡

ለእነዚህ ሰማዕታት ወገኖቻችን ይህን ጽሑፍ በመታሰቢያነት መቅረቡ ቢያንስ እንጂ አይበዛም፡፡ እኔም የምርጫው ትኩሳት (ነበልባል እሳት) ለበላቸው ወገኖች ይህችን ጽሑፍ በመታሰቢያነት ሳቀርብ፣ ለሟች ቤተሰቦች መፅናናትን በመመኘት ነው፡፡

ፈጣሪ፣ የንፁህን ዜጐቻችንን ነፍስ በክብር ተቀበላት!

እስክንድር ነጋ





## ምዕራፍ ፩

# ሕዝባዊ እምቢተኝነት

# Civil Disobedience

"Civil Disobedience" የሚሉትን ሁለት የእንግሊዘኛ ቃሎች ወደ አማርኛ ለመተርጐም ሲታገል የነበረ የዩኒቨርስቲ ዘመን ጓደኛዬን መቼም ቢሆን አልረሳውም፡፡ የጥቁር አሜሪካዊው ማርቲን ሉተር ኪንግ አድናቂ ነበር፡፡ "Civil Disobedience እኮ በእኛ ሀገር አይሰራም፡፡ ለምን ልተርጉመው ብለህ ትጨነቃለህ?" ብዬ በተደጋጋሚ አቀርብለት ለነበረው ጥያቄ፣ «ጊዜው ይመጣል» ይለኝ ነበር፡፡ በጊዜው እስቅበት ነበር፡፡ ዛሬ ግን፣ አድናቂው ሁኛለሁ፡፡ ሩቅ ማየት ይችል ነበር ማለት ነው፡፡ አሜሪካ መቅረቱ ሁልጊዜ ይቆጨኛል፡፡ ያቺ ሀገር፣ ብዙ ልጆቻችን ውጣ ቀርታለች፡፡

ያ ጓደኛዬ (ስሙን ያለፍቃዱ ማንሳት አልፈልግም) አሜሪካንን ምን ያህል እንደሚጠቅማት አላውቅም፡፡ በእርግጠኝነት መናገር የምችለው፣ ይቺን ምስኪን ሀገሩን የበለጠ እንደሚጠቅማት ነው፡፡ ይህን ጓደኛዬን የሆነ ጊዜ ላይ ደውዬ ሳነጋግረው «አንተ ተመልሰህ ምን ለውጥ አመጣህ?...» በማለት እንዲመለስ ያቀረብኩለትን ጥያቄ አጣጥሎብኛል፡፡

«እኔ ብቻዬን ለውጥ አመጣለኹ ብዬ አልተመለስኩም፡፡ ለውጥ የሚያመጡት አካል ለመሆን እታደላለኹ በሚል ተስፋ ነው የተመለስኩት» የሚል ምላሽ ሰጥቻቸዋለኹ፡፡

በእኔ በኩል፣ በጓደኛዬ ላይ ተስፋ አልቆርጥም፡፡ ወደ ሀገሩ እንዲመለስ እስከመጨረሻው እፍጨረጨራለኹ፡፡ እስከዛው ግን፣ ጓደኛዬ «ሕዝባዊ እምቢተኝነት» ("Civil Disobedience") በማለ ት ሲተነትንልኝ ከኖረው የማስታውሰውንና፣ እኔም እንደአቅሚቲ በግሌ የሠራኋትን አነስተኛ ጥናት አካትቼ ያቀናበርኩትን ላካፍላችኹ እወዳለሁ፡፡

## «ሕዝባዊ እምቢተኝነት» በጥንት ዘመን

ሁለተኛው የዓለም ጦርነት እየተጋጋለ ባለበት ወቅት፣ ማለትም፣ በ1940 (እ.ኤ.አ.) በፈረንሳይ ሰሜናዊ የባህር ዳርቻ በምትገኘው ዳንኪርክ፣ የጀርመን ጦርን የወደፊት ግስጋሴ መቋቋም ያቃተው አንድ እንግሊዛዊ የጦር መኮንን "But if not?" («ባይሆንስ?») የሚሉትን ሶስት ቃላት ያዘለ ሃረግ ቴሌግራም ወደ ለንደን ልኮ ነበር፡፡ «መቋቋም ቢያቅተንስ?...» ማለቱ ነበር፡፡ ቴሌግራሙን በእንግሊዝ መዲና ያነበበው ሰው፣ ሃረጉ የተመዘዘው ከመጽሐፍ ቅዱስ፣ ብሉይ ኪዳን (ትንቢተ ዳንኤል፣ ምዕራፍ 3/13 -18) መሆኑን ተረድቶ ነበር፡፡ ትንቢተ ዳንኤል፣ እንዲህ ይላል፡ -

*ናቡከደነፆርም በብስጭትና በቁጣ ሲድራቅንና ሚሳቅን አብደናጎንም፣ ያመጡ ዘንድ አዘዘ፡፡ እነዚህንም ሰዎች ወደ ንጉሡ ፊት አመጡአቸው፡፡ ናቡከደነፆርም ሲድራቅና ሚሳቅ አብደናጎም ሆይ፣ አምላኬን አለማምለካችኹ ላቆምኹትም ለወርቁ ምስል አለመስገዳችሁ እውነት ነውን? አሁንም የመለከቱንና የእንቢልታውን የመሰንቆውንና የክራሩን የበገናውንና የዋሽንቱን የዘፈኑንም ሁሉ ድምፅ በሰማችሁ ጊዜ ተደፍታችሁ ላሠራሁት ምስል ብትሰግዱ መልካም ነው፡፡ ባትሰግዱ ግን፣ በዚያ ጊዜ በሚነድድ እሳት እቶን ውስጥ ትጣላላችኹ፡፡ ከእጄስ የሚያድናችሁ አምላክ ማን ነው? ብሎ ተናገራቸው፡፡ ሲድራቅና ሚሳቅ አብደናጎም መለሱ ንጉሡንም ናቡከደነፆር ሆይ፣ በዚህ ነገር እንመልስልህ ዘንድ አስፈላጊያችን አይደለም፡፡ የምናመልከው አምላካችን ከሚነድደው ከእሳቱ እቶን ያድነን ዘንድ ይችላል፡፡ ከእጅህም ያድነናል፡፡ ንጉሥ ሆይ፣ ነገር ግን፣ ንጉሥ ሆይ፣ እርሱ ባያድነን፣ አማልክትህን እንዳናመልክ ላቆም ኸውም ለወርቁ ምስል እንዳንሰግድለት እወቅ አሉት፡፡ (ትንቢተ ዳንኤል ም.3 ቁ.13 -18)*





መጽሐፍ ቅዱስ፣ ለዓለማዊ መንግስት እምቢተኛነትን በገለፁ ግለሰቦችና ቡድኖች የተሞላ ነው፡፡ በብሉይ ኪዳን ውስጥ የሚገኙት አይሁዳውያን በተደጋጋሚ ከዓለማዊ መንግስቶቻቸው ጋር ሲፋጠጡ እንባበናል፡፡

በብሉይ ኪዳን፣ ትንቢተ ዳንኤል፣ ምዕራፍ 6 ላይ፣ ዳንኤል ለ30 ቀናት ጮክ ብሎ ለፈጣሪው እንዳይፀልይ ተከልክሎ ነበር፡ ፡ ዳንኤል ግን፣ ሙብቱን አንዲት ስንዝር እሳልፎ ቢሰጥ፣ ባላንጣዎቹ አንድ ክንድ ያህል እንደሚነጥቁት ተረድቶታል፡፡ በዚህም ምክንያት፣ መፀለዩን በመምረጡ፣ ከሞት ጋር ሊፋጠጥ ችሏል፡፡

በሀዲስ ኪዳን፣ የሉቃስ ወንጌል፣ ምዕራፍ 23 ስናነብ ደግሞ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ የተሰቀለው ዓለማዊ መንግስትን በመቃወሙ እንደሆነ እንረዳለን፡፡ የሐዋርያት ስራ፣ ምዕራፍ 14፡19 እና 5፡29 የክርስቶስ ተከታዮች፣ ነገሮች እየከረሩ ሲሄዱ ከሠው ልጅ ይልቅ፣ ፈጣሪን መታዘዝ እንዳለብን ይመክሩናል፡፡ ሐዋርያው ጳውሎስ ብዙ መልዕክቶቹን የፃፈው በሮማውያን ወህኒ ቤቶች ውስጥ ሆኖ ነበር፡፡ ዮሐንስም፣ ራዕዩን የፃፈው በስደት ቆይታው ነበር፡፡ ከእነኚህ ሐዋርያት ስራ የምንረዳው ነገር ቢኖር፣ ለዚህ ሁሉ ስቃይ የተዳረጉት «ሠላማዊ ዓመፅን» በመሣሪያነት ተጠቅመው መንግስታቸውን በመቃወማቸው ነው፡፡

## የሕዝባዊ እምቢተኝነት ፅንሠ-ሃሳብ

The Columbia Encyclopedia, ስድስተኛ ቅጂ (2001-05) እንደሚያስረዳን፣

*«ሕዝባዊ እምቢተኝነት ኢ-ፍትሃዊ ነው» ተብሎ ለሚታመን ህግ ለመታዘዝ እምቢተኛ መሆን ማለት ነው። በ«ሠላማዊ ዓመፅ» ውስጥ የሚሳተፉ ወገኖች፣ «ኢ-ፍትሃዊ ነው» ላሉት ሁኔታ ትኩረት ለማስገኘት ኃይልን ያላካተቱ ሠላማዊ የትግል ስልቶችን ይጠቀማሉ። ከፍተኛ አካላዊ ወይም ስነ-ልቦናዊ ጉዳትን፣ አልያም እስርን የመሰሉ የቅጣት ዓይነቶች እንደሚያደርሱባቸው እያወቁ፣ ህጉ እንዲለወጥ የተቻላቸውን ያህል ይጥራሉ። አሁን ባለንበት ዘመን፣ ከ«ሕዝባዊ እምቢተኝነት» መገለጫዎች መካከል ሠላማዊ ሠልፎች፣ ህንፃዎችን መውረር፣ እንዲሁም የስራ ማቆም አድማ ይገኙባቸዋል።»* ይላል።

የ«ሕዝባዊ እምቢተኝነት» ፍልስፍና በጥንታዊዎቹ የግሪክና የሮም ስልጣኔዎች፣ እንዲሁም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በስፋት የሚገኝ ፅንሠ ሃሳብ ነው።

አሜሪካዊው ፈላስፋ፣ ሄንሪ ዴቪድ ቶሮ፣ On the Duty of civil Disobedience (1849 እ.ኤ.አ.) በተሰኘው መጽሐፋቸው፣ ይህንኑ ፅንሠ ሃሳብ በስፋትና በጥልቀት የተነተኑበት በዘርፉ ካሉት ዓበይት ስራዎች መካከል ጎልቶ የሚታይ ነው። እኚህ ፈላስፋ በዚሁ መጽሐፋቸው ላይ፣ ስልጣኑንና ውክልናውን ለመንግስት የሰጠው ግለሰብ፣ ኢ-ፍትሃዊ ህጎችን በመቃወሙ በኩል፣ ህሊናው የሚለውን መከተል እንደሚኖርበት አፅንኦት ሠጥተውታል።

ማህተመ ጋንዲ፣ በደቡብ አፍሪካ የህንዳውያንን መብት ለማስከበርና ሀገራቸውን ከእንግሊዝ ቅኝ አገዛዝ ነፃ ለማውጣት





የተጠቀሙባቸው ሠላማዊ የትግል ዘዴዎች በአብዛኛው ከቶሮ ስራ የተወሰዱ ናቸው። ጋንዲ ደግሞ፣ «ሕዝባዊ እምቢተኝነት» ከህንድ ባህልና ትውፊት፣ እንዲሁም ከራሳቸው ግብረ-ገባዊ መለኪያዎችና ጠንካራ ዲሲፕሊን ጋር በማጣመር፣ በጥንታዊው የሳንስክሪት ቋንቋ «ዕውነትን መያዝ» የሚል ትርጉም ያለውን «ሳትያግራሃ» የተሰኘውን የ«ሠላማዊ ዓመፅ» ፅንሠ ሃሳብን አዳብረዋል። በርካታ ተከታዮችን ማፍራት የቻሉት ጋንዲ፣ እንግሊዞች በህንድ ላይ የጫኑትን ቅኝ አገዛዝ እንዲያበቃ የተጠቀሙት ይህንኑ በዲሲፕሊን የታነፀ የትግል ስልት ነበር። በ«ሕዝባዊ እምቢተኝነት» ታሪክ ስኬትን ካስመዘገቡት ጥቂት ትግሎች መካከል፣ የጋንዲ «ሳትያግራሃ» አንዱ ነበር።

የ«ሕዝባዊ እምቢተኝነት» ፍልስፍናንና ስልቶች ለዓላማቸው ማስፈፀሚያነት ከተጠቀሙት መካከል፣ ኃይማኖታዊ ቡድኖች፣ የእንግሊዝ የሠራተኞች ንቅናቄ፣ የሴቶች መብት ተሟጋቾች፣ ሠላም ወዳጆች፣ የጦርነት ተቃዋሚዎች፣ የአካል ጉዳተኞች ይገኙባቸዋል።

አሜሪካ፣ የ«ሕዝባዊ እምቢተኝነት» ድንቅ መሪ፣ ዶክተር ማርቲን ሉተር ኪንግ ናቸው። ኪንግ፣ በ1950ዎቹና 1960ዎቹ ዓመታት የጥቁር አሜሪካውያንን መብት ለማስከበር፣ የተለያዩ የሠላማዊ ትግል ስልቶችን በመምራት፣ ወሳኝና ቁልፍ ሚና ተጫውተዋል። ኪንግም ልክ እንደ ጋንዲ ብዙ ጊዜ ለእስር ተዳርገዋል። የፌዴራሉ መንግስት አዲስ የሲቪል መብቶች ህግ እንዲያወጣና በጉዳዩ ዙሪያ የህዝቡን አመለካከት ለመለወጥ፣ በ«ሠላማዊ ዓመፁ» ላይ በተሳተፉት ሰዎች ላይ የደረሱ ድብደባዎች፣ ጅምላ እስሮችና ግድያዎች ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል። ቀደም ሲል በዩ.ኤስ. አሜሪካ የተካሄዱት «ሕዝባዊ እምቢተኝነት» ከግራ ክንፈኞች የትግል ስልት ጋር የተሳሰሩ ተደርገው ይወሰዱ ነበር። ከ20ኛው ምዕተ ዓመት ማብቂያ ወዲህ ግን፣ የፀረ ውርጃ አቋም አራማጆችን ጨምሮ፣ ሌሎች ቀኝ ክንፈኞች «ሠላማዊ ዓመፅ»ን እንደ ትግል ስልት እየተጠቀሙበት ነው።

በ«ሕዝባዊ እምቢተኝነት» ውስጥ የሚሳተፉ ዜጐች፣ አቤቱታዎችን አቅርበው፣ ደብዳቤዎችን ፅፈው፣ በፍርድ ቤት ክስ መስርተው፣ ፍላጐቶቻቸውን ያስከብሩልናል የሚሏቸውን ዕጩዎች መርጠው፣ እንዲሁም ሌሎች አግባብነት ያላቸውን አሠራሮች ሞክረው የፈለጉትን ነገር ማሟላት የተሳናቸው ናቸው፡፡

በ«ሕዝባዊ እምቢተኝነት» ንቅናቄ ውስጥ ለሚገኙ ሰዎች፣ የግል ምቾታቸውን መስዋዕት ለማድረግ፣ ከማያውቁት አደጋ ጋር ለመፋጠጥ፣ ነፃነታቸውን አሳልፈው ለመስጠትና ወደ ዘብጥያ ለመውረድ ቆርጠው የተነሱ ናቸው፡፡ በሌላ አነጋገር፣ ወደ ንቅናቄው ያመራቸው ለዕውነትና ለፍትህ ያላቸው ፍቅር ነው፡፡ ባለፉት ሁለት አስርት ዓመታት በ«ሕዝባዊ እምቢተኝነት» ውስጥ የተሳተፉ አብዛኞቹ ሰዎች፣ የጋንዲ የ«ሠላማዊ ዓመፅ» ፍልስፍናና ስልቶች ተፅዕኖ ያደረባቸው ናቸው፡፡

## አለመተባበር

ከ«ሕዝባዊ እምቢተኝነት» የትግል ስልቶች መካከል አንዱ አለመተባበር ነው፡፡ በዚህ የትግል ስልት ውስጥ ከሚካተቱት አሠራሮች መካከል ለፖሊስ መረጃ ለመስጠት ፈቃደኛ አለመሆን፣ በመንገድ ላይ በመቀመጥ የትራፊክን እንቅስቃሴ ማስተጓጐል፣ የረሃብ አድማና በፍርድ ቤት ሂደት ለመካፈል ፈቃደኛ አለመሆን ይገኙባቸዋል፡፡ በሀገራችን፣ ፕሮፌ ሰር አሥራት ወልደየስ፣ ተከሰው ፍ/ቤት ቀርበው በነበረበት ጊዜ፣ «ጠበቃ አቁሜ አልከራከርም፡፡ ፍ/ቤቱ፣ የፈለገውን ሊወስንብኝ ይችላል» ያሉት፣ «አለመተባበር» ለሚለው የ«ሕዝባዊ እምቢተኝነት» ስልት በአብነት ሊቀርብ ይችላል፡፡

ጋንዲ፣ ስለዚህ የትግል ስልት ሲናገሩ፣ «ከእኩይነት ጋር አለመተባበር፣ ከጥሩው ጋር የመተባበርን ያህል ትልቅ ተልዕኮ አለው» ብለው ነበር፡፡





አለመተባበር፣ ዓለማችንን ከጭቆና ለማላቀቅ አዎንታዊ እርምጃ እየወሰድን መሆናችንን ለማረጋገጥ የምንጠቀምበት የትግል ስልት ነው፡፡ አለመተባበርን በትግል ስልትነት የሚያራምዱ ወገኖች ለስቃይና ለቅጣት ሊጋለጡ ይችላሉ፡፡ ለምን? ሲባል፣ ህግ አስከባሪዎች በጉዳዩ ዙሪያ በቂ ግንዛቤ ስለሌላቸው፣ በቁጥጥር ስር ከሚያውላቸው የፀጥታ አስከባሪ ጋር ለመግባባት ይቸገራሉ፡፡ የፀጥታ አስከባሪዎች ንቃት ሀሲና፣ ዝቅተኛ በሆነበት ኢትዮጵያ ውስጥ ደግሞ፣ ይህ ሁኔታ ጎልቶ ሊታይ ይችላል፡፡

ቅሬታቸውን መግለጽ የሚፈልጉ ሠዎች፣ አለመተባበርን እንደ የትግል ስልት የሚጠቀሙት በሚቀጥለው መርህ መሠረት ነው፡-

*ግብረ-ገባዊ ተቀባይነት የሌለውንም ነገር ለሚደግፍ ሂደት (ህግም ቢሆን) ተባባሪ መሆን ትክክል አይደለም፡፡*

## ህግና ፍትህ

«ሕዝባዊ እምቢተኝነት» ህጐችን ለመለወጥና የዜጐችን መብቶች ለመጠበቅ ውጤታማ መሣሪያ መሆኑ በተደጋጋሚ ታይቷል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም፣ ህጉና ፍትህ የማይጣጣሙባቸው ጊዜያት መኖራቸውንና በእንደ እዚህ ዓይነቱ ወቅት ህጉን ማክበሩ አግባብነት ላይኖረው እንደሚችል የሚያመላክተን የ«ሕዝባዊ እምቢተኝነት» ፅንሠ ሃሳብ ነው፡፡

«ህግ» እና «ፍትህ» የተለያዩ ፅንሰ ሃሳቦች ናቸው፡፡ ሁሉም ህጐች ፍትሃዊ አይደሉም፡፡ «ሕዝባዊ እምቢተኝነት» ህግን ከፍትህ ጋር ለማቀራረብ የሚደረግ ትግል ነው፡፡

## «ሕዝባዊ እምቢተኝነት» በአሜሪካ

በዩ.ኤስ. አሜሪካ የሁለት መቶ ዓመታት ታሪክ፣ «ሕዝባዊ እምቢተኝነት» በአሁኑ ወቅት ለሚታዩት በርካታ የፖለቲካና ማህበራዊ ለውጦች ቁልፍ ሚና ተጫውቷል፡፡ ከእነኝህ ታሪካዊ አጋጣሚዎች መካከል ዋነኞቹ ከዚህ በታች የተጠቀሱት ናቸው፡፡

1. በስተን ቲ ፓርቲ (The Boston Tea Party)

ዩ.ኤስ. አሜሪካ ነፃነቷ ከመቀዳጀቷ በፊት፣ የማሳቹስተስ ቅኝ ግዛት ዜጐች፣ በእንግሊዝ መንግስት ውስጥ ውክልና ሳይኖራቸው ቀረጥ ለመክፈል መገደዳቸውን በመቃወም፣ ከዚህችው ሀገር በመርከብ ተጭኖ የመጣውን ሻይ ቅጠል ወደ ባህር መጨመሩን መርጠዋል፡፡ ዩ.ኤስ. አሜሪካ ሉዓላዊት ሀገር ሆና እንድትመሠረት ወዳስቻላት የነፃነት ጦርነት ካመሩት በርካታ የ«ሕዝባዊ እምቢተኝነት» ድርጊቶች መካከል ዋነኛው ይኸው ነበር፡፡

2. የፀረ-ጦርነት ንቅናቄዎች

ፈላስፋውና ደራሲው፣ ሄንሪ ዴቪድ ቶሮ፣ ዩ.ኤስ.አሜሪካ በ1849 (እ.ኤ.አ.) በሜክሲኮ ላይ በከፈተችው ጦርነት ላይ ለመካፈል ፈቃደኛ ባለመሆኑ ወደ እስር ቤት ከተወረወረ ወዲህ፣ የፀረ-ጦርነት ንቅናቄዎች በዩ.ኤስ. አሜሪካ ታሪክ አካል ሆነዋል፡፡ ለዚህም የቅርብ ጊዜ አብነት የሚሆኑን፣ በቬየትናም የተካሄደውን ጦርነት፣ ዩ.ኤስ. አሜሪካ በኒካራጉዋና በሌሎች የማዕከላዊ አሜሪካ ሀገራት ውስጥ የምታራምደውን የጣልቃ ገብነት ፖሊሲ፣ እንዲሁም ከኢራቅ ጋር የተፋጠጠችባቸው ሁለቱ የባህረ ሠላጤው ግጭቶችን በተመለከተ አሜሪካውያን ተቃውሟቸውን ለመግለፅ የተጠቀሙባቸው የ«ሕዝባዊ እምቢተኝነት» የትግል ስልቶች ናቸው፡፡ ከእነኝህ ስልቶች መካከል ለጦርነቱ ዓላማ የሚውል ግብር አለመክፈል፣ በሠራዊቱ ውስጥ ለመመልመል ፈቃደኛ አለመሆን፣ የመመልመያ ማዕከላትን መውረር፣ በርካታ ህዝብ በሚተላለፍባቸው ጐዳናዎች ላይ መቀመጥ፣ የትራፊክ እንቅስቃሴን ማገድ፣ እንዲሁም ወታደራዊ መልማዮች በከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችና በኮሌጆች ቅጥር ግቢ እንዳይገቡ መከልከል ዋነኞቹ ነበሩ፡፡

3. የሴቶችን የመምረጥ መብት የማስከበር ንቅናቄ

ከ1848 እስከ 1920 (እ.ኤ.አ.) ድረስ ባሉት ዓመታት በሺህዎች የሚቆጠሩ ሴቶች የመምረጥ መብታቸውን ለማስከበር በሠላማዊ ሠልፎችና





በረሃብ አድማዎች ላይ በመሳተፍ፣ በተደጋጋሚ ለእስር ተዳርገዋል፡፡ በመጨረሻም ላይ፣ መብቶቻቸውን ለማስከበር ችለዋል፡፡

4. የፀረ ባርነት ንቅናቄ

የሃሪዬት ቱብማን በህቡዕ ይንቀሳቀስ የነበረ የባቡር መስመር («የነፃነት ባቡር» ይባላል) ብዙ ባሮችን ካሸሸበት ጊዜ አንስቶ ሰላማዊ የተቃውሞ እንቅስቃሴዎች ባርነትን ለማስወገድ እገዛ አድርገዋል፡፡

5. የሠራተኞች መብት ንቅናቄ

አይ.ደብልዩ.ደብልዩ. እና አይ.ሲ.አይ.አ የተሰኙት የሠራተኛ ማህበራት ያካሄዷቸው የስራ ማቆም አድማዎችና ሌሎች የ«ሠላማዊ ዓመፅ» ስልቶች፣ የህፃናት ሠራተኞች ብዝበዛ እንዲወገድ፣ የስራ ቦታ ሁኔታዎች እንዲሻሻሉ፣ የአንድ ሳምንት የስራ ሰዓት ብዛት 40 ሰዓታት ብቻ እንዲሆን፣ የስራ ቦታ ደህንነትና የሠራተኞች ጥቅማ-ጥቅም እንዲሻሻሉ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አድርገዋል፡፡

6. የሲቪል መብቶች ንቅናቄ

በማርቲን ሉተር ኪንግና በሌሎች ጥቁር አሜሪካውያን የተመራው የሲቪል መብቶችን የማስከበር ንቅናቄ፣ ዩ.ኤስ. አሜሪካን ሙሉ በሙሉ ቀይሯታል፡፡ «የዘር እኩልነት ኮንግሬስ» የተሰኘው ተቋም፣ በ1940ዎቹ ዓመታት ያዘጋጃቸው «የነፃነት ጉዞዎች» እና በአንድ ቦታ ተቀምጦ አለመንቀሳቀስ (ቁጭ በሉ) ለጥቁር አሜሪካውያን የሲቪል መብቶች መከበር ቀዳሚዎቹ የትግል ስልቶች ነበሩ፡፡ በዚህ መልኩ እየተጋጋለ የመጣው ትግል፣ በ1960ዎቹ የመጀመሪያ ዓመታት ፌንድቶ የፌዴራሉና የክልል መንግስታት ህጐቻቸውን እንዲያሻሽሉ አስገድዷቸዋል፡፡

7. የፀረ-ኑክሊየር ንቅናቄ

እንደ ካረን ሲልክዉድ በመሰሉ ሰዎችና በስሪማይል ደሴት የኑክሊየር ኃይል ማመንጫ ላይ በደረሰው ጉዳት የተቀሰቀሰው ይህ ንቅናቄ፣

በመላው ሀገሪቷ ያሉ ዜጎችን በ«ሕዝባዊ እምቢተኝነት» ስር አስተባብሯል፡፡ በመላው ሀገሪቷ በሚገኙ የኑክሊየር ኃይል ማመንጫ ተቋማት መጠነ ሰፊ የ«ሕዝባዊ እምቢተኝነት» ድርጊቶች ተከስተው ነበረ፡፡ ይህንንም ተከትሎ በመላው ዓለም የሚገኙ ሰዎች፣ የጦር ሠፈሮችን በመውረር፣ የሠላም ካምፖችን በመመስረት፣ በኑክሊየር ቦምቦችና መሣሪያዎች የምርት ሂደትና ትራንስፖርት ላይ እክል በመፍጠር፣ ሠላማዊ ሠልፎችን በማካሄድና ሌሎች ሠላማዊ የትግል ስልቶችን በመጠቀም ቅሬታቸውን ገልፀዋል፡፡

8. የፀረ-አፓርታይድ ትግል

በ1980ዎቹ ዓመታት የታየው የፀረ-አፓርታይድ ትግል አርአያ ያደረገው በ1960ዎቹ ዓመታት በዩ.ኤስ. አሜሪካ በተካሄደው የሲቪል መብቶች ንቅናቄ የ«ሠላማዊ ዓመፅ» ስልቶች ላይ ነበር፡፡ በህዳር 1984 (እ.ኤ.አ.) በበርካታ የዓለማችን ሀገራት ከሚገኙ የደቡብ አፍሪካ ኤምባሲዎች ፊት ለፊት ሠላማዊ ሰልፎች በየቀኑ ተካሂደዋል፡፡ ብዙ ሰዎች ከአንድ ዓመት ለበለጠ ጊዜ በየሳምንቱ ለእስር ይዳረጉ ነበር፡፡ በዩ.ኤስ. አሜሪካ በሚገኙ 26 ትላልቅ ከተሞች በተካሄዱ የፀረ-አፓርታይድ ሠላማዊ ሠልፎች ከስምንት ሺህ በላይ ሰዎች በቁጥጥር ስር ውለዋል፡፡ ይህ ድርጊት፣ ለደቡብ አፍሪካ የአፓርታይድ ሥርዓት መውደቅ ትልቅ አስተዋፅኦ አበርክቷል፡፡





# ምዕራፍ ፪

# የሠላማዊ ትግል ስልቶች ምንድን ናቸው?

ወደ ሠላማዊ ትግል ስልቶች ከመግባቴ በፊት፣ የሠላማዊ ትግሎችን አብነት ከታሪክ ለማጣቀስ እወዳለኹ፡፡ የምጀምረው ከሮማ ነው፡-

495 ዓ.ም - የሮማ ህዝብ፣ በመሪዎቹ ዘንድ ያሉትን ቅሬታዎች ለማስተካከል ከከተማዋ በመውጣት፣ ለበርካታ ቀናት ስራ ለመስራት ፈቃደኛ ሳይሆን ቀርቷል፡፡

1765-1775 ዓ.ም - በአሜሪካ በእንግሊዝ ቅኝ አገዛዝ ስር የሚገኘው ህዝብ፣ ገዢዎቹ ያወጧቸውን ሶስት ህጎችን የሚቃወሙ ሠላማዊ ትግሎችን በማካሄድ፣ በ1775 ለዘጠኝ ግዛቶች ነፃነት መረጋገጥ በሩን ከፍቷል፡፡

1850-1867 ዓ.ም - በፍራንሲስ ዲክ የሚመሩ የሃንጋሪ ብሄርተኞች፣ የኦስትሪያን አገዛዝ በመቃወም ባካሄዱት ሠላማዊ ትግል፣ ሀገራቸው በኦስትሪያ ሃንጋሪ ፌዴሬሽን ስር የራስ ገዝነትን አግኝታለች፡፡

1905-1906 ዓ.ም - የሩሲያ ገበሬዎች፣ ሠራተኞች፣ ተማሪዎችና ምሁራን ንጉሡ ነገሥቱ በህዝብ የተመረጠ የህግ አውጪ አካል ምስረታን ተግባራዊ እንዲያደርጉ በስራ ማቆም አድማዎችና ሌሎች የሠላማዊ ትግል ስልቶች አስገድደዋቸዋል፡፡

1917 ዓ.ም - የየካቲት 1917ቱ የሩሲያ አብዮት የተወሰነ ሁከትና ብጥብጥ ቢያስተናግድም፣ በአብዛኛው ግን ሠላማዊ ትግልን ያካተተ ነበር፤ ዘውዳዊው ስርዓት የተፈረካከሰውም ይህንን ትግል ተከትሎ ነው፡፡

1913-1919 ዓ.ም - በዩ.ኤስ. አሜሪካ ለሴቶች የመምረጥ መብት መከበር በተከታታይ የተደረጉ ሠላማዊ ሠልፎችና የረሃብ አድማዎች፣ ህገ-መንግስቱ የሴቶችን የመመረጥ መብት ባካተተ መልኩ እንዲሻሻል አድርገዋል፡፡

1920 ዓ.ም - በዎልፍጋንግ ካፕ መሪነት በጀርመን የዌይማር ሪፐብሊክ መንግስት ላይ የተካሄደው የመፈንቅለ መንግስት ሙከራ፣ ህዝቡ አዲሱ መንግስት ጋር ለመተባበር ፈቃደኛ አለመሆኑን ባሳየባቸው የስራ ማቆም አድማዎች ሳቢያ ሳይሳካ ቀርቷል፡፡

1923 ዓ.ም - አንደኛው የዓለም ጦርነት እንዳበቃ፣ የሩህር ሸለቆ በፈረንሳውያንና ቤልጂማውያን ቁጥጥር ስር መዋሉን የተቃወሙ ጀርመናውያን፣ ከባድ ጭቆና ቢያስተናግዱም፣ የባዕዳኑን ይዞታ ያስለቀቀ ሠላማዊ ትግል አካሂደዋል፡፡

1920-1947 ዓ.ም - በማህተመ ጋንዲ የተመራው የህንድ የነፃነት ንቅናቄ የተሳካው በሠላማዊ የትግል ስልቶች አማካኝነት ነው፡፡

1940-1945 ዓ.ም - በሁለተኛው የዓለም ጦርነት፣ በኖርዌይ፣ በዴንማርክና በኔዘርላንድስ የጀርመናውያንን ወረራ በመቃወም የተለያዩ ሠላማዊ ትግሎች ተካሂደዋል፡፡





1944 ዓ.ም - የኤል ሳል ቮዶር መሪ፣ ማክ ሲሚሊያኖ ሄርናንዴዝ ማርቲኔዝ፣ እንዲሁም የጓዓቴላማ መሪ፣ ዩር ጌ ኡቢኮ፣ ከአምባገነናዊ ስርዓታቸው ጋር የተወገዱት በሠላማዊ ትግል አማካኝነት ነበር፡፡

1955-1968 ዓ.ም - ጥቁር አሜሪካውያን የተለያዩ የሠላማዊ ትግል ስልቶችን በመጠቀም፣ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶቻቸውን አስከብረዋል፡፡

1968-1969 ዓ.ም - ቼኮዝሎቫኪያ በሶቪየት ኅብረት ተፅዕኖ ሥር መሆኗን በመቃወም በተቀጣጠለው ሠላማዊ ትግል፣ የዱብቼክ መንግስት ለጥቂት ጊዜ ነፍስ አግኝቶ በስልጣን ሊቆይ ችሏል፡፡ ሆኖም፣ ይህ ሠላማዊ ትግል ወዲያው በሶቪየት ኅብረት ወረራ ተጨናግፏል፡፡

1986 ዓ.ም - የፊሊንስ «ሕዝባዊ ኃይል» ንቅናቄ፣ ጨቋኙን የፌርዲናንድ ማርኮስን አምባገነናዊ ስርዓት በሠላማዊ ትግል አስወግዷል፡፡

## ስለሠላማዊ ትግል ዋነኛ ጭብጦች

ሠላማዊ ትግል፣ የተወሰኑ ነገሮች በማድረግ፣ ወይም ባለማድረግ የሚካሄድ ዓመፅ መሆኑ ይታወቃል፡፡ በዚህም መሠረት፣ ሠላማዊ ትግል የሚያካትታቸውን ነጥቦች ከዚህ ቀጥሎ ማንሳት እፈልጋለሁ፡-

1. ሠላማዊ ትግል ከታዛዥነት፣ ከፍርሃት፣ እንዲሁም እጅን አጣምሮ ከመቀመጥ ጋር የተያያዘ አይደለም፤
2. ሠላማዊ ትግል፣ እንደ ቃላት ጦርነት መታየት የለበትም፡፡ ሠላማዊ ትግል ከቃላት ባለፈ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ኃይልን አቀናጅቶ መጠቀምን የሚያካትት ትግል ነው፡፡
3. ሠላማዊ ትግል፣ የሠው ልጅ ተፈጥሮ «ጥሩ ነው» በሚለው ግምት ላይ የተመሠረተ አይደለም፤ ሠላማዊ ትግል፣ የሠው ልጅ «ጥሩ» እና «መጥፎ» ነው የሚለውን አተያይ ግምት ውስጥ ያስገባ ነው፡፡
4. ሠላማዊ የትግል ስልቶችን የሚጠቀም ሠው፣ ሠላም ወዳድ፣ ወይም ፃድቅ መሆን የለበትም፤ ሠላማዊ ትግልን በአብዛኛው ስኬታማ በሆነ መልኩ ሲጠቀም የሚስተዋለው «ተራው» ህዝብ ነው፡፡

5. ሠላማዊ ትግልን የተለያዩ ዓላማ ያላቸው ቡድኖችን በጋራ ሊያራምዱት ይችላሉ፡፡
6. ሠላማዊ ትግል በተወሰነ የዓለማችን ክፍል የተገደበ አይደለም፣ በተለያዩ ሀገራት የሚገኙ ህዝቦችም ሊጠቀሙበት ይችላሉ፡፡
7. የሠላማዊ ትግል ሂደት፣ የመንግሥት ወገን በሠላማዊ ትግል አራማጁ አካል ላይ የኃይል እርምጃ ከመውሰድ ይገታዋል ማለት አይቻልም፡፡
8. ሠላማዊ ትግልንን «ለመጥፎ» እና «ለበጐ» ዓላማ ከመዋል የሚያግደው ነገር የለም፡፡
9. ሠላማዊ ትግል፣ በዴሞክራሲያዊ ስርዓት ውስጥ በተፈጠሩ ውስጣዊ ግጭቶች ዙሪያ ብቻ የሚነሳ የትግል ስልት አይደለም፡፡ በአምባገነናዊ አገዛዞች፣ በባዕድ ወረራዎችና በፈላጭ ቆራጭ ስርዓቶች ላይም በስፋት ጥቅም ላይ ውሏል፡፡
10. ሠላማዊ ትግል፣ ከትጥቅ ትግል ጋር ሲነፃፀር፣ ድልን ለማስመዝገብ ብዙ ጊዜ አይፈጅም፡፡ በተለያዩ አጋጣሚዎች፣ ሠላማዊ ትግል በጥቂት ጊዜ ውስጥ የሚፈለገውን ግብ አሳክቷል፡፡ ድልን ለማስመዝገብ የሚያስፈልገው ጊዜ በተለያዩ ነገሮች ላይ የተመረኮዘ ቢሆንም፣ በዋነኝነት ግን የሠላማዊ ትግል አራማጆቹ ጥንካሬ ተጠቃሽ ነው፡፡





# ምዕራፍ ፫

# የሠላማዊ ትግል ስልቶች

በመላው ዓለም ዙሪያ የተካሄዱ የሠላማዊ ትግል ንቅናቄዎች ከተጠቀሙባቸው የትግል ስልቶች መካከል የረሃብ አድማዎች፣ አቤቱታዎች፣ ሠላማዊ ሠልፎች፣ ቁጭ በሉ፣ የስራ ማቆም አድማዎች፣ መንገድ መዝጋት፣. . . ይገኙባቸዋል፡፡ ተራው ህዝብ ኢ-ፍትሃዊነትን፣ ወይም ጭቆናን ለመታገል፣ አልያም ለውጥ ለማምጣት እነኚህን የሠላማዊ ትግል ስልቶች ተጠቅሟል፡፡

የትግል ስልቶቹ ውጤታማ እንዲሆኑ፣ ፖለቲካዊና ባህላዊ ሁኔታዎችን ከግምት ውስጥ ባስገባና፣ የአንድ ግዙፍ ዕቅድ አካል ባደረገ መልኩ በጥንቃቄ መመራት ይኖርባቸዋል፡፡

የኢየሱስ ክርስቶስ ከቀደምት የሠላማዊ ትግል ስትራቴጂስቶች መካከል እንደሚመደብ መጽሐፍ ቅዱስን ያነበበ ሰው ያውቀዋል፡፡ «ቀኝህን

በጥፊ ለመታህ ሰው፣ ግራህን ስጠው...» የሚለው የክርስቶስ አባባል ለዚህ አባባል ማስረጃ ሆኖ መቅረብ ይችላል፡፡ ሌላኛው ታሪካዊ የሠላም ትግል ምሳሌ፣ በአውሮፓ፣ ሴቶች፣ ለ100 ዓመታት የዘለቀውን የፈረንሳይና የእንግሊዝ ጦርነት እስኪቆም ድረስ ከባሎቻቸው ጋር የግብረ-ሥጋ ግንኙነት ለመፈፀም ፈቃደኛ ያልሆኑበት አጋጣሚ ነበር፡፡ በዚያ የሴቶች እርምጃ ሳቢያ ጦርነቱ ቆሟል፡፡

የሠላማዊ ት ል መንፈሳዊና ተግባራዊ ገፅታዎችን በቀመለከተ ጥልቀት ያለውን ስራ ያከናወኑ በርካታ ታዋቂ ሠዎች አሉ፡፡ ከእነኝህም መካከል ፖላንዳዊው ሌች ዋሌሳ፣ ሳይንቲስቱ አልበርት አንስታይን ተጠቃሾች ናቸው፡፡

## የረሃብ አድማ እንደ ሠላማዊ ትግል ስልት

*ማህተመ ጋንዲና የረሃብ አድማቸው*

ማህተመ ጋንዲ በህንድ የሚገኘውን የእንግሊዝ ቅኝ አገዛዝ በመቃወማቸው አራት ጊዜ ለእስር ተዳርገዋል፡፡ ጋንዲ ከተጠቀሙባቸው የሠላማዊ ትግል ስልቶች መካከል፣ የረሃብ አድማ አንዱና ዋነኛው ነበር፡፡ በዚህም መሠረት፣ በህንድ የእንግሊዝ ቅኝ አገዛዝንና በነፃይቷ ህንድ የሠፈነውን አምባገነናዊ ስርዓትን በመቃወም፣ ሁለት ጊዜ የረሃብን አድማ መትተዋል፡፡

የአየርላንድ ሪፐብሊካኖችና የረሃብ አድማቸው

በቢ ሳንድ፣ በ1981 (እ.ኤ.አ) በተካሄደው የረሃብ አድማ ከሞቱት እስር የአየርላንድ ሪፐብሊካን እስረኞች (ሰሜን አየርላንዱን ከእንግሊዝ አገዛዝ ነፃ ለማውጣት የሚታገሉ) መካከል ቀዳሚው ነበር፡፡ የረሃብ አድማ የሙቱት ሪፐብሊካኖች፣ በአየርላንድና በሰሜን አየርላንድ (የእንግሊዝ ግዛት) በሚገኙ ብሔርተኞች ዘንድ ከፍተኛ ድጋፍ አስገኝቶላቸዋል፡፡ በረሃብ አድማው ውስጥ ከተሳተፉት ሰዎች መካከል፣ ለአየርላንድና ለእንግሊዝ





ፓርላማ ሊመረጡ ችለዋል፤ ህዝቡም የመረጣቸው በእንግሊዝ መንግስት ግትር አቋም የተሰማውን ቅሬታ ለመግለፅ ነበር፡፡ አድመኞቹ፣ በአማካይ ለአስር ቀናት በዘለቀው የረሃብ አድማ፣ ከውኃና ከጨው በስተቀር ሌላ ነገር ወስደው አያውቁም፡፡ ብዙዎቹ፣ የረሃብ አድማውን ከ10 ቀናት በኋላ ሲያቆሙ፣ ጥቂቶቹ ግን በአቋማቸው ፀንተው ቀጥለዋል፡፡ ምንም ሳይቀምሱ ወራት ካሳለፉ በኋላ ሞተዋል፡፡

የረሃብ አድመኞቹ ከሞቱ በኋላ የተፈጠረውን ከባድ ህዝባዊ አመፅ ተከትሎ፣ የእንግሊዝ መንግስት ፖለቲካዊ ዓላማ ያነገቡትን እስረኞች ለየት ባለ መልኩ ፈርጇቸዋል፡፡ የረሃብ አድማው በከፍተኛ ሁኔታ የተዳከመውን የትጥቅ ትግል አራማጁን፣ የአየርላንድ ሪፐብሊካን ሠራዊት፣ ሞራል ለመገንባት ትልቅ አስተዋፅኦ አድርጓል፡፡

ኩርዳውያንና የረሃብ አድማቸው

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ፣ በቱርክ እስር ቤቶች የሚገኙ በርካታ የኩርድ ተገንጣዮች በረሃብ አድማ ምክንያት ህይወታቸውን አጥተዋል፡፡ በ2004 የፈረንጆች ዓመትም ወደ ስድስት የሚጠጉ ኩርዳውያን መሞታቸውን ይነገራል፡፡ ረሃብተኞቹ፣ ቱርክ ላይ ትልቅ የዲፕሎማሲ ኪሣራ አድርሰው ባታል፡፡ ቱርክ ወደ አውሮፓ ህብረት እንዳትቀላቀል እንቅፋት ሆነዋል፡፡

የሴቶች መብት ታጋዮችና የረሃብ አድማ

በ20ኛው ምዕተ ዓመት መግቢያ የሴቶችን የመምረጥ መብት ለማስከበር የተንቀሳቀሱ ታጋዮች፣ በእንግሊዝ እስር ቤቶች ውስጥ በተደጋጋሚ የረሃብ አድማዎችን መትተዋል፡፡ ከእነኝህም መካከል፣ የመጀመሪያዋ ማሪዮን ደንሎፕ ነበረች፡፡ ሌሎች ታጋዮችም እንዲሁ በተለያየ ጊዜ የረሃብ አድማ መትተዋል፡፡

የወህኒ ቤት ኃላፊዎቹ አድመኞቹን በግድ እንዲበሉ ሊያደርጓቸው ይሞክሩ ነበር፡፡ የወህኒ ቤቱ ኃላፊዎች በከፊል ቢሳካም፣ አንዳንዶቹ ግን

በአቋማቸው በመፅናታቸው በረሃብ አድማው በርካታ ታጋዮች ሞተዋል፡፡ ሞታቸው ግን፣ ለዓላማቸው መሳካት ዋነኛ ምክንያት ሆኗል፡፡

## አቤቱታ (Petition) እንደ ሠላማዊ ትግል ስልት

አቤቱታ፣ አብዛኛውን ጊዜ ለመንግስት ባለስልጣን፣ ወይም ህዝባዊ አካል፣ የሚቀርብ ጥያቄ ነው፡፡ ሠፋ አድርገን ስንመለከተው ደግሞ፣ አቤቱታ ለተወሰነ በርካታ ግለሰቦች የፈረሙበት ሰነድ መሆኑን እንረዳለን፡፡ አቤቱታው በፅሁፍ ብቻ ሳይሆን፣ በአንደበትም ሊቀርብ ይችላል፤ በዛሬ ዘመን ደግሞ፣ ኢንተርኔት ለዚሁ ዓላማ ሊውል ይችላል፡፡

እንደ ኢትዮጵያ በመሳሰሉ ሀገሮች፣ ህዝቡ በመንግስት ላይ ያደረበትን ቅሬታ የመግለፅ መብቱ በህገ-መንግስቱ ዋስትና አግኝቷል፡፡ ይህ አቤቱታ የማቅረብ መብት፣ በመንግስት ላይ ክስ የመመስረት መብትን ያካተተ ነው፡፡

የቀድሞው የደቡብ አፍሪካ አፓርታይድ መንግስት፣ ኔልሰን ማንዴላን ከእስር እንዲለቃቸው በሚልዮኖች የሚቆጠሩ ሰዎች የፈረሙበት አቤቱታ ቀርቦለት ነበር፡፡ ይኸው አቤቱታ በህግ ፊት ዋጋ ቢስ ቢሆንም፣ በሠነዱ ላይ የሰፈረው የፊርማ ብዛት ግን፣ ማንዴላን ነፃ ለማውጣትና የአፓርታይድ አገዛዝን ለማስወገድ ትልቅ የሥነ-ልቦና ሚና እንደተጫወተ ይገመታል፡፡ በዲፕሎማሲም በኩል ትልቅ እንደምታ አሳድሯል፡፡

## ማነቆ (PicKeting) እንደሠላማዊ ትግል ስልት

ማነቆ፣ በተቋም ደጃፍ ህዝብ የሚሰበሰብበትና፣ ሠዎች ወደተቋሙ ውስጥ እንዳይገቡ፣ ወይም ሲገቡ ተቃውሞ ለማቅረብ የሚደረግ የሠላማዊ ትግል ስልት ነው፡፡ ማነቆው ሁለት ግቦች አሉት፡፡ የመጀመሪያው፣ ተቋሙ ደንበኞችን፣ ወይም ሠራተኞችን በማሳጣት መጉዳትና ማዳከም ነው፡፡ ሌላኛው ግቡ ደግሞ፣ የጋዜጠኞችን ትኩረት መሳብ ነው፡፡





ማነቆ፣ የሠራተኛ ማህበራት በስራ ማቆም አድማ ወቅት የሚጠቀሙበት የተለመደ ዓይነት ስልት ነው፡፡ ይህን የትግል ስልት የሚጠቀሙት፣ የሠራተኛ ማህበሩ አፈንጋጭ አባላት፣ ሥራ እንዳይሠሩ ለመከላከል ነው፡፡

## የሥራ ማቆም አድማ እንደ ሠላማዊ ትግል ስልት

የስራ ማቆም አድማ፣ ሠራተኞች ስራ ለመስራት በጅምላ ፈቃደኛ የማይሆኑበት ክስተት ነው፡፡ የስራ ማቆም አድማዎች ለመጀመሪያ ጊዜ ጠቀሜታቸው የጐላው፣ እንግሊዝ ውስጥ በ1750 አካባቢ በተጀመረው ኢንዱስትሪያዊ አብዮት ነው፡፡ ዳሩ ግን፣ የፋብሪካ ባለቤቶች ከሠራተኞቹ የበለጠ ፖለቲካዊ ኃይል ስለነበራቸው፣ የስራ ማቆም አድማ በህገ-ወጥነት ተፈርጆዋል፡፡

አብዛኞቹ ምዕራባውያን ሀገራት የስራ ማቆም አድማን በከፊል ህጋዊ ማድረግ የጀመሩት በ19ኛው ምዕተ ዓመት ማብቂያ፣ ወይም በ20ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ነበር፡፡ የስራ ማቆም አድማ መንግስታት ፖሊሲዎቻቸውን እንዲለውጡ ለማስገደድ፣ ወይም ከስልጣናቸው ለማውረድ ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡ ለዚህም ዓይነተኛ ምሳሌ የሚሆነን፣ በሌች ዋሌሳ የተመራው የግዳንስክ የመርከብ ሠራተኞች የስራ ማቆም አድማ ነው፡፡ ይህ የስራ ማቆም አድማ፣ ፖላንድ ውስጥ ዴሞክራሲያዊ ነፃነትን ለማስፈን ለተደረገው ሠላማዊ ትግል ትልቅ አስተዋፅኦ አድርጓል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም፣ በምስራቅ አውሮፓ የኮሙኒዝም ስርዓት ውድቀትን ካመቻቹትና ካፋጠጡት ቁልፍ ክስተቶች መካከል የሚመደብ ነው፡፡

## ቁጭ በሉ (Sit in) እንደ ሠላማዊ ትግል ስልት

አራት የጥቁር አሜሪካውያን ኮሌጅ ተማሪዎች የመጀመሪያውን የቁጭ በሉ የሠላማዊ ትግል ስልትን የተጠቀሙት በ1959 (እ.ኤ.አ.) በሰሜን ካሮላይና ግዛት፣ ግሪ ንስቦሮ ከተማ ነበር፡፡ ከዚህ ክስተት ሶስት ወራት

ቀደም ብሎ፣ የሜቶዲስት ክርስትና ኃይማኖት ሰባኪው ጀምስ ሎውሰን በማህተመ ጋንዲ የሠላማዊ ትግል ፅንሠ-ሃሳብ ዙሪያ ስብሰባዎችን ያዘጋጁ ነበር፡፡ እነኝህ ተማሪዎች የሎውሰን ተፅዕኖ ያደረባቸው ናቸው፡፡

ከመቀመጫ ባለመነሳት ተቃውሞን የመግለፁ አካሄድ (ቁጭ በሉ) ተጠናክሮ የጀመረው፣ በየካቲት 13/1960 (እ.ኤ.አ) ጥቁር አሜሪካውያን መገበያየት እንጂ፤ በምግብ ቤቶቹ መስተናገድ በማይችሉባቸው የናሽቪል ከተማ የገበያ ማዕከላት ውስጥ ነበር፡፡ በናሽቪል የገበያ ማዕከላት ውስጥ ጥቁር አሜሪካዊያን ገብተው ምግብ እስኪቀርብላቸው ድረስ ከተቀመጡበት «አንነሳም» በማለት ችግር ፈጥረው ነበር፡፡ በዚያን ጊዜ፣ የአሜሪካ ህግ በግልፅ ደንግጐ እንደነበረው ከሆነ፣ ጥቁሮች ነጮች በሚስተናገዱበት ምግብ ቤቶች መግባት አይችሉም ነበር፡፡ ስለዚህ፣ ጥቁሮቹ፣ በእነዚያ ምግብ ቤቶች ውስጥ ገብተው ከተቀመጡበት «አንነሳም» ሲሉ፣ ህግ መጣሳቸው ነበር፡፡ ይህ ድርጊት በአጭር ጊዜ ውስጥ በመቶዎች የሚቆጠሩ ጥቁርና ነጭ ተማሪዎችን ሊስብ ችሏል፡፡

በሂደቱ ውስጥ የሚሳተፉት ሠዎች ከሠላማዊ ትግሉ እንዳያፈነግጡ በሚል «10 የሥነ-ምግባር ህጐች» ወጥተው ስራ ላይ እንዲውሉ ተደርጓል፡፡ ህጐቹ ለሁለት የተከፈሉ ናቸው፡፡ የመጀመሪያው፣ የሂደቱ ተሳታፊዎች ማድረግ የሌለባቸውን ያካተተ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ፣ ማድረግ ያለባቸውን ያስቀመጠ ነው፡፡

ማድረግ የሌለባቸው፡-

1. ጥቃት ሲደርስባቸው፣ መልሰ መማታት ወይም መሳደብ
2. ከትብሎ መሳቅ
3. ከድርጅቱ ሠራተኞች ጋር መነጋገር
4. የቡድን መሪው ካልፈቀደ በስተቀር ከመቀመጫ መነሳት
5. የመደብሮችን መግቢያና መውጫ መዝጋት፡፡





ማድረግ ያለባቸው፡-

1. በማንኛውም ጊዜ የወዳጅነትና የትህትና መልክ ማሳየት
2. ቀጥ ብሎ መቀመጥ
3. ማንኛውንም እሳሳቢ ነገር ለቡድን መሪው ሪፖርት ማድረግ
4. መረጃ ፈላጊዎችን ትህትና በተሞላው መልኩ ወደ ቡድን መሪው መላክ
5. የኢየሱስ ክርስቶስ፣ የማህተመ ጋንዲና የማርቲን ሉተር ኪንግን አስተምህሮዎች ማስታወስ፡፡

የመጀመሪያዎቹ እንቅስቃሴዎች በሠላማዊ መንገድ ነበር የተጠናቀቁት፡፡ በወቅቱ ግራ የተጋቡ በርካታ የገበያ ማዕከላት ስራ አስኪያጆች ምግብ ቤቶቻቸውን ለመዝጋት ተገድደው ነበር፡፡ ከጥቂት ቀናት በኋላ ደግሞ፣ ድርጊቱ ያበሳጫቸው ነጮች ከተማሪዎቹ ጋር ግብግብ መፍጠር ጀምረው ነበር፡፡ በዚህ አጋጣሚ በተፈጠረው ግርግር 81 ተማሪዎች ታስረዋል፡፡ ታሳሪዎቹ በፍትህ ስርዓቱ ላይ ያላቸውን ተቃውሞ ለመግለፅ ፍርድ ቤቱ የጣለባቸውን የገንዘብ ቅጣት ለመክፈልም ሆነ ለዋስትና የተጠየቁትን ገንዘብ ለማስያዝ ፈቃደኛ ሳይሆኑ ቀርተዋል፡፡

በዚህ ስልትም፣ እስር ቤቶችን የሚያጨናንቁት ተማሪዎች ብዛትም እያደገ ሄደ፡፡ በዚህም ሳቢያ፣ የጋዜጦች ሽፋን ሊያድግ ችሏል፡፡ ይህንንም ተከትሎ፣ በጥቂት ሳምንታት ውስጥ ስድስት የናሽቪል የገበያ ማዕከላት ምግብ ቤቶች ለጥቁር አሜሪካውያን በሮቻቸውን ክፍት ለማድረግ ተገደዋል፡፡ ሠላማዊ ትግሉ ድል አደረገ ማለት ነው፡፡

## ምዕራፍ ፬

# ሠላማዊ ትግል የሚሳካው እንዴት ነው?

### የሠላማዊ ትግል ጠቀሜታዎች

1. አምባገነናዊ አገዛዝን ይበልጥ ሊያጠናክር ከሚችል ሁከትና ብጥብጥ ይልቅ፣ አምባገነናዊ ስርዓትን ለማስወገድ የተሻለ ዘዴ ነው።
2. ህዝባዊ ትግል፣ የራሳቸው አጀንዳና የማያስተማምኑ አጋሮች ከሆኑት የውጭ መንግስታት ተፅዕኖ በተላቀቀ መልክ ራሱን ችሎ እንዲካሄድ ያመቻል።
3. በሠላማዊ ትግል ውስጥ መሳተፍ የሚችለው የአንድ ማህበረሰብ የተወሰነ ክፍል ብቻ ሣይሆን፣ ሙሉኑ ሠፊው ህዝብ ነው።
4. በትግሉ የሚጐዱት ወገኖች ብዛት፣ በሁከትና ብጥብጥ ከታጀበው ንቅናቄ ጋር ሲነፃፀር፣ እጅጉን አነስተኛ ነው።





5. ምንም ዓይነት የትጥቅ ትግል ስለማይኖር፣ ትግሉ የሚጠይቀው ኢኮኖሚያዊ ወጪ ዝቅተኛ ነው።
6. ማህበረሰቡ፣ በእርስ በእርስ ጦርነት የሚታየውን ያህል ጥፋትና ውድመት አይደርስበትም።
7. ከ«ድል» በኋላ አዲስ አምባገነናዊ ስርዓት በህዝቡ ላይ ለመጫን የተዘጋጀ ወታደራዊ ኃይል አይኖርም።
8. ሠላማዊ የትግል ስልት፣ መፃኢ ጨቋኞችን እንዴት መታገል እንዳለበት ለህዝብ እውቀትን በማስታጠቅ፣ ጠንካራ የዴሞክራሲ ሂደት ይፈጥራል።

ከጥቂት ዓመት ወዲህ፣ ጥቂት በማይባሉ ሀገራት ህዝቡን ሲያሰቃዩ የቆዩ ፈላጭ ቆራጭ አገዛዞች በሰላማዊ ትግል ሲፈረካከሱ አስተውለናል። ይህ ዓይነቱ ሁኔታ የተፈጠረው፣ የአምባገነናዊ ስርዓቱን መሠረት ቀስ በቀስ ካናጋ የሠላማዊ ዓመፅ እንቅስቃሴ በኋላ ነበር።

በምስራቅ ጀርመን፣ በቼኮዝላቫኪያ፣ በፊሊፒንስ፣ ስላትቪያ፣ በኤስቶኒያ፣ በሊቱዌኒያንና በፖላንድ የተዘመገበው ስኬታማ ውጤት፣ ሠላማዊ ትግል፣ ዓይነተኛ የትግል መሣሪያ እንደሆነ በቂ ማስረጃ ሳይሆነን አይቀርም። ከእነኚህ ሀገራት በተጨማሪ የኤል ሳልቫዶርና የጉዋቲማላ አምባገነናዊ አገዛዞች በተመሳሳይ መልኩ ተፈረካክሰው ወድቀዋል።

ደቡብ አፍሪካን ከአፓርታይድ ስርዓት ለማላቀቅ፣ የአርጀንቲናን ወታደራዊ አገዛዝ ለመሸርሸር፣ ለሀንጋሪ ነፃነት እስተዋፅኦ ለማድረግ፣ እንዲሁም፣ ህንድን ከእንግሊዝ ቅኝ አገዛዝ ነፃ ለማውጣት ሠላማዊ ትግል ቁልፍና ወሳኝ ሚና ተጫውቷል። ጥቁር አሜሪካውያንና የሶቪየት ህብረት አይሁዶች ሠላማዊ የትግል ስልትን በመጠቀም ለነፃነታቸውና ለመብታቸው መከበር ያደረጉት እንቅስቃሴ ውጤት አስገኝቶላቸዋል።

ዳሩ ግን፣ የበርማ ዴሞክራቶች በ1988 (እ.ኤ.አ)፣ የቻይና ዴሞክራቶች ደግሞ ከአንድ ዓመት በኋላ ያደረጉት ትግል ሳይሳካ ቀርቷል።

### ስለአምባገነኖች ማወቅ የሚገባን ቁም ነገሮች

1. አምባገነኖች የሚታሰበውን ያህል ጠንካሮች አይደሉም፡፡ ከአቅማቸው በላይ የሆኑ ነገሮች አሉ፡፡
2. አምባገነኖች ብዙ ጊዜ ከህዝብ የተሸሸጉ ውስጣዊ ድክመቶች፣ ችግሮችና ግጭቶች አሏቸው፡፡ ትግሉም ትኩረት መስጠት ያለበት ለእነኚህ ድክመቶች ነው፡፡

አምባገነናዊው ስርዓት፣ ሊቆጣጠራቸው ከማይችላቸው የህዝቡ የትግል አንድነት መንፈስ መጠናከርና የነፃነት ገለልተኛ ዴሞክራሲያዊ ቡድኖችና ተቋማት እድገት ጋር ለመፋጠጥ ሲገደድ፣ እኩይ ድርጊቱና እቅዱ እየተጋለጠበት መሆኑን ይረዳዋል፡፡ በአምባገነናዊው ስርዓት ስር ያሉትንና ተያያዥነት ያላቸውን ተቋማት ለማዳከምና ለመሸርሸር የስራ ማቆም አድማ፣ ከቤት አለመውጣት፣ ትእይንተ-ህዝብ፣ እንዲሁም ሌሎች መሠል እንቅስቃሴዎች ወሳኝነት አላቸው፡፡

ጥበብና ብልሃት የታከለበትና አብዛኛውን ህዝብ ያካተተ ሠላማዊ የትግል ስልት፣ አምባገነናዊ ስርዓቱን ማዳከሙና የዴሞክራሲያዊ ኃይሎችን ድል አድራጊነት ማረጋገጡ አይቀርም፡፡

አምባገነናዊ ስርዓት የሚፈረካከሰው ከዚህ ቀጥሎ የሠፈሩት እርምጃዎች ተግባራዊ ሲሆኑ ነው፡-

1. ኃይማኖታዊና ግብረ ገባዊ መሪዎች አገዛዙን በህገ-ወጥነት ሲያወግዙ፤
2. ሠፊው ህዝብ አምባገነኖቹን አልታዘዝም፣ አልተባበርም በማለት፣ ለዴሞክራሲያዊ አመራሩ ታዛዥነቱን ሲያሳይ፤
3. ጋዜጠኞችና አዘጋጆች (የመንግስትን ጨምሮ) የህዝቡን ፍላጐት ማንፀባረቅ ሲጀምሩ፤





4. የትራንስፖርት ስርዓቱ (ለምሳሌ፣ ታክሲዎች) ዴሞክራሲያዊ ኃይሎቹ በሚፈልጉት መልኩ ብቻ ሲንቀሳቀስ፤
5. የሲቪል ሠርቪስ ሠራተኞች የአምባገነናዊ ስርዓቱን ፖሊሲዎችና ትእዛዞች ችላ ሲሉ፤
6. ዴሞክራሲያዊ ታጋዮችን ለማሰር ፈቃደኛ የሚሆን ሲጠፋ፤
7. በሀገር አቀፍ ደረጃ ያሉ ሰራተኞች የስራ ማቆም አድማ ሲያደርጉ የአምባገነናዊው አገዛዝ ስልጣን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ይኮላሻል፡፡

ዴሞክራሲያዊ ኃይሎቹ ህላዊነት ያለውን ጠንካራ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ለመገንባት ሰላማዊ ትግሉ እንዳበቃ ከአምባገነናዊ ስርዓት ወደ ጊዜያዊው መንግስት የሚደረገው ሽግግር በምን ዓይነት መልኩ ተግባራዊ እንደሚሆን ቀደም ብለው በጥልቀት ሊያስቡበት ይገባል፡፡

## የሠላማዊ ትግል ቅድመ ሁኔታ ዓላማን ለይቶ ማወቅ

ከአምባገነኖች ጋር የተፋጠጠና ነፃነትን ተስፋ ያደረገ ኃላፊነት የሚሰማው ንቅናቄ፣ ዓላማው ምን እንደሚሆን አስቀድሞ መወሰን ይኖርበታል፡፡ የንቅናቄው ዓላማ አምቢተኝነት ለመጠቆም፣ ጥላቻን ለመግለፅ፣ ነፃነትን ለማሞገስና «ቀና አመለካከት ባላቸው ሰዎች ጉራ» እንደተሰለፉ ለማሳየት ነው? ወይስ፣ ንቅናቄው፣ አምባገነናዊውን ስርዓት ለማስወገድና በነፃነትና በዴሞክራሲያዊ መርሆች ላይ የተመሰረተ ዘላቂና ኃላፊነት የሚሰማው ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ለማቋቋም ለሚደረገው ሠላማዊ ትግል ቁርጦ የተነሣ ነው?

እምቢተኛነትን የሚጠቁሙ እንቅስቃሴዎችን ማድረግ አንፃራዊ በሆነ መልኩ ሲታይ ቀላል ነው፡፡ አምባገነናዊ ስርዓትን አስወግዶ ዘላቂነት ያለው ዴሞክራሲ ሥርዓትን መገንባት ግን፣ ከባድ ግብ ነው፡፡ ለእዚህ ግብ ስኬታማ መሆን፣ ሀሳቦችን የሚያፈልቁ፣ የሚያመዛዝኑ፣ የሚያቅዱ፣ በቂ

ዝግጅት የሚያደርጉና ስኬታማ ሊሆን በሚችል መልኩ የሚንቀሳቀሱ ሰዎችን ያቀፈ ኃላፊነት የሚሰማው ንቅናቄ ያስፈልጋል።

አምባገነናዊ ስርዓትን በሰላማዊ ትግል ለመሸርሸር ቆርጦ የተነሣ አካል፣ ከዚህ ቀጥሎ የተቀመጡትን አራት ወሳኝ ቅድመ ሁኔታዎች ተግባራዊ ማድረግ ይጠበቅበታል፡-

1. የሠላማዊ ትግልን አስፈላጊ ጉዳዮች፣ ታሪክ፣ እንዲሁም ስትራቴጂካዊ መርሆች ማጥናት፤
2. የዚህ ዓይነቱን ትግል እውቀት ማስፋፋት
3. በሀገሪቷ ውስጥ ባለውና ሰላማዊ ትግል በሚጠይቃቸው ሁኔታዎች ላይ የተመሰረተ ብልሃትን የተላበሰ የነፃነት ስትራቴጂካዊ እቅድ ማዳበር፤ እንዲሁም
4. ጭቁኑ ህዝብ ድክመቶቹን አስተካክሎ፣ ጥንካሬዎቹን አሳድጎና አምባገነናዊውን ስርዓቱን አስወግዶ፣ ስኬታማ ዴሞክራሲያዊ ሽግግርን እውን እንዲያደርግ ማስተባበር።

## ሠላማዊ ትግል መቋቋም የሚኖርበት ፈተናዎች

በትግሉ ወቅት ድጋፍ ለማግኘት ከአቅም በላይ ቃል መግባቱ፣ የኋላ ኋላ ቅሬታን ከማስከተሉም በላይ፣ በህዝቡ ዘንድ አምባገነናዊው ስርዓት ተመልሶ እንዲመጣ ምኞትን ሊቀስቅስ ይችላል። ስለዚህ፣ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል። ሰላማዊ ትግል፣ ከነፃነት በኋላ ይመጣሉ የሚላቸውን የተጋነኑ ተስፋዎችን ከማቅረብ መቆጠብ አለበት። ይሄ ደግሞ፣ ትልቅ ፈተና ነው። ህዝብ የሚንቀሳቀሰው ተስፋ ሲኖረው ብቻ ነው።

ሌላኛው ከባድ ፈተና፣ አምባገነናዊውን ስርዓት በራሱ መሣሪያ፣ ማለትም፣ ሁከትና ብጥብጥ፣ መልሶ ለመዋጋት ማሰቡ ነው። ይህን አማራጭ መከተሉ፡-

1. ወደ የዴሞክራሲያዊ ንቅናቄውን ሽንፈት ወይም





2. ወደ ዴሞክራሲያዊ ካባ ያጠለቀ አዲስ አምባገነናዊ ስርዓት ሊያመራ ይችላል።

ትኩረታችንን ሙሉ በሙሉ በአምባገነናዊው ስርዓት ላይ ስናደርግ፣ የማኅበራዊ ፍትህ ጉዳዮችን (ኢኮኖሚያዊ፣ የብሄረሰቦች እኩልነት፣ ወዘተ...) ችላ የማለት አዝማሚያ ሊፈጠር ይችላል። ለማኅበራዊ ፍትህ ትኩረት አለመስጠቱ፣ ይህን አንገብጋቢ ጉዳይ አምባገነናዊው ስርዓት ደጋፊዎችን ለማሰባሰብ እንዲጠቀምበት ቀዳዳ በመክፈት ዴሞክራሲያዊው ንቅናቄ ማግኘት የሚገባውን ድጋፍ ያሳጣዋል።

ዴሞክራሲያዊው ንቅናቄ ማስወገድ የሚኖርበት ሌሎች ፈታኝ ሁኔታዎችም አሉ። ከእነኝህም መካከል፣ የፖለቲካ ግድያ ወይም የሙስና ዒላማ እንዲሆን በሚያጋልጥ መልኩ አንድን ዴሞክራሲያዊ መሪ ከፍ ከፍ ማድረግ አንዱ ነው። ትግሉ ለዚህ ዓይነቱ አደጋ ከተጋለጠ፣ ህዝባዊው ንቅናቄ በመሪ እጦት ሳቢያ መዳከሙ አይቀርም።

አምባገናዊ ስርዓት ያከትማል የሚል እምነት የሌላቸው በርካታ ዴሞክራቶችም ሊኖሩ ይችላሉ። ይሄ ሌላ ፈተና ነው። እነኝህ ወገኖች፣ እንደበታቸው የሚናገረው ሌላ ቢሆንም፣ አምባገነናዊው ስርዓት ተገርስሶ ዴሞክራሲ ይሰፍናል የሚል እምነት የሌላቸው ዓይነቶች ናቸው። እንዲህ ዓይነት አመለካከት የሚያራምዱ ሰዎች ትልቁ ችግራቸው፣ በአምባገነናዊው ስርዓት አይበገሬነት ማመናቸው ነው። በዚህም ሳቢያ፣ አምባገነናዊ ስርዓቱን በተመለከተ እምቢተኛነትን ከመግለፅ ባለፈ፣ ያመረረ እርምጃ እንዲወሰድ አይፈልጉም። ከውስጥ ሆነው ዴሞክራሲያዊው ንቅናቄ ወደ ተግባር እንዳይሸጋገር ይፈታተኑታል።

## ምዕራፍ ፰

# የሠላማዊ ትግል ተሞክሮዎች

አሜሪካዊያን፣ ስለ «ሠላማዊ ትግል» ሰፊ ተሞክሮ ካላቸው ጥቂት የዓለም ህዝቦች መካከል በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው።. ብዙ ሰዎች፣ አሜሪካዊያን ከሰላማዊ አመፅ ጋር ያላቸውን ትስስር በዋናነት የሚያገናኙት እ.ኤ.አ. በ1950ዎቹ ከፈነዳው የጥቁር የመብት ትግል ጋር ነው። ተሞክሮው ግን፣ ቀደም ይላል። ከ1900ዎቹ (እ.ኤ.አ.) መጀመሪያ አንስቶ ሲለማመዱት ነው የኖሩት።

በዛሬ ዘመን «ዓለም መንደር ሆናለች» እየተባለ ነውና፣ በመልከዐ-ምድራዊ አቀማመጣችን ብዙ ብንራራቅም፣ ከእነሱ ተሞክሮ ቀሪዎቹ የዓለም ህዝቦች ሊማሩ ይችላሉ፣ እድሜ ለኢንተርኔት።

ሆኖም፣ የአሜሪካዊያን ተሞክሮን፣ ሁሉም ሀገሮች ሙሉ ለሙሉ መውሰድ ይችላሉ ብዬም አላስብም። የምንወስዳቸውም፣ የምንጥላቸውም ነገሮች አሉ ብዬ ነው የማምነው።





ለጊዜው፣ በእኔ በኩል፣ የአሜሪካዊያንን ተሞክሮ እንዳለ ነው የማስቀምጠው። ይቺን ጥቂት ገፆች ለመሙላት ብዙ ጥናት ማድረግ እንደነበረብኝ ማስገንዘብ እወዳለሁ። የዓለም ህዝቦች ከዚያ ተሞክሮ ምን መውሰድ ይችላሉ? የሚለውን፣ እናንት እንድትወያዩበት እተውላችኋለሁ።

ከዚህ በታች የሰፈሩት በቀጣዮቹ ርዕስ ጉዳዮች የተከፋፈሉ ናቸው።

- የሠላማዊ ሠልፎች ፈቃድ ማውጣት
- ማንነትን የሚገልፅ ሠነድ መያዝ
- ህዝባዊ እምቢተኝነትን እና ከዚህ መራቅ ያለባቸው ወገኖች
- የተለመዱ የህዝባዊ እምቢተኝነት ከሶችና ከፖሊስ ጣቢያ መለቀቅ
- እስር
- የ«ሠላማዊ ትግል ተቆጣጣሪ» መመደብ
- የሠላማዊ ሠልፈኞችና የፖሊስ መብቶች
- ህዝባዊ እምቢተኝነት እና በቁጥጥር ስር መዋል

*ፈቃድ ማውጣት*

ከ100 በላይ ሰዎች ለሚሳተፉበት፣ ወይም፣ ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ለሚንቀሳቀስ ሠላማዊ ሰልፍ ፈቃድ ማውጣቱ ይመረጣል። ፈቃዱ ካልተገኘ፣ ወደ አካባቢው መምጣቱ የማይቀረው ፖሊስ ሠላማዊ ሰልፉን ይበትነዋል፤ ጉዳትም ያደርሳል። ፈቃድ ማውጣቱ፣ ሠላማዊ ሰልፉን በተመለከተ ለፖሊሶች እንደ የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ የሚያገለግል ሲሆን፣ ወደ አካባቢው እንዲመጡና በሚፈልጓቸው ቦታዎች መሰናክሎችን ቀደም ብለው ለማስቀመጥ ያግዛቸዋል።

ፈቃድ ማግኘት ካልተቻለ፣ ሠላማዊ ሠልፉን ለማካሄድ ያቀደው አካል ከአንድ የህግ ባለሙያ ጋር መምከር ይኖርበታል። የህግ ባለሙያው፣

ዳግም በመጠየቅ፣ አልያም ወደ ፍርድ ቤት በማምራት፣ ፈቃዱን ማግኘት ይችል ይሆናል።

ማንነትን የሚገልፅ ሠነድ መያዝ

እንደሚታሰሩ ቀደም ብለው የሚያውቁ ሰዎች፣ በፖሊስ ዘንድ ተቀባይነት የሚኖራቸው የማንነት መግለጫ ሠነዶችን መያዝ ይኖርባቸዋል። በሰላማዊ ሰልፍ ወቅት፣ ብዙ ታሳሪዎች መኖራቸው የጋዜጠኞችን ትኩረት ስለሚስብ ጥሩ ነገር ነው። በዚህም ሳቢያ፣ ብዙ ሰላማዊ ሰልፈኞች ሆን ብለው መታሰራቸው የተለመደ ነገር ነው።

ፖሊስ ሠላማዊ ሠልፈኛውን/ዋን በቁጥጥር ስር ካዋለው በኋላ፣ ለተጨማሪ የወረቀት ሥራዎች ወደ ፖሊስ ጣቢያ ይወስደዋል።

ክሱ በከባድ ወንጀል ላይ የተመሰረተ ካልሆነ በስተቀር፣ ሠላማዊ ሠልፈኛው/ዋ፣ ፖሊስ ማንነቱን/ቷን፣ እንዲሁም የት እንደሚኖር/ምትኖር ማወቅ የሚችልበትን በቂ ማረጋገጫ የሚሰጥ መታወቂያ እስካለው/ላት ድረስ ብዙም ሳይቆይ ይለቀቃል/ትለቀቃለች።

በዚህ ዓይነቱ አጋጣሚ ከፍተኛ ጠቀሜታ የሚኖረው ፎቶግራፍ የተለጠፈበት መንጃ ፈቃድ ሲሆን፣ አንድ ተቋም፣ ድርጅት ወይም ኩባንያ ያወጣው የመታወቂያ ደብተርም ሊያገለግል ይችላል፤ ሀገራችን ውስጥ ደግሞ፣ የቀበሌ መታወቂያ ወረቀት የግለሰቡን ማንነት የሚገልፅ ሆኖ እናገኘዋለን።

የሠላማዊ ሠልፈኛዋ አድራሻ፣ የማወቁ ዓላማ፣ ሠላማዊ ሠልፈኛዋ ከእስር ከተለቀቀች በኋላ በቀጠሮው ዕለት ፍርድ ቤት ሳትቀርብ ስትቀር፣ ባለሥልጣናቱ ፈልገው እንዲያገኟት ነው። በቁጥጥር ስር የመዋል ዕቅድ ያላቸው ሰዎች፣ ሌላው ቢቀር ላይ ላዩን መፈተሻቸው አይቀርም። ፍተሻውን የሚያካሄደው ፖለስ በግለሰቡ ላይ ማንኛውንም ዓይነት ህገ-ወጥ ካገኘበት ታሳሪውን በእስር በማቆየት ተጨማሪ ክስ መመስረቱ አይቀርም።





ህዝባዊ እምቢተኝነት እና ከዚህ መራቅ ያለባቸው ወገኖች

ህዝባዊ እምቢተኝነት በሚታቀድበት አጋጣሚ በቁጥጥር ስር ይውላሉ ተብለው የተገመቱት ሰዎች በዚህ ሳቢያ ስለሚፈጠረው ውጤትና ስለህጉ በቂ ግንዛቤ ሊጨብጡ ይገባል። ፖሊሶቹ ሊመሰረቱባቸው ስለሚችሏቸው ክሶች፣ እንዲሁም፣ ፍርድ ቤቶች ሊወስኑባቸው ስለሚችሉት ብያኔዎች ማወቅ ይኖርባቸዋል። ከመታሰር አደጋ ጋር የሚጋፈጡት ሰዎች፣ ከዚህ በተጨማሪም፣ አስተማማኝ የመታወቂያ ሰነድ በመያዝ፣ እንዲሁም የዋስትና ድጋፍ የሚያደርግላቸውን ሰው በማዘጋጀት፣ በፖሊስ ቁጥጥር ስር የሚውሉበትን ጊዜ እንዴት ማሳጠር እንዳለባቸው በቂ ግንዛቤ መጨበጥ አለባቸው።

ከመንግሥት፤ ከደህንነት ወይም ከህፃናት እንክብካቤ ጋር በተያያዘ ሥራ ማመልከት የሚፈልጉ ሰዎች ቀደም ሲል ስለታሰሩባቸው ሁኔታዎች ሊመረምሩ፣ ወይም ሊጠየቁ ስለሚችሉ፣ በ«ሠላማዊ ዓመፅ» ውስጥ የሚያደርጉትን ተሳትፎ በተገቢው መልኩ ሊያመዛዝኑት ይገባል።

## የተለመዱ የህዝባዊ እምቢተኝነት ክሶች

በሠላማዊ ሠልፈኞች ላይ አብዛኛውን ጊዜ የሚመሠረቱት ክሶች፣ «ሁከት መፍጠርና የተከለለ ቦታ ጥሶ ማለፍ» ናቸው።

ሁከት መፍጠር፣ ፖሊስ አዋኪ አድርጐ በሚፈርጀው ድርጊት ውስጥ መሳተፍ ማለት ነው። በአሜሪካን ሀገር እነኝህ ክሶች ወንጀሎች ሳይሆኑ የህግ «ጥሰቶች» በመሆናቸው፣ ከትራፊክ ጥፋት ያለፉ አይደለም። በኢትዮጵያ ቀላል ወንጀሎች ናቸው።

ሌላኛው የተለመደ ዓይነት ክስ «በቁጥጥር ስር ላለመዋል መታገል» የሚለው ነው። በዚህ ክስ መሠረት፣ ታሣሪው ግለሰብ በፖሊስ ቁጥጥር ስር እንዳይውል መከላከል ኃይል ተጠቅሟል ማለት ነው። ይህ ጥፋት ቀላል ወንጀል ነው። ይህ ዓይነቱ ክስ የተመሰረተበት ግለሰብ

አብዛኛውን ጊዜ ከፖሊስ ጣቢያ ቢለቀቅም፣ ፍርድ ቤት እስኪቀርብ ድረስ የመታሰር ዕድሉ ከፍተኛ ነው።

ሌላኛው የተለመደ ዓይነት ክስ ደግሞ፣ «ረብሻ መፍጠር» የሚል ነው። በዚህ ክስ ለመወንጀል፣ ተጠርጣሪዋ ግለሰብ አራት ወይም ከዚያ የበለጡ ሰዎች በንብረት፣ ወይም፣ በሰው ላይ ጉዳት እንዲያስከትሉ፣ አልያም ጥፋት ወይም ጉዳት በማድረሱ ዙሪያ እንዲሳተፉ መገፋፋት ይኖርባታል። በድርጊቱ ውስጥ የተሳተፉት ሰዎች ከአስር በላይ ከሆኑና በሰው ላይ ጉዳት ወይም የንብረት ውድመት ከደረሰ፣ ክሱ ጠንከር ስለሚል ታሳሪዋ ከፖሊስ ጣቢያው አትለቀቅም።

እስር

በቁጥጥር ስር የዋሉ ሠላማዊ ሰልፈኞች ዳኛ ፊት እስኪቀርቡ ድረስ ከ24 እስከ 72 ሰዓታት ድረስ በፖሊስ ቁጥጥር ስር ሊውሉ ይችላሉ። ታሳሪው እስከ የሚቀጥለው የፍርድ ቤት ቀጠሮ ድረስ ታስሮ እንዲቆይ፣ ወይም እንዲለቀቅ፣ የሚወስነው ዳኛው ነው። አብዛኞቹ ተከሳሽ ሠላማዊ ሠልፈኞች ፍርድ ቤት በቀረቡ የመጀመሪያው አጋጣሚ ይለቀቃሉ።

## የህዝባዊ እምቢተኝነት ተቆጣጣሪዎች

ሠላማዊ ሠልፈኞች በብዛት በቁጥጥር ስር እንዲውሉ አስቀድሞ ከተወሰነ፣ ሂደቱን የሚከታተልና የሚቆጣጠር ሰው መመደብ ይኖርበታል። ይኸው ግለሰብ፣ ታሳሪዎቹ ተገቢውን የመታወቂያ ወረቀት መያዛቸውን ማረጋገጥ፣ የታሠሩት ሰዎች ዝርዝር መያዝ፣ እንዲሁም፣ ከተቻለ ወደ ፖሊስ ጣቢያው በመሄድ ነገሮች በሚፈለገው መልኩ መጓዛቸውን ማረጋገጥ ይኖርበታል። ይህ ዓይነቱ ኃላፊነት የተሠጠው ሰው፣ ወደ ሠላማዊ ሠልፉ ከመምጣቱ በፊት ወረቀትና እርሳስ መያዝ፣ እንዲሁም ማስታወሻዎችን ለመያዝ መዘጋጀት ይኖርበታል። ፖሊስ ጭካኔ የተመላበትን ድርጊት





ሲፈፅም ካስተዋለ፣ በድርጊቱ ውስጥ እጃቸውን ያስገቡ ፖሊሶችን ስም መመዝገብ አለበት። ካሜራ ቢኖረው ደግሞ፣ ይበልጥ ተመራጭ ነው።

## የህዝባዊ ሠልፈኞችና የፖሊስ መብቶች

በአሜሪካ፣ ማንኛውም ሰው «በህዝባዊ መድረኮች» (መንገዶች፣ የእግረኛ መተላለፊያዎች፣ የመናፈሻ ስፍራዎች፣ እንዲሁም የገበያ ማዕከላት) ሃሳቡ የመግለፅ መብቱ በህገ-መንግስት እውቅና አግኝቷል።

መንግስትና የፀጥታ አስከባሪ ኃይሎች የንግግሩን ይዘት (ለምሳሌ፣ በፖሊስ ላይ የሚሠነዘሩ ዘለፋዎችን ጨምሮ) መገደብ ባይችሉም፣ በንግግሩ ዙሪያ ተገቢ «የጊዜ፣ የቦታና የሁኔታ» ገደብ ማስቀመጥ ግን ይችላሉ። ስለዚህም፣ ፖሊስ ሠላማዊ ሠልፉ የህዝቡን ደህንነት ወይም ስርዓቱን አደጋ ላይ እንዳይጥል መቆጣጠር ይችላል። በአብያተ ክርስቲያናት፣ በቆንስላ ጽ/ቤቶች፣ በሆስፒታሎችና በሌሎች የተወሰኑ ህንፃዎች አጠገብ የሚካሄዱ ሠላማዊ ሠልፎችን በተመለከተ የወጡ ድንጋጌዎች አሉ።

ጠቅለል ባለ መልኩ ሲታይ፣ ማንኛውም ተናጋሪ ተሰብሳቢውን ህዝብ ከማነሳሳት፣ ወይም፣ ስሜቱን ከመቀስቀስ ሊከለከል አይችልም። ዳሩ ግን፣ ተናጋሪው ግለሰብ ተሰብሳቢውን ህዝብ ለንብረት ውድመት፣ ወይም በሰው ላይ ለሚደርስ ጉዳት፣ አልያም፣ ሌላ ዓይነት የህግ ጥሰት በሚጋብዝ መልኩ ካነሳሳ/ች፣ ድርጊቱ/ቷ በፖሊስ እንዲገታ መደረጉ አይቀርም።

ማጠቃለያ

ሠላማዊ ሰልፍ የሚተገበርበት ትክክለኛ፣ ወይም የተሳሳተ ዓይነት አካሄድ የለም፤ ትዕይንተ-ህዝቡ መካሄድ ያለበት ፖለቲካዊ ጉዳዮችን በሚያጎላ ሁኔታ መሆን አለበት።

አብዛኛውን ጊዜ፣ በህዝባዊ እምቢተኝነት ውስጥ የሚሳተፉ ሠላማዊ ሠልፈኞች ሲያደርጉ የሚስተዋለው የህንፃዎችን መግቢያ መዝጋት

(ለምሳሌ፣ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችን፣ ፋብሪካዎችን) ወይም፣ የትራፊክ እንቅስቃሴ ማሰናከል ሲሆን፣ በዚህም ድርጊታቸው እስርን በራሳቸው ላይ ይጋብዛሉ፡፡ ህዝባዊ እምቢተኝነቱ እንደተጀመረ፣ የፖሊስ አዛዡ ከሰላማዊ ሰልፈኞቹ ፊት በመቆም፣ ድርጊታቸውን እንዲያቆሙ ማስጠንቀቂያ አዘል ቃላት ሲወረውሩ፣ ቀሪዎቹ የፖሊስ ባልደረቦች ደግሞ፣ የእጅ ካቴና ይዘው ሠላማዊ ሰልፈኞቹን ዙሪያቸውን ይከቧቸዋል፡፡ ሠላማዊ ሰልፈኞቹ በያዙት አቋም ከቀጥሉ፣ በቁጥጥር ስር የማዋሉ ሂደት ተግባራዊ ይሆናል፡፡ በቀጣይነትም፣ ታሣሪዎቹን ወደ ፖሊስ ጣቢያ በሚወስዷቸው የፖሊስ ተሽከርካሪዎች ላይ ይጫናሉ፡፡

ሠላማዊ ሠልፉን ያዘጋጀውን ቡድን አንድ አባል፣ ሠላማዊ ሠልፈኞቹን በቁጥጥር ስር የማዋል ሂደቱን መከታተል፣ የታሰሩትን ሰዎች ዝርዝር መያዝ፣ ፖሊስ ተግባራዊ ያደረገውን አላስፈላጊ የኃይል አጠቃቀም መመዝገብ፣ እንዲሁም ታሳሪዎቹ መለቀቃቸውን ለማረጋገጥ ወደ ፖሊስ ጣቢያ ለመሄድ ዝግጁ መሆን ይኖርበታል፡፡





## ምዕራፍ ፮

# ቤተ-ክርስቲያንና ሠላማዊ ትግል

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ሀገራችን ላይ የመጡ የባዕድ ወራሪዎችን ለመመከት የተጫወተችውን ሚና ለዘላለም የሚወሳ ነው፡፡ አኩሪ ታሪኳም ነው፡፡

ዛሬ፣ ዘመኑ ተለውጦ፣ ይህ ምስኪን ህዝብ ወንዝ ተሻግረው ከሚመጡበት ጠላቶች ይልቅ፣ ከጉያው የበቀሉ አምባገነኖች ላለፉት 30 ዓመታት መከራ ሲያበሉት ኖረዋል፡፡ ታዲያ፣ ይቺ የሕዝብ የሆነች ቤተ-ክርስቲያናችን ከምዕመናን ጐን የምትቆምበት መንገድ የለምን? ብዬ ራሴን መጠየቅ ከጀመርኩ ሰነባብቻለሁ፡፡ በጉዳዩ ላይም ጥናት አድርጌ፣ የካቶሊክ ቤተክርስቲያን ተሞክሮ ይገኛ ቀርቤያለሁ፡፡

### የ«ሥነ-መለኮታዊ አርነት» ፅንሠ-ሀሳብ Liberation Theology

የፔሩ ዜጋ የሆኑት የሮማ ካቶሊክ ቄስ፣ ጉስታቮ ጉቲኤሬ፣ በ1973 (እ.ኤ.አ.) ለመጀመሪያ ጊዜ የተጠቀሙበት Liberation Theology («ሥነ-

መለኮታዊ አርነት» የሚለው የአማርኛ ሀረግ ለLiberation Theology ይቀርበዋል ብዬ እገምታለሁ)፣ የላቲን አሜሪካ ካቶሊክ ቄሶች የሚያራምዱት አስተምህሮ ነው፡፡ በዚህ ፍልስፍና መሠረት፣ ቤተ-ክርስቲያን የዓለማችንን ህዝብ ከድህነትና ከጭቆና ነፃ ለማውጣት የሚደረገው ትግል አካል መሆን ይገባታል፡፡ በሌላ አባባል፣ ቤተክርስቲያኗ፣ የዲሞክራሲ እንቅስቃሴ አጋር መሆን አለባት ነው የሚሉት፡፡

የ«ሥነ-መለኮታዊ አርነት» ንቅናቄ ተነሳሽነቱን በከፊል ያገኘው በ1962 (እ.ኤ.አ) በሮማ ካቶሊክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት፣ ዮሐንስ 23ኛ፣ ከተጠራው ሁለተኛው የቫቲካን ጉባዔና ከአምስት ዓመታት በኋላ ጳውሎስ 6ኛ ካወጡት የPopulorum progressi ኃይማኖታዊ ሰነድ ነው፡፡ ይኸው ሰነድ የዓለም አቀፋዊውን ኢኮኖሚያዊ ስርዓት ፍትሃዊነት ጥያቄ ውስጥ ያስገባ ነበር፡፡

የሮማ ካቶሊክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት፣ በዘመናዊ ኢንዱስትሪያዊ ማህበረሰቦች አማካኝነት የተፈጠሩትን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ በደሎችን ሲያወግዙና ለችግሮቹ የመፍትሄ ሀሳቦችን ሲያስቀምጡ ቆይተዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም፣ የኑክሊየር ጦር መሳሪያዎችን፣ የጦር መሳሪያ ፉክክርን፣ እንዲሁም፣ የበለፀጉ ሀገራት በድሆቹ ላይ የሚፈፅሟቸውን ብዝበዛዎች አጥብቀው ሲቃወሙና እንዲገቱ በተደጋጋሚ ጥሪያቸውን ሲያስተላልፉ ኖረዋል፡፡ በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊና በፖለቲካዊ ስርዓቶች ውስጥ የሰብዓዊ መብቶች መከበርንም ትኩረት የሚሰጡት ጭብጥ ሆኖ ዘልቋል፡፡

የ«ሥነ-መለኮታዊ አርነት» አራማጆች አቋም «ፈላስፎች እስከ አሁን ድረስ የዓለማችንን ተፈጥሮና ባህሪይ ሲያብራሩልን ቆይተዋል፣ የእኛ ተልእኮ ደግሞ፣ ይህችኑ ዓለማችንን መለወጥ ነው» ከሚለው አባባል ጋር የሚስማማ ነው፡፡ እንደ እነኝህ ወገኖች እምነት፣ ሥነ-መለኮት ምሁራን (ቄሶች) የንድፈ ሃሳብ አራማጆች ብቻ ሳይሆኑ ማኅበረሰባዊ ለውጥ ለማምጣት በሚደረገው ትግል ውስጥ የሚሳተፉ የተግባር ሰዎች ናቸው፡፡





የካቶሊክ ቤተክርስትያን፣ የሃዩቲው አምባገነን፣ ዣን-ክሎውድ ዱቫሊዬ («ፓፓ ዶክ»)፣ እንዲሁም በፊሊፒንሱ ፈላጭ ቆራጭ መሪ፣ ፈርዲናንድ ማርኮስ፣ ውድቀት ዙሪያ ስለተጫወተችው ሚና ብዙ ተብሏል፡፡ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ደግሞ፣ በደቡብ ኮሪያ የሚገኙ የክርስቲያን ካህናት የፀጥታ አስከባሪ ኃይሎች ለሚያባርሯቸው የስርዓቱ ተቃዋሚዎች መሸሸጊያ በመስጠት የዴሞክራሲ አጋሮች ሆነዋል፡፡ በኒካራጉዋ፣ ቤተክርስቲያኗ በ1979 (እ.ኤ.አ) ለአምባገነኑ አናስታሲዮ ሳሞዛ ከስልጣን መወገድ ድርሻዋን ተወጥታለች፡፡ የብራዚል ቀሳውስት በሀገሪቷ እስር ቤቶች በታሳሪዎች ላይ የሚፈፀመው አሰቃቂ ድርጊት እንዲቆም ያቀረቡት ጥሪ በ1979 (እ.ኤ.አ) በጐ ምላሽ አግኝቷል፡፡ በቀጣይነትም ነፃና ፍትሃዊ ምርጫ እንዲካሄድ ያቀረቡት ጥያቄ ተቀባይነትን አግኝቶ በ1985 (እ.ኤ.አ) እውን ሆኗል፡፡ በጥቅሉ፣ የካቶሊክ ቤተክርስቲያን፣ በላቲን አሜሪካ ታላቅ የዴሞክራሲ ኃይል ሆናለች፡፡ ይህ ማለት ግን፣ ቤተክርስቲያኗ ከአንድ የፖለቲካ ድርጅት ጋር ወግናለች ማለት አይደለም፡፡ ካቶሊክ ቤተክርስቲያን የታገለችው ለዲሞክራሲያዊ ሥርዓት እውን መሆን ነው፡፡ ይህ ሥርዓት እውን ከሆነ በኋላ፣ ሥልጣን የሚይዘውን ድርጅት ማንነት የሚወስነው ህዝብ ነው፡፡

## የ«ሥነ-መለኮታዊ አርነት» ታሪካዊ አመጣጥ

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ለ«ሥነ-መለኮታዊ አርነት» እየተሰጠው ያለው ትኩረት ክስተቱን አዲስ ቢያስመስለውም፣ ጥንታዊ መሠረት ያለው ፅንሥ-ሀሳብ ነው፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ በብሉይና በሀዲስ ኪዳኖች ላይ ከሠፈሩት አብነቶች መካከልም ጥቂቶቹን ለአንባቢያን ግንዛቤ እንዲያስጨብጡ በሚል በገፅ 137 እና 138 ላይ አቅርቤያቸዋለሁ፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተካተተው ክርስቲያናዊ መልእክት፣ ድሀውንና ጭቁኑን ወገን ነፃ ለማውጣት ያለመ ዘዴ እንደሆነ በግልፅ ተቀምጧል፡፡

በላቲን አሜሪካ፣ ቤተክርስቲያኗ የፖለቲካ ጉዳዮችን እንድታስተናግድ የመጀመሪያው ጥሪ የቀረበላት በ15ኛው ምዕተ ዓመት የሮማው ካቶሊክ ርዕሰ ሊቀ ጳጳሳት፣ አሌክሳንደር 6ኛ፣ የስፔይንና የፖርቹጋል ንጉሦች፣ በአውሮፓ ለሚያደርጉት እንቅስቃሴ ቤተክርስቲያኗ፣ ድጋፍ የምትሰጥ ከሆነ፣ በላቲን አሜሪካን ሰፊ ይዞታ እንደሚሰጣት ቃል በገቡላት ጊዜ ነበር። ከዚያን ጊዜ አንስቶ፣ በእኛ ሀገር «የሲሶ መንግስት» እንደሚባለው በላቲን አሜሪካ የፖለቲካው ሥርዓት አካል ሆና ኖራለች።

ቤተክርስቲያኗ የለውጥ ሐዋርያ ሆና፣ ዘመናዊው ማዕበል የተቀሰቀሰው ግን፣ በ1960ዎቹ ነበር።

ከዚህ ስር ነቀል አተያይ የፈለቀው አስተምህሮ «ሥነ-መለኮታዊ አብዮት» (Recolution/Liberation Theology) የሚል መጠሪያ ተሰጥቶታል። የዚህ ንቅናቄ ዋነኛው አቀንቃኝ፣ ኮሎምቢያዊው ቄስ ካሚሎ ቶሬስ፣ ከዓማፂያን ቡድኖች ጋር ወግነው በሚታገሉበት ወቅት በ1966 (እ.ኤ.አ.) ተገድለዋል።

ያም ሆነ ይህ ግን፣ ንቅናቄው በጳውሎስ 6ኛ በተጠራውና በ1965 (እ.ኤ.አ.) መጨረሻ አካባቢ ከተካሄደው ሁለተኛው የቫቲካን ጉባዔ በኋላ ኃይልና ጥንካሬ እያገኘ ሄዷል።

በመርሁ (የሥነ-መለኮታዊ አብዮት) መሠረት፣ ቤተክርስቲያኗ መሰረቷን የጣለችው በድህውና በተጐሳቆለው ማህበረሰብ ዙሪያ ስለሆነ፣ ኑሯቸውን ለማሻሻል ልታግዛቸው ይገባል።





በመጽሐፍ ቅዱስ የተጠቀሱ

የ«ሥነ-መለኮታዊ አርነት» አብነቶች

*ኦሪት ዘሌዋውያን ም.25 ቁ.35-38*

ወንድምህ ቢደኸይ እጁም በአንተ ዘንድ ቢደክም እፅናው፣ እንደ እንግዳና እንደ መፃተኛም ከአንተ ጋር ይኑር። ወንድምህ ከአንተ ጋር ይኖር ዘንድ ከእርሱ ምንም ወለድ ወይም ትርፍ አትውሰድ፤ ነገር ግን አምላክህን ፍራ። ብርህን በወለድ አታበድረው፤ መኖህንም በትርፍ አትስጠው።

*ትንቢተ ኢሳይያስ ም.61 ቁ.1-2*

የጌታ የእግዚአብሔር መንፈስ በእኔ ላይ ነው፤ ለድሆች የምሥራችን እሰብክ ዘንድ እግዚአብሔር ቀብቶኛልና፤ ልባቸው የተሰበረውን እጠግን ዘንድ፣ ለተማረኩትም ነፃነትን ለታሰሩትም መፈታትን እናገር ዘንድ ልኮኛል።

*የሉቃስ ወንጌል ም.1 ቁ.51-52*

በክንዱ ኃይል አድርጎአል፤ ትዕቢተኞችን በልባቸው አሳብ በትኖአል፤ ገዢዎችን ከዙፋናቸው አዋርዶአል፤ ትሑታንንም ከፍ አድርጎአል።

*የሐዋርያት ሥራ ም.4 ቁ.32-36*

ያመኑትም ሕዝብ አንድ ልብ አንዲት ነፍስ ነበሩአቸው፤ ገንዘባቸውም ሁሉ በአንድነት ነበር እንጂ ካለው አንድ ነገር ስንኳ የራሱ እንደሆነ ማንም አልተናገረም። ሐዋርያትም የጌታን የኢየሱስ ክርስቶስን ትንሳኤ በታላቅ ኃይል ይመሰክሩ ነበር፤ በሁሉም ላይ ታላቅ ፀጋ ነበረባቸው። በመካከላቸው አንድ ስንኳ ችግረኛ አልነበረምና፣ መሬት ወይም ቤት ያላቸው ሁሉ እየሸጡ የተሸጠውን ዋጋ ያመጡ ነበርና፤

በሐዋርያትም እግር አጠገብ ያኖር ነበር፤ ማናቸውም እንደሚፈልግ መጠን ለእያንዳንዱ ያካፍሉት ነበር።

*ወደ ኤፌሶን ሰዎች ም.6 ቁ.12-13*

መጋደላችን ከደምና ከሥጋ ጋር አይደለምና፣ ከአለቆችና ከሥልጣናት ጋር ከዚህም ከጨለማ ዓለም ገዢዎች ጋር በሰማያዊም ስፍራ ካለ ከክፋት መንፈሳውያን ሰራዊት ጋር እንጂ።

*የያዕቆብ መልእክት ም.5 ቁ.1-6*

አሁንም እናንተ ባለጠጎች፣ ስለሚደርስባችሁ ጭንቅ ዋይ ዋይ እያላችሁ አልቅሱ። ሀብታችሁ ተበላሽቶአል፣ ልብሳችሁም በብል ተበልቶአል። ወርቃችሁም ብራችሁም ዝጎአል፣ ዝገቱም ምስክር ይሆንባችኋል። ሥጋችሁንም እንደ እሳት ይበላል። ለኋለኛው ቀን መዝገብን አከማችታችኋል። እነሆ፣ እርሻችሁን ያጨዱት የሰራተኞች ደመወዝ በእናንተ ተቀምቶ ይጮኻል፣ የአጫጆችም ድምፅ ወደ ጌታ ፀባዖት ጆሮ ገብቶአል። በምድር ላይ ተቀምጠላችኋል፣ በሴሰኝነትም ኖራችኋል፣ ለእርድ ቀን እንደሚያወፍር ልባችሁን አወፍራችኋል። ፃድቁን ኮንናችሁታል፣ ገድላችሁትማል፤ እናንተን አይቃወምም።

## የ«ሥነ-መለኮታዊ አርነት» የአሰራር ዘዴዎች

በ«ሥነ-መለኮታዊ አርነት» እንቅስቃሴ ውስጥ የሚሳተፉ ካህናት የሚጠቀሙት ዋነኛ መሳሪያ መጽሐፍ ቅዱስ ነው። የሥነ-መለኮታዊ አርነትን ትምህርት የሚማሩ ግለሰቦች፣ መጽሐፍ ቅዱስን በቃላቸው እንዲይዙ የማይጠየቁ ቢሆንም፣ ስለአካባቢያቸው ያላቸውን ግንዛቤ ከኢየሱስ ክርስቶስ ቃል ጋር እንዲያዛምዱ ይጠየቃሉ። የዚህ መርህ ዋነኛው አቀንቃኝ፣ ብራዚላዊው ምሁር ፓውሎ ፍሬይሬ፣ የትምህርቱ ሂደት





መጀመር ያለበት ከድሀው፣ ወይም ከጭቁኑ ማህበረሰብ፣ አተያይ አንፃር ነው ባይ ናቸው።

የ«ሥነ-መለኮታዊ አርነት» ፅንሠ-ሀሳብ አራማጆች ተግባር፣ ግንዛቤ ማስጭበጥና ወንጌልን መስበክ ብቻ አይደለም። የሰብዓዊ መብት ተሟጋች አካላትን ከማቋቋም ባለፈ፣ እንደ የመሬት ስሪት ለውጥ፣ የራስ-አገዛዝ ፕሮጀክቶችና የገበሬዎች የህብረት ስራ ማህበራትን የመሰሉ አዳዲስ ሀሳቦችን በማፍለቅ፣ ለተግባራዊነታቸው ይንቀሳቀሳሉ።

### ሃዬቲና ሥነ-መለኮታዊ አርነት

ዣን-በርትራን አሪስቲድ (የኋላ ኋላ የሃዬቲ ፕሬዝዳንት) የቅስና ትምህርታቸውን በሚከታተሉበት ወቅት፣ የ«ሥነ-መለኮታዊ አርነት» ተፅዕኖ አድሮባቸው ነበር። ለአሪስቲድ፣ «ሥነ-መለኮታዊ አርነት» ማለት የዣን ክሎውድ ዱቫሊዬ («ፓፓ ዶክ») አምባገነናዊ አገዛዝን መቃወምና፣ የድሀውን ህዝብ መብቶች ማስከበር የሚል ትርጉም ነበረው።

አሪስቲድ በ1979 (እ.ኤ.አ) ኃይማኖታዊ ትምህርታቸውን እንዳጠናቀቁ፣ አለቆቻቸው ፖለቲካዊ እንቅስቃሴያቸውንና አመለካከታ ቸውን ለማቀዝቀዝ በማሰብ፣ ወደ ባህር ማዶ ልከዋቸው ነበር። በዚህም መሰረት፣ በመጀመሪያ ያመሩት የሥነ-መለኮት ትምህርታቸውን ወደቀጠሉባት እስራኤል ነበር። በቀጣይነትም ወደ ለንደንና በሥነ-መለኮት የማስተርስ ዲግሪ ወዳገኙባት የካናዳዋ ሞንትሪያል ከተማ አቅንተዋል። አሪስቲድ፣ ቅስናቸውን ለመቀበል በ1982 (እ.ኤ.አ) ለአጭር ጊዜ ወደ ሃዬቲ ተመልሰው ሄደዋል።

በ1985 (እ.ኤ.አ) በርዕሰ ከተማዋ፣ ፖርት-አ-ፕሪንስ፣ በድሆች መንደር ውስጥ ለሚገኝ አንድ ደብር መጋቢ ሆነው የተሾሙት ቄስ አሪስ ቲድ፣ የዱቫሊዬን መንግሥት የተቃወሙ ብዙ ቡድኖችን አደራጅተዋል፣ መርተዋልም።

በየካቲት 1986 (እ.ኤ.አ.)፣ በእነ አሪስቲድ ተቃውሞ የተዳከሙት ዱቫሊዬ ሀገሪቷን በመልቀቅ ለስደት ህይወት ሲዳረጉ፣ በቀጣዮቹ አራት አመታት የሃዩቲን አስተዳደር የተረከበው የቀድሞው አምባገነናዊ ስርዓት የሚደግፉ ሲቪሎችንና የጦር መኮንኖችን ያቀፈ ቡድን ነበር፡፡ በዚህ አዲስ የአስተዳደር መዋቅር ያልተደሰቱት አሪስቲድ፣ ይህን አምባገነናዊ ስርዓት ለመቃወም የተሰለፉትን የሀገሪቷን ዜጎች ማደራጀቱንና መምራቱን ገፍተውበታል፡፡ በ1988 (እ.ኤ.አ.)፣ አሪስቲድ አባል የሆኑበት የሳሌሺያን ማህበር (የካቶሊክ ቤተክርስቲያን ማህበር) ከመንግስት በደረሰበት ጫናና ግፊት «አሪስቲድ ሁከትና ብጥብጥ ቀስቅሰዋል» በሚል ሽፋን ከቤተክርስቲያን አባልነታቸው እስከመሰረዝ ደርሶ ነበር፡፡

ይህም ሆኖ ግን፣ ከ1804 (እ.ኤ.አ.) ወዲህ ለመጀመሪያ ጊዜ በታህሳስ 1990 (እ.ኤ.አ) በተካሄደው ነፃና ፍትሃዊ ምርጫ፣ አሪስቲድ የሃዩቲ ፕሬዝዳንት ሆነው ተመርጠዋል፡፡ የሃዩቲ ዴሞክራሲ አብዮት፣ በቄስ የተመራ የመጀመሪያው የዴሞክራሲ አብዮት ለመሆን በቅቷል፡፡

ደቡብ አፍሪካና ሥነ-መለኮታዊ አርነት

«ሥነ-መለኮታዊ አርነት» ዘረኝነት (አፓርታይድ) በተንሰራፋባት ደቡብ አፍሪካም የተንፀባረቀ ፅንሠ-ሃሳብ ነበር፤ ጥቂት የማይባሉ ተራማጅ አመለካከት የነበራቸው የቤተ-ክህነት ኃላፊዎች ይህንኑ ስርዓት ሲታገሉ ኖረዋል፡፡

በዚህም መሠረት፣ የደቡብ አፍሪካ ቄሶች «ጨቋኙም ተጨቋኙም ለአንድ ቤተ-ክርስቲያን ታማኝ ነን ባዮች ናቸው፡፡ ሁለቱም ወገኖች በአንድ አይነት መልኩ ይጠመቃሉ፤ ያንኑ የክርስቶስ ደምና ስጋ ይቋደሳሉ፡፡ ሁለቱም ወገኖች ተቀምጠው የሚያስቀድሱት በአንድ ቤተ-ክርስቲያን ውስጥ ነው፡፡ ከቤተ-ክርስቲያን ውጭ ግን፣ ክርስቲያን ፖሊሶችና ወታደሮች፣ ክርስቲያን ህፃናትን ወይም እስረኞችን መደብደቡን፣ ማሰቃየቱንና መግደሉን ቀጥለውበታል፡፡ ሌሎች ክርስቲያኖች ደግሞ፣ ሀገራቸው ውስጥ ሠላም





እንዲሰፍን በየጊዜው ይፀልያሉ፡፡ ቤተ-ክርስቲያኗ ከመከፋፈሏም ባሻገር፣ የፍርድ ቀኗም እየደረሰ ነው፡፡ ዝም ብለን መመልከት የለብንም፡፡ ለፍትህ መቆም አለብን፡፡ ቤተ-ክርስቲያን፣ መጥፎውን «መጥፎ»፣ ጥሩውን «ጥሩ» ማለት መቻል አለበት» የሚለውን ቁልፍ ነጥብ በውስጡ ያቀፈውና «ኬይሮስ» («የሀቅ ጊዜ») የተሰኘውን ሠነድ ለህትመት አብቅተዋል፡፡

ከዚህ በኋላ፣ ቤተ-ክርስቲያን የአፓርታይድን አገዛዝ የሚታገሉበት መድረክ ሆናለች፡፡

በደቡብ አፍሪካ፣ ቤተ-ክርስቲያን አፓርታይድን በመታገሉ ሂደት ያበረከተችው አስተዋፅኦ፣ ቄስ ዴዝሞንድ ቱቱ፣ የኖቤል የሰላም ተሸላሚ በመሆናቸው ይገለፃል፡፡ ቤተ-ክርስቲያኗ፣ በትግሉ ሂደት ሳቢያ ከመቼውም ጊዜ በላይ ተጠናክራ ወጥታለች፡፡

ማጠቃለያ

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የሚወጡ አሃዞች እንደሚያመለክቱት፣ በዓለማችን 1.06 ቢልዮን ክርስቲያኖች ይገኛሉ፡፡ «ሥነ-መለኮታዊ አርነት»፣ 400 ሚልዮን የእምነቱ ተከታዮች በሚኖሩባቸው ዌስት ኢንዲስ፣ ማዕከላዊና ደቡባዊ አሜሪካ ጥንካሬውን ከጊዜ ወደ ጊዜ እያጐለበተ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪም፣ በአፍሪካ ውስጥ ያለው ተቀባይነት እያደገ መጥቷል፣ ኢትዮጵያም የዚህ ተፅዕኖ ተቋዳሽ ትሆናለች የሚል ተስፋ አለኝ፡፡ 21ኛው ምዕተ ዓመት ሲያበቃ፣ ከክርስትና እምነት ተከታዮች መካከል ግማሽ ያህሉ የሚኖሩት «ሥነ-መለኮታዊ አርነት» በህይወታቸው ላይ ትልቅ ለውጥ ማስመዝገብ በሚችልባቸው የሶስተኛ ዓለም ሀገራት ውስጥ ነው፡፡

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተካተተው «የኃጢያት ስርየት»፣ ከጭቆናና ከኢ-ፍትሃዊነት ነፃ የመውጣት ሂደት ጋር እኩል ተደርጐ መታየት ይኖርበታል፡፡ «ኃጢያት የሚገለፀው የሰው ልጅ በቢጤው ላይ በሚፈፅመው ኢ-ሰብዓዊ ድርጊት ነው፡፡» «ሥነ-መለኮታዊ አርነት» ደግሞ፣

አንድን ጐረቤት መውደድ፣ ፈጣሪን ከመውደድ ጋር የማይነጣጠል ነው የሚል አመለካከት የሚያራምድ ፅንሰ-ሀሳብ ነው፡፡

የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ፣ የሰው ልጅ ለፍትህና ለሰብዓዊነት መከበር በሚደረገው ትግል በርካታ አብነቶችንና አርአያዎችን በጉልህ ያሳየናል፡፡ በብሉይ ኪዳን፣ አራት ዘፀአት ውስጥ፡ የእስራኤላዊያን ከግብፅ ጭቆና መላቀቅ፣ እንዲሁም የኢየሱስ ክርስቶስ ህይወትና ሞት ለዘመናችን የሰው ልጅ የነፃነት ትግል በናሙናነት የሚያገለግሉ ክስተቶች ናቸው፡፡ እነኝህ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አጋጣሚዎች፣ ለነፃነት የሚደረገውን ዓለማዊ ትግል መንፈሳዊ ትርጉም አጉልተው የሚያሳዩን ናቸው፡፡

ቤተ-ክርስቲያንና ዓለማችን ተለያይተው መኖር አይችሉም፡፡ ቤተ-ክርስቲያኗ በዓለማችን ውስጥ የምትጫወተውን ሚና ከጊዜ ወደ ጊዜ ማሳደግ ይጠበቅባታል፡፡ ከጭቁኑ የማህበረሰቡ ክፍል ጐን መሰለፍ፣ እግዚአብሔር የሰው ልጅ ለፍትህ መስፈን በሚደረገው ትግል ውስጥ ገለልተኛ አለመሆኑን የሚጠቁመን ነው፡፡





## ምዕራፍ ፺

# ህዝባዊ እምቢተኝነት በኢትዮጵያ ሊሠራ ይችላል ወይ?

የህዝባዊ እምቢተኝነት ፅንሰ ሃሳብ በሰፊው እያነጋገረ ባለበት በአሁኑ ጊዜ፣ «በኢትዮጵያ ይሠራል ወይ?» ብለው የሚጠራጠሩ ሰዎች እንዳሉ አውቃለሁ፡፡ በእኔ በኩል፣ ለጊዜው፣ «ይሠራል» ወይም፣ «አይሠራም» ለማለት አልፈልግም፡፡ ወደዚያ ከመግባት ይልቅ፣ ከአሜሪካና ከህንድ ባሻገር በሌሎች ሀገሮች ውስጥ ሠርቶ ያውቃል ወይ? በሚለው ጥያቄ ዙሪያ የሰራሁትን ጥናት ላካፍላችሁ እወዳለሁ፡፡ እነሆ፡-

ቺሊ

በ1980ዎቹ ዓመታት የላቲን አሜሪካ ዓይነተኛ መገለጫ የሆኑት አምባገነናዊ ስርዓቶች በአብዛኛው የተወገዱት፣ ህዝቡ ባካሄዳቸው ህዝባዊ እምቢተኝነት አማካኝነት ነው፡፡ ከእነኝህ ሀገራት መካከልም፣ ቺሊ አንዷ ናት፡፡ እንደ ፊሊፒንስ ህዝብ ለበርካታ ዓመታት በአምባገነናዊ ስርዓት ስር

የማቀቁት ቺሊያውያን፣ የጄኔራል አውጉስቶ ፒኖሼን አገዛዝ በ«ሠላማዊ ዓመፅ» ለመታገል ተነሳሽነቱን ያገኙት፣ ከዚህችው የሩቅ ምስራቅ ሀገር ህዝባዊ ንቅናቄ ተሞክሮ በመውሰድ ነበር፡፡ ቺሊያውያን በሰላማዊው ትግል ሂደት የሚያደርጉትን ጥረት ሲገልፁ የቆዩት፣ «ጠብታ ውኃ የጭቆናን አለት ቀስ በቀስ ይሸረሽረዋል» በማለት ነበር፡፡

በቺሊ፣ የሰላማዊ ትግል የተቀጣጠለው በሚገርም መልኩ ነበር፡፡ አጠር አድርጌ እንዲህ አቅርቤዋለሁ፡- በ1986 (እ.ኤ.አ) ግራ ክንፈኛ የደፈጣ ተዋጊዎች ጄኔራል ፒኖሼን ለመግደል ባደረጉት ሙከራ፣ አምስት ጠባቂዎቻቸውን ገደሉ፡፡ ለዚህ ድርጊት አፀፋዊ እርምጃ ለመውሰድ ቆርጦ የተነሳው ሠራዊቱ፣ የአገዛዙን አምስት ተቃዋሚዎች በቁጥጥር ስር ለማዋል ከውሳኔ ላይ ይደርሳል፡፡ ከእነኝህም መካከል የተካተተ አንድ የሰብዓዊ መብቶች ተሟጋች ጠበቃ፣ የፀጥታ አስከባሪ ኃይሎች አፍነው እንደሚወስዱት ለጐረቤቶቹ በማስጠንቀቁ፣ ሊከላከሉለት ዕቅድ ነደፉ፡፡ አፈናው በታቀደበት ምሽት ሊንጋ አካባቢ፣ ወደ ጠበቃው መኖሪያ ቤት ለመግባት የሚሞክሩ ጭምብል ያጠለቁ ሰዎችን የያዙ መኪኖች ከአካባቢው ደረሱ፡፡ ሰዎቹ በተለያዩ ዘዴዎች ግጥም ተደርገው የተዘጉትን የቤቱን በሮች ለመክፈት ሞክረው ሲያቅታቸው፣ በብረት ርብራብ የተቸነከሩትን መስኮቶች ለመስበር ይታገሉ ጀመር፡፡ ይህን ጊዜ የጠበቃው ቤተሰብ አባላት በመኖሪያ ቤታቸው ውስጥ ያሉትን አምፖሎች በሙሉ በማብራት፣ ድስቶቻቸውን በመቀጥቀጥና ፊሽካዎችን በመንፋት፣ ተመሳሳይ ድርጊት ለመፈፀም ከጐናቸው የተሰለፉትን ጐረቤቶቻቸው ከእንቅልፋቸው አነቋቸው፡፡ ወዲያው፣ ጐረቤቶቹም መብራታቸውን አብርተው ድስቶቻቸውን መቀጥቀጥና ፊሽካ መንፋት ጀመሩ፡፡

ተዘጋጅተው በጠበቋቸውና ለዓላማቸው ቆርጠው በተነሱት ነዋሪዎች ግራ የተጋቡት አፋኞችም፣ አካባቢውን ለቅቀው ከመሄድ በስተቀር ሌላ አማራጭ አልነበራቸውም፡፡





በቀጣይነትም፣ ሌሎች ቡድኖች መንግስት በቁጥጥር ስር የሚያውላቸውን ሰዎች ለስቃይ የሚዳርግበትን እስር ቤቶች በጥንቃቄ በማጥናት፣ ይህን እኩይ ተግባር የሚያጋልጡበትን ዘዴዎች ነደፉ፡፡ ከእነኝህ ዘዴዎች መካከል፣ ዒላማቸው ውስጥ ካስገቡት እስር ቤት አጠገብ በሚገኝ አጥር ላይ ራሳቸውን በሰንሰለት አቆራኝቶ ማሰር አንዱ ነበር፡፡ ሌሎች የስርዓቱ ተቃዋሚዎች ደግሞ፣ የትራፊክ እንቅስቃሴ በሚበዛበት ሰዓት እስር ቤቱ ወዳለበት አካባቢ በማምራት፣ «እዚህ ህዝብን ያሰቃያሉ» የሚል በጨርቅ ላይ የተፃፈ መፈክር ለመንገደኛው በግልፅ ያሳዩ ነበር፡፡ ይህንን ከሚያደርጉ ሰዎች መካከል፣ የፀጥታ ሰራተኞች ከመድረሳቸው በፊት ጥቂቶቹ ከህዝቡ መሃል ገብተው ሲሰወሩ፣ ቀሪዎቹ ደግሞ፣ በቁጥጥር ስር እስኪውሉ ድረስ ከአካባቢው ሳይርቁ የፀጥታ አስከባሪ ኃይሎቹን መምጣት ይጠባበቃሉ፡፡ ይታሰራሉ፡፡

ከተለያዩ ማዕዘናት ጫናው እየበረታበት የመጣው የቺሊ መንግስት፣ በጥቅምት 1988 (እ.ኤ.አ.) ህዝቡ ወታደራዊ አገዛዙ በስልጣኑ መቀጠል አለመቀጠሉን በተመለከተ ሪፈረንደም እንዲያካሂድ ጥሪውን አስተላለፈ፡፡ በአገዛዙ ተቃዋሚዎች ላይ መጠነ ሰፊ የማስፈራራት ዘመቻ ቢከፈትም፣ ህዝቡ ከዓላማው ዝንፍ የሚል አይነት አልነበረም፡፡ ህዝቡ ከስጋቱና ከፍርሃቱ እንዲላቀቅ የሚያግዙትና ምርጫውን በተመለከተ በቂ ግንዛቤ ያስጨበጡት ስብሰባዎች በተለያዩ ከተሞች ይካሄዱ ጀመር፡፡ የፊሊፒንስ አምባገነን መሪ፣ ፈርዲናንድ ማርኮስ፣ ተቃዋሚዎች እገዛ ያልተለየው ይኸው የቺሊ ህዝብ ህዝባዊ እምቢተኝነት፣ ከተጠበቀው በላይ ውጤት አስገኝቷል፡፡ ከመራጩ ህዝብ መካከል 95% ድምፅ ለመስጠት ሲመዘገብ፣ የፒኖሼ ተቃዋሚዎች 54.7% ድምፅ አግኝተዋል፡፡ ይህንንም ተከትሎ፣ ከአንድ ሚልዮን ህዝብ በላይ ድሉን ለማክበር በመዲናዋ፣ ሳንቲያጐ፣ በሚገኝ አንድ የመናፈሻ ስፍራ ተሰባሰቧል፡፡

## ብራዚል

በ1980ዎቹ የመጨረሻ ዓመታት የላቲን አሜሪካ አምባገነናዊ ስርዓቶች በተከታታይ የወደቁት በትጥቅ ትግል ሳይሆን፣ በሠላማዊው ህዝብ፣ ማለትም፣ ተማሪዎች፣ እናቶች፣ ሠራተኞች፣ ኃይማኖታዊ ቡድኖች፣ ያላሰለሰ ጥረት አማካኝነት ነበር፡፡ ብራዚል ውስጥ ለፍትህ መስፈን የተደረገው ትግል፣ በሀገሬው በሚነገረው የፖርቹጋል ቋንቋ firmeza permamente («እልህ አስጭራሽ ፅናት») በመባል ይታወቅ ነበር፡፡ ብራዚል፣ የአንድም ሰው ደም ጠብ ሳይልባት ከወታደራዊ አገዛዝ ወደ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ተሸጋግራለች፡፡

## አርጀንቲና

«ደብዛቸው የጠፉ ሰዎች እናቶች» የሚባሉ የአርጀንቲና የቤት እመቤቶች በወታደራዊው አገዛዝ ስር «ደብዛቸው የጠፉ ሰዎች» (desparacidos) ያሉበትን ቦታና ሁኔታ ለማወቅ ያደረጉት ቅስቀሳና የሻማ ማብራት ስነ-ስርዓት፣ በአርጀንቲና፣ የዴሞክራሲ ባህል አብዮት አስከትሏል ማለት ይቻላል፡፡ እናቶች፣ በዓለም ታሪክ፣ የዴሞክራሲያዊ ባህል አብዮት ግንባር ቀደም ተዋናዮች የሆኑበት አጋጣሚ፣ የአርጀንቲናው ብቸኛ ተጠቃሽ ነው፡፡ ታሪክ መቼም አይረሳቸውም፡፡

## ኡራጓይ

በርዕሰ ከተማዋ፣ ሞንቴቪዲዮ፣ በ«ፍትህና ሠላም አገልግሎት» (Serpaj) አነስተኛ ቢሮ ውስጥ የተካሄደው የረሃብ አድማ፣ በኡራጓይ ወታደራዊ ጁንታ ላይ የመጀመሪያውን ህዝባዊ ተቃውሞ ከመቀስቀሱም ባሻገር፣ ወደ ዴሞክራሲ የሚደረገውን ጉዞ ያፋጠነ ንቅናቄ እንዲጀመር ሁኔታዎችን አመቻችቷል፡፡ ከትንሽ ነገር፣ ትላልቅ ታሪኮች እንደሚወለዱ የታየበት አጋጣሚ ነበር፡፡





## ሃዩቲ

ለዴሞክራሲ የተደረገው ትግል ይበልጥ አስቸጋሪ የሆነባት ሀገር ብትኖር፣ ሃዩቲ ናት፡፡ ያም ሆኖ ግን፣ ህዝቡ የሚያጋጥሙትን ከባድና አስቸጋሪ ፈተናዎች በሠላማዊ መንገድ ለመቋቋም ድፍረቱ፣ ወኔውና ቆራጥነቱ ነበረው፡፡ ጭቆናን የሚጠራርግ ማዕበል (Lavalas ተብሎ የሚጠራው) ፀሎትን፣ ሰላማዊ ሰልፈኞችንና ሌሎች መሰል የትግል ዘዴዎችን ያካተተ ነበር፡፡

ከንቅናቄው መሪዎች መካከል አንዱ፣ ቄስ ዣን በርትራንድ አሪስቲድ፣ በአለቆቻቸው (ጳጳሳት) ከመወገዝ ባለፈ፣ አጥቢያቸውን ለቅቀው የሠራዊቱ ጠንካራ ይዞታ ስር ወደሚገኝ ቤተ ክርስቲያን እንዲዛወሩ ይታዘዛሉ፡፡ በዚህ የተበሳጩት የደብራቸው ተማሪዎች፣ በርዕሰ ከተማዋ፣ ፖርት-አ-ፕሪንስ፣ በሚገኘው ብሔራዊ ካቴድራል የፊት ለፊት መቀመጫዎቹን በሙሉ ያዟቸው፡፡ ከእነሱም መካከል ሰባቱ ለስድስት ቀናት የዘለቀ የረሃብ አድማ በመምታት፣ ጳጳሳቱ ሃሳባቸውን እንዲቀይሩ አስገድደዋቸዋል፤ አሪስቲድም በአጥቢያቸው መስራቱን ቀጠሉ፡፡

ቢታህሳስ 1990 (እ.ኤ.አ) ደግሞ፣ አሪስቲድ የሀገሪቷ ፕሬዝዳንት ሆነው ለመሾም በቅተዋል፡፡

## ቻይና

በ1989 (እ.ኤ.አ.) የፀደይ ወቅት ለቻይናዊያን አዲስ የታሪክ ምዕራፍ መባቻ መስሎ ነበር፡፡ ለአንድ ሟች የዴሞክራሲ መሪ መታሰቢያነት የተዘጋጀው የእግር ጉዞ፣ በአጭር ጊዜ ውስጥ በህዝቡ ውስጥ ለረዥም ጊዜ ታፍኖ የቆየው ብሶት እንዲገነፍል ምክንያት ሆኗል፡፡ የኋላ ኋላ ሠራተኞች የተቀላቀሏቸው ተማሪዎች፣ «ህዝባዊ ኃይል» እና «እናሸንፋለን» የሚሉትን መፈክሮች በማንገብ፣ ለዴሞክራሲ መስፈን፣ ለሙስና መወገድ፣ ለነፃ ፕሬስ መስፋፋትና ለሌሎች ዴሞክራሲያዊ ለውጦች ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ማሰማት ጀመሩ፡፡

እነኝህን ተቃዋሚዎች በርዕሰ ከተማዋ፣ ቤይጂንግ፣ ቲያናንሜን አደባባይ የተቀላቀሏቸው በሙቶ ሺህዎች የሚቆጠሩ ቻይናውያን፣ መንግስታቸው ለጥያቄዎቻቸው ተገቢውን ምላሽ እንዲሰጣቸው በሰላማዊ መንገድ ያሰማሳለስ መጠየቁን ቀጠሉበት፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ የተካሄደውን የረሃብ አድማ የተቀላቀሉት ሰዎች ብዛት በጊዜ ሂደት በሙቶዎች የሚቆጠሩ ሆኑ፡፡ የንቅናቄውን መንፈስ ከደገፉት መካከል ፖሊሶች፣ ወታደሮች፣ እንዲሁም በርካታ ጄኔራሎች ይገኙባቸው ነበር፡፡ መንግስት እንቅስቃሴውን ባለበት ለመግታት የላካቸው የመጀመሪያዎቹ ወታደሮች፣ በሠላማዊ ሠልፈኞቹ መካከል አቀባበል፣ ስጦታና ቅንነት የተሞላው መንፈስ ተንበረከኩ፡፡ ሊገድሏቸው የተላኩት፣ ተቀላቀሏቸው፡፡

ይህንንም ተከትሎ የመንግስት ትላልቅ ባለስልጣናት ከተማሪዎቹ ጋር በቴሌቪዥን አማካኝነት የተሰራጨ ውይይት አካሄደው ነበር፡፡ ዳሩ ግን፣ ንቅናቄው ከቁጥጥር ውጭ በሆነ መልኩ ወደ ሌሎች ከተሞች መዛመቱን ያጤነው በሀሳብ የተከፋፈለውና ግራ የተጋባው የቻይና መንግስት፣ በርዕሰ ከተማዋ የሚገኙትን ወታደሮች፣ ትዕዛዝ ከመቀበልና ጭካኔ የተመላበትን ኃይል ከመጠቀም ወደኋላ እንደማይሉ ባመነባቸው የሰሜን ቻይና ወታደር ተካቸው፡፡ በዚህም መሰረት፣ ሰኔ 4 ቀን በቲያናንሜን አደባባይ የተፈፀመው ጭፍጨፋ፣ በቻይና ውስጥ የተቀጣጠለውን ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ አጨናግፎታል፡፡

የቻይና መንግስት፣ የቲቤትን ህዝብ ዴሞክራሲያዊ መብቶች ጭካኔ በተሞላው መልኩ ለመጨፍለቅም ሞክሯል፡፡ በስደት የሚገኙት የቲቤታዊያን መሪና የ1989 (እ.ኤ.አ.) የኖቤል የሠላም ተሸላሚው፣ ዳላይ ላማ፣ ህዝባቸው ለነፃነቱ በሚያደርገው ትግል ሠላማዊ ዘዴዎችን ከመጠቀም ለአፍታም እንኳን እንዳይቆጠብ ዘወትር ጥሪያቸውን እንዳስተላለፉ ነው፡፡ እንደዳላይ ላማ ዕምነት፣ እነኝህ ጥረቶች በቲያናንሜን አደባባይ የታፈነውን የቻይናውያንን ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ የሚያስተጋቡ ናቸው፡፡ ዳላይ ላማው እንደሚሉት፣ የ«ሠላማዊ ዓመፅ»ን መንገድ





መከተሉ፣ በአሁኑ ወቅት ሊታሰቡ የማይችሉ ፖለቲካዊ መብቶችን በጊዜ ሂደት ከቻይና መንግስት መዳፍ ፈልቅቆ ለመውሰድ ያበቃል፡፡ ለጊዜው ግን፣ ህዝባዊ እምቢተኝነት በቻይና አልሰራም፡፡ እምባገነኖች ተደላድለው እየኖሩባት ነው፡፡

## በርማ

ቻይና ውስጥ የታየው ዓይነት ንቅናቄ እ.ኤ.አ. በ1988 በርማ ውስጥም ተንፀባርቋል፡፡ በርዕሰ ከተማዋ፣ ራንጉን፣ በዚሁ ዓመት በጋ ወቅት ጨቋኙን ወታደራዊ አገዛዝ በመቃወም፣ ተማሪዎች የህዝባዊ እምቢተኝነት ንቅናቄ ጀምረው ነበር፡፡ ተማሪዎቹ የጀመሯቸው ሰላማዊ ሰልፎች፣ የተለያዩ ሙያተኞች፣ የንውስ ከበርቴው መደብ አባላትና ሰራተኞች ተቀላቅለዋቸዋል፡፡

በዚህ የተጋጋለና ግርግር በበዛበት ወቅት፣ አንግሳን ሱኡ ክዩ በአጭር ጊዜ ውስጥ ታዋቂነትን አግኝታለች፡፡ የዘመናዊት በርማ አባት፣ አንግሳን፣ ልጅ የሆነችው አንግ ሳን፣ ከአንድ የኦክስፎርድ ፕሮፌሰር ጋር ትዳር መስርታ ኑሮዋን እንግሊዝ ውስጥ አድርጋ ነበር፡፡ ዳሩ ግን፣ በእናቷ በፅኑ መታመም ምክንያት ከባህር ማዶ ወደ ራንጉን በተመለሰች ማግስት በዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ ልትሳብ ችላለች፡፡ በዚህም መሰረት፣ ሊተኩሱባት በተዘጋጁ ወታደሮች መሃል ሰንጥቃ እስከማለፍ የደረሰ አስተዋፅኦ ለትግሉ አበርክታለች፡፡

በዴሞክራሲያዊው ንቅናቄ ስልጣናቸው ስጋት ውስጥ መግባቱን የተረዱት መሪዎች፣ ደም አፋሳሽ እርምጃ ለመውሰድ ከውሳኔ ላይ ደረሱ፡፡ በዚህም መሰረት፣ በሺህዎች የሚቆጠሩ ያልታጠቁ ዜጎች ሲገደሉ፣ ሌሎች በርካቶች ደግሞ ወደ ጫካዎቹ ገብተው ተሸሸጉ፡፡

የሆኖ ሆኖ፣ በግንቦት 1990 ያለወታደራዊው አገዛዝ ፍላጎት በተካሄደው ብሄራዊ ምርጫ፣ ህዝቡ ድምፁን በብዛት የሰጠው ከጥቂት

ወራት በፊት በቁም እስር በዋለችው አንግሳን ሱኡ ከዩ ለሚመራው የዴሞክራሲ ብሄራዊ ሊግ ፓርቲ ነበር፡፡ ወታደራዊው መንግስት ግን፣ የምርጫውን ውጤት ውድቅ በማድረግና አንግ ሳን ለአምስት ዓመታት በቁም እስር በማቆየት ሀገሪቷን መግዛቱን ቀጠለ፡፡ የ1991 የኖቤል የሰላም ተሸላሚዋ አንግ ሳን፣ ቆራጥነቷና የመንፈስ ጥንካሬዋ በርማውያን ለነፃነታቸው በሚያደርጉት ሰላማዊ ትግል የጥንካሬ፣ የብርታትና የወኔ ምንጭ ሆኗቸዋል፡፡ እስከአሁን ባለው ሁኔታ ግን፣ በበርማም፣ ህዝባዊ እምቢተኝነት አልሰራም ማለት ይቻላል፡፡ ወታደራዊው መንግሥት አሁንም ስልጣን ላይ ነው፤ እድሜ ለቻይና ድጋፍ፡፡

የመካከለኛው ምስራቅ የሠላም ሂደት ከመጀመሩ ትንሽ ቀደም ብሎ በፍልስጤማውያንና በእስራኤላውያን መካከል ያለው ግጭት ከእውነታው ያፈነገጠ ምስል ይሰጠው ነበር፤ ለዚህም ትልቁን አስተዋፅኦ ያበረከቱት የዜና አውታሮች ናቸው፡፡ ዳሩ ግን፣ ከ1967 (እ.ኤ.አ.) ወዲህ፣ የፍልስጤማውያን ትግል ሁለት ገፅታዎች ነበሩት፤ እነሱም የትጥቅና ሠላማዊ ትግሎች ነበሩ፡፡ «ኢንቲፋዳ» የሚል መጠሪያ የተሰጠው ሠላማዊ ትግል በመላው ዓለም ዝነኛ ሆኗል፡፡ «ኢንቲፋዳ» ከዚህ ቀጥሎ የሠፈሩትን የህዝባዊ እምቢተኝነት ስልቶችን ያካተተ ሁሉን አቀፍ ንቅናቄ ነበር፡፡ ከእነዚህም መካከል፦

* የእስራኤል ፖሊሲዎችና አሰራሮች በመቃወም፣ ትምህርት ቤቶችና የንግድ ተቋማት ያካሄዷቸው የስራ ማቆም አድማዎች
* እስራኤልና ፍልስጤሞችን በሚያከራክሩ መሬቶች ላይ፣ የእርሻ ፕሮጀክቶችን ተግባራዊ ማድረግ
* በትግሉ ሂደት ዘመዶቻቸው የሞቱባቸውን ቤተሰቦችና እስረኞችን የሚጠይቁ ኮሚቴዎች ማቋቋም
* እስራኤል ሠራሽ ምርቶችን አለመግዛት





* መንደርተኞች ያለምንም ተጨባጭ ምክንያት ሲታሰሩ፣ ነዋሪዎቹ ከታሳሪዎቹ ጋር ያላቸውን የትግል አንድነት መንፈስ ለመግለፅ እነሱንም እንዲያስሯቸው ለመጠየቅ ወደ እስር ቤቶች በብዛት መጉረፍ
* ፍልስጤማውያን ራሳቸውን የሚችሉባቸው አማራጭ ተቋማትን መገንባት፡፡

እስራኤላውያኑ ለዚህ ህዝባዊ እምቢተኝነት የሰጡት ምላሽ ጭካኔ የተሞላበት ነበር ለማለት ያስደፍራል፡፡ በፍልስጤማውያን ላይ ከተወሰዱት እርምጃዎች መካከል፣ የሰላማዊ ሰልፈኞችን አጥንት ሆን ብሎ መስበር፣ የተጠርጣሪ ቤተሰቦች መኖሪያ ቤቶችን ማፍረስ፣ የተወሰኑ አካባቢዎች ለወራት እስኪዘልቅ ጊዜ ድረስ በመዝጋት ህዝቡ እንዳይሰራና ወደ ሆስፒታል ሄዶ እንዳይታከም ጭምር መከልከል ይገኙባቸዋል፡፡

ዳሩ ግን፣ የኢንቲፋዳው ፍትሃዊ ጥያቄዎችና የህዝባዊ እምቢተኝነት ስልቶች፣ ለግጭቱ ፍትሃዊና ሠላማዊ መፍትሄ ለማፈላለግ የሚጥሩትን እስራኤላውያን አቋም በማጠናከሩ በኩል ትልቅ አስተዋፅኦ አበርክተዋል፡፡ «ኢንቲፋዳ» በፈጠረው የፖለቲካ ሁኔታ፣ የኖርዌይ መንግስት በ1992 (እ.ኤ.አ.) በፍልስጤማውያንና በእስራኤላውያን መካከል 14 ምስጢራዊ ስብሰባዎች እንዲካሄዱ ሁኔታዎችን ያመቻቸ ሲሆን፤ በቀጣዩ ዓመት፣ ማለትም፣ መስከረም 13/1993 (እ.ኤ.አ.) በዋይት ሃውስ በተደረገ ሥነ-ሥርዓት እስራኤልና ፍልስጤም የሠላም ስምምነት ሊፈራረሙ ችለዋል፡፡

በሁለቱም ወገኖች ዘንድ የተሰለፉ ፅንፈኞች የሰላም ሂደቱን ለማኮላሸት ያልፈነቀሉት ድንጋይ አልነበረም፡፡ የጠቅላይ ሚኒስትር ኢሳቅ ራቢን መገደልና የመንግስታቸው በምርጫው መሸነፍ፣ ለሰላም ሂደቱ ታላቅ እንቅፋት ነበር፡፡ ዳሩ ግን፣ የአሁኑ የእስራኤል ጠቅላይ ሚኒስትር፣ ወግ አጥባቂ አሪየል ሻሮን፣ መንግስታቸው በኃይል ከያዛቸው የጋዛ ሠርጥ

አካባቢዎች ህዝባቸውን በማስወጣት፣ ለፍልስጤማውያን ኢንቲፋዳ ወይም ህዝባዊ እምቢተኝነት መንበርከካቸውን ለዓለማችን ህዝብ በገሃድ አሳይተዋል፡፡

## ቼኮዝሎቫኪያ

በ1968 (እ.ኤ.አ.) «ሰብዓዊነትን የተላበሰ ሶሻሊዝም» ለመፍጠር በቼኮዝሎቫኪያ ውስጥ የተካሄደው ሠላማዊ ንቅናቄ መደምሰስ፣ ከሙኒዝም ለሰላማዊ ለውጥና ለዴሞክራሲያዊ ግልፅነት ያልታደለ ስርዓት መሆኑንና «ሠላማዊ ዓመፅ» የሚሰራው በህንድና በዩ.ኤስ.አሜሪካ እንጂ፣ በኮሙኒስታዊ አገዛዞች ስር አይደለም የሚለውን አቋም ይበልጥ አጠናክሮት ነበር፡፡ ይህ ደግሞ በተራው፣ ለቀዝቃዛው ጦርነት፣ ለኑክሊየር የጦር መሳሪያዎች ባለቤትነት ለሚደረገው ፉክክር፣ እንዲሁም ለሶስተኛው የዓለም ጦርነት ስጋት የበኩሉን አስተዋፅኦ አበርክቷል፡፡

የዋርሶ ቃል ኪዳን ሀገራት ሠራዊት በ1968 (እ.ኤ.አ.) ህዝባዊ እምቢተኝነቱን ለማንበርከክ ወደ ቼኮዝሎቫኪያ ዘልቆ ሲገባ፣ ለጥቂት ቀናት የሚዘልቅ የተበታተነ ተቃውሞ ያጋጥመኛል የሚል ግምት ነበረው፡፡ ዳሩ ግን፣ ቼኮዝላቫኪያን የማንበርከኩ ሂደት ስምንት ወራትን ፈጅቷል፡፡ የቼኮዝሎቫኪያ ግዙፍና የሰለጠነ ሰራዊት ከጦር ሰፈሩ እንዳይወጣ በመታዘዙ፣ ወራሪውን ኃይል የመከተው ሰላማዊ የትግል ስልቶችን ባልተጠበቀ መልኩ የተጠቀመው ሲቪሉ ህዝብ ነበር፡፡ የሀገሪቷ የመንግስት የዜና አውታሮችም «ወረራውን የጋበዙት የቼክ መሪዎች ናቸው» የሚለውን የተዛባ መረጃ ከማሰራጨት ተቆጥበዋል፡፡ ሲቪሉ ህዝብ ከተቀመጠባቸው የህዝባዊ እምቢተኝነት ስልቶች መካከል ቀጣዮቹ ይገኙባቸዋል፡-

* ወራሪውን ኃይል ግራ ለማጋባት የመንገድ ላይ ምልክቶችን መቀያየር

* ታንኮቹ በሚያልፉባቸው ጐዳናዎች መቀመጥ

* በታንኮች ላይ በመውጣት፣ ወታደሮቹን ማነጋገር





* በህቡዕ የሚንቀሳቀሱ ሬዲዮ ጣቢያዎች አማካኝነት ቁልፍ መረጃዎችንና መመሪያዎችን ማስተላለፍ፡፡

ወረራው በመጨረሻ ላይ ቢሳካም፣ ምንም ያልታጠቀ ህዝብ ኃይል እንዳለው የታየበት አጋጣሚ ሆኗል፡፡ ጀግናው የቼኮዝሎቫኪያ ህዝብ ሊከራ ይገባል፡፡

## የቀድሞዋ ሶቪየት ኅብረት

የፕሬዝዳንት ሚካኤል ጐርባቼቭ የ«ግላስኖስት» («ግልፅነት»)፣ «ፔሬስትሮይካ» («የመዋቅር ለውጥ»)፣ እንዲሁም «ዴሞክራትሳትሲያ» («ዴሞክራሲ») ፖሊሲዎችን ተከትሎ የታየው የሶቪየት ኅብረት ህዝብ ተነሳሽነት፣ ለለውጥ ዝግጁ የሆነ ድባብ ለመፍጠር ትልቅ እገዛ አድርጓል፡፡ ቀደም ሲል፣ እንደ አንድሬይ ሳኻሮቭና ዮሌና በነር የመሰሉ የሰብዓዊ መብት ተሟጋቾች፣ ዓለም አቀፋዊ ተቀባይነት ያላቸውን የሰብዓዊ መብት መርሆዎች በሀገሪቱ ውስጥ ተግባራዊ እንዲሆኑ ያላሰለሰ ሠላማዊ ጥረት ሲያደርጉ ቆይተዋል፡፡ ገድላቸው፣ በዓለም ህዝብ ዘንድ ለዘላለም የሚታወስ ነው፡፡ በተለይ የሳኻሮቭ የጐላ ነው፡፡ ከእነኝህ ወገኖች በተጨማሪም፣ ኃይማኖታዊ፣ ሠላም ወዳድና የአካባቢ ጥበቃ ቡድኖች፣ አርቲስቶች፣ እንዲሁም ገጣሚዎች በተለያየ መልኩ ፈላጭ ቆራጩን የኮሙኒስት ሥርዓት በሠላማዊ መንገድ ሲታገሉ ኖረዋል፡፡

የጎርባቼቭን የለውጥ እንቅስቃሴ ተከትሎ በሀገሪቷ ውስጥ የተንሰራፉትን ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚ፣ ፖለቲካዊ፣ ባህላዊ፣ ወዘተ... ችግሮች ማቃለልን ዓላማቸው ያደረጉ በሺህዎች የሚቆጠሩ ቡድኖች፣ በመላው ሀገር ተንቀሳቅሰዋል፡፡ ለአጭር ጊዜ ለውጥም አምጥተዋል፡፡ ለምሳሌ፣ በሐምሌ 1990 (እ.ኤ.አ) 100,000 የሳይቤሪያ የድንጋይ ከሰል ማዕድን ሰራተኞች ያካሄዱት የስራ ማቆም አድማ፣ በአጭር ጊዜ በስተምዕራብ ወደምትገኘው ዩክሬይን ሊዛመት ችሏል፡፡ በመካከላቸው ጠንካራ ዲሲፕሊን የነበረት

እነኚህ የማዕድን ሠራተኞች፣ በከተሞቻቸው የሚገኙትን የመጠጥ ግሮሰሪዎች በመዝጋት፣ ትላልቅ ትዕይንተ-ህዝቦችን አካሂደዋል።

በመላ ሀገሪቷ ዙሪያ በተደረጉት ምርጫዎች የለውጥ አራማጅ ዕጩዎች በሰላማዊ መንገድ ወደ ፖለቲካው መድረክ ብቅ ማለት ጀመሩ። ከ1917 (እ.ኤ.አ) የሩሲያ አብዮት ወዲህ የመጀመሪያው ነፃና ፍትሃዊ ምርጫ በ1989፣ ሲደረግ የኮሙኒስት ፓርቲውን የስልጣን ሞኖፖል በሰበረ መልኩ በዕውነተኛና በትክክለኛ የህዝብ ድምፅ የተመረጡ ሁለት ሺህ ሰዎች የፓርላማ አባል ሆኑ።

## ሊቱዌኒያ

በመጋቢት 11/1990 (እ.ኤ.አ) ሊቱዌኒያ ነፃነቷን ያወጀች የመጀመሪያዋ የሶቪየት ሪፐብሊክ ሆነች። የሶቪየት መንግሥት ግን እውቅና አልሰጥም ብሎ አሻፈረኝ አለ። ቀሪው ዓለምም ነፃዋን ሊትዌኒያን እውቅና ነፈጋት።

የዚህች ሀገር ህዝብ ለዘመናት ያስተናገደውን የሩሲያ የባህል ጫናን በመቃወም፣ የራሱን ባህላዊ ዘፈኖች፣ ክብረ በዓላትን፣ ኃይማኖታዊ ስርዓቶችንና ትውፊቶችን ተግባራዊ ማድረጉን ተያያዘው። የህዝቡን የህዝባዊ እምቢተኝነት ተነሳሽነት ለማበረታታት በሚል፣ «ጋንዲ» የተሰኘው ፊልምም በመላ ሊቱዌኒያ በቴሌቪዥን እንዲሰራጭ ተደርጓል። ሀገሪቷ እንዳይፈረካከስ፣ ማዕከላዊ መንግሥት በሊቱዌኒያ ላይ ማዕቀብ ቢጥልም፣ ውጤት አላመጣም። ከጥቂት ወራት በኋላ፣ ማዕከላዊ መንግስቱ፣ ወታደሮቹን ወደ ርዕሰ ከተማዋ፣ ቪልኒየስ በመላክ፣ የሀገሪቷን የቴሌቪዥን ማማ ከጥቃት ለመከላከል ከተሰለፉት ያልታጠቁ ሰላማዊ ሰልፈኞች መካከል 14ቱን ገድሏል። ሊቱዌኒያ፣ በጦር መሳሪያ የተደገፈ ምላሽ ከመስጠት ይልቅ፣ ዜጎቿ የህዝባዊ እምቢተኝነት ስልቶችን እንዲጠቀሙ አሳሰባለች። ሊቱዌናውያንም ተግባራዊ ያደረጉት ይህንኑ ነበር። ፓርላማቸውን የጦር መሳሪያ ባልታጠቁ ዜጎች ሲያስጠብቁ፣ በበጐ





ፈቃደኝነት ላይ ተመስርቶ የተቋቋመውን የሚሊሺያ ኃይል ደግሞ የህዝባዊ እምቢተኝነት ስልጠና እንዲወስዱ አድርገዋል።

ይህ ፍጥጫ ሳያልቅ፣ እንደ ድንገት ሞስኮ ውስጥ መፈንቅለ መንግስት ይሞከራል። እነኚህ ኃይሎች ጐርባቼቭንና ቤተሰባቸውን በቁጥጥራቸው ስር ቢያውሏቸውም፣ በህዝቡ ዘንድ ከፍተኛ ተቃውሞ ስላጋጠማቸው ግን፣ ያሰቡት ሳይሳካላቸው ቀርቷል። ይህንንም ተከትሎ፣ ሊቱዌኒያንና ሌሎች የባልቲክ ሀገሮች ወደ ነፃነት የሚያደርጉት ጉዞ የተሳካ ሆኗል።

## ማጠቃለያ

የተባበሩት መንግስታት ጠቅላላ ጉባዔ፣ የ21ኛው ምዕተ ዓመት የመጀመሪያው አስርት ዓመት የ«ሠላማዊ ትግል» አስርት ዓመት እንዲሆን፣ በህዳር 1998 በሙሉ ድምፅ ወስኗል። ይህም አካሄድ፣ ሰብዓዊነትን ይዘን ለመዝለቅ መያዝ የሚገባንን እሴት ያስቀመጠልን ነው።



ጋዜጠኛ ተመስገን ደሳለኝ

# ክፍል አምስት
# የሕዳሴው አብዮት





- የ«ቀለም» አብዮት. . .
- «አብዮታዊ ሁኔታ»
- ሠላማዊ ትግል? ወይስ . . .
- ለወጥ ወይ ለሰለባ?
- የሕዳሴ አብዮት!
- የኢትዮጵያ ሕዳሴ
- የ«ሕዳሴ አብዮት» ተዋስኦ
- የሕዳሴው ፊት መሪዎች
- የትግሉ ስልቶች . . .
- የአብዮቱ የመጀመሪያ ጥያቄዎች
- የመኸሩ ወቅት . . .

# ምዕራፍ አንድ

# የ«ቀለም» አብዮት. . .

የቀዝቃዛው ጦርነት ማብቃትን ያበሰረው የጀርመን ግንብ ሊፈርስ ሶስት ዓመታት ብቻ በቀሩበት ከዕለታት በአንዱ ቀን፣ ቅጥ ባጣ አምባ - ገነንነቱ እና ሀገሪቷን የግል ርስቱ በማድረግ የሚታወቀው፣ የፊሊፒንሱ ፕሬዝዳንት ፈርዲናንድ ማርቆስ፣ «ታሪካዊ» የሚባል ትልቅ ስህተትን ፈፀመ፤ ጠንካራ ተፎካካሪው እንደሚሆን ቅድመ -ግምት ተሰጥቶት የነበረውን የተቃዋሚው ቡድን መሪ ካስገደለ ከጥቂት ጊዜያት በኋላ እንዲካሄድ የፈቀደውን የይስሙላ ምርጫ በአሳፋሪ መልኩ አጭበርብሮ አሸናፊነቱን አወጀ፡፡ ይህን ጊዜ የሕዝቡን ትዕግስት መሟጠጥ የተረዱና መነሻቸው ካቶሊክ ቤተ-ክርስቲያን የሆኑ ቁጡ ወጣቶች ድንገት እንደ ደራሽ ውሃ የማኒላ ጎዳናዎችን አጥለቀለቁ፡፡ ከየካቲት 22 እስከ የካቲት 25 ለሶስት ተከታታይ ቀናት ባካሄዱት ሕዝባዊ ንቅናቄም ጡንቸኛውን ማርቆስ ከመንበሩ ፈነቀሉት፡፡ ፊሊፒናውያኑ አመፀኞች፣ በሀገሬው ባህልና ጥንታ ዊ እምነት መሠረት እንቅስቃሴው ሰላማዊ መሆኑን ለመግለፅ ሲሉ በማኒላ አውራ መንገዶች ተቃውሞውን ለማክሸፍ ታንክ ጠምደው ለተሰለፉት ወታደሮች ቢጫ አበባ እየሰጡ ማለፋቸውን ተከትሎ፣ አመፁ «ቢጫ





አብዮት» ለመሰኘት በቃ፡፡ ይህ አዲስ ክስተትም በዳህራዊዎቹ ጥቂት ዓመታት በምስራቅ አውሮፓ ሀገራት ለተቀጣጠሉ አብዮቶች በቀለም መሰየም ታላቅ አብነት ሊሆን መቻሉን በጉዳዩ ዙሪያ የተደረጉ ጥናቶች ያስረዳሉ፡፡ በዚች ክፍለ-አህጉር በ1990ዎቹ ኢጋማሽ የተቀጣጠሉት አብላጫዎቹ ሕዝባዊ አመፆች፣ እንደየሀገራቱ ባሕልና ወግ የተለያዩ ቀለማትን በትዕምርትነት መጠቀም መጀመራቸውም የሚያስረግጠው ይህንኑ እውነታ ነው፡፡

የ2002ቱ የኢራኑ አብዮትም «አረንጓዴ» የሚል ስያሜ ያገኘው፣ የተቃውሞ መሪው ሆሰኒ ሞሳቪ የምርጫ ቅስቀሳ ላይ ከተጠቀመበት ቀለም ተወስዶ ሲሆን፤ የቅርቡ የግብፅ አብዮትም በድሮዋ ፈርኦናዊት ምድር ልማድ መሠረት የትንሳኤ፣ የህይወትና የፀሐይ ተምሳሌት በሆነው «ሎተስ» በተባለ አበባ እንዲሰየም በአብዮተኞቹ ተመርጧል (የድህረ -ሙባረክ ግብፅን ወደጥንት ታላቅነቷ የመመለስ ግብን ይተረጉማል በሚል)፡፡

...ይህ ሁነትም ቀድሞ (አብዛኛውን ጊዜ) በግራ -ዘመሞች (በኮሙኒስቶች) ይመራ የነበረው ጠብ -መንጃ ቅልቅሉ አብዮት ተመራጭነቱ እየደበዘዘ በመሄዱ፣ በአምባ-ገነን ሥርዓታት ላይ የሚነሱ ሠላማዊ የተቃውሞ ንቅናቄዎች ሁሉ በ«ቀለም አብዮት» እየተጠሩ መምጣታቸው የተለመደ ክስተት ለመሆኑ አይነተኛ ማሳያ ነው፡፡

## የቀለም አብዮቶቹ በረከቶች

በምስራቅ አውሮፓ በአድቃቂው የማሕበረ -ሱታፌ (ሶሻሊስት) ሥርዓት ውድቀት ማግስት ብቅ ያሉት መሪዎች ዴሞክራሲያዊ ተቋማትን በመገንባት ሽግግሩን መምራት ባለመቻላቸው እና ነፃ ማሕበረ -ሰብ ለመፍጠር የተነቃቃውን ልሂቅ ህልሞች በኃይል ማጨንገፋቸው፣ የቀለም አብዮቶች አይነተኛ የትግል ምርጫ እንዲሆኑ ማስገደዱን ስለጉዳዩ

የሚያወሱ ድርሳናት ያስረግጣሉ፡፡ በመጨረሻው የኮሙኒዝም መንኮታኮት ዋዜማ እና በዚህ ከፍለ-ዘመን መባቻ ላይ ግዙፎቹን ሥርዓታት ያፈራረሱ ማሕበረ-ሰባዊ መነቃቃቶች (አብዮቶች) ከኮሙኒዝም ወደ ዲሞክራሲያዊ አስተዳደር መሸጋገርን ዋነኛ ዓላማ ከማድረጋቸው በተጨማሪ፣ ባተገባበር የጋራ መለዮ እንዳላቸው ይታወቃል፡፡ በተለይ በአደባባይ ድንኳን ዘርግቶ ለሳምንታት ወይ ለወራት በመቀመጥ፤ አሊያም ለተከታታይ ቀናት ሠላማዊ ሰልፎችንና የሥራ ማቆም አድማዎችን በመምታት መንግስታዊ ተቋማትን የሚያሽመደምዱበት ስልት… ለተመሳሰሏቸው ግንባር-ቀደም ተጠቃሽ መገለጫዎች ተደርገው ይወሰዳሉ፤ አብዛኛዎቹ የምርጫ መጭበርበርን ተከትለው የሚቀጣጠሉ አብዮቶች መሆናቸውም ይበልጥ ያመሳስላቸዋል፡፡ ለዚህም ከፊሊፒንሱ «ቢጫ አብዮት» እስከ የጆርጂያው «ፅጌረዳ»፤ ከካዛኪስታኑ «ሮዝ» እስከ የዩክሬኑ «ብርቱካንማ አብዮት» ድረስ የተመለከትናቸው የአደባባይ ተቃውሞዎች በድህረ-ምርጫ ወቅት መቀስቀሳቸውን ማስታወሱ በቂ ነው፡፡ እንዲሁም ንቅናቄዎቹ በሙሉ በሲቪል ድርጅቶች አሊያም በወጣቶች ስብስብ መመራታቸው ሌላው የወል ባህሪያቸው ነው ማለት ይቻላል፡፡

በጥቅሉ ባለፉት አስር ዓመታት ያየናቸው የቀለም አብዮቶች በዋናነት በመንገዱ ነፍስ-አባት ጂን ሻርፐ ‹ቅዱሳን› መፃህፍት የተቃኙ ሲሆኑ፤ በተለይም የአንሳንሱኪን ረዥም እስር ላስከተለው ለ1985ቱ የበርማ እንቅስቃሴ የጻፈው «ከአምባገነንነት ወደ ዴሞክራሲ» የተሰኘ ስራው፣ ለታህሪር ወጣቶች ጭምር በመመሪያነት ማገልገሉ ይታወሳል፡፡ የዚህ የ86 ዓመቱ አዛውንት ጸሐፊ ዋነኛ ጭብጥ *«ገዢዎች የሚሰነብቱት ሕዝብ እስከፈቀደ ድረስ ብቻ ነው፡፡ ዜጎች የመገዛት ፈቃዳቸው ቀስ በቀስ እየቀነሰ ከሄደ አምባ-ገነኖቹ መውደቃቸው አይቀርም፡፡ ይህንንም ለማድረግ እነርሱ የሚያሸንፉበትን የብረት ትግል ከመምረጥ ይልቅ፣ ሠላማዊ ሕዝባዊ አምቢተኝነት ብቸኛው መንገድ ነው»* የሚል መሆኑ ለተቀባይነቱ አስተዋፅኦ ያደረገለት ይመስለኛል፡፡





በሌላ በኩል የቼኮዝሎቫኪያው የ«ቬልቬት» (ጆንትል) እና የዩጎዝላቪያው «ቡልዶዘር» አብዮቶች በስኬታማነት ለመጠቀስ የሚበቁ ናቸው፡፡ በህዳር ወር 1981 ዓ.ም የተከበረውን አለም አቀፍ የተማሪዎች ቀን አስመልክቶ ፕራግ ከተማ በተሰባሰቡት ተማሪዎች ላይ ፖሊስ የወሰደው የኃይል ጭፍለቃ ያስቆጣቸው ግማሽ ሚሊየን ዜጎች ወደ መዲናይቱ አደባባይ በመትመም ያካሄዱት «የፕራግ ፀደይ» የተሰኘ ሕዝባዊ ዓመፅ፣ ኮሙኒስት ሥርዓቱን ያንኮታኮተው በቀናት ልዩነት ውስጥ ነበር፡፡ በርግጥ ለዚህ ዓመፅ መነሳሳት፣ አብዮቱን እንዲመራ ከቤቱ የተጠራው ቫክላቭ ሆቬልና ጓዶች አቋቁመውት የነበረው «ቻርተር 77» የተሰኘው የሙብት ተሟጋች ሲቪክ ማሕበር የፊት-አውራሪነቱን ይወስዳል፡፡ ብዙዎቹ አባላቱም ሀገሪቱ ቼክ እና ስሎቫክ ተብላ ለሁለት ከተከፈለች በኋላም በፖለቲካ ውስጥ ወሳኝ ሚና እንደነበራቸው ይታወሳል፡፡ ሌላኛው «አትፖር» በተሰኘ የወጣቶች ንቅናቄ ተመርቶ አምባ-ገነኑን ስሎዶቫን ሚሎሶቪችን መፈንቀል የቻለው የ«ቡልዶዘር አብዮት» የተሰኘው ሕዝባዊ አመፅም፣ በሠላማዊነቱና በመልካም ምሳሌነቱ ከቀለም አብዮቶቹ ጋር አብሮ ይዘከራል፡፡ ይህን መሰሉን የአብዮት ቅርፅ በኢትዮጵያ አውድ ለመፈተሽ፣ እሱ የምንላቸውን ገፊ አብዮታዊ ሁኔታዎችን እና የስርዓቱ የማይፈቱ ጉድለቶችን አስ ተሳስረን መዳሰስ ይኖርብናል፡፡

የማሻገሩን አበርክቶ መዘንጋት የለብንም፡፡ የየካቲቱ አብዮት እንደ ፕሮፌሰር ባሕሩ ዘውዴ አገላለፅ ‹በደስታና በተስፋ ተጀምሮ፤ በሰቆቃና በፀፀት ቢደመደምም› ከ66 እስከ 68 ዓ.ም መጨረሻ ድረስ ፈጥሮት የነበረው የአደባባይ ውይይትና የማሕበረ-ሰቡ የነቃ ተሳትፎ ለዚህ ጭብጥ ሁነኛ ማሳያ መሆን ይችላል፡፡

በኢህአዴግ ኢትዮጵያ የአብዮትን አስፈላጊነት ጠቅሶ አስተያየት መስጠቱ የሥርዓቱ አገልጋዮችን ብቻ ሳይሆን፣ ለውጥ ፈላጊውንም ሲያስበረግገው (አልፎ አልፎም እንደ እርስ-በእርስ ግጭት ናፋቂ ቆጥሮ እስከማውገዝ ሲያደርሰው) መስተዋሉ የተለመደ ሆኗል፡፡ ይህ ግን ታላቅ ስህተት ይመስለኛል፡፡ በምስራቅ አውሮፓም ሆነ በሰሜን አፍሪካ አገራት የተከሰቱት የዘመኑ አብዮቶች መነሻቸው አማራጭ ማጣት እንጂ፤ አብሪት በወጠራቸው አሊያም የሥልጣን ጥማት ባከለፈለፋቸው ግለሰቦች ገፋፊነት የተካሄዱ አለመሆናቸውን ራሳቸው የንቅናቄው ሰለባዎችም የሚክዱት አይደለም፡፡

የሆነው ሆኖ የሩሲያ አብዮት መሪ ቪላድሚር ኤሊች ሌኒን፣ የጉልበት አገዛዝ እንደቀድሞው በጭፍሊቃ መቀጠል አለመቻሉ በአንድ በኩል፤ ተጨቋኞች ለተቃውሞ ማጉረምረማቸው በሌላ በኩል በተመሳሳይ ወቅት መከሰትን «አብዮታዊ ሁኔታ» ሲል ይገልፀው እንደነበረ ይታወሳል፡፡ ይህ የጉምቱ አብዮተኛ ድምዳሜም የዛሬይቱ ኢትዮጵያን ወቅታዊ ገፅታ በሚገባ የሚወክል መሆኑን እንደሚከተለው በማስረጃ አስደግፌ ለማተት እሞክራለሁ፡፡

## «አብዮታዊ ሁኔታ»

በኢትዮጵያችን ከ66ቱ እና 83ቱ ቀጥሎ ሦስተኛው አብዮት አይቀሬ የሚሆንበት ምክንያት በሁለት ተከፍሎ የሚታይ ሲሆን፤ ይኸውም ሕዝባዊ ቁጣ ቀስቃሽ ኩነቶች እና አማራጭ መንገዶች መዘጋት በተመሳሳይ





ወቅት መከሰት የሚል ነው፡፡ እነዚህን ሁለት አንጓ ጉዳዮችም በአዲስ መስመር ነጣጥለን፣ ተንትነን እንያቸው፡፡

የመጀመሪያው «ቁጣ ቀስቃሽ ኩነቶች» በሚል የጠቀስኩት ከሞላ ጎደል በሚከተሉት ችግሮች ይገለጣል፡- ሥርዓቱ ከእነአስከፊ አምባ-ገነን ባህሪው ከሁለት አስርታት በላይ በስልጣን መቆየቱ የፈጠረው መሰላቸት፣ ቅጥ ያጣው መንግስታዊው ሙስና፣ ስልታዊ የሙበት ጭፍሊቃ መረብ መዘርጋት፣ የመናገርና የመደራጀት ዲሞክራሲያዊ መብቶችን በ«ሕግ» ስም ማፈን፣ የዋጋ ንረትና የሥራ-አጥ ቁጥር በአስደንጋጭ ሁኔታ ማሻቀብ (በተለይም ከትምህርት ተቋማት ተመርቀው ለሚወጡት ወጣቶች ሥራ-አጥነት ብቸኛው ተጠያቂ ገዢው-ፓርቲ መሆኑ)፣ በአገሪቱ አስከፊ ድህነት መንሰራፋቱ፣ የፍትሕ እጦት፣ የፕሬስ አፈና እየከፋ መምጣቱ (እንደ «ፍትህ»፣ «ፍኖተ ነፃነት»፣ «ልዕልና»፣ «ሰለፊያ» ጋዜጦች፤ እንዲሁም «አዲስ ታይምስ» እና «የሙስሊሞች ጉዳይ» ያሉ መጽሔቶችን በኃይል ወደመዝጋት ከመሻገር አልፎ ተርፎ ማሕበራዊ ድረ-ገፆች፣ የአሜሪካ እና የጀርመን ድምፅ የሬዲዮ ስርጭት፣ አልጀዚራ እና ኢሳትን የመሳሰሉ ሚዲያዎችን «ሽብር ቀስቃሽ» በሚል ውንጀላ ለማፈን በሙቶ ሚሊዮን ዶላር የሚቆጠር የድሀ ሕዝብ ሃብት ማባከኑ)፣ በተለያዩ ከተሞች የታየው የዜጎች ከርስት መፈናቀል፣ የመሬት ቅርምት፣ እያቆጠቆጠ የነበረው የብዙሃን ፓርቲ ሥርዓት በ2002ቱ ምርጫ በአውራ ፓርቲ መጠቅለሉ፣ የሲቪክና ሙያ ማሕበራት ከተፅእኖ መላቀቅ አለመቻል፣ የጭቁኑ ወታደር ኑሮ ከእጅ ወደአፍ መሆን፣ የአርሶ-አደሩም ሆነ የከተሜው ሕይወት አለመለወጥ፣ የብሔር ጥያቄ ከሽፈት ከእርስ በእርስ ፍጥጫ ተሻግሮ በተለያዩ ክልሎች የዘውጉ ቋንቋ ተናጋሪ ያልሆኑ ዜጎች መፈናቀል ማስከተሉ፣ ሕዝብን ከድህነት የሚታደግ የኢኮኖሚ እድገት አለመታየቱ፣ በሠላማዊና ሕጋዊ መንገድ ፍትሃዊ ጥያቄዎቻቸውን ባቀረቡ የእስልምና እምነት ተከታዮች ላይ በአርሲ፣ በወሎ፣ በአዲስ አበባና በመሳሰሉት አካባቢዎች በፀጥታ ኃይሎች የተፈፀመው ግድያ እና የጅምላ እስር፣ ማሕበረ ቅዱሳንን ለማፍረስ

በሰብዓዊ መብቶች ላይ የሚሰሩትን መያዶች «የኒዮ ሊበራሊዝም እግረኛ ወታደሮችና ተለዋጭ ተቃዋሚዎች» ሲል መኮነኑ፣ የአዋጁን በጆሮ አስረግጦ ይናገራል፡፡ እናም «ሊበሏት ያሰቧትን አሞራ...» ካልሆነ በቀር፣ ኢህአዴግ አለቅጥ እግንና ሀገር-ምድሩን በደም የሚያጨቀይ «ጭራቅ» አስመስሎ ፍርሃት ለማንበር እየሞከረበት ያለው «የቀለም አብዮት» የራሱ ንድፈ-ሃሳብ የሌለው፣ ሠይፍ የማያማዝዝ፣ ፍፁም ሠላማዊ መሆኑ ከቶም ቢሆን ሊጠፋው እንደማይችል በግልፅ ይታወቃል፡፡

አገዛዙ ‹መሰል አብዮት በዚህች አገር እንዳይቀሰቀስ› በሚል ስጋት እንቅልፍ አጥቶ ሲባንን የሚያድረው እና የለውጥ መንገዶችን በጠቅላላ ለመዝጋት ሌት ተቀን የሚዳክረው፣ የአረቡ «ፀደይ» መነቃቃት የጨቋኞቹን የሰሜን አፍሪካ መሪዎች መንበር በጥቂት ቀናት ውስጥ መገልበጡ የፈጠረበት ድንጋጤ ስለመሆኑ በርካታ ማሳያዎች አሉ፡፡ በወቅቱ ነፍሱን ይማረውና መለስ ዜናዊ በአደባባይ «ሕዝቡ ያምፃል ብለን ሳንተኛ አናድርም» ሲል ለማስተባበል ቢሞክርም፤ በጥቂት ወራት ውስጥ ብቻ በርካታ የተቃዋሚ ፓርቲ አባላትን፣ ጋዜጠኞችን፣ የሙብት ተሟጋቾችን (አክቲቪስቶችን)... በዚሁ ጉዳይ ወንጅሎ እስር ቤት መክተቱ የንግግሩን አራምባ-ቆቦነት ያስረገጠ እርምጃ ነበር፡፡

በተጨማሪም የፓርቲው የግል ፕሮፓጋንዳ ማሰራጫ ልሳን እንዲሆን በተፈረደበት የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ጣቢያ ባለፉት ሶስትና አራት ዓመታት ብቻ በተለያዩ ሀገራት የተካሄዱ አብዮቶች አሉታዊ ጎን ላይ ያተኮሩ ዘገባዊ (ዶክመንተሪ) ፊልሞች እና «የሕትመት ዳሰሳ» በተሰኘ ፕሮግራሙ እየደጋገመ በማቅረብ አታክቶናል፤ ለወደፊቱም ይበልጥ እስኪያንገሽግሽን ገና ያታክተናል፡፡ በእነዚህ ፊልሞች እና ዝግጅቶች የአረቡ «ፀደይ»ንም ሆነ «የቀለም አብዮት»ን ደም አፋሳሽነት እየተደነቃቀፉ ብሔራዊ ፍርሃትን ለማንበር ከሞከሩ ዙምቢ «ተንታኞች» እና «ጋዜጠኞች» ድረስ ተሳታፊ ቢሆኑም፤ በስማ በለው የሰሜን አፍሪካውያንን ለውጥ መሻት እና የዩክሬንን





ሕዝብ አደባባይ መውጣት «ፍሪደም ሃውስ»ን ከመሳሰሉ ዓለም አቀፍ ተቋማት ጋር ደርበው ከመርገም ያለፈ ተጨባጩን የሀገራችንን እውነታ የሚያስረግጥ እንዳች ሊያሳምን የሚችል ፍሬ ያለው ነገር ሲናገሩ አልተደመጡም፡፡ ከዚሁ ጎን ለጎንም «ሚሊየነር ገበሬዎችን አፈራሁ»፣ «የምርጫ ሥርዓት ገነባሁ»፣ «ለአስራ አንድ ተከታታይ ዓመታት ከ10 በመቶ በላይ ዓመታዊ የኢኮኖሚ እድገት አስገኘሁ»፣ «የብሔር ብሔረሰቦችን መብት እስከ መገንጠል አስከበርኩ»፣ «ቀለበት መንገድ ሰራሁ»፣ «አባይን ልገድብ ነው»... ጂኒ ቁልቋል የሚለው ተራ ፕሮፓጋንዳ መልሰው መላልሰው በማስተጋባት የለውጥ መንፈሱን ለማጠልሸት የሄዱበት ርቀትም መልሶ ራሳቸውን ለትዝብትና ሀፍረት የዳረገ ይመስለኛል፡፡

በርግጥም የድህረ-መለሱ ኢህአዴግ የፖለቲካ ማሻሻያ ከማድረግ፤ በመከላከያ ሠራዊቱ፣ በፌደራል ፖሊስ እና በደህንነት ሰራተኞቹ ደፍጣጭነት መተማመንን መርጦ፤ ‹ነገም ዝምታው እንዳረበበ፣ አደባባዩም የፀጥታ ዳዋ እንደወረሰው፣ የእኛም መንበረ-ሥልጣን እንደተረጋጋ መሽቶ ይነጋል› በሚል ቀቢፀ-ተስፋ ተወስዷል፡፡ ይህም ታሪክ ራሷ በተቃራኒው ቆማ የሦስተኛው አብዮት ሰለባ እንዲሆን ለመበየኗ አመላካች ነው ብዬ አምናለሁ፡፡

በመዲናይቱ የተከሰተው ሕዝባዊ ንቅናቄ ምን ያህል የሚይዝ የሚጨብጠውን አሳጥቶት እንደነበረ ለመረዳት፣ በማግስቱ እስመሳይ ባህሪውን ባጋለጠ መልኩ በሃያና ሰላሳ ሺዎች የሚቆጠሩ የከተማይቱን ነሪዎች (አብዛኞቹ በተቃውሞው ያልተሳተፉ) ከየቤታቸው እንዴት አፋፍሶ ለግፍ እስር እንደዳረጋቸው ማስታወሱ በቂ ነው፡፡ በወቅቱ ከስተቱ አገሪቱን ለሁለት ቀናት መንግስት-አልባ አስመስሏት እንደነበረ በተሳታፊነትም በታዛቢነትም ሁኔታውን የተከታተልን ዜጎች ሁሉ አንዘነጋውም፡፡

፪

በ1995 ዓ.ም የሲዳማ ተወላጆች፣ ክልላዊነትን እና የሀዋሳ ከተማ ዕጣ-ፈንታን በሚመለከት ጥያቄ አንስተው በደቡብ ክልል ርዕሰ-መዲና ለተቃውሞ አደባባይ የወጡ ጊዜም፣ አብዮታዊ-ግንባሩ ምን ያህል ፈታኝ ሁኔታ ውስጥ ወድቆ እንደነበረ ማስታወሱ ለዛሬው ጠ/ሚኒስትርም ሆነ ለብዙዎቻችን የሚከብድ አይሆንም፤ ሥርዓቱ ያዘመታቸው የመከላከያና የፌደራል ፖሊስ ሠራዊት አባላት ሕጋዊውን የሲዳማ ተወላጆች ጥያቄ ለመቀልበስ፣ ጎዳናዎቹን በደም-አበላ በማጥለቅለቅ የፈፀሙት አሳዛኝ የጅምላ ጭፍጨፋ (ዘር ማጥፋት) በታሪክ መዝገብ ጥቁር ገፅ ላይ በማይፋቅ መልኩ ተከትቧል፡፡ ይህም ሆኖ የዚያ ሠላማዊ ተቃውሞ ውጤት፣ ለፌደራል መንግስቱ፣ ክልሉን በኃላፊነት ሲመራ የነበረውን ኃይለማርያም ደሳለኝን፣ በሽፈራው ሽጉጤ እንዲተካ ያስገደደ የሽንፈት ፅዋ አስጎንጭቶ አልፏል፡፡

፫

በምርጫ 97 ዋዜማ ሚያዝያ 30 «ዴሞክራሲን እናወድስ» በሚል መሪሕ-ቃል «ቅንጅት» በጠራው ስብሰባ ላይ ተገኝቶ መስቀል አደባባይን ያጥለቀለቀው የሕዝብ «ሱናሚ»፣ ሥርዓቱን ለከባድ ድንጋጤ አጋልጦ፣ በሀፍረት አኮራምቶ፣ ለከፋ ሰቃይ ዳርጎት እንደነበረስ ከቶ ማን ሊዘነጋ ው





ይቻለዋል? ያኔ የተመለከትነው ገዥው-ፓርቲን ከፍተኛ ስጋት ላይ የጣለ አስደንጋጭ ትዕይንት፣ ዛሬም ድረስ ለሚተገብረው የቅድመ-ምርጫ አደን መስዋዕት እየዳረገን እንደሆነ ሁላችንንም የሚያስማማ እውነታ ነው (በዕለቱ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ‹ምናልባት ሕዝቡ ከአደባባዩ መልስ በቁጣ ገንፍሎ የቤተ-መንግስቱን አጥር ገርስሶ ሊገባ ይችል ይሆናል› በሚል ፍርሃት ከእነ ቤተሰቡ ደብረዘይት አየር ኃይል ግቢ ተሸሽጎ አሳልፏል የሚለው ወሬ ከሹክሹክታም በዘለለ በከተማዋ በስፋት ተናፍሶ ነበር)፡፡

፬

ሕዝበ-ሙስሊሙ ከ2004 ዓ.ም ወርሃ ታሕሳስ ጀምሮ እያቀጣጠለው ያለው የተቃውሞ ትግልም፣ አገዛዙን ምን ያህል በፍርሃት እንዳራደው ለመረዳት በጉዳዩ ዙሪያ በየጊዜው የሚወጡ እርስ-በርስ የተምታቱ መግለጫዎችን እና በረብ-የለሽ «ዘጋቢ» ፊልሞቹ በሀሰት ለመወንጀል የሄደበትን ርቀት መመልከቱ በቂ ነው፡፡ ይህንን ፍፁም ሠላማዊና ስልጡን የተቃውሞ ንቅናቄን ለማፈን የተወሰዱት የኃይል እርምጃዎችም፣ የእነ አባይ ፀሀዬን የይስሙላ ዲሞክራሲያዊ ባህሪ ለዓለም አቀፉ ማሕበረ-ሰብ ከማጋለጡ ባለፈ፣ ድርጅታቸው-ኢህአዴግን ለሳልሳዊ የውስጥ ክፍፍል መዳረጉን የመረጃ ምንጮች ያወሳሉ፡፡

## ስለምን ነፍጥ አናነሳም?

ከላይ ይህ ሥርዓት ለሕዝብ ፍላጎት እንዲገዛ ሊገደድ የሚችለው በሠላማዊ ትግል ብቻ እንደሆነ በማሳያዎች ለማስረገጥ ሞክሬያ ለሁ፡፡ በዚህ ንዑስ-ርዕስ ደግሞ ብረት የማንሳትን ተገቢነት የሚያቀነቅኑ ልሂቃን፣ ለትግሉ ስልት አግባብነት የሚያነሷቸውን መከራከሪያዎች በሁለት መልኩ እናያቸዋለን፡-

በቀዳሚነት ከገዥው-ፓርቲ ተፈጥሯዊ ባህሪ ጋር እያይዘው፣ ለአቻቻይ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ የሚያስፈልጉ ባህሪያት በፍፁም

ሲጠበቅ፤ ዋና ፀሀፊው ሌንጮ ለታ እና የተወሰኑ መሪዎቹ በቦሌ በኩል በመመለስ «ወይ እኛንም አብራችሁ እሰሩን፤ አሊያም ጓደኞችንን መልሱልን?» በማለት ከመረጡት የኃይል ትግል ጋር የማይጣጣም ስል ት ተግብረው አረፉት፤ በዚህም የልብ ልብ የተሰማው ኢሀአዴግ፣ የድርጅቱን አባላትም ሆነ አሮምኛ ተናጋሪውን በጅምላ በ«ስመ ኦነግ» እየወነጀለ ለአስከፊ እስር መዳረጉ፣ በክልሉ ላይ ከባድ ፍርሃት አነበረ፡፡ ይህ ፖለቲካዊ ስህተትም ለዛሬው ሽንፈቱ ዋነኛ ተጠቃሽ ሲሆን፤ የተቃውሞ ጎራ ትግሉንም ከሥርዓት ለውጥ ወደ አስረኛ ማስፈታት ያወረደ ቀዳሚ ኩነት ሆኖ በታሪክ ተከትቧል፡፡

## መኢሕድ

የፐ/ር አስራት ወልደየስ «የመላው አማራ ሕዝብ ድርጅት» (መአሕድ) ከሽፈትም ከኦነግ ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ መአሕድ በምስረታው ማግስት ያገኘው መጠነ-ሰፊ የሕዝብ ድጋፍ፣ ህወሓት/ኢሀአዴግ በ17 ዓመታት ከሰበሰበው ሁሉ ይልቅ እንደነበረ አይዘነጋም፡፡ ይህ አይነቱ ፈጣን ግስጋሴም ሊያስከትለው የሚችለውን የቁጣ ናዳ አስቀድሞ የተረዳው «ብልጣ-ብልጡ» ኢሀአዴግ፣ ሊቀ-መንበሩን ጉምቱ የሕክምና ሊቅ ጨምሮ ጥቂት የአመራር አባላቱን እስር ቤት ወረወረ፡፡ ከዚያማ ድርጅቱ «ኢታገልለታለሁ» የሚለውን የፖለቲካ ሥልጣን የመቆጣጠር ዓላማውን «መሪዎቻችን ይፈቱ!» ወደሚል አኮስሶ ባለበት ሲረግጥና ሲዳክር ለ13 ዓመታት ከቆየ በኋላ፣ በስተመጨረሻ ህላዌነቱ አከትሞ ወደ ሕብረ -ብሔር (መኢአድ) ድርጅትነት መሸጋገሩ ታወጀ፡፡ ከስተቱም አብዮታዊው ግንባሩ የተቃውሞ ጎራውን እንቅስቃሴ ወደፈለገው አቅጣጫ መዘወሩን (ማስቀየስ መቻሉን) በሚገባ እንደተካነበት ያስረገጠ ሆኖ አልፏል፡፡

## ቅንጅት

ዛሬ ዛሬ እንደ ንግስተ ሳባ ዘመን የሩቅ ጊዜ ታሪክ ያህል ይሰማኝ የጀመረው ምርጫ 97ም ሌላኛው የነገረ -አውዱ አስረጂ መሆን ይችላል፡፡





በተመሰረተ ጥቂት ወራት ውስጥ ከጫፍ ጫፍ ሀገራዊ ንቅናቄ መፍጠር የቻለው ግዙፉ ቅንጅት በአብዛኞቹ የምርጫ ጣቢያዎች አሸናፊ መሆኑ በተለያዩ አጣሪ አካላት በመረጋገጡ፤ የኢሀአዴግን «መንግስት ለመመስረት የሚያስችለኝ ድምፅ አግኝቻለሁ» ጨዋታን ከውስጥም ከውጭም አምኖ የተቀበለ አንድም እንኳ አልነበረም፡፡ በአዲስ አበባ አንዳንድ አካባቢዎች ይህንን ዓይን ያወጣ ስርቆት በሠላማዊ መንገድ ለመቃወም በሞከሩ ዜጎች ላይ በተወሰደው ርህራሄ አልባ የኃይል እርምጃ በርካታ ንፁሃን ለህልፈት እና ለአካል ጉዳት ሲዳረጉ፣ በተወሰኑ የክልል ከተሞች ደግሞ ከፍተኛ ሕዝባዊ ማጉረምረም መፈጠሩ አይዘነጋም፡፡ ግና፣ «ብልሆቹ» የኢሀአዴግ «ሌጊስ ቆጶሳት» በተካኑት ስልት የቅንጅቱን መሪዎች ከያሉበት ሰብስበው እስር ቤት ከተቱ፤ ትግሉም ከተነሳበት «የተዘረፍነው ድምፅ ይመለስ!» ወደ «መሪዎቻችን ይፈቱ!» ቀኝ ኋላ ዞሮ፣ የሥርዓቱ ዕድሜ እንዲቀጥል ስለመፍቀዱ የእኔ ትውልድ የአይን ምስክር መሆኑ ርግጥ ነው፡፡

## ሕዝበ-ሙስሊሙ

ከ2004 ዓ.ም (ከ«እፎይታ ጊዜ»ው በቀር) አንስቶ ካለማቋረጥ በተቀጣጠለው የሙስሊሙ ኃይማኖታዊ ነፃነትን የማስከበር ትግልም፣ የንቅናቄው አስተባባሪዎች ‹ቃሊቲ የታጎሩትን መሪዎች የማስፈታት ዓላማ በአራተኛነት የተያዘ ነው› ቢሉም («አህባሽን በግዴታ ማጥመቅ ይቁም»፣ «መጅሊሱ ወደ ሕዝቡ ይመለስ» እና «ነፃ ሕዝባዊ ምርጫ ይካሄድ» የሚሉት ሶስቱ መሪ ጥያቄዎች የተቃውሞ መነሾ እንደሆኑ ልብ ይ ሏል)፤ የሕዝበ-ሙስሊሙ በተለይም የቅርብ ጊዜዎቹ የመስጂዶቹ እምቢ -ባይነቶች፣ ሥርዓቱ ለማደነቃቀፍ (ዓላማውን ለማስቀየስ) ባዘጋጀው የ«ይፈቱ» ማዕቀፍ ስር የተገደበ የመምሰል አዝማሚያው ነው በዚህ አውድ እንድጠቅሰው ያስገደደኝ፡፡ የሁለት አስርታቱን የተቃውሞ ልምድ በቅጡ የመረመሩ የሚመስሉት የ«ድምፃችን ይሰማ» ወጣቶች፣ በዚህ የተለመደ የትግል ቅልበሳ ላለመጠለፍ የሚያደርጉት ብርቱ ሙከራ እንዳለ ብ ገነዘብም፣ ከቀደመው «ጥቁር ሽብር» ወዲህ በቀጣይ በሚኖሩት የትግል ወቅቶች ዋነኛ የትግል

ማድረጋቸው የማታ ማታ ለስ ኬት አብቅቷቸዋል፡፡ እነሆም የታሪክ ምሁራን «ሕዳሴ» (Renaissance) ብለው የሚጠሩት ይህንን ሁነት ነው፡፡

ሕዳሴ የታሪክ ሀዲድን ተከትሎ የኋሊት በመመለስ የማንፃት (የመታደስ) ተግባር የሚያከናውን የሳይንስ ዘርፍ ነው፡፡ ይህ ማለት ግን ጥንታዊውን ዘመን ዛሬ ላይ እንዳለ ማንበር ሳይሆን፤ የቀደመውን ሥልጣኔ የወደቀበትን ህፀፅ መርምሮ ለዘመኑ የሚበጀውን አንጥሮ በማውጣት፤ ያረበበውን ማሕበራዊ ፍዝነት እና ኋላቀርነት አንገዋሎ በመጣል ላይ የሚያተኩር ፍልስፍና መሆኑ አፅንኦት ሊሰጠው ይገባል፡፡ ምዕራባውያኑ ለደረሱበት የሥልጣኔ ከፍታ ዋናው መሰረት የተጣለው በሕዳሴው ዘመን ስለመሆኑ ራሳቸው ይመሰክራሉ፡፡ ኮፖርኒከስ፣ ጋሊሊዮ፣ ቦይል፣ ሀአርቬይ፣ አይዛክ ኒውተን፣ ሊዎናርዶ ዳ ቪንቺ፣ ሚካኤል አንጀሎን የመሳሰሉ ጉምቱ ጠቢባን የሥራ ውጤትም አብርሆት (ኢንላይትመንት) የሚባለውን ዘመን ወልዷል፤ ይህም ወደ ኢንዱስትሪ አብዮት አሸጋግሮ ለዛሬው ዘመናዊነት መደላድልን ስለማመቻቸቱ የታሪክ ድርሳናት ያትታሉ፡፡

በዘመኑ የሕዳሴው መንገድ ቀያሽ ተደርጎ የሚጠቀሰው ገዥ -ሃሳብ፣ የሰውን ልጅ በቀዳሚነት በሚያጠናውና ሰዋዊነት (Humanism) ተብሎ በሚጠራው ዘርፍ ላይ የተመሰረተ ሲሆን፤ ይህ አስተሳሰብ በሀገረ -እንግሊዝ በተስፋፋበት በ16ኛው ክፍለ ዘመን የተነሳው ፀሐፊ -ተውኔት ዊሊያም ሼክስፒር፣ ኃይማኖታዊ ክብረ በዓላትን፣ ስሜት-ተኮር እንቅስቃሴዎችንና ሥነ-ምግባር ላይ ብቻ ያውጠነጥን የነበረውን የድራማ ዘውግ፣ ወደ አለማዊ ይዘትነት በመቀየር ለሀገራዊ ፍቅር መነቃቃት እና የአርበኝነት መንፈስን በማስረፅ ረገድ ወደር የማይገኝለት ሚና ለመጫወቱ ትውልድ ተሻጋሪ ስራዎቹ ግንባር ቀደም ምስክሮች ናቸው፡፡

በጥቅሉ የ«ሕዳሴ» ፅንሰ-ሀሳብ የግሪክና የላቲን ብሉይ መድብሎች ላይ ቆሞ ፍልስፍናን እና መሰል የእውቀት ዘርፎችን መተርጎምን የያዘ የብርሃን ንቅናቄ በመሆኑ፤ የግለሰብን አለማዊ ከፍታ ለማስረገጥ፤ የሰውን





ልጅ ምክንያታዊነት፣ የምርምር ክሂልና የኪነ -ውበት ፈጠራ ማሳደግን ዋነኛ ማዕከሉ ያደረገ ብርቱ የለውጥ መንፈስ ነው ተብሎ ቢደመደም ማጋነን አይሆንም፡፡ በዚህ መንፈስ ምሪት መጪውን የኢትዮጵያ ሕዳሴ ገፆች፣ ሊያካትታቸው ከሚገቡ ማኅበረሰባዊ ፍላጎቶች (ከእስልምና ኃይማኖት ተከታዮች እና ከኦሮሞ ጥያቄ) አንፃር እና ሊያመጣቸው ከሚጠበቁ አገራዊ ፋይዳዎች አኳያ በቀጣይ ምዕራፎች እንመለከታለን፡፡

# ምዕራፍ ስድስት

# የኢትዮጵያ ሕዳሴ

በሚሊኒየሙ ክብረ-በዓል ዋዜማ «ሕዳሴ» የሚለውን ቃል በጥራዝ ነጠቅነት የቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ መጠቀሙን ተከትሎ፣ ከከቡራን ሚንስትሮች እስከ የቀበሌ ካድሬዎች የንግግር መከፈቻና መዝጊያ ሆኖ ከአንደምታው ተነጥሎ እያገለገለ ይገኛል፡፡ በአባይ ወንዝ ላይ እየተሰራ ያለው የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫንም «የሕዳሴ ግድብ» ሲሉ ሰይመውታል፤ ምንም እንኳ የትኛውን ያለፈ ታሪካችንን እንደሚያድስ አፍታተው ባይነግሩንም፡፡ በ2006 ዓ.ም የተከበረውን የግንቦት ሃያ በዓል በማስመልከት በቴሌቪዥን መስኮት ቀርቦ በወሬ ደረጃ ብቻ የሚያውቀውን የበረሃ ገድል እየተደነቃቀፈ የተረከልን ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለማርያም ደሳለኝም ቢሆን «የግንቦት ሃያ ድል ኢትዮጵያ ወደ ቀድሞ ገናናነቷ እንድትመለስ (እንድትታደስ) የጠቀመ ነው» ከሚል መታበይ አልፎ፣ የትኛውን የገናናነት ዘመናችንን ለመመለስ እንደተቻለ ለይቶ





አላስቀመጠልንም፡፡ በርግጥ እርሱ እያወራ የነበረው የአክሱም ስልጣኔን በተመለከተ ከሆነ፣ የ21ኛው ክፍለ ዘመን ታላቁ ስላቅ ተብሎ በታሪክ ማህደር ሊመዘገብለት ይገባል፤ በተለይም የአቶ መለስ ዜናዊን «የአክሱም ሀውልት ለወላይታው ምኑ ነው?» ሽርደዳን ስናስታውስ፡፡ በተቀረ «ሕዳሴ» ብሎ ለመሰየም በቅድሚያ መታደስ የሚገባው ጥንታዊ ሥልጣኔ ስለመኖሩ ማመን እንደሚጠይቅ፣ በአንድ ወቅት የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ፕሬዚዳንት ለነበረ ሰው ይጠፋዋል ብዬ አላስብም፡፡

ኢህአዴግ ከምኒሊክ በፊት የነበረችዋን ኢትዮጵያ እንደማያውቃት ሲለፍፍም ሆነ ታሪኳን በ100 ዓመት ገድቦ፣ የቀደመው የሥልጣኔ አሻራንም የአንድ ወይም የሁለት ቋንቋ ተናጋሪ ማሕበረ -ሰብ ግንጥል ውብት አስመስሎ ዕድሜ ሥልጣኑ ሙሉ ሲሰብክ ኖሮ፣ ዛሬ ‹የጥንቱን ገናናነት እንመልሳለን› ማለቱ፤ ራሱ ካነበረው የሥርዓት አወቃቀር ጋር ፊት ለፊት እንደሚያላትመው የዘነጋው ይመስለኛል፡፡ ምናልባትም «ስለሕዳሴ የማወራው ለፕሮፖጋንዳ ፍጆታነት አይደለም!» ካለን ደግሞ፣ የኢትዮጵያን የሶስት ሺህ ዘመን ቀደምት ታሪክ በይፋ መቀበሉን ያወጀ (ያመነ) ያህል ልንወስደው እንችላለን፡፡ ግና፣ ይህ አይነቱ የሰነበተ አቋም ድንገት በሞቅታ የሚለወጥ ሳይሆን፣ ብዙ ማብራሪያዎችን እና ደም ያፋሰሱ ጠማማ ታሪኮችን የማቃናት ከባድ ሥራ የሚጠይቅ መሆኑን ማስታወስ ግድ ይላል፡፡ በተረፈ የኢህአዴግ ‹ሕዳሴ ዘ-ልፈፋ› በታሪክ ብያኔው ያኮረፉትንና ‹ቅድሚያ ኢትዮጵያዊነት› የሚሉትን ዜጎች በሀሳዊ የፕሮፓጋንዳ ማግኔት ወደፓርቲው ለመንተት የሚጠቀምበት ተራ የማጭበርበሪያ ስልት ከመሆን አይዘልም ባይ ነኝ፡፡

በዚህ አውድ መከረኛይቱን ኢትዮጵያ ከአደገኛው ማዕበል የሚታደጋት ቀጣዩ ሕዝባዊ ንቅናቄ «የሕዳሴ አብዮት» በሚል ማዕቀፍ ስር ይወድቅ ዘንድ ገፊ-ምክንያቱ፣ የሥርዓት ለውጥ ብቻውን ለሀገሪቱ ትንሳኤ በቂ አለመሆኑን አፅንኦት ለመስጠት ነው፡፡ ስለምን? ቢሉ፣ በተለይም

ከ1983ቱ የመንግስት ቅያሬ በኋላ የተከሰቱ አስጨናቂ ችግሮች መፍትሄ ያገኙ ዘንድ ዳግም የመታደስ (እንደገና የመወለድ) አስፈላጊነትን አማራጭ አልባ ምርጫ በማድረጋቸው ነው፡፡ በተለይም ዘመናትን ያስቆጠሩ የአንድነት አዕማዶችን ባፈራረሰ መቃብር ላይ የተተገበረው የብሔር ፖለቲካ ያስከተለው የጎሳ ከፍፍልን ጨምሮ፣ ከባሕላዊ እሴቶች ማፈንገጥ፣ የትምህርት ጥራት ማሽቆልቆል፣ የኃይማኖት መቻቻል ወደ ታሪክነት መቀየር፣ የሕሊና ታማኝነት መደብዘዝ እና ከሰው ልጅ ይልቅ ቁስ መከበሩ... ከሞላ ጎደል አብዮቱን በታሪክ ማንፃት ሽለቆ የማለፍ ተልዕኮ እንዲያነግብ ገፍቶታል፡፡ በርግጥም የቀድሞ የታላቅነት መገለጫችን የሆነው የአክሱም ሥልጣኔ ከቡድ መንፈስ፤ የዛጉዌ፣ የሐረር እና የጎንደር አስደማሚ ሥነ - ሕንፃ፤ የገዳ ሥርዓት ዲሞክራሲያዊ ባሕሪ፤ በጠቢባን የተዋቀረው የከፋው «ምክሬቾ» እና መሰል ከቡድ እሴቶች ለዚህ ዘመን መዋጀት የሚበቃ ሽራፊ ምስጢረ-ጥበብን ሸሽገው ስለመያዛቸው ከቶም ቢሆን ቅንጣት ታህል አለመጠራጠራችን አብዮታዊ ሕዳሴን ቀዳሚ አጀንዳ እናደርገው ዘንድ ያስገድደናል፡፡

## የ«ሕዳሴ አብዮት» ቀዳሚ ግብ

ለዘመናት የተንሰራፋውን ሀገራዊ ደዌ ይፈውሳል ብዬ ተስፋ የማደርግበት የ«ሕዳሴ አብዮታ»ችን መፍትሔ ሊሰጥባቸው ከሚገቡ ጉዳዮች መሀል በቀዳሚነት የኦሮምኛ ቋንቋ ተናጋሪው ማሕበረ -ሰብ እና የእስልምና እምነት ተከታዮች የመብት ጥያቄ ናቸው ብዬ አምናለሁ፡፡ በኦሮሞ ጥያቄ እና በሙስሊሙ ጉዳይ ላይ የሚኖረን ክርክር፣ ያለፉትን አሚጋች የታሪክ ኩነቶችንና ስብዕናዎችን ለአካዳሚው ከበብ በመተው፤ ሁለቱ የማሕበረ-ሰብ ክፍሎች ኢትዮጵያን ዳግም በመበየን እና በአብዮቱ ሊኖራቸው የሚገባ ሚና ዋነኛ መሆን ይኖርበታል፡፡ ከ ኃይማኖቱም ሆነ ከኦሮምኛ ቋንቋ ተናጋሪው ማሕበረ -ሰብ ለሕዳሴው እውናዊነት የሚበጁ





የዘነጋናቸውን ዕሴቶችን መመርመር እና እነርሱንም በተዋስኦው ውስጥ አጥብቆ መግፋት፣ አንዱ ቀጣይ የቤት ስራችን መሆን አለበት፡፡ ሆኖም በቅድሚያ ይህ የዳግም ልደት አብዮታዊ ጉዞ ለሁለቱ ማሕበረ -ሰቦች ቅሬታ መፍትሔ ማበጀት ይኖርበታል፡፡ ይኸን የምለው የሌሎቹን ዋጋ በመዘንጋት ሳይሆን፣ በአንገብጋቢነቱ ስለማምን ነው፡፡

ምክንያቱም የብሔር ጥያቄ የኢትዮጵያን ማዕከላዊ መንግስት ለመናድ ቅርብ የነበረባቸው ዘመኖችን መመልከታችንን ልንስተው አንችልም፡፡ በዚህ መንገድ አልፈንም በዋናነት በአግባቡ መመለስ ካቃቱን ጥያቄዎች መሀከል በኦሮሚኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች የሚነሳው ዋነኛው መሆኑ አያከራክርም፡፡ በርግጥ ይህ ጥያቄ ጠርዘኛ ልሂቃኑ በሚያቀርቡት ልክ ባይሆንም፤ መሬት የረገጡ ማንነታዊ ቅሬታዎችን ተንተርሶ መነሳቱ ግን መካድ የለበትም፡፡ እናም ኢትዮጵያችንን በማደስ ጉዞ፤ ኦሮሞነት ከሀገሪቱ ምንነት ብያኔ የተነጠለ ሆኖ የመጣበትን የታሪክ አጋጣሚ ሂደት በመግታት፣ የብሔሩን መለዮዎች የኢትዮጵያዊነት ብያኔ ገዢ መተርጎሚያና መዳረሻ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

የኢትዮጵያን እስልምና ነባራዊነትን ማፅናት በተመለከተም ቢሆን፣ ኃይማኖቱም ሆነ ተከታዮቹ በአፄያዊዎቹ አፈና ውስጥ ለሺ ዓመታት የመቆየታቸውን እውነታ ተቀብለን፤ በኢትዮጵያዊነት ትዕምርታዊ ገ ፆች ውስጥ ቀዳሚ አዋጭነታቸውን መቀበሉ ለመታደሳችን ስኬታማነት ታላቅ አስተዋፅኦ አለው፡፡ ከዚህ አኳያም ሁለቱን ጉዳዮች በዚህ ምዕራፍ ዘርዘር አድርገን ብናያቸው የተሻለ ነው ብዬ አምናለሁ፡፡

የሥራ ቋንቋነት እንዲያገለግል ኦህዴድ ተፅእኖ የሚፈጥር አልሆነም፤ ሌላው ቀርቶ ጥያቄውን በሠላማዊ መንገድ ያነሱ ፖለቲከኞችም ሆኑ የክልሉ ተወላጆች «ኦነግ» ተብለው የምድር ፍዳቸውን ሲቀበሉ መታደጉ ቀርቶ ጉዳያቸው በሀገሪቱ ሕግ መሰረት መታየት አለበት ብሎ የተሟገተ የለም። ከዚህ አንፃርም የዕኩይ ድርጊቱ ተጠያቂ ጉልበተኛው ህወሓት ብቻ ነው ማለት ገራገርነት ይመስለኛል፤ የገዛ ወ ገኑን ራሱን የ«ትግራይ ነፃ አውጪ» ብሎ ለሚጠራ የማፍያ ቡድን እንደ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘመኑ አስቅሮቶ ይሁዳ አሳልፎ የሰጠው ኦህዴድም ጭምር የድርሻውን መውሰዱ አይቀሬ ነውና። ይህም ሆኖ ከአንዳንድ ምልክቶች በመነሳት ጥያቄዎቹ መልስ እስከሳገኙ ድረስ፣ የቱንም ያህል የእስር ቤት ደጃፎች ቢጨናነቁ፣ የቱንም ያህል የእስረኞቹ ሰቆቃ እያደር ቢበረታ በመጪው ዘመን በኦሮሚያ ምድር በፍርሃት ዝም-ጭጭ ብሎ የሚተኛ ሊኖር እንደማይችል በርግጠኝነት መናገሩ «ሟርተኛ» አያስብልም።

፪

የኦሮምኛ ተናጋሪውን ያደረ ቅራኔ በመፍታት የአንድነት ዘብ ለማድረግ፣ የሀገሪቱ ታሪክ እና ባሕል በዳግም ብያኔ መታደሱ ግድ ነው ብዬ አምናለሁ። የክልሉ ማሕበረ-ሰብ በዘመናዊው መንግስት ምስረታም ሆነ ከባእድ ወረራ መታደጉ ላይ ታላቅ አበርክቶ ቢኖረውም፣ በሀገሪቷ ታሪክ ውስጥ ሚናው ደብዝዞ እንዲገለፅ በአፄዎቹ መገደዱ ኀምዛዛ እውነታ ነው፤ ከምዕተ-ዓመታት በኋላም ቢሆን የቋንቋው ተናጋሪ ያልሆነው አብዛኛው ኢትዮጵያዊ ይህንን ስሁት አረዳድ አምኖ ሊያርመው ቀርቶ፣ እውቅና ሊሰጠው እንኳ አለመፍቀዱ፣ ጉዳዩን በተደጋጋሚ እንደታዘብነው ወደ«ውጡ ከሀገራችን» አይነቱ አስደንጋጭ ኩነት ገፍቶታል። ከዚህ በተቃራኒው በጥቂት የብሔሩ ልሂቃን የሚንፀባረቀው (ሀገርን ለፍርሰት ሊያጋልጥ የሚችለው) ሸውራራ የታሪክ አረዳድን እና የቅኝ አገ ዛዝ ትርክትን ማጥራት ሌላው ወሳኝ የቤት ሥራ ሆኗል፤ ምክንያቱም ከጥያቄው ጋር





ተያይዘው የሚነሱ የተቃውሞ ድምፆች ማጠንጠኛ ‹ባሳለፍነው መቶ ዓመት ለቅኝ አገዛዝ ተዳርገናል፣ ሥርዓታዊ በሆነ መዋቅር የሥልጣን ባይተዋር ሆነን ቆይተናል፣ ከሌላው የኢትዮጵያ ሕዝብ በተለየ መልኩ ከሰብአዊ ፍጡር በታች ተቆጥረን ተረግጠናል...› የሚል መንፈስ እንዲይዝ እየተለጠጠ ነው። ይህ የታሪክ ትንተና ስሁት መሆኑን የምንረዳ ው በየትኛውም መንግስታዊ ሥልጣን ጊዜ (ሀገሪቱ በጎበዝ አለቆችም ሆነ በነገሥታቱ ጠንካራ መዳፍ ስር፣ አሊያም በወታደራዊው ደርግ በተያዘችበት ዘመን) በግንባር ቀደምትነት በመንበሩ ላይ ይፈራረቁ ከነበሩት አማርኛና ትግርኛ ተናጋሪዎች የማይተናነስ ዕኩል ሚና እንደነበራቸው የቋንቋው ተናጋሪ ምሁራን በማስረጃ አስደግፈው ባዘጋጁቸው ድርሳኖቻቸው ያተቱትን ስናስተውል ነው።

ለማሳያም «የጎንደር ዘመን» ተብሎ ከሚጠቀሰው (እ.ኤ.አ ከ1636-1769 ዓ.ም ድረስ የዘለቀው) ማዕከላዊ መንግስት ውድቀት በኋላ የተተካውና «ዘመነ መሳፍንት» እየተባለ በታሪክ የሚጠቀሰው አገራዊ የአስተዳደር ዘይቤ ጠንሳሽና ተግባሪ የኦሮምኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች እንደነበሩ ማስታወሱ በቂ ነው። በወቅቱ የመንግስቱ መቀመጫ ከሰሜን ጎንደር ወደ ደብረ-ታቦር የተዘዋወረ ሲሆን፣ የግዛት ወሰኑ ደግሞ ጎንደርን፣ ወሎን፣ ጎጃምን፣ ከፊል ሸዋን እና ትግራይን የሚያካትት እንደነበር መዛግብቱ ያወሳሉ። በዘመኑ ሥልጣኑን የጠቀለሉትና «የጁ (ወራ-ሼክ) ስርወ-መንግስት» በሚል ስም የሚጠሩት የኦሮምኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች እንደነበሩ የብሔሩ ምሁራን በተለያዩ ድርሳኖቻቸው ነግረውናል። በ2006 ዓ.ም «የውገና ድርሰቶችና የታሪክ እውነቶች» በሚል ርዕስ ዳጎስ ያለ ጥራዝ ያሳተሙት ታቦር ዋሚ «በኢትዮጵያ ታሪክ ዘገባዎች አላግባብ ዘመነ መሳፍንት ሲባል የቆየው የየጁ ዘመንና ታሪካዊ ሚና» በሚለው ንዑስ ርዕስ ሥር በርካታ መጽሐፍትና የጥናት ጽሑፎችን በመጥቀስ በወቅቱ ሥልጣኑ በኦሮምኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች እጅ እንደነበረ በስፋት አብራርተዋል። ታቦር በትርክታቸው፡-

*አቋርጦ ልክ የአካባቢው ሕዝብ ጋር ሙሉ በሙሉ ተዋህደዋል /አሲሚሌትድ ሆኗል/ ሊባል ይችላል።»* (ገፅ15-)

የታሪክ ምሁሩ ፕሮፌሰር ታደሰ ታምራት በ1991 ዓ.ም «ኢትዮጵያዊነት ከመሰረቱ» በሚል ርዕስ ባሰናዱት ጥናታዊ ጽሑፍ እንዲህ ሲሉ የገለፁትን እዚህ ጋ ልጥቀሰው፡ -

*«በክርስቲያኖች አካባቢ የሚሰፍረው ኦሮሞ የክርስትና ኃይ ማኖትን መቀበሉን ብቻ ሳይሆን፣ የማዕከላዊ መንግስት መግባቢያ የሆነውንም የአማርኛ ቋንቋ መናገር እንደሚጀምር ነው። ከጊዜ ብዛት ደግሞ፣ ቀስ እያለ እንዲያውም፣ የኦሮምኛውን ቋንቋ ጨርሶ ይተውና፣ አማርኛ ብቻ ይናገራል። ትውልዶችም እያለፉ ሲሄዱ፣ የልጅ ልጆቹ ጨርሰውም አማራ ይሆናሉ። በሰሜን ሸዋና አሁን ወሎ፣ በጥንት ጊዜ ግን አማራ ይባል በነበረው፣ ከፍለ -አገር ውስጥ ባሉት ብዙ አውራጃዎች፣ በጎጃም፣ በጌምድርና በደምቢያ የሰፈረው ኦሮሞ፣ በመጨረሻ ላይ ጥሩ አማራ እየሆነ የሄደው በዚህ አይነት ነው።»*

ይህ ጉዳይ እውነት ብቻ ሳይሆን ሙብት እንደሆነ አምኖ መቀበሉ ሀገራዊ አንድነታችን የተጋመደበትን የባሕል፣ የቋንቋ፣ የአስተዳደርና መሰል ጉዳዮችን ትስስሮሽ ያሰረግጣል። ይሁንና የተወሰኑ የኦሮሞ ልሂቆች የአፄ ምኒሊክ ፈረሰ ሐረርና አርሲ መርገጡን አለቅጥ እያሰጮኹ «የቅኝ -ግዛት ወረራ» አድርገው ከማቅረባቸውም በዘለለ፣ ይህ አይነቱን ጥሬ ሀቅ ለመቀበል ቀርቶ ለመስማት አይፈቅዱም። ከዚህ በግልባጩ በተለይም በቋንቋው ተናጋሪዎች የተዘጋጁትና የጠቀስኳቸው ድርሳናት የሚነግሩን ደግሞ ኦሮሞ ከሌላው ብሔር ጋር ትንቅንቅ ገጥሞ በለስ ቀንቶት ድል ባደረገ ቁጥር መንግስታዊ ሥልጣን መጠቅለሉን ብቻ ሳይሆን፤ በሀገሪቱ ታሪክ ጭቆና እንጂ ቅኝ አገዛዝ የሚባል ነገር አለመኖሩንም ጭምር ነው። ከኤርትራ እስከ ሞያሌ፤ ከጋምቤላ እስከ ሶማሌ በተዘረጋው ሰፊ የኢትዮጵያ





ግዛት ላይ በተደጋጋሚ ከተቃጡ የባዕዳን ወረራዎች በቀር፣ ቅኝ -ገዢም ሆነ ቅኝ-ተገዢዎች ስለመኖራቸው የሚያትት አንድም የታሪክ መረጃ ተፈልጎ ታጥቷል። መቼም «ድሮ ነፃ ሀገር ነበረን» በሚል ዛሬ ላይ የመገንጠልን ጥያቄ ሲያነሱ፤ አሊያም አንድ ብሔርን በነፍጠኛነት፣ በወራሪነት፣ ለም መሬት በመንጠቅ... ሲኮንኑ የምናደምጣቸው ጠርዘኛ ልሂቃን የጥንቱ ‹የኦሮሚያ የግዛት ወሰን ጎንደርን እና ትግራይን ያጠቃልል ነበር› ስለማሊታቸው ሰምተን አናውቅም። ይህ ካልሆነ ደግሞ በዚህ ስነ -አመክንዮ መሰረት ያውም መቀመጫውን ደብረ-ታቦር ላይ አድርጎ ከትግራይ እስከ ሸዋ የሚደርሱ ሰፋፊና በሥነ-መንግስት አንደምታ በቂ ተሞክሮ ያላቸው ማሕበረ-ሰቦችን ያስተዳድር የነበረ ሥርወ-መንግስት፣ የበለጠ ጉልበተኛ ተነስቶበት፣ በተራው ከመንበሩ በኃይል ሲገለበጥ ባለጊዜውን ‹ ቅኝ-ገዢና ኢ-ሰብአዊ› እያሉ ለመኮነን መሞከሩ ከተራ ፍረጃ ተሻግሮ ውሃ የሚያነሳ ሙግት ሊሆን አለመቻሉ በገሀድ የሚታይ እውነታ ነው ብዬ አምናለሁ።

ግና፣ እዚህ ጋ ሊዘነጋ የማይገባው ጉዳይ፣ በተለይም ከአፄ ምኒሊክ መንገሥ ወዲህ የኦሮሞ ማሕበረ-ሰብ ቋንቋውን ጨምሮ የባሕል እሴቶቹ ተውጠው፣ የአገሪቱ ወካይ እንዳይሆን መጨፍለቁን ነው፤ እንደምሳሌም የገዳ ሥርዓት ምንም እንኳ ሁሉም የቋንቋው ተናጋሪ የሚጠቀምበት ባይሆንም (የ«ጊቤ ግዛት» ተብለው የሚታወቁት ኦሮምኛ ተናጋሪዎች፡ -ጅማ፣ ሊሙ፣ ጎማ፣ ጉማ እና ጌራ ከገዳ ይልቅ በንጉሣዊ ሥርዓት ሲተዳደሩ፤ ወለጋና ኢሊባቡርን የመሳሰሉ አካባቢዎችም በ«ሞቲ» ይመሩ እንደነበር ልብ ይሏል) የአክሱም ሐውልትን ወይም የጎንደር ግንብን ያህል በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ቦታ አለማግኘቱ አይካድም። እንዲሁም በሌላ ቋንቋ ተናጋሪው ዘንድ «ጣኦት ማምለክ» ተደ ርጎ የሚቆጠረው የኢሬቻ ክብረ-በዓል አረዳድ ስሁት ስለመሆኑ ቢረፍድም የመመስከሩ ጠቀሜታ የጎላ ነው። ይህ የምሲጋና ሥነ-ስርዓት በአገሪቱ ታሪክ ተገቢውን የክብር ስፍራ ሳያገኝ መገፋቱን በማመን፣ ሚዛንን ማስተካከል ግድ ይላል።

*«የኦሮሞ ሕዝብ ከፍተኛ አብዮታዊ ሚና ተግባራዊ እንዳይሆን አፍኖ ይዞ የሚገኘው ዋናው እንቅፋት የአማራ ‹የትልቅ ብሔር› ትምክተኝነት ነው፡፡»* (ገፅ 46)

ይሁንና ትምህርታቸውን አቋርጠው ብረት ከነከሱት የሰሜን ፋኖች በታሪክ የላቀና የመጠቀ ዕውቀት ባለቤት የነበሩት ፕሮፌሰር ታደሰ፡ -

*«የዚህ አይነት ለውጥ የተደረገው ወደ አማርኛ ብቻ እንዳልሆነ በአትኩሮት መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ ለምሳሌ የትግርኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች በሚበዙበት አካባቢ ሊሰፍሩ የቻሉ ኦሮሞዎች፣ በተለይ በትግራይ ደቡብ ጫፍ የሚገኙ አውራጃዎች ውስጥ፣ ትግርኛ የሚናገሩና፣ ከጊዜ ብዛትም ጨርሶውንም ትግሬ የሆኖ እንደሚገኙ ይታመናል»*

ሲሉ ከላይ በጠቀስኩት ጥናታዊ ጽሑፋቸው ላይ የተነተኑትን ማስተዋሉ የተሻለ ነው ብዬ አምናለሁ፡፡

ይህ ምስክርነት የሚያስረግጥልን ዋነኛ ቁም -ነገር ረዥም ዘመናትን ያሳለፍነው በአንድ ብሔር ጉልበታምነትና ጭካኔ ስንቀጠቀጥ ሳይሆን የተለያዩ ቋንቋ ተናጋሪ ግለሰቦች ጥምረት ፈጥረው ሲበዘብዙንና ሲጨቁኑን መቆየታቸውን ነው፡፡ እናም እውነታው ዛሬ አንዳንድ ጠርዘኛ ልሂቃን እንደሚሉት ነገሥታቱ ሆነ ብለው ሌሎችን ጨፍልቀው እነርሱ የወጡበትን ብሔረ-ሰብ አባላት ለይተው በ«ገዥ መደብ» ሲቀቡ አይደለም፡፡ ሌላው ቀርቶ ስለአርሲና ባሌ የሚነገሩ የተዛቡ ታሪኮች ከመከሰታቸው ቀድሞ ቤጌምድርና ትግራይ ውስጥ የኃይል ት ንቅንቅ ተፈጥሮ የአካባቢው ተወላጆች ነን የሚሉትን፣ ኦሮምኛ ተናጋሪው አሸንፎ በማንበርከክ ለ86 ዓመታት ያህል ሥልጣን ይዞ መቆየቱን ከላይ በሚገባ አይተናል፡፡ መቼም የጁዎች፣ ጎንደሮችን ድል አድርገው ሥርወ -መንግስታቸውን ደብረ-ታቦር ላይ የመሰረቱት በምርጫ ካርድ (ያለነፍጥ) ነበር ካልተባለ በቀር፣ አንዱን ወገን በሂትለርነት ኮንኖ ሌላውን በግፉአንነት ማውሳቱ ፍትሐዊ





ካለመሆኑም በላይ፤ የሚጠቅመው ከመከ ራ ነፃ እንዲወጣ የምንዋትትለትን ሕዝብ ሳይሆን፣ የአገዛዙን ዕድሜ ለማራዘም ነው፡፡

እነዚህ በራሱ በቋንቋው ተናጋሪዎች ብቻ ከተዘጋጁ ድርሳናት የጠቀስኳቸው ሁነቶች፣ በአሳማኝ ማስረጃ ያልተረጋገጠውን (አፈ -ታሪኩን) የአኖሌ ጡት ቆረጣ ትርክት ተአማኒነት ያሳጡታል፡፡ ይህ ግን ምኒሊክም ሆኑ ከእርሳቸው በፊት የነበሩ ነገሥታት ድል ያደረጉትን ሠራዊት እጅ -እግር የመቁረጣቸውን የጭካኔ ልማድ በሬ -ወለደ ነው እንደማለት አይደለም፤ በትክክልም ያደርጉት እንደነበረ በበርካታ ድርሳናት የተረጋገጠ ነውና፡፡ እንዲያውም በአንድ ወቅት አፄ ቴዎድሮስ፣ በሸዋ ላይ ሾመውት የነበረው የምኒሊክ አጎት አቤቶ ሠይፈ «ሸፍቶብኛል» በሚል አንኮበር ድረስ መጥተው ወግተው ድል ካደረጉት በኋላ ሠራዊቱ በሙሉ አንድ እጅና አንድ እግሩ እንዲቆረጥ በማድረጋቸው አገሬው ሰምና ወርቅ በለበሰ ቅኔ እንዲህ ብሎ መግጠሙ የጉዳዩን እውነታነት ለ ማስረዳት በቂ ነው፡-

*«አፄ ቴዎድሮስ አጅግ ተዋረዱ*
*የሸዋን ሰው ሁሉ እጅ ነስተው ሄዱ»*

የሆነው ሆኖ አንድ ማሕበረ -ሰብ በደምም ሆነ በስምምነት መገንባቱን የዓለም ታሪክ ይናገራል፡፡ ግንባታው በደም በተቀባ ታሪክ መካከል የማለፉ አጋጣሚም በራሱ አገሪቱን ባቢሎን ለማስባል ምክንያት አይሆንም፡፡ ‹ይሁን› ከተባለ ግን ኢትዮጵያን በዓለማችን ብቸኛዋ አገር ልናደርጋት እንገደዳለን፡፡ ቀደምት አባቶች ማሕበረ -ሰብን ለዘለዓለም በአንድነት ለማፅናት ከጠብ -መንጃ በተጨማሪ ቋንቋ፣ ባሕል፣ መልከዓ -ምድርና መሰል ጉዳዮችን ለማስተሳሰር ይሞክሩ እንደነበረ ይታወሳል፤ ብዙውን ጊዜም ከሠላማዊው ስምምነት ይልቅ፣ በኃይል ማስገበርን ይመርጡ ነበር፡፡ በኢትዮጵያችን ይህ መንገድ ካስገኘው ትልቁ ውጤት በተቃርኖ፣ ታሪክን የዚህ ዘመን የመበየኛ «ፖለቲካ» በማስመሰል የልዩነት በርን ለማስፋት ለሚሞክሩ ሥልጣንን የሚያሰሉ ኃይሎ ች የመጫወቻ ካርድ

ሆኖ እያገለገለ ነው፡፡ ግና፣ እንስፓርታና ትሮይ በኃይል መገበራቸው የዛሬዋን ሄለናዊ ግሪክ መፍጠር መቻሉን እንጂ፤ በዚህ ዘመን መነፅር ቀቃኝቶና ለብይን ቀርበ የ«እንገነጠላለን» ጥያቄ ስለማስነሳቱ ተሰምቶ አይታወቅም፡፡ ፕሮፌሰር ታደሰም «ኢትዮጵያዊነት ከመሰረቱ» በሚለው ጥናታዊ ጽሑፋቸው ጉዳዩን፡-

*«በመላው ዓለም ውስጥ ያለው ማንኛውም ሕዝብ፣ ምንም ሳይለወጥ፣ የጥንት ሀልውናውን ብቻ እንደያዘ፣ ጥንት ከሰፈረበት አካባቢ ምንም ሳይነቃነቅ፣ በጎረቤቱ ከሚኖሩ ሌላ ሕዝቦች ጋር ምንም ንክኪ ሳይኖረው የቆየ ሕዝብ ጨርሶ አይገኝም»*

ሲሉ አጠናክረውታል፡፡ የአገርን የመጨረሻ ቅርፅ ያበጁ ማሕበረ-ሰባዊ ውሎች ከፖለቲካዊ ፍቺ ይልቅ፣ አንድነትን ለማፅናት ያላቸውን አስተዋፅኦ ያህል፣ ሂደቱ የዜጎችን እልቂት፣ የማንነት ጭፍለቃን፣ የኃይማኖት ድፍጠጣን፣ የባሕል ወረራን... የማድረሱን አይቀሬ ነትም በቅንነት መረዳትን ይጠይቃል፤ መግቱም ከዚህ አውድ ሊርቅ አይገባውም፡፡

ፖለቲካዊ ውሳኔዎች ማሕበረ-ሰባዊ እሴቶችን ዘንግተው ጊዜያዊ ትርፍን ብቻ ታሳቢ ካደረጉ ከትውልድ ትውልድ በቀላሉ የማይቋጭ ከባድ የቤት ስራ ሰጥቶ የሚያልፍ ጠባሳ መተዋቸው አከራካሪ አይደለም፡፡ ይህም ሆኖ በኦሮሚያ ከማንነት ጭፍለቃ፣ በታሪክ ከመዛንጋት እና የፌዴራሊዝም ሥርዓቱ በትክክል ካለመተግበሩ ጋር የተያያዙ ጥያቄዎችን ተከ ትሎ፣ ዝነኛው የቃሊቲ ማጎሪያ ለቋንቋው ተናጋሪ ወጣቶች ሌላኛው የሲኦል ቤት የሆነበትን ኩነት ማስተባበል አይቻልም፡፡ የብሔሩ ልሂቃን ባላጠሩት ወይም በከፋፈሏቸው መሰረታዊ ልዩነቶች መንስኤነት ወከለነዋል የሚሉት ማሕበረ-ሰብ የስቃዩ ገፈት ቀማሽ እንዲሆን መግፋታቸውን ሳንዘነጋ ማለት ነው፡፡ ወደዚህ ድምዳሜ የሚያደርሰንም ‹ጥያቄዎቹ ከመገንጠል በመለስ ሁነኛ ምላሽ የላቸውም› የሚሉትን ያህል፤ ‹ስርየቱ ዲሞክ ራሲያዊ አንድነት ብቻ ነው› የሚሉ፤ አሊያም ሀገሪቱን እስከወዲያኛው በብቸኝነት በመግዛት





ዙሪያ የሚያጠነጥኑ ኃይሎች በአንድ ብሔር ጥያቄ አፈታት ላይ የተያዙ አቋሞች የመሆናቸው እውነታ ነው፡፡ ከእነዚህ ፖለቲካዊ ምላሾች መካከል መገንጠል ወይም በብቸኝነት የሥልጣን ይገባኛል ጥያቄ ተግባራዊ የሚሆንበት አጋጣሚ ቢፈጠር፣ የሀገር ህልውናን የተሸከሙ እዕማዶች ፈራርሰው፤ ዘመናትን የተሻገረው ማሕበራዊ ትስስር ተበ ጣጥሶ እገር-አልባ የተበታተነ ትውልድ መውለዳቸው አይቀርም፡፡ እናም ኦሮሚያን ከተቀረው የአገሪቱ አካል መገንጠል፣ ዛሬም ክልሉ በተዋቀረበት መልክዓ-ምድራዊ ቅርፅ ውስጥ ሌሎች ህዳጣኖችን ማስተናገድ የሚያስችል ሥርዓት ማበጀት እንደማይቻልም (ከብሔር ፌደራሊዝሙ ትግበራ በኋላ ያየናቸው ጉድለቶች ዳግም እንደማይከሰቱ ተገንጣይ ልሂቃኑ በቂ መከራከሪያ እንኳ ሲያቀርቡ አልሰማንም) ሆነ የተዳፈኑ ሌሎች ጥያቄዎች ፈ ንቅለው ከመውጣትና በማያቋርጡ አዳዲስ ችግሮች የቋንቋውን ተናጋሪ ከመናጥ አይታደግም፡፡ በብቸኝነት የመግዛት ጥያቄም ቢሆን (ኦሮሞ ብዙ ከመሆኑ አኳያ ሁሉም የቋንቋ ተጋሪውን ልሂቅ ብቻ ለይቶ ይመርጣል ከሚል ምክንያተ-አልቦ መነሻነት) የበላይ ልሁን ባይነትን ከማንፀባረቁ እና ኢ-ዲሞክራሲያዊ ከመሆኑም ባሻገር የዘመኑን መንፈስ የሚፃረር ነው፡፡

ወይድንም ጠላን ኦሮምኛ ተናጋሪው እንደከዚህ ቀደሙ የልሂቃኑ ን ያልተፈተነ ፖለቲካዊ የመፍትሔ ሃሳብ ብቻ አንጠልጥሎ፣ ከወንድምና እህቶቹ ጋር ለዘመናት የገነባውን ሁለንተናዊ ትስስር ጥሎ እንዲነጉድ የሚገፋበት እኩይ ቀመር የሚያከትምበት ጊዜ ላይ መድረሳችንን መገንዘቡ ብልህነት ነው ብዬ አምናለሁ፡፡ ስለምን ቢሉ? ያለፈው ታሪካችን በደም መገንባቱ ባይካድም፣ ዛሬም ዕጣ-ፈንታችን በዚህ ሊደመደም አይቻለውምና ነው፡፡ እነዚህን ችግሮች በማያዳግም ሁኔታ ለመፍታት፣ በቀዳሚ ነት ኦሮምኛ ተናጋሪው ክፍል እና የአንድ ጠቅላይ ኢትዮጵያ አቀንቃኝ ሆነው የምናገኛቸው ወገኖቻችን መካከለኛውን የመቻቻል መደላድልን ለመፍጠር በስጥቶ መቀበል መርህ የተቃኘ መፍትሔን አምነው የመተግበር ተነሳሽነት ሊኖራቸው እንደሚገባ አምናለሁ፡፡ ዶ/ር መረራ ጉዲና «የኢትዮጵያ ፖለቲካ

የኃይማኖት እና የብሔር ልዩነት ከሕዝበ-ሙስሊሙ ጎን መቆምን አማራጭ አልባ ማድረጉን አምኖ መቀበሉ ከዘገየ ፀፀት ይታደጋል፡፡ በተለይም በሀገሪቱ ፖለቲካ የዳበረ የተሳታፊነት ልምድ ያላቸው የኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት ተከታዮች ለዘብተኝነት ያበቃ ዘንድ ወቅቱ ግድ ማለቱን ማስተዋል ብልህነት ነው (በርግጥ የተቃውሞ እንቅስቃሴው በመስጊድ ብቻ መገደቡ ክርስቲያኑ እንዳይተባበር አንድ እንቅፋት መሆኑን አልዘነጋሁም)፡፡ ከዚህ በተጨማሪም አንዳንድ የኦርቶዶክስ እምነት ተከታዮች የሙስሊሙ የተቃውሞ ንቅናቄን «የነርሱ ጉዳይ ነው» አይነት ገለልተኛ አቋም ላይ ለመድረሳቸው ገፊ-ምክንያት ተብሎ የሚታመነው፣ በፐ/ር ሀጋይ ኤርሊክ ‹የግራኝ ስጋት› (Syndrome) በሚል የተገለፀው አደንዛዥ ስነ-ልቦና ሊሆን እንደሚችል ይገመታል፡፡ ኢትዮጵያውያኑ ክርስቲያኖች ከ500 ዓመታት በፊት አህመድ ኢብን አልጋዚ የሄደበትን የፖለቲካ ስልጣን ፍለጋ አውዳሚ የጦርነት መንገድ፤ በክርስትና መቃብር ላይ የእስልምናን የበላይነት ለማንበር እንደተሞከረ ተደርጎ ለሚቀርበው መላምት መታመናቸው ወደዚህ ጠርዝ የገፋቸው ይመስለኛል፡፡ ግና፣ ይህን መሰሉ አካሄድ ማኪያቬሊያዊ አስተምህሮን እንደ ቅዱስ ቃል የሚያከብረውን ኢህአዴጋዊ-አገዛዝ ዕድሜ ከማራዘም በቀር ቅንጣት ፋይዳ የሌለው በመሆኑ፣ ስጋቱን አራግፎ በመጣል ያለ አንዳች ልዩነት በሕብረት መቆሙ አገሪቱን ወደፊት ለመውሰድ ወሳኝ ሚና ይኖረዋል (በአልነጃሺ/አርማህ መሀከል ያለውን የሚታረቅ የማይመስል ቅራኔ ሳንዘነጋ)፡፡

እየተነጋገርንበት ባለው የ«ሕዳሴ አብዮት» ሀቲት፣ ሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን ላይ ቆመን፣ ከአራት መቶ ዓመታት በፊት በተከሰተ (ሊያውም ስምምነት ላይ ሊያደርሱ ያልቻሉ ትርክቶች ባሉበት ሁነት) ይህን ዘመን መቃኘት ረብ የለሽ ነው ብዬ አስባለሁ፡፡ ወደፊት ለመራመድ የክርስቲያኑ ቀዳሚ የቤት ስራ መሆን ያለበት፣ በሕዳሴው የምትፀነሰዋ ኢትዮጵያ ከሙስሊም ጋር በብቻነት መዋረስ እንደሌለባት ሁሉ፤ እስከአሁን





እንደተሸከመቻቸው የሚታሰቡትን ኦርቶዶክስ ቀመስ ትዕምርታዊ እሴቶችንም ለመግራት መፍቀድን ይጠይቃል፡ ፡

ከእስልምና ልሂቃን አንዱ ኡስታዝ ሀሰን ታጁ፣ ለዚህ አይነቱ አንድነት የሚያግዙ ሦስት ነጥቦችን ያነሳል፡፡ *«ሰይፉን ፍለጋ»* በሚል ርዕስ በቅርቡ ባሳተመው ድርሳኑ፣ ሙስሊም በቀደሙ ጊዜያት በኦርቶዶክስ በዓላት ላይ የመሳተፍ የግዴታ ቀንበሩን መጣሉ አለመቻቻል ተደርጎ መቅረብ እንደሌለበት በዋናነት ይጠቅሳል፡፡ ከዚሁ ጋር አያይዞ፣ ባለፉት ሁለት አስርታት የተመለከትነውን የእምነቱ ተከታዩን «እስልምና ን ወደ ማፅደቅ» መመለስ እንዳለመቻቻል፤ አልያም ሌላ ድብቅ ዓላማ እንዳለው በማስመሰል በጥርጣሬ ማየቱ አደገኛ ስለመሆኑ አጽንኦት ሰጥቶበታል፡፡ «...ቴዎድሮስ ጨፍጭፎናል፣ ዮሐንስ አርዶናል፣ ዘርአያዕቆብ እምነታችንን አንቋሽሿል... መሰል የታሪክ እውነቶችን መካድ የትም አያደርስንም» ሲልም ያስታውሳል፡፡ እነዚህን የኡስታዙ ምክረ-ሐሳቦች የጠቀስኩት፣ ቢያንስ የታሪክ ተዋስኦ ላይ ተፃራሪ ሙግቶች የሚቀርቡ ባቸውን ኩነቶች ትተን፣ በታዳሺቷ ኢትዮጵያ በሚበጀው ብያኔ ውስጥ ሙስሊሙን ለመቀላቀል በእጅጉ እንደሚጠቅመን ከልብ በማመን ነው፡፡

ሌላው መሰረታዊ ጥያቄ ደግሞ፣ ከሕዝበ-ሙስሊሙስ ምን ይጠበቃል? የሚለው ነው፡፡ እንደ ሐሰን ታጁ ትንተና አንዱ አስፈላጊ ጉዳይ፣ ኃይማኖቱም ሆነ ተከታዮቹ በተለይም በዘመናዊቷ ኢትዮጵያ መሪዎች ተረግጠው መቀጥቀጣቸው የማይስተባበል ሀቅ ቢሆንም፣ ባለፉት የታሪክ ሁነቶች ላይ ተመስርቶ ጦር መወራወርን ትተው ወደፊት በሚወስዱን ጭብጦች ዙሪያ ለመነጋገር ከመፍቀድና ከመድፈር ውጪ የቀረ ምርጫ አለመኖሩን መገንዘብ እንዳለባቸው ነው፡፡ የሆነው ሁሉ የተነገረውን ያህል ቢሆንም/ባይሆንም፣ አሁን ያለንበትም ሆነ የነገ ዕጣ ፈንታችን በማይበጠሱ ክሮች መገመዱን ተቀብሎ ከመነጣጠልና በጎሳ ከመከፋፈል ይልቅ በሕብረት መነሳት ወደመታደሳችን የሚያደርሰን ብቸኛው መንገድ ነው ብዬ አምናለሁ፡፡ ኡስታዝ ሐሰን ከላይ ባወሳሁት መጽሀፉ፤ ዶ/ር

እንድሪስ ሙሐሙድ ለፒኤችዲ ማሟያ ካዘጋጀው የጥናት ሥራው ላይ የጠቀሰውም ይህንን ሐቅ በሚገባ ያጠናከረዋል፡ -

*«የአሁኑ ትውልድ ላለፉ ግፎች እና መድሎዎች እውቅና በመስጠቱ በአስተሳሰቡም ሆነ በተግባር የማስተካከያ እርምጃዎችን መውሰድ፤ እንዲሁም ጥላቻን ዘርቶ ከማብቀል ሎታቀብ ይኖርበታል፡፡ በታሪካዊ ጭቆናዎች ምክንያት የተፈጠሩ ማሕበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ባሕላዊ መበላለጦች የሚካሱበት መንገድም ሊኖር ይገባል፡፡ ምናልባትም በንዲህ አይነት ልባዊ ጥረቶች ያለፉ ቁስሎች ሊሻሩና መጪው ዘመን ጤናማነቱ ሊረጋገጥ ይችል ይሆናል፡፡ ከዚህ ውጪ እውነታውን በመድፈቅና በማድበስበስ ጤናማና ጠንካራ ማሕበረሰብ መገንባት አንችልም፡፡»* (ገፅ 388)

ዛሬ በአስቃቂው ቅሊንጦ እስር ቤት የሚገኘው የመፍትሔ አፈላላጊው ኮሚቴ አባል አሕመዲን ጀበልም «ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች ከ615-1700 የጭቆናና የትግል ታሪክ» በሚል ርዕስ በ2003 ዓ.ም ለንባብ ባበቃው ቅጽ አንድ መጽሐፉ መግቢያ ላይ የታሪክን ፋይዳ እንዲህ ሲል ገልፆታል፡ -

*«ታሪክ ትናንትን ለማወቅ፣ ዛሬን ለመረዳትና ለነገ ለማቀድ ያግዛል፡፡ ታሪክ ያለው ሕዝብ በአግባቡ ከተጠቀመበት ታሪክ ይሰራል፡፡ ወደፊት መጓዝ የፈለገ መጀመሪያ ወደኋላ ተመልሶ ታሪኩን ይፈትሻል፡፡ የአባቶቹንና የአያቶቹን ገድል ሲረዳ በምን ሁኔታ ውስጥ እንዳለፉ ግልጽ ብሎ ይታየዋል፡፡ የዛሬው እርሱነቱ የበርካታ ሂደቶች ውጤት መሆኑን ይረዳል፡፡ የአባቶቹንም ስህተት አይደግምም፡፡ የነርሱ ጠንካራ ተሞክሮ ኃይል ይሆነዋል፡፡»* (ገፅ 19)

አብዱልከሪም ታጁ በ«ፋክት» መጽሔት ቅጽ 2 ቁጥር 55 ‹ወደ ጥንቱ መመለስ!?» በሚል ርዕስ ላስነበበን ጽሑፍ መደምደሚያ ያደረገውን ሃሳብም እዚህ ጋ ማከል ሙግቱን ያጠነክረዋል፡ -





*‹የነ አማሆይ ወተት፣ የነ ሲቲ መይሙና አገር፡፡ የነ የኔታ፣ የነ አብዋ፣ የነ አባዬ፣ የነ ጌትዬ፣ የነ አባ ገዳ አገር፡፡ የነ አብርሽት (የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊት ሙስሊም)፣ የነ ድል ወንበራ፣ የነ ምንትዋብ፣ የነ አትዬ ባይቱ፣ የነ አትዬ መነን አገር፡፡ የነ ኢዛና፣ የነ ነጃሺ፣ የነ ፋሲለደስ፣ የነ አባ ጂፋር፣ የነ ሐሰን እንጃሞ… አገር፡፡ የክርስትና፣ የእስልምና፣ የዋቄፈታና የሌሎች ባሕላዊ ኃይማኖቶች ሀገር፡፡ እነዚህ ሁሉ ናቸው እንግዲህ ማንነታችን የተገመደባቸው ልዩ፣ ጠንካራና ቀለመ-ብዙ ክሮች፡፡ ባሕላችን የተሸመነባቸው ድርና ማጎች፡፡»*

…በኢሕአዴግ ስር ያለፍናቸው ዓመታት እንዳስረገጡት ጭቆናው ሙስሊሙን ለይቶ የተተገበረ ካለመሆኑ አኳያ፣ በመጪው የ«ሕዳሴ አብዮት» ኢትዮጵያን ከውድቀት ለማዳን ወደ መሀከለኛው ፖለቲካ መምጣት በእጅጉ አስፈላጊ ነው፡፡ ለዚህም ሕዝበ-ሙስሊሙ (ልክ እንደ እሮምኛ ተናጋሪው ሁሉ) ቀዳሚው አዋጪ መሆን የሚኖርበት፣ ኢሕአዴግ ላይ በእምነትና በጥርጣሬ መካከል ሲዋልል የከረመበት አካሄድ ኃይማኖቱን በመጨፍለቅ መደምደሙን በግላጭ መመልከቱ ነው፡፡ የከሸፈቱ ሂደት የሚነግረን አንድ እውነትም፣ መምጣቱ አይቀሬ ነው ብለን በምንከራከርለት የመታደስ አብዮት ይህ የማሕበረ-ሰብ ክፍል ከፊት ለመሰለፍ ካንገራገረ፣ ወደ ጨፍላቂነት ሊያፈገፍግ የሚችል ሥርዓት የሚመጣበትን ዕድል ዳግም መፍቀድ እንደሆነ መገንዘብ እንደሚያሻው ነው፡፡ (በነገራችን ላይ በሶስተኛው አብዮት ለበርካታ ሀገራዊ ጉዳዮች መወሳሰብና አለመግባባቶች መግፍኤ የሆኑት «አሻጥራዊ የፖለቲካ ባሕል፣ የብሔር፣ የመሬት ጥያቄ እና መሰል ጭብጦች የማያዳግም ምላሽ እንዲያገኙ ቅድመ-ዝግጅት ካልተደረገ ለአራተኛ አብዮትም መነሾ ሊሆኑ መቻላቸውን ማሳሰቡ ተገቢ ነው ብዬ አምናለሁ)

## ምዕራፍ ሰባት

# የ«ሕዳሴ አብዮት» ተዋስኦ

የ«ሕዳሴ አብዮት» በጠንካራ ትውልዳዊ መሰረት ይገነባ ዘንድ፤ በተነሱት ሃሳቦች ዙሪያም ሆነ ተለጣጭ ርዕሰ -ጉዳዮች ላይ አሀዱ የሚባሉ የአደባባይ ውይይቶች በእጅጉ አስፈላጊ እንደሆኑ መዘንጋት የለበትም፤ የአብዮቱ ተግባሮትም ጅማሮ ከዚህ መሆኑን ልብ ይሏልና። በቀዳሚነትም የሕዳሴው አብዮት፣ ካለምሁራዊ ተዋስኦ የምንፈልጋትን ከራሷ ጋር የታረቀች ኢትዮጵያን እንደማያመጣልን መተማመን ላይ መድረስ ይኖርብናል። ምክንያቱም የፌደራል መንግስቱ አወቃቀር በዘውግ ተኮር ልባሶች የሚቀነቀኑ ፖለቲካዊ ግቦችን ያዘለ መሆኑን እናምናለንና። ይህም፣ ማሕበረ-ሰባችንን ለተሻለ የፖለቲካ ሥርዓት ግንባታ ከማሳተፍ ይልቅ፣ ወደኋላ እንዲንሸራተት አስተዋፅኦ ማድረጉ ግልፅ ነው። የሚመጣው አብዮት፣ የኢትዮጵያን የቁልቁለት ጉዞ በመግታት፣ እንደሀገር መቀጠል እንድትችል ብቻ ሳይሆን፣ ሁሉንም ፍላጎቶች የሚያካትት ይሆን ዘንድ፣





በዚህ መንፈስ የተቃኘ የአደባባይ ሙግት አይነተኛ ሚና እንዲኖረው ግድ ብሏል። በተዋስኦ ጅማሮም፣ ከላይ እንዳየነው የአውሮፓን ሥልጣኔ በፅኑ መሰረት ላይ ያስረገጡት አስላሳዮቻቸው እንደሆኑ ሁሉ፤ በእኛም አውድ ቢያንስ ለመነሻነት ሀሳቦቻቸውን ወደ አደባባዩ ተዋስኦ አብዝተን ልናካትትላቸውና የሕዳሴያችን ምሁራን ሊሆኑ ይገባል ብዬ የማምንባቸው ሶስት መምህራን አሉ፤ መስፍን ወልደማርያም፣ መሳይ ከበደ እና ተከስተ ነጋሽ።

እዛውንቱ ጠቢብ ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም በተለይም «መክሸፍ እንደ ኢትዮጵያ ታሪክ» በሚለው መጽሐፋቸው፣ የኋላው መዘንጋቱ (የጥንታዊዋ ኢትዮጵያ ሥልጣኔ) የችግሮቻችን ምንጭ መሆኑን አጽንኦት ሰጥተው አሳስበዋል። በገፅ 12 ላይም እንዲህ በማለት በቁጭት ይጠይቃሉ፡-

> *«ከአንድ ሺህ ዘጠኝ መቶ ዓመታት በፊት ሰረገላ ነበር፣ የመስኖ እርሻ ነበር፣ የግንብ ቤት ነበር፣ ሕዝብ የሚገበያየው በገንዘብ ነበር፤ ከአራት መቶ ዓመታት በፊት ጋሪ ነበር፣ ድልድይና የግንብ ቤቶች ተሰርተው ነበር፤ የዚህ ሁሉ የሥራ ጥበብ ለምን ከሸፈ? የአክሱም ሀውልቶችን የመስራት ጥበብ ለምን ከሽፎ ቀረ? የላሊበላን ከድንጋይ የተፈለፈሉ አብያተ ክርስቲያናት የመስራት ጥበብ ለምን ከሸፈ? የጎንደርን ቤተ-መንግስቶች የመስራት ጥበብ ምን አከሸፎ አስቀረው? እነዚህ ሁሉ የድንጋይ ስራ ጥበቦች በሚታዩበት አገር በደሳሳ ጎጆ ውስጥ መኖር ከትውልድ ወደትውልድ የሚተላለፍ ባሕል መሆኑ በምን ምክንያት ነው?»*

ይህን መሰሎቹ የፕሮፍ ተጠይቆችን በጥልቅና በቅንነት ከመረመርን፣ መድብሉ መፍትሔዎችንም ማካተቱን ለመገንዘብ አዳጋች አይደለም። በርግጥም ለእኒህ ጉምቱ ምሁር ወትዋች ድምፆች ጆሮ መስጠት ከቻልን፡- ተራሮችን-ሜዳ፣ አባጣ-ጎርባጣ ጎዳናዎችን-የተደላደለ

አድርገው የሚያቀኑ ከቡድ ሃሳቦችን ማበርከት እንደማይሳናቸው አምናለሁ።

ቀድሞ ግራ-ዘመም የነበሩት የፍልስፍና መምህር ፕ/ር መሳይ ከበደም ሌላኛው የሕዳሴው ምሁር ይሆናሉ ብዬ አስባለሁ፤ በዋናነት ከ40ዎቹ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ መምህራን ጋር በተባረሩ ማግስት ባሳተሟቸው መጻሕፍት እና ጥናታዊ ጽሑፎች («Survival and modernization» እና <Aleqa Asres Yenesew and The west> የመሳሰሉ)፣ የቀደሙ ሀገር-በቀል የኢትዮጵያ ሊቃውንትን ሙግቶች በማብራራት ይታወቃሉ። ‹ወደ ምንጫችን የመመለስን ጥሪ የሚያስተጋቡት ፕሮፌሰሩ፣ ኢትዮጵያ አሁን ካለችበት ማጥ ለመውጣትም ሆነ ወደፊት እንድትገፋ፣ ለረዥም ዘመን ካስተናገደቻቸው ዕሴቶች መካከል ረብ ያላቸውን መመለስ እንደሚገባት አብዝተው ተከራክረዋል። በእነዚህም ሆነ በቀጣይ በሚያሰናዷቸው ሥራዎቻቸው ላይ በቂ ትኩረት ካደረግን የሕዳሴ አብዮታችንን ለማሳለጥ የሚበጁ ሀገርኛ ብልሃቶችን መሸመታችን አጠራጣሪ አይሆንም።

አሥመራ የተወለዱት የታሪክ አጥኚው ፕ/ር ተከስተ ነጋሽም ሌላው ተጠቃሽ ናቸው። በተለይም በትምህርት ሥርዓቱ መሻሻል ላይ አበርክቶ ለማድረግ በመሞከራቸው ("The crisis of Ethiopian education: some implications for nation building" እና "The Ethiopian education: from crisis to the brink of collapse" መሰል ጥናቶቻቸውን ልብ ይሏል) በዚህ አውድ የማነሳቸው እኚህ ምሁር፣ እንደ ፕ/ር መሳይ ሁሉ፣ ዘመናዊው የትምህርት ሥርዓት አውሮፓ ተኮር እና ኢትዮጵያ-ጠል በመሆኑ ወደፊት መራመድ እንዳላስቻለን ሳይታክቱ ከመናገር ባለፈ፤ ቋንቋ የሚሸከመውን ሀገራዊ ማንነት ከመረዳት አኳያ አማርኛን እና ኦሮምኛን የሥርዓተ-ትምህርቱ ቋንቋዎች ማድረግ ብቸኛው ከውድቀታችን መውጫ መንገድ መሆኑን በጥናቶቻቸው ማስረገጣቸውን





ደግመን ደጋግመን ብናስተውለውና ብንወያይበት አበርክቶው የትምህርት ፖሊሲውን ከውድቀት ከማዳኑም በዘለለ፤ ከቋንቋ ጋር ተያይዘው ለሰነቡቱ ቅራኔዎችም መፍትሔ ይሆናል ብዬ አምናለሁ።

በአናቱም ከዚህ ቀደም ኦሮሚያን ለመገንጠል ይታትሩ የነበሩት አቦ ሌንጮ ለታ በ2006 ዓ.ም የስደት ማረፊያ ባደረጉበት አውሮፓ ከጥቂት የአንግ ጓዶቻቸው ጋር በመሆን «የኦሮሞ ዲሞክራሲያዊ ግንባር (ኦዴግ)» በሚል ስያሜ በመሰረቱት ድርጅታቸው «የፖለቲካ ፕሮግራሜ» ብለው የዘረዘሯቸው ነጥቦች በመታደስ መንገድ ላይ ለመቆማቸው ጠቋሚ ምልክት በመሆኑ፤ እንዲሁም የኡስታዝ ሐሰን ታጁ የመቻቻል ትርጓሜና የአንድነት የመፍትሔ ሃሳብ (በተለይም የነገሥታቱን ዘመን በማስታወስና በማጎን የታሪክ ወቀሳና ሮሮ ላይ ማተኮሩን ማለዘቡ ከተሳካለት) የሕዳሴው ተዋስኦ አዕማዶች ሊሆኑ የሚችሉ ይመስለኛል።

በጥቅሉ የመስፍን ወልደማርያምን የከሸፈት ኃልዮት ማሕበረ-ባሕላዊ እና ሥርዓታዊ ምንጮች መፈተሽና ማብራራት፤ የመሳይ ከበደን የሀገሪቷ የቀደሙ ስልጣኔዎች መገታት ለመሻገር ዘመናዊነትን ከልማዳዊ ማንነቶቻችን ጋር በመለንቀጥ እንደገና አቧራውን ማራገፍ ይቻላልንም ሆነ፤ የተከስተ ነጋሽን የትምህርት ሥርዓታችንን በሀገረኛ፣ አማርኛ እና ኦሮምኛ ቋንቋዎች ሙሉ ለሙሉ መቀየር የሚለውን ሙግት ከሌንጮ እና ሀሰን የዕርቅና የአንድነት ሃሳቦች ጋር አስተሳስሮ (ያልጠቀ ስኳቸው ሌሎችም አንጋፋ ጠቢባን እንደሚኖሩ ሳልዘነጋ) በቀጣይም አውሮፓውያን ከአምስት መቶ ዓመታት በፊት ከጨለማ የወጡበትን ብልሃት መመርመርን ይበልጥ አጠንክረው ከተከተሉ፣ ሀገር የመታደግ ተልዕኮዎቻችንን ከዳር ለማድረስ ጉልበት ይሆኑናል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ።

# ምዕራፍ ስምንት

# የሕዳሴው ፊት-መሪዎች

ገዥው-ግንባር የመረጠው ስሁት መንገድ፣ ኢትዮጵያችንን ለሳልሳዊው አብዮት እያዘጋጃት ለመሆኑ ማሳያዎችን በደምሳሳውም ቢሆን ለመጥቀስ ሞክሬያለሁ፡፡ ከዚህ ጎን ለጎን ተፈላጊው የለውጥ መስመርም «የሕዳሴ አብዮት» የሚል ስያሜ ይዞ፣ ሁሉን አሳታፊ ፖለቲካዊና ማሕበራዊ ንቅናቄ በመፍጠር አገሪቱን በዳግም ውልደት ለማንፃት ብቸኛ አማራጭ የመሆኑ ጉዳይ በስነ-አመክንዮ ተሰናስሎ ቀርቧል፡፡ ...እነሆም በዚህ ምዕራፍ ደግሞ አብዮቱን ከዳር ለማድረስ በፊት መሪነት መሰለፍ ይኖርባቸዋል ብዬ የማስባቸውን ተቋማት እና የማሕበረ-ሰብ አካላት እዘረዝራለሁ፡፡

### *የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት*

*ታሪክ ቀይረው ያለፉ መሰል ዓለም አቀፍ ተሞክሮዎችን ብንፈትሽ፣* የእኛን የ«ሕዳሴ አብዮት» አይነት የለውጥ መንፈስ በፊት መሪነት





ማስተባበር ከቻሉት ውስጥ በአብዛኛው የሲቪክ ተቋማት መሆናቸው በገሃድ የሚታይ እውነታ ነው፡፡ ምክንያቱም ይህን መሰሉ የፓርቲ ልዩነትን የተሻገረ እና ዘውግ ዘለል የሆነ ሕዝባዊ ንቅናቄ ላይ ሁሉንም ዜጎች አስተባብረው ሊያሳትፉ የሚችሉት አወቃቀራቸው ማሕበረ-ሰብን ብቻ መሰረት ያደረጉ ሲቪል ተቋማት የመሆናቸው መግፍኤ ነው፡፡ ይሁንና ጉዳዩን ከኢትዮጵያችን ወቅታዊ ሁናቴ ጋር ስናነፃፅረው እንዲህ አይነቱን የተቀደሰ ተልዕኮ ለማስፈፀም የሚችል አንድም ነፃ እና ጠንካራ የሲቪክ ተቋም አለመኖሩ ለማንም ግልፅ ነው፡፡ እናም ሂደቱ ይፈጥን ዘንዳ ተለዋጭ አማራጭ መጠቀሙን ግድ ያደርገዋል፡፡ በርግጥ አንዳንድ ወገኖች ለእንዲህ አይነቱ ጊዜ በሠላማዊ መንገድ የሚንቀሳቀሱ የፖለቲካ ፓርቲዎችን መጠቀሙ ብዙም ችግር እንደማይፈጥር ሲናገሩ ይደመጣሉ፡፡ ይህ ግን አደገኛና ያልተጠበቀ ክስረት ሊያስከትል የሚችል ይመስለኛል፡፡ መግቱን ለማስረገጥ ቀላል ምሳሌ ብናነሳ፣ ድርጅቶቹ የየራሳቸው የተለያየ ዓላማ አንግበው የሚታገሉ በመሆኑ ከተሳታፊነት አልፈው በመሪነት መምጣታቸው መንግስታዊ ሥልጣኑን ለመጠቅለል የቀራቸውን ርቀት በማለካከት፣ ንቅናቄውን ከሁሉን አሳታፊነት ወደቡድንነት፤ ከዲሞክራሲያዊ ሽግግር ወደሥልጣን ነጠቃነት (መፈንቅለ መንግስት) የመቀየር አደገኛ ክስተት ውስጥ ለማስገባት ‹አይሞክሩም› ብሎ መተማመኛ መስጠት አይቻልም፡፡ እንዲያውም ይህ አካሄድ በሌሎች ሀገራት ለከሸፉ አብዮቶች በማሳያነት መጠቀሱም ይታወቃል፡፡ እናም ለእኛ አንኳቢጋቢ ጉዳይ መፍትሔውን አዲስ (ከዚህ ቀደም ያልተሞከረ) አማራጭን ከራሳችን ነባራዊ እውነታ አንፃር መፈለግ ላይ ማተኮሩ ይበጃል ብዬ ስለማምን፣ በግሌ አማራጭ ይሆናል የምለውን ተቋም እጠቁማለሁ፤ ይኸውም በተለያዩ ከተሞች የሚገኙ ዩንቨርስቲዎቻችንን ነው፡፡ እነዚህን ተቋማት በሚገባ ለመጠቀም በተመሳሳይ ወቅት መጀመር የሚኖርበትን የሕዳሴ አብዮት፣ ሁሉም መንግስታዊ ዩኒቨርስቲዎች የሚገኙበትን ከተሞች ጨምሮ አጎራባች አካባቢዎችን ለማስተባበር ኃላፊነት የሚወስዱበት መንገድን በጥንቃቄ

ማመቻቸቱ የሚሳካበትን ስልት ከወዲሁ መቀየስ የሚቻል ይመስለኛል፡፡ ርግጥ ነው በዛሬው እውነታ ላይ ሆነን በተለይም የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የገባው ፓርቲ የፖለቲካ መናኸሪያ የመሆናቸውን ነገር ግምት ውስጥ አስገብተን ስናምሰለስለው፣ ሁነቶቹ አልጋ በአልጋ ሊሆኑ እንደማይችሉ ከማንም የተሰወረ አይሆንም፡፡ ግና፣ በየተቋማቱ የየትኛውም ፓርቲ አባል ያልሆኑም የሆኑም ለውጥ አራማጅ መምህራንና ተማሪዎች በራስ ተነሳሽነት በመሰባሰብ የማስተባበሩን ኃላፊነት ተረክበው ከፊት መስመር እንዲሰለፉ የማንቃትና ማብቃት ሥራ መስራት ይቻላል ብዬ አምናለሁ፡፡ በ2006 ዓ.ም መጨረሻ እና በዚህ ዓመት መጀመሪያ ገዥው -ግንባር የዩንቨርስቲ መምህራንና ተማሪዎችን ባረጀው -በፈጀው አብዮታዊ ዲሞክራሲ ለማጥመቅ እና ልማታዊ መንግስት መሆኑን በስብከት ለማሳመን በሞከረበት ወቅት የተሰነዘሩበትን ተግዳሮቶች እና ጠንካራ ተቃውሞዎች ስናስተውል ሃሳቡን ወደ መሬት ለማውረድ «አብዮታዊ ሁኔታ» መኖሩን ከማመላከቱም በተጨማሪ፣ ከንቅናቄው ስፋት አኳያ ከባድ መስዋዕትነት የማስከተሉን አጋጣሚ እጅግ ያጠብበዋል፡፡ ይህ ዕቅድ የሚሳካ ከሆነ ደግሞ ዩኒቨርስቲዎቹ በዕኩል ውክልና አንድ የጋራ ማዕከል (አዲስ አበባ ለዚህ አመቺ ሊሆን ይችላል) አቋቁመው፣ ሕዝባዊ እምቢተኝነቱ በትግበራም ሆነ በሚነሱ ጥያቄዎች ዙሪያ ተመሳሳይነት (ወጥነት) እንዲኖረው በማድረግ አብዮቱን ከሀገርና ሕዝብ ጥቅም አስተሳስረው መምራት የሚችሉበትን ዕድል ይፈጥሯሉ፡፡

### *የእንስቶች ሚና...*

የ«ሕዳሴ አብዮት» በዋናነት የሚያተኩርበት ሌላው ጉዳይ፣ ከአራት አስርታት በፊት በያ ትውልድ ፈታኝ የትግል ጉዞ ላይ ትልቅ ተሳትፎ የነበራቸውን እንስቶች የተኳቸው የዛሬዎቹ የፆታ አቻዎቻቸው ለምን ከእንቅልፍ በከበደ እርምም ውስጥ ሰጠሙ? የሚለውን ጥያቄ በመፈተሽ መፍትሔ ማፈላለጉ ላይ ነው፡፡ ከአውሮፕላን ጠላፊዋ ማርታ መብራቱና





ታደለች ኪዳነማርያም እስከ መኢሶኗ ንግስት አዳነ፤ እንዲሁም ከእልፎቹ የኢሕአፓ ትንታግ ጓዲቶች እስከ ወያኔዎቹ አረጋሽ አዳነ እና ቀሺ ገብሩ ያሉ ተዘርዝረው የማያልቁ የዚያ ዘመን እንስት እናብስቶች እንቅስቃሴ እንደዋዛ አከትሞ፣ በብርቱካን ሚደቅሳ፣ ርዕዮት አለሙ፣ እንደ ፈቲያ መሀመድ ያሉ ቁጥራቸው የበዛ ሙስሊም ሴት ቀራጦችን... በመሰሉ ጥቂት ጀግኖች ተገድቦ መታየቱ፣ በቀድሞው ታሪክ መታደስን አማራጭ የለሽ ያደርገዋል፡፡ ለዚህ የእንስቶቻችንን ፌኒክስነት ለመመለስ ከጥንቱ ይልቅ የትላንቱ የእናቶቻችን ጊዜ በተምሳሌነቱ ተስተካካይ የለውም፡፡ እነርሱ በያ ትውልድ ተጋድሎ የጊዜውን ጎታች የፆታ አመለካከት በመጋፋትና የወንዶችን ትምክህታዊ ዓለም በመነቅነቅ ደማቅ ታሪክ ለመስራት የታደሉ ፈርጦች እንደሆኑ አስመስክረው አልፈዋልና፡፡

የእኔ ዘመን አብዮተኛ ሴቶችም፣ በኮታ ሳይሆን በእውነተኛው ዕኩልነት እንዲገለጡ ግዴታቸውን ከወዲሁ ለመወጣት የሰመጡበትን ዝምታ መስበር ይኖርባቸዋል፡፡ ከወቅታዊው የሀገሪቱ ሕዝብ ቁጥር እኩሌታውን የሚይዙት እንስቶቻችን በነቂስ ያልተሳተፉበት አብዮት በየትኛውም መስፈርት ውጤታማ ይሆናል ተብሎ አይታሰብም፡፡ በግልባጩ እነርሱን በዕኩልነት ማካተቱ ካልተሳካ ለውጡ ከመዘግየቱም በዘለለ ከፉ ጠባሳ ሊኖረው ስለሚችል፣ «ያለሴቶች ተሳትፎ የኢትዮጵያ ሕዳሴ እውን አይሆንም!» አይነቱን ዘመነኛ ኢህአዴጋዊ ቧልት እና ፕሮፓጋንዳን በማጋለጥ፣ እንስቶቻችንን አደባባይ የሚያውል ንቃት መፍጠሩ፣ በተለይ ቀድሞውንም በጀግንነት የተሰለፉ (ምንም እንኳ ጥቂቶች ቢሆኑም) የፆታ አቻዎቻቸው ትኩረት ሊሰጡት ይገባል ብዬ አምናለሁ፡፡

### *የታጠቀው ኃይል ተጠሪነት...*

የዓለም ታሪክ አምባ-ገነኖች እብደታቸውን እንዲተገብሩ ያስቻላቸው የታጠቀው ኃይል (ጦር ሠራዊት፣ ደህንነት እና ፖሊስ) ተጠሪነቱን ከሕግ ይልቅ ለግለሰቦች (ለገዥው-ፓርቲ) እንዲሆን

(እንደማያስጠይቅ) ከዘለፋ በራቁ ጨዋ ቃላት መወትወቱ ጠቃሚ ነው፡፡ ይህን ታላቅ ተልዕኮ ለማሳካት በተለይም የአዛዦቹም ሆነ የተራው ሠራዊትና ደህንነት ቤተሰብ፣ ጎረቤት፣ ጓደኞች፣ ዘመድ -ወዳጅ ወገኖች ቀዳሚውን ኃላፊነት መሸከም እንደሚኖርባቸው ለማስታወስ እወዳለሁ፡፡

*የገዥው - ፓርቲ አባላት...*

ሌላው አስቀድሞ መዘጋጀት የሚገባው ጉዳይ፣ አብዮቱ በራሱ በገዥው-ፓርቲ ውስጥ ያሉ በፖለቲካ ቀኖናዊነት ያልተጠለፉና ሀገራዊ ለውጥ ፈላጊ ለዘብተኛ የአመራር አባላት እና የበታች ካድሬዎች በንቅናቄው ወቅት ‹የኢህአዴግ መንግስት ወይም ሞት!› ለማለት የማያመነቱ ግትር ጓዶቻቸውን አግልለው፣ ይህንን ኃላፊነት እንዲወስዱ ጫና የማድረግን አስፈላጊነት የሚመለከት ነው፤ ምክንያቱም ይህ ሕዝባዊ እምቢተኝነት በምንም መልኩ ግንባሩን በጠላትነት ፈርጆ የሚያሳድድ አለመሆኑን ግንዛቤ መውሰድ ያስፈልጋልና፡፡ የሕዳሴው አብዮታችን የ‹ጊሎትን› ማሽን የማይታጠቅ፣ ልጆቹን የማይበላ፣ በአጥፍቶ መጥፋት ጨዋታ የማይመራ... መሆኑን ማስረገጥ ግድ ይላል፡፡ እንዲሁም ከድህረ -97ቱ የምርጫ ፖለቲካ ድቀት እና ይህን ተከትሎ በመጣው የተቃውሞ ስብስብ መዳከም የተነሳ፣ ‹ፓርቲውን በአዝጋሚው መንገድም ቢሆን እየገፉ መሄድ ይቻላል› በሚል የተቀላቀሉ ብቻ ሚሊዮኖች እንደሆኑ ይታወቃል፡፡

እውነት እውነት እላችኋለሁም፡- እነዚህን ወንድሞችና እህቶች በሂደቱ ውስጥ ለማሳተፍ፣ የአብዮቱን መሪ ህልም እንዲያምኑበት ማድረጉ ‹ለነገ የማይባል› የቤት ሥራ ነው፡፡ እነርሱን እያካተትን በተጓዝን መጠን፣ ሌሎቹም የፓርቲው አባላት ትግሉን በመቀላቀል፣ የራሳቸውንም ጥያቄዎች ጭምር አንስተው ሥርዓቱ ወደመነጋገር እንዲመጣ ጫና የማሳደራቸው ዕድል እየሰፋ መሄዱ እ ሙን ነው፡፡ በሌሎች የፕላኔታችን አገራት በእቅድ የተመሩ አብዮት ስኬቶችን ስንመረምር የእነዚህን መሰል አካላት ተሳትፎ ለውጤቱ ማማር አስተዋፅኦ ማድረጉን መረዳታችን አይቀርም፡፡ በነገራችን





ላይ በመታደላችን ዘመን ለቀደሙ ወንጀሎችም ሆነ ሀገራዊ ውድመቶች ሂሳብ ማወራረድን ታሳቢ ማድረግ ፍፁም አብዮቱን መካተት ከመሆኑም በላይ፣ የታሪካችንን አስቀያሚ ገፅ በመድገም ቁልቁል መዘቀጥ እንደሆነ መተማመን ይኖርብናል፡፡ ግባችን ኢትዮጵያን እያደሱ ወደፊት ማራመድ እስከሆነ ዘንዳ፣ የተሻለ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን የመፍጠሪያው መንገድ ላይ ብቻ ማተኮር ብቸኛው መፍትሄ ነው፡፡ ያለፈው ዘመን ሰማዕታትን እየዘከርን፣ የተፈፀሙ ግፍና በደሎችንም አዲሱን ትውልድ ለማስፈራሪያ (ለፖለቲካ ጥቅም) ሳይሆን ለማስተማሪያ እያዋልን ለአጥፊዎቹ ምህረት እያደረግን በይቅርባይነትና በመቻቻል ላይ የምታብበውን ኢትዮጵያን መመስረት የሕዳሴው አብዮት ግብ ሊሆን ይገባዋል የሚል የፀና እምነት አለኝ፡፡

ለ

እዚህ ጋ የማነሳው የኢትዮጵያችን ነባራዊ ሀቅ፣ አብዮቶ ች ከተተገበረባቸው ሀገራት አንድ ለየት የሚል ገፅ ያለው ከመሆኑ ጋር የሚያያዝ ነው:: ሁላችንም እንደምናውቀው፣ እነርሱም በይፋ እንደሚለፍፉት የገዢው ግንባር አባላት ተከፋፍለው በሀገሪቷ ኢኮኖሚ የአንበሳውን ድርሻ ወስደዋል:: ከማዕድን ቁፋሮ እስከ ጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪ፤ ከፋይናንሺያል ተቋማት እስከ አልኮል ምርቶች ድረስ የተቆጣጠሩበትን መንገድ ማዳከም፣ ሕዝባዊ ጉዳት ሳይከተል ቀጥታ የሥርዓቱን የመጨቆኛ ምንጭ ማድረቁን ቀላል ያደርገዋል:: በርግጥ አገዛዙ ከእነዚህ የፓርቲዎቹ ተቋማት ምንም አይነት አገልግሎት ላለመጠቀም የሚደረገውን አድማ በመጠምዘዝ፣ እንደተለመደው ሂደቱን በአንድ ቋንቋ ተናጋሪ ላይ ያነጣጠረና ብሔሩን ሆን ተብሎ ለመጉዳት ታስቦ እንደተደረገ አስመስሎ የሚነዛውን መርዛማ ፕሮፓጋንዳ ከወዲሁ ለማጨናገፍ፣ ከድርጅቶቹ ምርቶቹን ያለመግዛት ውሳኔ፣ ከማንኛውም ብሔር ተወላጆች የንግድ ሥራ ጋር እንደማይገናኝ ማመን እና መተማመንን መፍጠር ቀዳሚው ተግባር ሊሆን ይገባዋል:: በ«ኤፈርት» የበለፀገች ትግራይ፣ በ«ዲንሾ» ያደገች ኦሮሚያ፣ አልያም በ«ጥረት» የተጠቀመ የአማራ ክልል አለመኖሩን... መጀመሪያውኑ ከልብ ተገንዝበን ከተንቀሳቀስን፣ ፓርቲ ተኮር ድርጅቶቹን ማግለል አስቸጋሪ አይሆንብንም:: የተቃውሞ እንቅስቃሴው ቀጣይ ቅቡል መሪዎችም ይሆን ጭብጥ ሳይዛባ ሕዝቡ ዘንድ በሚገባ ማስረፅ አንዱ ኃላፊነታቸው መሆኑን ሊዘነጉት አይገባም::

ሐ

የኢኮኖሚ ትብብር መንፈግን የግድ የሚያደርገው ሌላው ጉዳይ፣ ግብር (ታክስ) ያለመክፈል ሕዝባዊ እምቢተኝነትንም ስለሚያጠቃልል ነው:: የጭቆናው አገዛዝ ተጠናክሮ የቆመው በታክስ ሥርዓቱ ላይ





መሆኑንም ሆነ ለሥልጣን ዕድሜ ማራዘሚያው ይህንኑ መንገድ መጥቀሙን በቅጡ መገንዘብ ከቻልን ታክስ ባለመክፈል፣ የቆመበትን መሰረት መቦርቦር የሚቻልበትን ዕድል ማስፋቱን ማስ ታወስ አስፈላጊ ነው ብዬ እስባለሁ::

*የአደባባይ እምቢተኛነት...*

ዛሬ ላይ ስለመታገያ መንገዶቹ ብዙ ነጥቦችን ዘርዝሮ ማቅረቡ ላያስፈልግ እንደሚችል ይሰማኛል:: ምክንያቱም በአገዛዝ ውስጥ የሚመረጡ የትግል ስልቶች በይፋ ከማቅረብ ይልቅ፣ በተቃውሞው አደረጃጀት ጥልቅ ዝግጅት እንደየአውዱ እየተመረጡ ቢተገበሩ የተሻለ ውጤታማ እንደሚሆኑ አምናለሁ:: ከዚህ አንፃርም ጥቂት ነጥቦችን ብቻ አንስቼ አልፋለሁ:: በእነ ጂን ሻርፕ እና መሰል የትግሉ መምህራን ተደጋግሞ የሚጠቀሰው «የአደባባይ መቀመጥ» የሚባለው ለሠላማዊው አመፅ ግንባር ቀደም ተደርጎ ይጠቀሳል:: ለረዘሙ ቀናት/ሳምንታት አደባባዮችን ሞልቶ፣ ተጨባጭ ፖለቲካዊ ማሻሻያም ሆነ መሰረታዊ የሥልጣን ሽግግር እስኪደረግ ድረስ የመተካካት ስልት በተከተለ እና ግላዊ የዕለት ተዕለት የኑሮ መመሰቃቀሎችን ባገናዘበ (በእጅጉ ጉዳቶቹን በሚቀንስ) መልኩ በፈረቃ ፕሮግራ ም የሚደረግ እንደሆነ ይታመናል:: በትዕምርትነትም ሰንደቀ-ዓላማን ጨምሮ የእስልምናን፣ የክርስትናን እና የአይሁድ እምነት ምልክቶችን ለመሰባሰቢያነት በመጠቀም፣ በዋና ዋና ግልፅ ሕዝባዊ የመሰባሰቢያ ስፍራዎች ላይ የሰላም ድንኳኖችን መዘርጋት፣ የመማፀኛ ፊርማ ማሰባሰብ፣ በሕንፃዎች አናትና በግድግዳዎች ላይ ለውጥ የሚጠይቁ መፈክሮችንና ምስሎችን መለጠፍ፣ የመኪና ጥሩንባንና ሌሎች ከፍተኛ ድምፅ ሰጪ መሳሪያዎ ችን ያለማቋረጥ ማስጮኸ፣ የቤት ውስጥ መቀመጥ፣ የሥራ፣ የትምህርትና የረሃብ አድማዎችን መምታት፣ በማሕበራዊ ጉዳዮች ላይ ማደም፣ በየእምነት ተቋማቱ ቢጋራ ፀሎት ማድረግ... በዚሁ ስር የሚካተቱ ተግባራት ናቸው::

ድጋፎቹን ከነዚህ ሀገራትና ተቋማት እንዳያገኝ ጠንካራ ዲፕሎማሲያዊ ጫና የሚካሄድበትን ስልት መቀረፅ በእጅጉ አስፈላጊ ነው። ከዚሁ ጋር ተያይዞ፣ አፈናውን ለማራዘም በርትተው በሚሰሩት የሥርዓቱ ፊት -አውራሪዎች ላይ፤ የጉዞ ማዕቀቦችን ጨምሮ ሌሎች ወደ ድርድሩ ማዕ ቀፍ እንዲመጡ የሚያስገድዱ ግላዊ ጫናዎች እንዲጠናከሩባቸው መጣር፣ ተጨማሪ የትግሉ መንገድ መሆን ይኖርበታል። በርግጥ ይህ የቤት ሥራ በዋናነት በኢትዮጵያውያን ዲያስፖራ ትከሻ ላይ የሚወድቅ እጅግ ጠቃሚ አበርክቶ ነው ብዬ ማመኔን እንዲህ በገሃድ መመስከር ይኖርብኛል።





# ምዕራፍ አስር

# የአብዮቱ የመጀመሪያ ጥያቄዎች

ባለፈው ምዕራፍ የተጠቀሱት ሠላማዊ የትግል ስልቶች ሥራ ላይ ውለው እና ሕዝባዊ ንቅናቄው በሚገባ ተጠናክሮ ከቀጠለ በኋላ መንግስት እጁን ተጠምዝዞ (ተገድዶ) እንዲተገብራቸው መነሳት ያለባቸው ቀዳሚ ጥያቄዎች (ለለውጡ መደላድል ይሆናሉ ብዬ የማስባቸው) የሚከተሉት ናቸው፡- በመላ ሀገሪቱ ባሉ ማረሚያ ቤቶች የሚማቅቁ የፖለቲካ፣ የሕሊና እና የሀይማኖት እስረኞችን ያለምንም ቅድመ ሁኔታ መፍታት፤ በውጪ ሀገር ያሉ ተቃዋሚ ድርጅቶች፣ ምሁራን፣ ጋዜጠኞችና የመብት ተሟጋቾች ያለልዩነት ወደ ሀገር ቤት ገብተው በነፃ እንዲንቀሳቀሱ መፍቀድ፤ በሚሊኒየሙ ማግስት የፀደቁትን የመያዶች፣ የፕሬስ እና የፀረ -ሽብር አዋጆችን (አፋኝ ሕጎችን) መሰረዝ፤ በሀገሪቱ የመንግስት ምሥረታ ላይ የአፈና መዋቅር ሆኖ የሚያገለግለውን ምርጫ ቦርድ አፍርሶ አብዛሃ ኢትዮጵያዊን ሊያሳምን በሚችል ገፅ እንደገና ማዋቀር፤ ለዴሞክራሲ

ዋና ፋይዳ ከለውጡ በኋላ የሚፈጠር ማሕበ ረ-ሰብ የነቃ እንደመሆኑ፣ መጪዎቹ የሥልጣን ተረካቢዎች በቁመቱ ልክ ካልሆኑ (ካልመጠኑት) ለእነርሱም አስቸጋሪ እንደሚሆን የማስረገጡ እውነታ ነው፡፡ ይህን ታላቅ ሁነት በተግባር በተፈፀመ ማስረጃ ለመረዳት የቅርቡ የአረቡ መነቃቃት ማየቱ ብቻ በቂ ነው፡፡ የግብፅ ሕዝብ ከአብዮቱ በፊትና በኋላ ያለውን የንቃት ልዩነት ማንም የሚያስተውለው ነውና፡፡ ዛሬ ላይ የምንመለከተው ማሕበረ-ሰብ የሆስኒ ሙባረክን የጭቆና-አገዛዝ በተራዘመ ቻይነትና ትዕግስት ካሳለፈበት ዘመን አንፃር ሲታይ ፍፁም ፖለቲካዊ ስለመሆኑ በብዙዎች ተወስቷል፡፡ ለእያንዳንዱ አገራዊ ጉዳይ ያገባኛል በማለት መሟገትን የዕለት ተዕለት ስራው አድርጎታል፡፡ ከዚህ አብዮታዊ ሃሳብ ትይዩ በብረት የሚመጣ ለውጥ፣ ተመልሶ ማሕበረ-ሰባዊ ፍዝነት ውስጥ እንደሚጥለን መረዳታችንም፣ መጪውን የአብዮት አማራጭ ብቸኛው ትውልዳዊ ዕዳ ወደማድረጉ ገፍቶታል፡፡ ከሞት ይልቅ ህይወት፣ ከድቀት ይልቅ ጥንካሬ፣ ከመበታተን ይልቅ አንድነት የሚሰጠንን ሠላማዊ የለውጥ ንቅናቄ ስለመከወን ደግመን ደጋግመን ማሰላሰል ደግሞ የዘመኑ አስገዳጅ ኃላፊነት እንደሆነ በፍፁም ሊዘነጋ አይገባውም፡፡





# የመሸሩ ወቅት . . .

ይህን መሰል በሕዝብ እምቢተኝነት እና አደባባይ በመዋል የሚከወን የለውጥ ጥያቄ ማቅረቡ ሥርዓቱ ከሃያ ሰስት ዓመት በላይ ከመቆየቱ አኳያ የተቻኮለ እንደማይሆን አምናለሁና፤ ከላይ ከተጠቀሱት ዋና ዋና አብዮታዊ ጉዳዮች አንፃር፤ እንዲሁም በአንድ ወቅት አቶ መለስ ዜናዊ «ልጄ ፋኖ ተሰማራ እንድትል አልፈልግም» እንዳለው ሁሉ፤ ህወሓት በኢትዮጵያችን ታሪክ የመጨረሻው «ነፃ አውጪ» ብረት ነካሽ ድርጅት ይሆን ዘንድ ከተስማማን፣ ለትግበራው 2007 ዓ.ም በሁለት ምክንያቶች ከመቼውም የበለጠ የተመቻቸ ይመስለኛል፡-

፩

ሕዝባዊ ቁጣዎች ከዕለት ወደዕለት ተባብሰው የሰው ልጅ ሊኖረው የሚገባውን የትዕግስት ዳርቻ የጣሱ መሆናቸው እና ራሱ ገዥው ፓርቲ በውስጥ ትግል መናቆሩ ከፍተኛ ደረጃ ላይ የደረሰበት አጋጣሚ በአመፁ በቀላሉ እንዲፍረከረክ ያደርገዋል፡፡ በተለይ ደግሞ ይህ የውስጥ መተጋገል ሊታረቅ ወደማይችል ልዩነት እያመራ ከመሆኑ አኳያ፣ በሚያስከትለው ከፉ ውጤት ሀገሪቷንም ይዞ እንዳይሞት የ«ሕዳሴ አብዮት» ይታደገዋል ብዬ አምናለሁ፡፡

፪

በዚህ ዓመት የሚደረገውን አምስተኛ ዙር ሀገር አቀፍ ምርጫን የማራዘሙ አስፈላጊነት ከሕዝባዊ ጥያቄው መካከል ግንባር -ቀደም ከመሆኑ አይቀሬነት አኳያ ለአገዛዙ በቂ የጥሞና ጊዜ መስጠት የማስቻሉ ጠቀሜታ፣ አንድም የሂደቱን መንገድ ለማደላደል የሚያስችል አበርክቶ ይኖረዋል፤ ሁለትም በአፋና ስር የሚካሄደውን ምርጫ ሕጋዊ በማስመሳል «ሕዝብ የአምስት ዓመት ኮንትራት ሰጥቶናል» በሚለው የተለመደ ፕሮፓጋንዳ በማጭበርበር ወደ ኃይል እርምጃ የሚገባበትን መንገድ ለመዝጋት፤ ሶስትም ለዚህ የይስሙላ ምርጫ የሚወጣውን የሀገር ሀብትና ውድ ጊዜን ከብክነት ማዳኑ ግድ ስለሆነ ነው፡፡

...በመጨረሻም እየተነጋገርንባቸው ያሉት እነዚህ ታላላቅ አጀንዳዎች እውን ይሆኑ ዘንድ ቀጠሮውን በልቦናችን ይዘን፣ ራስን በውስጥ ዝግጅት ማስናዳቱ ለነገ የማይተው የቤት ስራችን መሆኑንም ጨምሮ መረዳት ያሻል፤ በዚህም የሕዳሴያችን ንቅናቄ እንደ ቀዳሚዎቹ ሁለት አብዮቶች አዲስ መዘዝ ሳይሆን፣ አዲስ ተስፋ እንዲያመጣ እናስችላለን ብዬ እሰባለሁ፡፡

በርግጥም ያቺ ትንሳኤ አብሳሪ ዕለት በኢትዮጵያችን ምድር ከቶም ቢሆን እቻ የላትምና፣ በእያሌ ናፍቆት ስለመጠበቋ ዛሬ ላይ እንዲህ መመስከሩ ከምኞት የተሻገረ መሆኑን አስረግጬ ብናገር ማጋነን አይሆንምና፤ እነሆም ፀሀይቱ ሙቀቷን ለግሳ፣ ጨረቃም ከነሙሉ ክብሯ ብርሃኗን ፈንጥቃ፣ ከዋክብትም ያለስስት ደምቀው እየተጣቀሱ. . . የተሰለቸውን የጭቆና አጋዛዝ እናጨልም፣ የግፍ ሥርዓቱን ቀንበር እንገረስስ ዘንዳ በድምቀት ሊያጅቡን የሚበረቱበት ዘመን ላይ ደርሰናልና - ንቁ፡፡ ያለመዘናጋትም የጥሪ ምልክቶችን ተከታተሉ፡፡ ለዚህም አስቀድሞ በየአካባቢያችሁ ራሳችሁን እያደራጃችሁ፣ ፍቅርን እየሰበካችሁ፣ የጥላቻ ተከሎችን እየነቀላችሁ ጠብቁ - ጊዜው እጅግ በጣም፣ እጅግ ተቃርቧልና፡፡

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!!!





# ዋቢ መጻሕፍት


- ፕ/ር ባሕሩ ዘውዴ፡ የኢትዮጵያ ታሪክ ከ1847 እስከ 1983፡ 2003ዓ.ም
- ፕ/ር ታደሰ ታምራት፡ ኢትዮጵያዊነት ከመሰረቱ፣ 1991ዓ.ም
- ፕ/ር መስፍን ወ/ማርያም፡ ኢትዮጵያዊነት በደርግና በወያኔ ያገዛዝ ሥርዓቶች፣ 1991ዓ.ም
- ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም፡ «መክሸፍ እንደ ኢትዮጵያ ታሪክ»፡ 2005ዓ.ም
- ሚሊዮን ነቅንቅ፡ «ትልቋ ኢትዮጵያ የብዙ ነገዶች ማኅበረሰብ»፡ 1993ዓ.ም
- ዶ/ር ላጵሶ ጌ. ድሌቦ፡ የኢትዮጵያ የገባር ሥርዓትና ጅምር ካፒታሊዝም፡ 1983 ዓ.ም
- አንዳርጋቸው ጽጌ፡ የአማራ ሕዝብ ከየት ወዴት፡ ሰኔ 1985 ዓ.ም፡
- እሸቱ ኢረና ዲባባ፡ የኦሮሞ ታሪክ ከጥንት እስከ 1890ዎቹ መጨረሻ፡ 2001ዓ.ም
- እሸቱ ኢረና ዲባባ፡ «የኦሮሞ ታሪክ»፡ 2003ዓ.ም.
- ጳውሎስ ኞኞ፡ አጤ ቴዎድሮስ፡ 1985ዓ.ም
- ከዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ ጋር በግል የተደረገ ውይይት
- ዓለሙ ኃይሌ፡ «የኢትዮጵያ ታሪክ፡ የአፄ ሱስንዮስ ዜና መዋዕል»፡ 2005ዓ.ም
- ዶ/ር እንድሪስ ሙሐመድ አወሊያ...ከመጋቢት እስከ መጋቢት፤ ያልታተመ ጽፍ፡ 2004ዓ.ም
- አሕመዲን ጀበል፡ ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች ከ615-1700 የጭቆናና የትግል ታሪክ፡ ቅጽ አንድ፡ መጋቢት 2003
- አቤል አለማየሁና ኤልያስ ገብሩ፤ ኢትዮጵያን ማን ይታደጋት? 2005ዓ.ም

- Doctor Merara Gudina "Contradictory Interpretations of Ethiopian History: The need for a new consensus"
- ዶ/ር መራራ ጉዲና፡ የኢትዮጵያ ፖለቲካ ምስቅልቅል ጉዞና የሕይወቴ ትዝታዎች፡ 2005ዓ.ም
- ግዛው ዘውዱ፡ የኢትዮጵያ ታሪክ ትርክትና ታሪካችን፡ 2005 ዓ.ም
- The Columbia Encyclopedia, ስድስተኛ ቅጂ (2001-05)
- ሄንሪ ዴቪድ ቶሮ፣ On the Duty of civil Disobedience፡ 1849
- Jean Sharp፡ From dictatorship to democracy ፡
- Piter Gill፡ Famine and foreigners in Ethiopia:
- ኤርምያስ ለገሰ: የመለስ ትሩፋቶች: 2006ዓ.ም
- «የትግል ጥሪ» መጽሔት፡ 1979ዓ.ም፡ ወርሃ ግንቦት-ሰኔ
- ታቦር ዋሚ፡ «የውግና ድርሰቶችና የታሪክ እውነቶች»፡
- የኦሮሞ ክልል ባሕልና ቱሪዝም ቢሮ፡ የኦሮሞ ታሪክ እስከ አሰራ ስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን፡
- ኡስታዝ ሀሰን ታጁ፡ ሠይፉን ፍለጋ፡2006ዓ.ም
- «ፋከት» መጽሔት ቅጽ 2፡ ቁጥር 55
- ቻሌንጅ፡ መጽሔት የሰሜን አሜሪካ ተማሪዎች ማህበር መጽሔት፡ 1965ዓ.ም. እ.ኤ.አ.

በ‹‹ኤፈርት›› የበለፀጉች ትግራይ፣ በ‹‹ዲንሾ›› ያደገች ኦሮሚያ፣ አልያም በ‹‹ጥረት›› የተጠቀመ የአማራ ክልል አለመኖሩን... ከልብ ተገንዝበን፣ ለህልውናችን የቀን ተቀን ኑሮ እጅግ ወሳኝ የሆኑትን የምርት ውጤቶች ሳይቀር ከመንግስታዊ ተቋማቱ ባለመግዛትና የምርት ሂደቱንም ከውስጥ በማጨናገፍ እንዲዳከሙ ማድረግ፣ ሥርዓቱን በአጭር ጊዜ ውስጥ ለማሽመድመድ እጅግ ውጤታማ ስልት እንደሆነ አምናለሁ:: ከዚህ ሌላ የጭቆናው አገዛዝ ተጠናክሮ የቆመው በታክስ ሥርዓቱ ላይ መሆኑን እና ይህንኑ መንገድ ለሥልጣን ዕድሜ ማራዘሚያው መጥቀሙን በቅጡ ተረድተን ግብር (ታክስ) ባለመክፈል፣ የቆመበትን መሰረት መቦርቦርና መናድ ይቻላል::

◆ ◆ ◆ ◆

ርግጥ ነው ሁላችንንም ግራ-ገቡ ኢህአዴግ ፍርሃት በናጠው ቁጥር ሲያሻው በገፍ ወህኒ እያጎረ፣ ሲፈልግ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውን እንኳን ያልጨረሱ ብላቴኖችን ግንባር በጥይት እየፈረከሰ፣ በል ሲለው ደግሞ ይህንን መከራ እና ስቃያችንን የምንተነፍስበት ሚዲያ እያሳጣን በምሬት እንደሞላን አንክድም:: ይህ ሁሉ ሆኖም ግን ድርጅቱ የተካነበትንና ለፍልሚያ በጥድፊያ የሚመርጠውን ጠብ-መንጃ አናነሳም:: ጠብ-መንጃ የማናነሳው ልበ-ሙሉነታችን ‹‹ተራሮችን እንቀጠቅጥን›› ከሚለው ትውልድ ያነሰ ሆኖ በመገኘቱ አይደለም፣ ሚሊዮናት ዘመን ተጋሪዎቹ ለሀገር ጉዳይ፣ ለሕዝብ ጥቅም ግንባራቸውን እንደማያጥፉ አውቃለሁና፣ አሊያም ደግሞ የደኑ መመንጠር ምሽግ ስላሳጣን ወይም የምናፈገፍግበት መሬት ስለጠፋንም አይደለም:: ብረት-ጠል የሆንነው፣ በሠላማዊ ሕዝባዊ ዓመፅ ይህን ሥርዓት አስቁሞ፣ ኢትዮጵያን ማደስ እንደሚቻል ካለን የፀና እምነት ባሻገር፣ ነባራዊውም ሁነት ጮኾ የሚያስረግጥልን ይሄንን በመሆኑ ብቻ ነው:: በአንድ ወቅት መለሰ ዜናዊ ‹‹ልጄ ‹ፋኖ ተሰማራ...› እንድትል አልፈልግም›› እንዳለው፣ ይህ ሠላማዊ የመጨረሻ ሙከራ በኢትዮጵያ ሰማይ ስር ዳግም ነፍጥ እንዳይነሳ አስተማማኝ ዋስትናን ሰጥቶ እንደሚጠናቀቅ አንጠራጠርም::

ከመጽሐፉ ውስጥ ገጾች የተወሰዱ